



# ኒኮላይ ፡ ጐጐል ።

# ታራስ ፡ ቡልባ ።

## ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።

*From the Library of*

*ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃን*

*FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANN*

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።





# ኒኮላይ ፡ ጐጐል ።

# ታራስ ፡ ቡልባ ።

## ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።

*From the Library of*

***ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃን***

***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNE***

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።

ተርጓሚው ፤ በካፋ ፡ ኃይለ ፡ የሱስ።

Н. В. Гоголь

ТАРАС БУЛЬБА

ПОВЕСТЬ

*На амхарском языке*

Г $\frac{70301-585}{014(01)-75}$ без объявл.

## ምዕራፍ ፡ አንድ ።

«እስቲ ፡ ዘወር ፡ ብለህ ፡ ልይህ ፡ ልጄ! እንዴት ፡ ያለ ፡ ማስፈራሪያ ፡ መስለሃል! ደግሞ ፡ የምን ፡ የቄስ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ፡ የለበስኸው? በተማሪ ፡ ቤት ፡ ሁሉም ፡ የሚለብሱት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እንዴ?»

ቡልባ ፤ በኪዬቭ ፡ በሚገኘው ፡ ከፍተኛ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ የተመለሱትን ፡ ሁለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ የተቀበላቸው ፡ እንዲህ ፡ ባሉ ፡ ቃላት ፡ ነው ።

ልጆቹ ፡ ገና ፡ ከፈረሶቻቸው ፡ መውረዳቸው ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ ፍርጥም ፡ ያሉና ፡ እንደማናቸውም ፡ ወጣት ፡ ተማሪ ፡ ዓይነ ፡ አፋሮች ፡ ነበሩ ። ወላጃቸው ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ስለተቀበላቸው ፡ እጅግ ፡ ደንግጠው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ ።

«ቆዩ ፡ እስቲ! እስቲ ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ ላስተውላችሁ!» ብሎ ፡ እያዟዟረ ፤ «እንዴት ፡ ያለ ፡ ዘርፋፋ ፡ ካፖርት ፡ ነው ፡ የለበሳችሁ! እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዓለም ፡ ታይቶም ፡ አይታወቅ ። እስቲ ፡ አንዳችሁ ፡ ትንሽ ፡ ሩጡ! ቀሚሳችሁ ፡ ጠልፎ ፡ ሲያጋድማችሁ ፡ እስቲ ፡ አያለሁ ፡» አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፤ «አትሳቅብን ፡ አባባ ፤ አትሳቅ!» አለው ።

«እዩት ፡ ደግሞ ፡ ኩራቱን! ለመሆኑ ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ የማልስቀው?»

«ምክንያቱም ፤ ምንም ፡ አባቴ ፡ ብትሆን ፤ ከሳቅህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስክር ፡ እደበድብሃለሁ!»

«እንዴት! አንተ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! የገዛ ፡ አባትህን ፡ ትደበድባለህ?» አለና ፡ ቡልባ ፡ በመገረም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ፈግፈግ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

«አባቴ ፡ ብትሆንስ? ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዲሰድበኝ ፡ አልፈቅድለትም ።»

«ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ድብድብ ፡ የምትገጥመኝ? በቡጢ ፡ ነው?»

«በሆነው ፡ ነገር ።»

«ደግ ፤ እንግዲያው ፡ በቡጢ ፡ ይሁን ። በቡጢ ፡ ጠብ ፡ እንዴት ፡ ያለህ ፡ ወንድ ፡ እንደሆንህ ፡ እስቲ ፡ አያለሁ!» አለና ፡ ቡልባ ፡ ከናዱን ፡ ሰበሰበ ።

ከዚያ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ተለያይተው ፡ የተገናኙት ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ በናፍቆት ፡ ሰላምታ ፡ ፈንታ ፡ ግብ ፡ ግብ ፡ ገጥመው ፡ በቡጢ ፡ ይቀጣቀጡ ፡ ጀመር ።

ቀጭን ፡ የገረጣና ፡ ገራገር ፡ ፊት ፡ ያላቸው ፡ የልጆቹ ፡ እናት ፡ ተወዳጅ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለመሳም ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኙ ፡ ቀርተው ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ እንደቆሙ ፤ «እዩልኝ ፡ ሰዎቹ! ሽማግሌው ፡ አበደ! ጨርሶ ፡ አዕምሮውን ፡ ነስቶታል! ከዓመት ፡ በላይ ፡ ተለይተውን ፡ የቆዩት ፡ ልጆቻችን ፡ ገና ፡ ከመግባታቸው ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ መደባደብ ፡ ጀመረ!» ብለው ፡ ጮኹ ።

ቡልባም ፡ ቆም ፡ አለና ፤ «እንዴ ፤ ለመሆኑ ፡ ደህና ፡ ይማታልና! ኧረግ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ግሩም ፡ ተደባዳቢ ፡ ሆኗል! እንዲያውም ፡ ባልሞከረው ፡ ይሻለኝ ፡ ኖሯል ። እንግዲህ ፡ ጥሩ ፡ ኮዛክ ፡ ይወጣዋል ፡ ማለት ፡ ነው! መልካም ፡ ነው ፡ ልጄ ፤ እንኳን ፡ ደህና ፡ መጣህ! አሁን ፡ አባትህን ፡ መሳም ፡ ትችላለህ!» አለና ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ ተቃቅፈው ፡ ተሳሳሙ ። «እንዲያ ፡ ነው ፡ ልጄ! ከኔ ፡ ጋር ፡ እንደተማታኸው ፡ ለሌላም ፡ ሰው ፡ ጠንክረህ ፡ መመከት ፡ አለብህ! ለማንም ፡ ቢሆን ፡ ፊት ፡ አትስጥ! ሆኖም ፡ ልብስህ ፡ እጅግ ፡ የሚያስቅ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ይኸ ፡ የተንዘላዘለው ፡ ገመድ ፡ ምንድን ፡ ነው?» ካለ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ታናሸየው ፡ ልጅ ፡ ዞሮ ፤ «አንተ ፡ ሞኝ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ትገተራለህ? በል ፡ ና ፡ አንተ ፡ የውሻ ፡ ልጅ ፤ አትሞክረኝም ፡ እንዴ?» አለው ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታናሸየውን ፡ ልጅ ፡ አቅፈው ፡ ይስሙ ፡ የነበሩት ፡ እናትዮዋ ፤ «ያንተ ፡ ሃሳብ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው! ለመሆኑ ፡ ልጆች ፡ ከገዛ ፡ አባታቸው ፡ ጋር ፡ ሲደባደቡ ፡ ማን ፡ ሰምቶ ፡ ያውቃል? አሁን ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ጠፋና ፡ ነው? እሱ ፡ ለራሱ ፡ ገና ፡ ሕፃን ፤ ደግሞ ፡ ከሩቅ ፡ መንገድ ፡ መግባቱ ፡ ነው ። ደክሞታል ። ማረፍና ፡ እህል ፡ መቅመስ ፡ ሲገባው ፡ አንተ ፡ ካልተደባደብን ፡ ትለዋለህ!» አሉ ። ይህ ፡ እናቱ ፡ የሚከራከሩለት ፡ ሕፃን ፡ የተባለው ፡ ልጅ ፡ እድሜው ፡ ከሃያ ፡ ዓመት ፡ በላይና ፡ ቁመቱም ፡ ሎጋ ፡ ነበር ። እናትዮዋ ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፤ «አሁን ፡ ማረፍና ፡ እህል ፡ መቅመስ ፡ ሲገባው ፡ ድብድብ ፡ ካልገጠምን ፡ ትለዋለህ!» ብለው ፡ በቁጣ ፡ ተናገሩ ።

ቡልባም ፡ «ለካ ፡ ሴታ ፡ ሴት ፡ ነህ! እናትህ ፡ የምትልህን ፡ አትስማት ፡ ልጄ ፤ እሷ ፡ ሴት ፡ ናትና ፡ ምንም ፡ አታውቅም ። ለአንተ ፡ የሚገባህ ፡ ኑሮ ፡ ለጥ ፡ ያለው ፡ መስክና ፡ ጥሩ ፡ ፈረስ ፡ ነው! ተመልከት ፡ ይህን ፡ ጐራዴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የአንተ ፡ እናት ፡ ማለት ። በተማሪ ፡ ቤት ፡ አእምሯችሁን ፡ የሞሉት ፡ መጻሕፍቱ ፡ ፍልስፍናው ፡ ሌላውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማይረባ ፡ ነው!» አለና ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ለማተም ፡ የማይገባ ፡ ቃል ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ። ከዚያም ፡ ቀጠለና ፡ «እንዲያውም ፡ በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ወደ ፡ ዛፖሮዥዬ ፡ ብልካችሁ ፡ ይሻላል ፤ መዘግየት ፡ የለባችሁም ፡ የሚያስፈልጋችሁን ፡

ትምህርት ፡ የምታገኙት ፡ እዚያ ፡ ነው ። ለእናንተ ፡ ትምሀርት ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ እሱ ፡ ነው ። አእምሮም ፡ ልታገኙ ፡ የምትችሉት ፡ እዚያው ፡ ብቻ ፡ ነው!» አላቸው ።

ባልቴትዋ ፡ እናታቸው ፡ በዓይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ተንቀርዞ ፡ «አንድ ፡ ሳምንት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በቤታቸው ፡ የሚቆዩት? ልጆቼ ፡ እቤታቸው ፡ በመምጣታቸው ፡ ለመደሰት ፡ እንኳን ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኙ ፤ ቤታቸውንም ፡ ለማወቅ ፡ ጊዜ ፡ ሳይበቃቸው ፡ እኔም ፡ አይቼ ፡ ሳልጠግባቸው ፡ ሊሔዱ ፡ ነው?» ብለው ፡ በኃዘን ፡ ጠየቁ ።

«በቃሽ ፡ አትነጫነጭብኝ ፡ አንቺ ፡ ባልቴት! አንድ ፡ ኮዛክ ፡ እድሜውን ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ለማሳለፍ ፡ አልተፈጠረም ፤ በቀሚስሽ ፡ ውስጥ ፡ ሸፍነሽ ፡ እንቁላል ፡ እንደምትፈለፍል ፡ ዶሮ ፡ ልትታቀፊያቸው ፡ ትፈልጊያለሽ ። ይልቅስ ፡ አሁን ፡ ሒጅና ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለሽን ፡ ሁሉ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ሥሪልን ። የማር ፡ ብስኩት ፤ ቂጣ ፡ ገንፎ ፡ የምትይውን ፡ ልክስክስ ፡ ምግብ ፡ አንፈልግም ። አንድ ፡ ሙሉ ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ፍየል ፤ አርባ ፡ ዓመት ፡ የቆየ ፡ ጠጅ ፡ እንዲሁም ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ቮድካ ፡ አቅርቢልን ። ደግሞ ፡ በቮድካው ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ቅመማ ፡ ቅመምሽን ፡ እንዳትጨምሪበት ፤ ንጹህ ፡ ቮድካ ፡ ነው ፡ የምንፈልገው ፡» አለና ፡ ቡልባ ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሁሉ ፡ ክፍል ፡ ይበልጥ ፡ ወደሚያምረው ፡ ክፍል ፡ አስገባቸው ። በክፍሉ ፡ ውስጥም ፡ እቃ ፡ ሲያደራጁ ፡ የነበሩ ፡ ሁለት ፡ ቆንጃጅት ፡ ገረዶች ፡ ተጣድፈው ፡ ክፍሉን ፡ ጥለው ፡ ወጡ ። የፈሩበትም ፡ ምክንያት ፡ ቁጡና ፡ ጥብቅ ፡ የሆኑት ፡ ወጣት ፡ ጌቶቻቸው ፡ በመምጣታቸው ፡ የተነሳ ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወንድ ፡ ሲያዩ ፡ እየጮኹ ፡ መሮጥና ፡ ፊታቸውንም ፡ በቀሚሳቸው ፡ እጅጌ ፡ መጋረድ ፡ የሴቶች ፡ ልማድና ፡ ጠባይ ፡ ስለሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ልማድ ፡ ለማክበር ፡ ብለው ፡ ይሆናል ። በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የቤቱ ፡ እቃ ፡ ዘመኑ ፡ በሚጠይቀው ፡ አኳኋን ፡ የተዘጋጀ ፡



ነበር ። አሁን ፡ ያ ፡ ዘመን ፡ በዘፈንና ፡ በተረት ፡ ብቻ ፡ ተቀርጾ ፡ ነው ፡ የሚገኘው ። እነዚህንም ፡ ዘፈኖችና ፡ ተረቶች ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኡክሬይን ፡ የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ እንዳይተባበር ፡ ባደረገችው ፡ የመጀመርያ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ይዘፈኑ ፡ እንደነበሩት ፡ አሁን ፡ በኡክሬይን ፡ ውስጥ ፡ የሚዘፍናቸው ፡ የለም ። የክፍሉ ፡ ግድግዳዎችና ፡ ወለል ፡ እንዲሁም ፡ ጣራው ፡ ልክክ ፡ ብለው ፡ በጭቃ ፡ ተለስነዋል ። ጐራዴዎች ፤ የፈረስ ፡ አለንጋዎች ፤ የወፍና ፡ የአሣ ፡ መረቦች ፤ ጠመንጃዎች ፤ በጌጥ ፡ የተሠሩ ፡ የባሩድ ፡ ቀንዶች ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፈረስ ፡ እቃዎች ፡ በግድግዳ ፡ ላይ ፡ ተሰቅለው ፡ ይታያሉ ። የክፍሉ ፡ መስኮቶች ፡ አሁን ፡ በጥንታዊያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብቻ ፡ እንደሚገኙት ፡ ያሉ ፡ ትንንሽና ፡ በክብ ፡ መስተዋት ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ። የመስኮቶቹና ፡ የበሮቹ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቶአል ። ከአንድ ፡ ጥግ ፡ በኩል ፡ ካለ ፡ ቁም ፡ ሳጥን ፡ ላይ ፡ ከአረንጓዴና ፡ ከሰማያዊ ፡ ቀለማት ፡ ብርጭቆ ፡ የተሠሩ ፡ ማብረጃዎች ፤ የብር ፡ ጽዋዎች ፡ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ የተሠሩ ፡ በዚያ ፡ የዘመቻ ፡ ዘመን ፡ እንደተለመደው ፡ ከብዙ ፡ ሰው ፡ ተላልፈው ፡ ከቡልባ ፡ እጅ ፡ የገቡ ፡ የቬኔጺያን ፤ የቱርክና ፡ የቸርካሲያን ፡ ሥራ ፡ የሆኑ ፡ ብርጭቆና ፡ መለኪያዎች ፡ ተደርድረዋል ። በክፍሉ ፡ ጥግ ፡ ጥግ ፡ ዞረው ፡ የገጠሙት ፡ አግዳሚ ፡ ወንበሮች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ከቅዱሳኑ ፡ ሥዕል ፡ ሥር ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ ጠረጴዛ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ከአጌጡ ፡ ጡቦች ፡ የተሠራው ፡ ምድጃ ፡ እነሆ ፡ ሁሉ ፡ በያመቱ ፡ ለእረፍት ፡ ወደቤታቸው ፡ ለሚመጡት ፡ ለሁለቱ ፡ ወጣቶች ፡ የተለመዱ ፡ ነገሮች ፡ ነበሩ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለእረፍት ፡ ወደቤታቸው ፡ ሲመጡ ፡ ገና ፡ ፈረሶች ፡ ስላልነበሩዋቸውና ፡ እንዲሁም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ፈረስ ፡ መቀመጥ ፡ ከተማሪዎች ፡ ልማድ ፡ ውጭ ፡ ስለነበር ፡ በእግራቸው ፡ ነበር ፡ የሚመጡት ። ለወንድነታቸው ፡ ምልክት ፡ የነበራ

ቸው ፡ ረጅም ፡ ጉንጉን ፡ ጐፈሪያቸው ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ይህንኑንም ፡ መሣሪያ ፡ የያዘ ፡ ማናቸውም ፡ ኮዛክ ፡ ሊጐትተው ፡ መብት ፡ ነበረው ። ቡልባ ፡ ከፈረሶቹ ፡ መንጋ ፡ ሁለት ፡ ሰንጋዎች ፡ መርጦ ፡ የላከላቸው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ በተመረቁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

የልጆቹን ፡ መምጣት ፡ ለማክበር ፡ ሲል ፡ ቡልባ ፡ የመቶ ፡ አለቆችና ፡ እንዲሁም ፡ በሱ ፡ ጓድ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የጦር ፡ ሹማምንት ፡ ጋብዞ ፡ ስለነበር ፡ ከነሱ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ከጥንት ፡ ጓደኛው ፡ ከካፒቴን ፡ ድሚትሮ ፡ ቶቭካች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ «ተመልከቱ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ጐልማሶች ፡ እንደሆኑ! በቅርቡ ፡ ወደ ፡ ሴች ፡ ልልካቸው ፡ ነው ፡» አለና ፡ ወዲያው ፡ ልጆቹን ፡ አስተዋወቀ ። እንግዶቹም ፡ ለቡልባና ፡ ለሁለቱ ፡ ወጣቶች ፡ ደስታቸውን ፡ በመግለጽ ፡ የታሰበው ፡ አሳብ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑንና ፡ ለአንድ ፡ ወጣት ፡ ጐልማሳም ፡ ከዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፡ የበለጠ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ ገለጹላቸው ።

«በሉ ፡ ወንድሞቼ ፡ መኮንኖች ፤ በገበታው ፡ በመረጣችሁት ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጡ ። አሁን ፡ ልጆቼ ፡ መጀመርያ ፡ ትንሽ ፡ ቮድካ ፡ እንጠጣ!» አለ ፡ ቡልባ ። «የእግዚአብሔር ፡ ፀጋ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ይሁን! ለጤናችሁ ፡ ልጆቼ ፤ ለአንተ ፡ ለአስታፕ ፤ ለአንተም ፡ ለአንድሬይ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ አህዛብን ፡ ሁሉ ፡ ቱርኮችን ፡ ታታሮችን ፡ እንዲሁም ፡ የእኛን ፡ እምነት ፡ ከተጋፉ ፡ ፖሊሾችን ፡ ጭምር ፡ እንድትመቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድሉን ፡ ያጐናጽፋችሁ ። በሉ ፡ ጽዋችሁን ፡ አንሱ ፤ ቮድካው ፡ ጥሩ ፡ አይደለም? በላቲን ፡ የቮድካ ፡ ስም ፡ ምንድነው? አየህ ፡ ልጄ ፤ ላቲኖች ፡ ሞኞች ፡ ኖረዋል ። በዓለም ፡ ላይ ፡ እንኳ ፡ ቮድካ ፡ መኖሩን ፡ አያውቁም ። ያ ፡ የላቲን ፡ ጥቅሶች ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ማን ፡ ነበር? እኔ ፡ መቼም ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ እንደነገሩ ፡ ነኝ ፡ ስለዚህ ፡ እርግጠኛ ፡ አይደለሁም ፤ ጐራሲይ ፡ ኖሮአል?»



በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፡ ኦስታፕ ፡ በልቡ ፡ «ይኼው ፡ ነው ፡ እንግዲህ! ይህ ፡ ብልጥ ፡ ሽማግሌ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ሲያውቅ ፡ ውሸቱን ፡ የማያውቅ ፡ ይመስላል ፡» ብሎ ፡ አሰበ ።

ታራስም ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፡ «እንደሚመስለኝ ፡ አርሂማንደሪቱ ፡ ቮድካ ፡ ለማሽተት ፡ እንኳን ፡ አይፈቅድላችሁም ፡ ነበር ። አሁን ፡ እውነቱን ፡ ንገሩኝ ፡ ልጆቼ ፤ ጀርባችሁንና ፡ አካላታችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይገርፏችሁ ፡ አልነበረም? ምናልባትም ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ስታስቸግሩ ፡ በጅራፍ ፡ አልገረፏችሁም ? ይኸውም ፡ በቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ እሮብንና ፡ ሃሙስንም ፡ ጭምር ፡ አልነበረም?» አላቸው ።

ኦስታፕም ፡ «ያለፈ ፡ ነገር ፡ ማውራት ፡ ፍሬ ፡ የለውም ፤ የሆነው ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖአል ፡» ሲል ፡ አንድሬይ ፡ ተቀበለና ፡ «እስቲ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አሁን ፡ ይሞክር? እስቲ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አሁን ፡ ይንካኝ? አንድ ፡ ታታር ፡ ባይ ፡ የኮዛክ ፡ ጐራዴ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ አሳየዋለሁ !» አለ ።

«ጐሽ ፡ ልጄ ፤ ደግ ፡ ተናገርክ ፡ እንዲያውም ፡ ካመጣኸውስ ፡ እኔም ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ መሔዴ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ አብሬአችሁ ፡ ነው ፡ የምሔደው ፤ እዚህ ፡ የምቀረው ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ ነው? ስንዴ ፡ ልዘራ? ቤት ፡ ልጠብቅ? በግና ፡ አሳማ ፡ ላግድና ፡ የሚስቴን ፡ ቀሚስ ፡ ልለብስ ፡ ነው? ኧረ ፡ ወዲያ ፡ በሽታ ፡ ያንሳት! እኔ ፡ ኮዛክ ፡ ነኝ ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ ለኔ ፡ አይደለም ፤ ጦርነት ፡ ባይኖርስ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ? ከእናንተው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ዛፖሮዥዬ ፡ አብሬ ፡ ሔጄ ፡ እደሰታለሁ ። እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ እሔዳለሁ!» አለና ፡ ሽማግሌው ፡ ቡልባ ፡ ወኔው ፡ እየተቀሰቀሰና ፡ እየጋለ ፡ ሔዶ ፡ በመጨረሻ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ቆመና ፡ «እንዲያውም ፡ ነገ ፡ እንሔዳለን! ለምን ፡ እንዘገያለን? እዚህ ፡ የምንጠብቀው ፡ ምን ፡ ጠላት ፡ አለን? ከዚህ ፡ ጐጆ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለን? እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለኛ ፡ ምናችን ፡ ናቸው? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቶፋና ፡

የሥራ ፡ ተሰጥኦ ፡ እጅግ ፡ ያደንቁት ፡ ነበር ። አንድ ፡ ኮዛክ ፡ የማያውቀውና ፡ የማይሞክረው ፡ ምንም ፡ ተግባር ፡ አልነበረም ። የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠምቃል ፤ ሰረገላ ፡ ያንጻል ፤ ባሩድ ፡ ይቀምማል ፡ እንዲሁም ፡ ማናቸውንም ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ከመቻሉም ፡ በላይ ፡ ሲደሰትና ፡ ሲደግስም ፡ ምንም ፡ ወደር ፡ በሌለው ፡ በታወቀው ፡ የሩሲያውያን ፡ ልማድ ፡ ነው ። ዋና ፡ ተግባሩ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ታጥቆ ፡ ተሰለፎ ፡ ከሆነው ፡ ከተመዘገበው ፡ ኮዛክም ፡ ሌላ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ በአስቸኳይ ፡ ፈረሳቸውን ፡ ጭነውና ፡ ታጥቀው ፡ የሚገኙ ፡ ፈቃደኛ ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩ ። ለጦር ፡ ክተት ፡ ለማለት ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ኤሳኡሎቹ ፡ በየገበያው ፤ በየመንደሮችና ፡ በየከተሞች ፡ አደባባዮች ፡ በሰረገላ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ፤

«ስሙ ፡ እናንት ፡ ጠላ ፡ ጠማቂዎችና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጣዮች! የወፈረውን ፡ ገላችሁን ፡ ለዝንቦች ፡ እየመገባችሁ ፡ መቀመጡና ፡ ጠላ ፡ መጥመቁ ፡ በቃችሁ! ኑና ፡ የመኳንንትነት ፡ ዝና ፡ ተጐናጸፉ! እናንተም ፡ አራሾች ፤ ስንዴ ፡ ዘሪዎች ፤ የበግ ፡ እረኞች ፤ እናንት ፡ የሴት ፡ ወዳጆች! ማረሻ ፡ ተከትላችሁ ፡ ስትኩዋትኑ ፡ ቢጫ ፡ ጫማችሁን ፡ ጭቃ ፡ መንከሩ ፡ በቃችሁ ፤ ሴት ፡ ስታባርሩ ፡ የመኳንንትነት ፡ ኃይላችሁን ፡ ማባከኑ ፡ ይበቃል! የኮዛክን ፡ ድል ፡ ለመጐናጸፍ ፡ እነሆ ፡ ሰዓቱ ፡ ደረሰ!»

እነዚህ ፡ ቃላት ፡ ልክ ፡ በደረቀ ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ እንደሚጣል ፡ እሳት ፡ ናቸው ። አራሹ ፡ ማረሻውን ፡ ይሰብራል ፤ መጠጥ ፡ ጠማቂዎች ፡ ደንበጃንና ፡ በርሚሎቻቸውን ፡ ያነካክታሉ ፤ አናጢዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ የሥራ ፡ መሣሪያቸውንና ፡ እቃቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይበታትናሉ ። እያንዳንዱ ፡ ወንድ ፡ ፈረሱን ፡ ይጭናል ። ባጭሩ ፡ የሩሲያውያን ፡ ጠባይ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ አሸብርቆና ፡ ጐልቶ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ታየ ፡ ማለት ፡ ነው ።



ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ጠንካራና ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሆነው ፡ ጠባዩ ፡ የታወቀ ፤ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ አብሮአቸው ፡ ከተፈጠረው ፡ ከነባር ፡ ኮሎኔሎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የፖሊሾች ፡ ጠባይ ፡ በሩሲያውያን ፡ መኳንንት ፡ ላይ ፡ መታየት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ። ብዙዎቹ ፡ መኳንንት ፡ የፖሊሾቹን ፡ አለባበስና ፡ የመንደላቀቅ ፡ የምቾች ፡ ኑሮ ፡ ይቀስሙ ፡ ጀመር ። ይህ ፡ ለቡልባ ፡ አላስደሰተውም ። እሱ ፡ የኮዛኮችን ፡ ቀላል ፡ ኑሮ ፡ ስለሚመርጥ ፡ ከጓደኞቹ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ዋርሶ ፡ ወገን ፡ የሚያዘነብሉትን ፡ ሁሉ ፡ የፖሊሽ ፡ ጌቶቻቸው ፡ ቅምጥሎች ፡ በማለት ፡ ይሸሻቸው ፡ ነበር ። ይህ ፡ የማይደክም ፡ ፍጥረት ፡ ራሱን ፡ ለኦርቶዶክስ ፡ እምነት ፡ ጥበቃ ፡ የተመረጠ ፡ አድርጐ ፡ ይገምት ፡ ነበር ። አንድ ፡ መንደር ፡ በግብር ፡ ሰብሳቢዎቹ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሹማምንት ፡ ተጨቆንን ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ በፈቃዱ ፡ ሔዶ ፡ በተከታዮቹ ፡ ኮዛኮች ፡ እርዳታ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሕግን ፡ ያስከብራል ። ሰይፍ ፡ የሚመዘዝባቸው ፡ ሶስት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ፤ የሚል ፡ ሕግ ፡ አወጣ ። አንደኛ ፡ የፖላንድ ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢዎች ፡ ለኮዛክ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ ሳይሰጡ ፡ ከነክንብንባቸው ፡ የቆሙ ፡ እንደሆን ፤ ሁለተኛ ፡ በኦርቶዶክስ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ዘለፋ ፡ ሲደርስ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የዘር ፡ ልማድ ፡ ሲሻር ፤ ሶስተኛም ፡ ጠላቶቹ ፡ ሙሰልማን ፡ ወይም ፡ ቱርክ ፡ የሆኑ ፡ እንደሆን ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ለክርስቲያንነት ፡ ክብር ፡ ሲባል ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ማንሣት ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ።

አሁን ፡ ገና ፡ ሳይሔድ ፡ ጀምሮ ፡ ሴች ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱን ፡ ልጆቹን ፡ ጦር ፡ ከቀመሱት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንደሚያስተዋውቃቸውና ፡ የልጆቹን ፡ የመጀመሪያ ፡ የጦር ፡ ልምምድም ፡ እንደሚመለከት ፡ በማሰብ ፡ ፈነደቀ ። መጀመሪያ ፡ ለብቻቸው ፡ ሊልካቸው ፡ አስቦ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ትኩስ ፡ ጉልበታቸውንና ፡ ሎጋ ፡ አቋቋማቸውን ፡ ሲመ

ለከት ፡ ጠንካራ ፡ የወንድነት ፡ ውበታቸው ፡ ወኔውን ፡ ቀስቅሶት ፡ ነገውኑ ፡ አብሮአቸው ፡ ሊሔድ ፡ ቆረጠ ። ገና ፡ ከአሁኑ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ የጉዞውን ፡ ድርጅት ፡ ጀምሮ ፡ ለልጆቹ ፡ ፈረሶች ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ አብረዋቸው ፡ የሚሔዱ ፡ አሽከሮች ፡ ይመርጥ ፡ ጀመር ። ኤሳኡል ፡ ቶሽካች ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ጦሩን ፡ ወደ ፡ ሴች ፡ እንዲያዘምት ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶት ፡ በሰፈሩ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ተወከለ ። ቡልባ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ቮድካው ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ትንሽ ፡ ሞቅ ፡ ቢለው ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ አልዘነጋም ። ፈረሶቹ ፡ ውኃ ፡ እንዲጠጡና ፡ ጥሩ ፡ ስንዴ ፡ ፈስሶላቸው ፡ እንዲያድር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ሲመለስ ፡ በመጠኑ ፡ ደክሞት ፡ ነበር ።

«በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆቼ ፤ አሁን ፡ እንተኛ ። ነገም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ እሱ ፡ ያቀደልንን ፡ እንፈጽማለን ። ስለአልጋ ፡ አታስቢ ፡ አሮጊቴ ፤ እውጭ ፡ እንተኛለን ፡» አለ ።

ጨለማው ፡ ገና ፡ መውደቁ ፡ ነው ። ቡልባ ፡ ግን ፡ የሚተኛው ፡ በጊዜ ፡ ስለነበር ፡ በሰፊ ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ተጠቅሎ ፡ እውጭ ፡ በተዘረጋ ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ። ወዲያው ፡ ከመተኛቱም ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደውና ፡ ያንኳርፍ ፡ ጀመር ። የእሱን ፡ ምሳሌ ፡ በመከተል ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ በየስፍራው ፡ የተጋደሙት ፡ ሁሉ ፡ ማንኳረፍ ፡ ቀጠሉ ። ዘበኝነት ፡ እንዲቆም ፡ ታዞ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ወጣቶቹ ፡ ጌቶች ፡ ስለመምጣታቸው ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ጠጥቶ ፡ ስለነበር ፡ ከሌሎቹ ፡ በፊት ፡ እንቅልፍ ፡ የወሰደው ፡ እሱ ፡ ነው ።

አሳዛኝዋ ፡ እናቲቱ ፡ ብቻ ፡ አልተኙም ። ጐን ፡ ለጐን ፡ በተኙት ፡ ልጆቻቸው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አቀርቅረው ፡ በግድ ፡ የለሽነት ፡ የተቆጣጠሩትን ፡ የልጆቹን ፡ ጠጉር ፡ በእጃቸው ፡ እያሻሹና ፡ እያፍታቱ ፡ በእንባቸው ፡ አራሱዋቸው ። በዓይኖቻቸው ፡ በሙሉ ፡ ስሜታቸው ፡ ቢመለከቱዋቸውም ፡ ሊጠግቧቸው ፡ አልቻሉም ። ጡታቸውን ፡ አጥብተው ፡ ታቅፈውና ፡ ተከባክበው ፡ አሳድገዋቸዋል ። አሁን ፡ ግን ፡ አይቶ ፡ ለመጥገብ ፡ እንኳን ፡ ያላቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አጭር ፡ ነው ። «ልጆቼ ፡ ውድ ፡ ልጆቼ! ምን ፡ ትሆኑ ፡ ይሆን? ምን ፡ እድል ፡ ያጋጥማችሁ ፡ ይሆን?» እያሉ ፡ ሲያለቅሱ ፡ በጊዜው ፡ ውብ ፡ በነበረው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በተጨማደደው ፡ ፊታቸው ፡ እንባቸው ፡ ይወርድ ፡ ነበር ። በእውነትም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንደሌላው ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ የእኒህም ፡ ሴትዮ ፡ ስቃይ ፡ ከባድ ፡ ነው ። የፍቅር ፡ ጊዜአቸው ፡ በወጣትነት ፡ ዘመናቸው ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ኮስታራው ፡ ወዳጃቸው ፡ የሚሰቱን ፡ ፍቅር ፡ በጐራዴው ፤ በጦር ፡ ጓደኞቹ ፡ በጦር ፡ ልምምዶቹ ፡ ለወጠው ። በዓመት ፡ ለሁለት ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ተገናኝተው ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ይለያያሉ ። አብረው ፡ በሚኖሩበትም ፡ ጊዜ ፡ የሴትየዋ ፡ ኑሮ ፡ ይኼ ፡ ነው ፡ አይባልም ፤ ስድብና ፡ ዱላም ፡ ሳይቀር ፡ ችለው ፡ ሲኖሩ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚያዩት ፡ የፍቅር ፡ ምልክት ፡ የችሮታ ፡ ያህል ፡ ነበር ። የዛፖሮዥዬ ፡ የነፃነት ፡ ኑሮ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ በሰጣቸው ፡ ሚስት ፡ የለሽ ፡ መኳንንት ፡ መካከል ፡ እኒህ ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፡ ነበሩ ። ደስታ ፡ ያላገኘው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመናቸው ፡ ፈጥኖ ፡ አለፈ ፤ የተዋቡት ፡ ጉንጮቻቸውና ፡ ደረታቸው ፡ በአበባነት ፡ ጊዜያቸው ፡ ሳይሳሙ ፡ ያለጊዜያቸው ፡ ጠውልገው ፡ ተጨማደዱ ። ፍቅራቸው ፤ ስሜታቸው ፤ ማናቸውም ፡ የሴት ፡ ልጅ ፡ የልስላሴ ፡ ተፈጥሮ ፡ ሁሉ ፡ በእናትነት ፡ ፍቅር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተመሰረተ ። በልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ አቀርቅረው ፡ በፍቅር ፡ ስሜትና ፡ በሃዘን ፡ ተጨበጡ ። ተወዳጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ተነጥለዋቸው ፡ ሊሄዱ ፡ ነው ፤ ምናልባት ፡ ወደፊትም ፡ አይገናኙ ፡ ይሆናል! ማን ፡ ያውቃል ፤ ምናልባት ፡ በመጀመሪያው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ታታሮች ፡ አንገታቸውን ፡ ቆርጠው ፡ እናቲቱ ፡ ሰውነታቸው ፡ የት ፡ እንደወደቀ ፡ እንኳን ፡ ሳያውቁ ፡ ይቀሩ ፡ ይሆናል ፡

ወይም ፡ ጆቢራ ፡ ይቧጨቃቸዋል ። እናቲቱ ፡ ግን ፡ ከልጆቻቸው ፡ ለአንዷት ፡ ጠብታ ፡ ደም ፡ እንኳ ፡ ያላቸውን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ቢሰጡ ፡ በወደዱ ። ኃይለኛው ፡ እንቅልፍ ፡ የከደናቸውን ፡ የልጆቹን ፡ ዓይኖች ፡ በማልቀስ ፡ እየተመለከቱ ፡ «ወይኔ ፤ ቡልባ ፡ ሲነቃ ፡ የመነሻቸውን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርገው ፡ ይሆን? ምናልባት ፡ ነገ ፡ ለመነሣት ፡ ያሰበው ፡ ስለሰከረ ፡ ይሆናል ፡» ብለው ፡ አሰቡ ።

ሌሊቱ ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ ጨረቃዋ ፡ ደምቃ ፡ ግቢውንና ፡ በአደባባዩ ፡ የተኙትን ፡ ኮዛኮች ፡ ብርሃን ፡ አልብሳቸዋለች ። ሴትየዋ ፡ ግን ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ከተወዳጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ሳይለዩ ፡ እንቅልፍም ፡ ሳያስቡ ፡ ራስጌያቸው ፡ እንደተቀመጡ ፡ ናቸው ። ፈረሶቹ ፡ የንጋቱ ፡ መቃረብ ፡ ተሰምቶአቸው ፡ ረግተው ፡ ተጋድመዋል ፤ የዛፎቹ ፡ ጫፍ ፡ ጫፍ ፡ በነፋሱ ፡ ኃይል ፡ መንሾካሾክ ፡ ጀምሮ ፡ ሹክሹክታው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ከሥር ፡ ወደአሉት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ደረሰ ። ሴትየዋም ፡ ምንም ፡ ሳይደክማቸው ፡ ምነው ፡ ሌሊቱ ፡ ማለቂያ ፡ ባልኖረው ፡ ብለው ፡ እየተመኙ ፡ እስኪነጋ ፡ ተቀመጡ ። ከወደ ፡ መስክ ፡ ፈረስ ፡ ሲያሽካካ ፡ ተሰማ ፤ የጋለ ፡ ብረት ፡ የመሰለ ፡ ብርሃንም ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ተፈነጠቀ ።

ቡልባ ፡ በድንገት ፡ ነቃና ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። ባለፈው ፡ ማታ ፡ የሰጠውን ፡ ትዕዛዝ ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ አስታወሰ ።

«አሁን ፡ የኔ ፡ ጐልማሶች ፡ እንቅልፍ ፡ ይበቃል! ተነሱ! ፈረሶችን ፡ አጠጡ ፡» አለና ፡ «የታለች ፡ ባልቴትዋ ፡ ሚስቴ? በይ ፡ ፍጠኚ ፡ ባልቴት ፡ ሚስት ፤ የምንበላው ፡ አዘጋጅልን ፤ ረጅም ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ የምንሄደው ፡» ብሎ ፡ አዘዘ ። ሁልጊዜ ፡ ሚስቱን ፡ ሲጠራ ፡ ባልቴት ፡ ሚስት ፡ እያለ ፡ ነበር ።

አሳዛኝዋ ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ የመጨረሻ ፡ ተስፋቸው ፡ ተቆርጦ ፡ በሃዘን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገቡ ። እሳቸው ፡ እንባ ፡ እየ



ተናነቃቸው ፡ ቁርስ ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ቡልባ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተራወጠ ፡ የልጆቹንም ፡ መሣሪያ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ መረጠ ። ተማሪዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ ወዲያው ፡ ተለወጡ ። ጭቃ ፡ ባጠለቀው ፡ ጫማቸው ፡ ፋንታ ፡ በተረከዛቸው ፡ ላይ ፡ የብር ፡ ጠርዝ ፡ ያላቸው ፡ ቀያይ ፡ የሞሮኮ ፡ ጫማዎች ፡ አደረጉ ። እንደ ፡ ጥቁር ፡ ባሕር ፡ ሰፊ ፡ ሆነው ፡ ሺ ፡ ቦታ ፡ የተጣጠፉት ፡ ሱሪዎቻቸውም ፡ ባለወርቀዘቦ ፡ ሽምቀቅ ፡ ነበሩ ። ከሽምቀቆውም ፡ ጐፍላ ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻና ፡ ሌላም ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ተንጠልጥለዋል ። እሳት ፡ ከመሰለ ፡ ቀይ ፡ ጨርቅ ፡ የተሠራ ፡ ካዛኪን ፡ ባጌጠ ፡ ጨርቅ ፡ ድግ ፡ ወገባቸው ፡ ላይ ፡ ታብቶ ፡ በውስጡ ፡ ጌጠኛ ፡ የቱርክ ፡ ሽጉጦችና ፡ ጐራዴዎች ፡ ተሸጠዋል ። ብዙ ፡ ጸሐይ ፡ ያልነካው ፡ ፊታቸው ፡ የበለጠ ፡ ተዋበ ። የወጣትነት ፡ ጺማቸው ፡ ጥቁርነትም ፡ ለፊታቸው ፡ የበለጠ ፡ ንጣት ፡ ሰጥቶት ፡ የጐልማሳነት ፡ ጥንካሬና ፡ ጤና ፡ ይታይባቸው ፡ ነበር ። ከጥቁር ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ የተሠራው ፡ በወርቀዘቦ ፡ ያጌጠ ፡ መለዮአቸውን ፡ ሲደፉ ፡ እጅግ ፡ አማረባቸው ። አዬ ፡ ያልታደሉ ፡ እናት! ልጆቻቸውን ፡ እንዲህ ፡ ሆነው ፡ ሲያዩዋቸው ፡ ምንም ፡ ቃል ፡ ሊናገሩ ፡ ስለአልቻሉ ፡ በዓይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ተንቀረዘዘ ።

«ልጆቼ ፤ አሁን ፡ ሁሉም ፡ ተዘጋጅቶአል ፤ ጊዜ ፡ አናጥፋ! ነገር ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ የክርስቲያንነት ፡ ልማዳችን ፡ እንደሚጠይቀው ፡ መንገድ ፡ ከመጀመራችን ፡ በፊት ፡ ሁላችንም ፡ ቁጭ ፡ ማለት ፡ አለብን ፡ » አለና ፡ ቡልባ ፡ ሲናገር ፡ በአክብሮት ፡ በር ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ የነበሩት ፡ አሽከሮች ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተቀመጠ ።

«በይ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆችሽን ፡ መርቂያቸው ። በጀግንነት ፡ እንዲዋጉ ፤ ለክርስቲያንነት ፡ እምነት ፡ እንዲሰለፉና ፡ የመኳንንትነት ፡ ክብራቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፤ ይህን ፡ ባያደርጉ ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ ሳይ

ተው ፡ እንዲጠፉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸልይላቸው! በሉ ፡ ልጆቼ ፤ ወደ ፡ እናታችሁ ፡ ቅረቡ ፤ የእናት ፡ ጸሎት ፡ ወንድን ፡ ልጅ ፡ በምድርም ፡ ሆነ ፡ በባህር ፡ ይጠብቀዋል ፡» አለ ፡ ቡልባ ።

እንደ ፡ ማናቸውም ፡ እናት ፡ ደካማ ፡ የሆኑት ፡ ሴትዮ ፡ ልጆቻቸውን ፡ አቅፈው ፡ እያለቀሱ ፡ ሁለት ፡ ትንንሽ ፡ የቅዱሳን ፡ ሥእሎች ፡ በአንገታቸው ፡ ላይ ፡ አንጠለጠሉላቸው ።

«የአምላክ ፡ እናት ፡ ትጠብቃችሁ ፡ ... እናታችሁን ፡ አትርሱኝ ፡ ልጆቼ ፡ ... ስለሁናቴአችሁም ፡ ወረቀት ፡ ላኩልኝ ፡ ... » በማለት ፡ ብቻ ፡ እናቲቱ ፡ ንግግራቸውን ፡ ፈጸሙ ።

«በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆቼ ፡ እንነሣ!» አለ ፡ ቡልባ ።

ፈረሶቹ ፡ ተጭነው ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ ቆመዋል ። ቡልባ ፡ ጋኔል ፡ በተባለው ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ሲቀመጥ ፡ እጅግ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ ፈረሱ ፡ ክብደቱ ፡ ተሰምቶት ፡ ተቅበጠበጠ ።

እናትዮዋ ፡ ልጆቻቸው ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ መውጣታቸውን ፡ ሲመለከቱ ፡ አስተያየቱ ፡ ለስለስ ፡ ያለ ፡ ወደመሰላቸው ፡ ወደ ፡ ታናሽየው ፡ ልጅ ፡ ሮጠው ፡ ሄደው ፡ እርካቡን ፡ ያዙና ፡ የኮርቻውን ፡ ቀዳማ ፡ አንቀው ፡ አልለቅ ፡ አሉት ። ወዲያው ፡ ሁለት ፡ ጠብደል ፡ ኮዛኮች ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ አላቀቋቸውና ፡ ተሸክመው ፡ ወደቤት ፡ አስገቡዋቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ መንገደኞቹ ፡ የአጥሩን ፡ በር ፡ ሲወጡ ፡ ሴትዮዋ ፡ እየሮጡ ፡ ተከትለው ፡ ደረሱና ፡ በሚያስደንቅ ፡ ጉልበት ፡ ፈረሱን ፡ አቁመው ፡ አንዱ ፡ ልጃቸው ፡ ላይ ፡ ሲጠመጠሙ ፤ አሁንም ፡ እንደገና ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ። ወጣቶቹ ፡ ኮዛኮች ፡ አባታቸውን ፡ በመፍራት ፡ እንባቸውን ፡ ውጠው ፡ ልባቸው ፡ እየተጨነቀ ፡ ጉዞ ፡ ቀጠሉ ። አባትዮውም ፡ እንዳይታወቅበት ፡ ሸፍኖ ፡ ያዘው ፡ እንጂ ፡ ውስጡን ፡ ሐዘን ፡ ተሰምቶት ፡ ነበር ። ቀኑ ፡ ነፋሻማ ፡ ጭው ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሜዳው ፡ ሣር ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ ያንጸባርቃል ፤



ወፎቹ ፡ ያለስልት ፡ የሚንጫጩ ፡ ይመስላሉ ። ወዲያው ፡ ዞወር ፡ ብለው ፡ ቢመለከቱ ፡ መንደራቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እንደሰመጠ ፡ ሁሉ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚታያቸው ፡ ሁለቱ ፡ የቢታቸው ፡ የጢስ ፡ መውጫዎችና ፡ እንዲሁም ፡ በሕፃንነታቸው ፡ እንደ ፡ ጦጣ ፡ ይንጠለጠሉባቸው ፡ የነበሩት ፡ ዛፎች ፡ ጫፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ የሚታየው ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ የተዘረጋው ፡ ለጥ ፡ ያለ ፡ መስክ ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ መስክ ፡ ጤዛ ፡ ባዘለው ፡ ሣሩ ፡ ላይ ፡ ሲንከባለሉበትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ አንዳንድ ፡ የኮዛክ ፡ ልጃገረድ ፡ ሲጠብቁ ፡ ልጃገረዶቹም ፡ በወጣት ፡ እግራቸው ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጠው ፡ ሲሮጡ ፡ ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አስታወሳቸው ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ የሚታየው ፡ ብቻውን ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የቆመው ፡ የውሃ ፡ መሳቢያ ፡ ገመድ ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ረጅም ፡ ምሰሶ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከኋላቸው ፡ የቀረው ፡ ሜዳ ፡ ከሩቅ ፡ ሲመለከቱት ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ እንዳይታይ ፡ ሸፍኖ ፡ የያዘ ፡ ተራራ ፡ ይመስላል ።

ልጅነት ፡ ደህና ፡ ሰንብች ፤ ጨዋታ ፡ ደህና ፡ ሰንብች ፤ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ!

## ምዕራፍ ፡ ሁለት ።

ሶስቱም ፡ ፈረሰኞች ፡ በፀጥታ ፡ ይጓዛሉ ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ስለአለፈው ፡ ጊዜው ፡ ያስባል ። ያለፈው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ውል ፡ አለ ። ማናቸውም ፡ ኮዛክ ፡ ዕድሜው ፡ ሁሉ ፡ በወጣትነት ፡ ቢፈጸም ፡ ስለሚመኝ ፡ ላለፈው ፡ ለልጅነት ፡ ዘመኑ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዳለቀሰ ፡ ነው ። ቡልባ ፡ ሴች ፡ ሲደርስ ፡ ከቀድሞ ፡ የጦር ፡ ጓደኞቹ ፡ እንማንን ፡ እንደሚያገኝ ፡ ያስብ ፡ ጀመር ። የሞቱትም ፡ ትዝ ፡ እያሉት ፤ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ምነው ፡ ቢኖሩ ፡ ኖሮ ፡ የሚላቸውን ፡

አስታወሰ ። በዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ ተንቀርዝዞ ፡ ሸበቶ ፡ ራሱ ፡
በሃዘን ፡ አቀረቀረ ።
ልጆቹ ፡ በበኩላቸው ፡ ስለሌላ ፡ ነገር ፡ ያስቡ ፡ ነበር ።
የሚያስቡትን ፡ ከመጥቀስ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ስለነሱ ፡ መግ
ለጽ ፡ ሳያስፈልግ ፡ አይቀርም ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ወጣቶች ፡
ገና ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ አመታቸው ፡ ኪዬቭ ፡ ወደሚገኘ
ው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተላኩ ። የተማሩትን ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡
ቢያስረሱዋቸውም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ጨዋ ፡ የሚባሉት ፡ ሰ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማስገባት ፡ እን
ደ ፡ ግዴታ ፡ አድርገው ፡ የሚቆጥሩት ፡ ነገር ፡ ነበር ። እነ
ዚህ ፡ ልጆች ፡ መጀመሪያ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሲገቡ ፡ እንደ ፡
ሌሎቹ ፡ አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ አስቸጋሪዎች ፡ ነበሩ ። ሲቆ
ዩ ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ አስተዳደጋቸው ፡ ተለውጦ ፡ በትም
ህርት ፡ ቤቱ ፡ ሕግ ፡ ታነጸ ። ታላቅየው ፡ አስታፕ ፡ ገና ፡ በመ
ጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ኮብልሎ ፡ ሲሄድ ፡
ተይዞ ፡ ተመለሰና ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ተገርፎ ፡ ትምህርቱን ፡
እንዲቀጥል ፡ ተደረገ ። አራት ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ የመማሪያ ፡ መጽ
ሐፉን ፡ መሬት ፡ ቆፍሮ ፡ ሲቀብር ፡ አራቱንም ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡
ተገርፎ ፡ አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ ተሰጠው ። አምስተኛውንም ፡
መጽሐፍ ፡ እንደገና ፡ በቀበረው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አባቱ ፡
የሚሰጥህን ፡ ትምህርት ፡ ከአላጠናቀቅህ ፡ በቀር ፡ ዛፖሮ
ዥዬን ፡ በፍጹም ፡ አታየውም ፤ እንዲያውም ፡ ገዳም ፡ አስገ
ብቼህ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ እዚያው ፡ እንድትቀመጥ ፡ አደር
ግሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ስለዛተበት ፡ ፈርቶ ፡ ተወው ። ቀደም ፡ ብሎ ፡
እንደተረዳነው ፡ ትምህርትን ፡ በማጥላላት ፡ የተናገረው ፡
ያው ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ራሱ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ መስ
ጠቱ ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ። አስታፕ ፡ አባቱ ፡ በማስፈራራት ፡
ከመከረው ፡ ጀምሮ ፡ በሚጠላቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ ተግ
ቶ ፡ አቀረቀረና ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ጐበዝ ፡ የሚባሉ
ትን ፡ ተማሪዎች ፡ በለጣቸው ።



በዚያን ፡ ዘመን ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ ከኑሮው ፡
ጋር ፡ እጅግ ፡ የተለያየ ፡ ነበር ። ተማሪዎቹም ፡ በኑሮአቸው ፡
አነስተኛውን ፡ ትምህርት ፡ እንኳን ፡ ከጥቅም ፡ ላይ ፡ ለማዋ
ል ፡ ሥፍራ ፡ አያገኙለትም ፡ ነበር ። መምህራኑ ፡ ራሳቸው ፡
ልምምድ ፡ ስለሚያንሳቸው ፡ የተማሩትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡
በማዋል ፡ ረገድ ፡ ከተማሪዎቹ ፡ የባሱ ፡ ነበሩ ። ጥብቅ ፡ የሆ
ነው ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ኑሮና ፡ የልበ ፡ ሙሉ ፡ ጐረምሶች ፡
ብዛት ፡ ከትምህርት ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ተግባሮችን ፡
ለመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። መጨቆን ፤
ተደጋግሞ ፡ በረሃብ ፡ መቀጣት ፤ እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡
ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ልበ ፡ ሙሉውንና ፡ ጠንካራውን ፡ ጐልማሳ ፡
ኋላ ፡ በዛፖሮዥዬ ፡ እየገነነ ፡ ወደሚሄደው ፡ የግድ ፡ የለሽነት ፡
ጠባይ ፡ ይመሩታል ። የተራቡት ፡ ተማሪዎች ፡ በኪዬቭ ፡ መን
ገዶች ፡ ሲዘዋወሩ ፡ ለሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ስጋት ፡ ነበሩ ። በገበያ ፡
ተቀምጠው ፡ ዳቦ ፤ የዱባ ፡ ፍሬና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮ
ች ፡ የሚሸጡት ፡ ሴቶች ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ ሲያልፍ ፡ ያዩ ፡
እንደሆን ፡ ጫጩቶችዋን ፡ ከጠላት ፡ ለማዳን ፡ እንደምታቅ
ፍ ፡ አሞራ ፡ እቃቸውን ፡ ከድነው ፡ ይይዛሉ ። ጓደኞቹን ፡
እንዲጠባበቅ ፡ የተሾመው ፡ የተማሪዎች ፡ አለቃ ፡ ራሱ ፡ የሚ
ያስፈሩ ፡ ትልልቅ ፡ የሱሪ ፡ ኪሶች ፡ ስለነበሩት ፡ እንዲት ፡
ነጋዴ ፡ ሴት ፡ ለመሸጥ ፡ ያስቀመጠችውን ፡ እቃ ፡ ሁሉ ፡ በአ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ከቶ ፡ ለመሄድ ፡ የሚችል ፡ ነበር ።
ተማሪዎቹ ፡ ለብቻቸው ፡ የተለየ ፡ ዓለም ፡ አበጁ ። የሩ
ሲያና ፡ የፖላንድ ፡ መኳንንት ፡ ወደሚገኙበት ፡ ከፍተኛ ፡
ደረጃ ፡ እንዲቀላቀሉ ፡ አይፈቀድላቸውም ። የትምህርት ፡ ቤቱ ፡
አስተዳዳሪ ፡ ራሳቸው ፡ አዳም ፡ ኪሴል ፡ ተማሪዎቹ ፡ ከሕዝ
ብ ፡ እንዳይቀላቀሉና ፡ ጥብቅ ፡ ቁጥጥርም ፡ እንዲደረግባቸው ፡
አዝዘዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትዕዛዝ ፡ አስፈላጊም ፡ ባልሆነ ፡
ነበር ። ምክንያቱም ፡ መምህራኑ ፡ ባይታዘዙም ፡ እንኳን ፡
ጥብቅ ፡ ቁጥጥራቸውን ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ አያውቁም ። ሲጋረ

ፉም ፡ ከጨካኝነታቸው ፡ የተነሣ ፡ የተገረፉት ፡ ተማሪዎች ፡
ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ ቍሪአቸውን ፡ ሲያኩ ፡ ይሰነብቱ ፡ ነበር ።
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለብዙዎቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ትንሽ ፡ በርበሬ ፡ ጣል ፡
ካለበት ፡ ጥሩ ፡ ቮድካ ፡ ብዙም ፡ የጠነከረ ፡ ሆኖ ፡ አይሰማ
ቸውም ፡ ነበር ። አንዳንዶቹም ፡ ፀየጊዜው ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡
መገረፍ ፡ ሲመርራቸው ፡ መንገዱን ፡ ካወቁትና ፡ ተይዘው ፡
ካልተመለሱ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ዛፖሮዥዬ ፡ ጠፍተው ፡
ይሄዳሉ ።

አስታፕ ፡ ቡልባ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ወደ ፡ ትምህርቱና ፡
ወደ ፡ መንፈሳዊነትም ፡ ለማዘንበል ፡ ቢጣጣር ፡ ዱላው ፡
አልቀረለትም ። ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የኮዛ
ክ ፡ ጠንካራ ፡ ጠባዩን ፡ የበለጠ ፡ ከማጠንከር ፡ በቀር ፡ ምንም ፡
አልለወጠውም ። አስታፕ ፡ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ ጥሩ ፡ ጓደኛ ፡
ሆኖ ፡ የሚገመት ፡ ነበር ። የሰውን ፡ አታክልት ፡ ለመዝረፍ ፡
ሌላም ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ተግባሮች ፡ ለመፈጸም ፡ ጓደ
ኞቹን ፡ መርቶአቸው ፡ አያውቅም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡
ዓይነት ፡ የተንኮል ፡ ማሕበር ፡ ሲቋቋም ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡
ቀዳሚ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ቢደርስበት ፡
ጓደኞቹን ፡ አሳልፎ ፡ አይሰጣቸውም ፡ ነበር ። ጓደኞቹን ፡
እንደያሳጣ ፡ የሚያደርገው ፡ ምንም ፡ ሽመልና ፡ አለንጋ ፡
አይገኝም ። ከድብድብና ፡ ይህን ፡ ከመሳሰሉ ፡ የጦርነት ፡
ተግባሮች ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ተንኮል ፡ በሃሳቡ ፡ አይገባም ። ለጓ
ደኞቹ ፡ ልቡ ፡ ንጹህና ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ደግና ፡ ሩኅሩኅም ፡
ነበር ። የአሳዛኝዋ ፡ እናቱ ፡ እንባ ፡ ልቡን ፡ ነክቶታል ፤ አሁ
ንም ፡ ያሳዘነውና ፡ አንገቱን ፡ ያስደፋው ፡ ይኼው ፡ ነው ።

የታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ የአንድሬይ ፡ አስተያየት ፡ የነቃ
ና ፡ ከታላቁ ፡ ይበልጥ ፡ እንደመብሰል ፡ ያለ ፡ ነበር ። ትምህ
ርቱን ፡ በፈቃደኝነትና ፡ ያለችግር ፡ ነው ፡ የዘለቀው ። ከወን
ድሙ ፡ ይበልጥ ፡ ብልጥና ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ የአደገኛ ፡ ተንኮ
ል ፡ መሪ ፡ ነበር ። ብልጠቱም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከቅጣት ፡



ያድነዋል ፤ ወንድሙ ፡ አስታፕ ፡ ግን ፡ መሽቆጥቆጥን ፡ በመጥ
ላት ፡ ይቅርታ ፡ ለመለመን ፡ በፍጹም ፡ ሳያስብ ፡ ወዲያው ፡
ኮቱን ፡ አውልቆ ፡ ለመገረፍ ፡ ይጋደማል ። አንድሬይም ፡ የጀ
ብዱ ፡ ፍላጐት ፡ በልቡ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይነዳል ። ነገር ፡ ግን ፡
የሱ ፡ ልብ ፡ ለሌላ ፡ ስሜቶችም ፡ ክፍት ፡ ነበር ። አሥራ ፡ ስም
ንተኛ ፡ ዓመቱን ፡ ሲያልፍ ፡ በፍቅር ፡ ስሜቱ ፡ መጋል ፡ ጀ
መረ ። ሴት ፡ በሕልሙ ፡ መምጣት ፡ አዘወተረች ። የፍልስ
ፍና ፡ ክርክር ፡ በሚደረግበት ፡ በትምህርት ፡ ሰዓትም ፡ ንጹህ ፤
የረጋችና ፡ ዓይነ ፡ መልካም ፡ ሆና ፡ ትታየዋለች ። የአጐጠ
ጐጠው ፡ ደረትዋ ፤ የለሰለሰው ፡ ውብ ፡ ክንድዋና ፡ ከቀሚ
ስ ፡ ዘልቆ ፡ የሚታየው ፡ ትከሻዋ ፡ ከዓይኑ ፡ አልለይ ፡ አለ ።
ለጋውን ፡ አካላትዋን ፡ የሚሸፍነው ፡ ቀሚስዋ ፡ እንኳን ፡
ሳይቀር ፡ ሕልም ፡ እየሆነ ፡ ይታየው ፡ ጀመር ። በዚያ ፡ እድ
ሜው ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ከመዝመቱ ፡ በፊት ፡ ስለሴት ፡ ማሰብ ፡
ለአንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሃፍረትና ፡ ውርደት ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡
ይህንን ፡ የወጣትነት ፡ የፍቅር ፡ ስሜቱን ፡ ለጓደኞቹ ፡ አይገል
ጽም ፡ ነበር ። ተማሪ ፡ ቤት ፡ በነበረበት ፡ በመጨረሻው ፡ ዓ
መት ፡ የተንኮል ፡ አድማዎችን ፡ መምራቱን ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡
በኪዬቭ ፡ ከተማ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ በአታክልት ፡ በተከበቡት ፡
ቤቶች ፡ መካከል ፡ ብቻውን ፡ መጓዝ ፡ አዘወተረ ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ የኡክሬኒያንና ፡ የፖሊሽ ፡ መኳንንት ፡ መኖሪያ ፡ ወደ
ነበረው ፡ አሁን ፡ አሮጌው ፡ ኪዬቭ ፡ ወደሚባለው ፡ሰፈርም ፡
ይሄድ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ሰፈር ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ እንደቆ
መ ፡ የአንድ ፡ የፖሊሽ ፡ መኳንንት ፡ ሰረገላ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሲ
ሄድበት ፡ ለትንሽ ፡ ሲስተው ፡ የሚያስፈራ ፡ ጢም ፡ ያለው ፡
የሠረገላው ፡ ነጅም ፡ በያዘው ፡ አለንጋ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡
አቀመሰው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ በንዴት ፡ ገነ
ፈለና ፡ በድፍረት ፡ የሠረገላውን ፡ መሽከርከሪያ ፡ በጠንካ
ራ ፡ እጆቹ ፡ ይዞ ፡ አቆመው ። የሠረገላው ፡ ነጅም ፡ ጠቡን ፡

ልጃገረድ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ወፍራም ፡ አስቀያሚ ፡ ፊት ፡ በመስ
ኮቱ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ።

አሁን ፡ እንድሬይ ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮና ፡ ዓይኖቹን ፡
ከፈረሱ ፡ ጋማ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ የሚያሰላስለው ፡ ይህንኑ ፡
ነበር ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ታላቁ ፡ መስክ ፡ ለምለም ፡ አረን
ጓዴ ፡ አጐናጽፎ ፡ አቅፎአቸው ፡ በዙሪያቸው ፡ ባለው ፡ ረ
ጅም ፡ ሣር ፡ ተውጠው ፡ ከላይ ፡ ዘልቆ ፡ የሚታየው ፡ ጥቁሩ ፡
የኮዛክ ፡ ቆባቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቡልባ ፡ ተውጦበት ፡ ከነበረው ፡ ከግል ፡ አሳቡ ፡ ነቃና ፡
«ምነው ፡ ዝም ፡ አላችሁ ፡ የኔ ፡ ጐልማሶች? እንደ ፡ ባህታዊ ፡
ተከዛችሁሳ! ሃሳባችሁን ፡ ሁሉ ፡ ለሰይጣን ፡ ጣሉለት ! ትን
ባሆአችሁን ፡ አቀጣጥሉና ፡ ፈረሶቻችንን ፡ ኮልኩለን ፡ እን
ደወፍ ፡ እንብረር!» አለ ።

ኮዛኮቹ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ቀስቅሰው ፡ በጓሣው ፡ ውስጥ ፡
ጠለሙ ፡ ጥቁር ፡ ቆባቸውም ፡ እንኳን ፡ ተሰወረ ። ጋልበው ፡
ለማለፋቸው ፡ የነበረው ፡ ምልክት ፡ ጥሰውት ፡ ያለፉት ፡ ሳር ፡
ብቻ ፡ ነበር ።

ፀሐይዋ ፡ ከፍ ፡ ብላ ፡ ሜዳውን ፡ በሞቃት ፡ ብርሃንዋ ፡
አልብሳዋለች ። ጭፍግግ ፡ ያለው ፡ ሃሣብ ፡ ሁሉ ፡ ከኮዛኮቹ ፡
አእምሮ ፡ ጠፍቶ ፡ ሔዶ ፡ ልባቸው ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ይርገበ
ገብ ፡ ጀመር ።

ሜዳው ፡ ከፊታቸው ፡ እየተዘረጋ ፡ ሲሔድ ፡ የበለጠ ፡
ያማረ ፡ ሆነ ። አሁን ፡ ኖቮሮሲያ ፡ የሚባለው ፡ እስከ ፡ ጥቁር ፡
ባህር ፡ ያለው ፡ ደቡባዊ ፡ አገር ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ድን
ግል ፡ ለምለም ፡ መስክ ፡ ነበር ። ያን ፡ ወሰን ፡ የሌለውን ፡ ለጥ ፡
ያለ ፡ መስክ ፡ ምንም ፡ ማረሻ ፡ ገና ፡ አልነካውም ። እንደ ፡
ጫካ ፡ የሚውጠውን ፡ ይህን ፡ ረጃጅም ፡ ሳር ፡ እየጣሱት ፡
የሚያልፉት ፡ ፈረሶች ፡' ብቻ ፡ ነበሩ ። እንደዚያ ፡ ያለ ፡ የተ
ፈጥሮ ፡ ውበት ፡ በየትም ፡ አልነበረም ። የምድርዋን ፡ ገጽ ፡



በሚሊዮን ፡ የሚቆጠሩ ፡ አበቦች ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያሉበት ፡
ወርቅማ ፡ አረንጓዴ ፡ ውቅያኖስ ፡ ያለበሰው ፡ ይመስል ፡ ነ
በር ። ረጃጅምና ፡ ቀጫጭን ፡ በሆኑት ፡ የሳር ፡ ዘለላዎች ፡ መካ
ከል ፡ ሰማያዊ ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለ
ማት ፡ ያላቸው ፡ አበቦች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ብለዋል ፤ ከየት ፡ እን
ደመጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ ስንዴ ፡ በጓ
ሳው ፡ ውስጥ ፡ አፍርቶ ፡ ይታያል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቆቆች ፡
ከሳሩ ፡ ሥር ፡ አንገታቸውን ፡ ብቅ ፡ አድርገው ፡ ይመለከ
ታሉ ። የሺ ፡ አእዋፍ ፡ ዜማ ፡ ሜዳውን ፡ ሞልቶታል ፤ በሰማ
ዩ ፡ ላይ ፡ ጭልፊቶች ፡ በእርጋታ ፡ እያንዣበቡ ፡ ቁልቁል ፡
ያለውን ፡ ሳር ፡ አተኩረው ፡ ይመለከታሉ ። ሰማይና ፡ መሬ
ት ፡ የገጠመ ፡ ከሚመስልበት ፡ ስፍራ ፡ ዝዮች ፡ እየጮኹ ፡ በአ
ጀብ ፡ ሲበሩ ፡ ይታያሉ ። ከሳሩ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ አሞራ ፡
ተነሥታ ፡ በሰማያዊው ፡ አየር ፡ እየታጠበች ፡ በረረች ። ወዲ
ያው ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፡ እስክትመስል ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አየር ፡
ርቃ ፡ ተጓዘች ። አሁን ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ክንፍዋ ፡ በጸ
ሃይ ፡ ብርሃን ፡ ብልጭ ፡ ሲል ፡ ይታያል ። አዬ ፡ መስኩ ፡ አገር ፡
እንዴት ፡ የተዋብክ ፡ ነህ!

መንገደኞቻችን ፡ ለምሳ ፡ የሚቆሙት ፡ ለጥቂት ፡ ደቂ
ቃዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ አጃቢዎቹ ፡ አስር ፡
ኮዛኮች ፡ በእንጨት ፡ ደንበጃኖች ፡ የተሚነውን ፡ ቮድካ ፡ አው
ርደው ፡ ለመጠጫ ፡ የሚያገለግሉትንም ፡ ቅሎች ፡ ያቀርባሉ ።
የሚበሉት ፡ ዳቦ ፡ ወይም ፡ የስንዴ ፡ ብስኩት ፡ ከአሳማ ፡ ሥጋ ፡
ጋር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ አንዳንድ ፡ መለኪያ ፡ ቮድካ ፡
ይጠጣሉ ። ቡልባ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ሞቅ ፡ እንዲ
ለው ፡ ስለማይፈልግ ፡ ከአንድ ፡ መለኪያ ፡ በላይ ፡ አይፈቅ
ድም ፤ ከዚያ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ጉዞአቸውን ፡ ይቀጥላ
ሉ ። በአመሻሽ ፡ ላይ ፡ የመስኩ ፡ መልክ ፡ ይለወጣል ። ልዩ ፡
ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ያለው ፡ ሰፊ ፡ ገጹ ፡ የጸሐይዋ ፡ ብርሃን ፡ እየ
ሸሸ ፡ ሲሔድ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አብሮ ፡ ይደብዛል ። ጥቁር ፡ አረ

ንጓዴ ፡ ቀለም ፡ የተቀባ ፡ በሚመስለው ፡ ሜዳ ፡ ላይም ፡ ጭጋግ ፡ ይዘረጋል ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ እየአንዳንዱ ፡ አበባና ፡ እጽዋት ፡ ሁሉ ፡ መአዛቸውን ፡ ይተነፍሳሉ ። በታላቅ ፡ ብሩሽ ፡ የተቀቡ ፡ የሚመስሉ ፡ ጽጌረዳ ፡ ቀለምና ፡ ወርቅማ ፡ መስመሮች ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ተዘርግተው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ስስና ፡ ነጭ ፡ ቁርጥራጭ ፡ ደመና ፡ ይታያል ። ንጹህና ፡ አስደሳች ፡ አየር ፡ እንደ ፡ ለስላሳ ፡ የባህር ፡ ማእበል ፡ የሳሩን ፡ ጫፍ ፡ ጫፍ ፡ በእርጋታ ፡ እያንቀሳቀሰ ፡ ሽው ፡ ይላል ። ቀኑን ፡ ሞልቶት ፡ የነበረው ፡ የሙዚቃ ፡ ድምጽ ፡ ይጠፋና ፡ በምትኩ ፡ ሌላ ፡ ድምጽ ፡ ይሰማል ። ዝጉርጉር ፡ ፍልፈሎች ፡ ከየጉድጓዳቸው ፡ ወጥተው ፤ በኋላ ፡ እግሮቻቸው ፡ ቆመው ፡ ፉጨታቸው ፡ በሜዳ ፡ ያስተጋባል ። የፌንጣዎች ፡ ጫጫታም ፡ እያየለ ፡ ሔደ ፤ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከአንድ ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ኩሬ ፡ የሚመጣ ፡ የባህር ፡ አሞራ ፡ ጩኸት ፡ ቃጭል ፡ መስሎ ፡ ይሰማል።

መንገደኞቹ ፡ ይቆሙና ፡ ለሌሊት ፡ መስፈሪያቸው ፡ ቦታ ፡ ይመርጣሉ ። ከዚያ ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ የብረት ፡ ድስታቸውን ፡ ይጥዱና ፡ ገንፎቻውን ፡ ይቀቅላሉ ። ከእራት ፡ በኋላ ፡ ኮዛኮቹ ፡ የተቀየዱ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ እንዲግጡ ፡ በሜዳው ፡ ይለቁና ፡ በካባቸው ፡ ተጠቅልለው ፡ ይጋድማሉ ። ከዋክብት ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከቷቸዋል ። የሌሊቱ ፡ ጭርታ ፡ ጉልህ ፡ አድርጐ ፡ የሚያሰማውን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ነፍሳት ፡ ድምጽ ፡ ጆሮዎቻቸው ፡ እየሰሙ ፡ እንቅልፍ ፡ ይወስዳቸዋል ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ድንገት ፡ ነቅቶ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፡ የሚያበሩ ፡ ትሎች ፡ ከሩቅም ፡ ከቅርብም ፡ ሲያብለጨልጩ ፡ ያያል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በየመስኩና ፡ በየወንዙ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ የደረቀው ፡ ሳር ፡ በቁዋያ ፡ እሳት ፡ ሲያያዝ ፡ ብርሃኑ ፡ በጨለማው ፡ ሰማይ ፡ ተፈንጥቆ ፡ ይታያል ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ የባህር ፡ አሞሮች ፡ ጥቁር ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ሲበሩ ፡ የጽጌረዳ ፡ አበባ ፡ የመሰለው ፡ ብርሃን ፡ ያ



ርፍባቸውና ፡ ቀይ ፡ መሃረቦች ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚበሩ ፡ ይመስላሉ ።

መንገደኞቹ ፡ ምንም ፡ እንቅፋት ፡ ሳያጋጥማቸው ፡ ቀጠሉ ። በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ ዛፍ ፡ አላለፉም ፤ ያው ፡ የተዋበውና ፡ ነፃው ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ መስክ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ በድኔፐር ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ያለው ፡ ጫካ ፡ ጫፍ ፡ ጫፉ ፡ ሰማይ ፡ ገጠም ፡ መስሎ ፡ ይታያቸዋል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ታራስ ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፡ መስሎ ፡ በሩቁ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ለልጆቹ ፡ እያመለከተ ፡ «ተመልከቱ ፡ ልጆቼ ፤ እዚያ ፡ ወዲያ ፡ አንድ ፡ ታታር ፡ ይጋልባል!» አላቸው ። ትንሹ ፡ ባለጢም ፡ የታታሩ ፡ ፊት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ በጠባብ ፡ ዓይኖቹ ፡ ከሩቅ ፡ ከአስተዋላቸው ፡ በኋላ ፡ አየሩን ፡ እንደውሻ ፡ አሽትቶ ፡ ኮዛኮቹ ፡ አሥራ ፡ ሶስት ፡ መሆናቸውን ፡ ሲገነዘብ ፡ እንደ ፡ ብሆር ፡ ፈርጥጦ ፡ ጠፋ ። ቡልባም ፡ «ታዲያስ ፡ ጐልማሶች! ያን ፡ ታታር ፡ ትደርሱበት ፡ ይሆን? ግን ፡ ቢቀር ፡ ይሻላል ፤ ምንም ፡ አትደርሱበትም ፤ ፈረሱ ፡ ከኔው ፡ ዲያብሎስ ፡ እንኳን ፡ የፈጠነ ፡ ነው ፡» አለ ። ሆኖም ፡ ቡልባ ፡ ድንገት ፡ ደፈጣ ፡ ያጋጠመን ፡ እንደሁ ፡ ብሎ ፡ በመስጋት ፡ መጠንቀቁን ፡ ችላ ፡ አላለም ። ወዲያው ፡ ወደ ፡ ድኔፐር ፡ ወደምትፈሰው ፡ ታታርካ ፡ ወደተባለቸው ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ጋልበው ፡ ሔደው ፤ ዱካቸውን ፡ ለማጥፋት ፡ ከነፈረሶቻቸው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ በዋና ፡ ብዙ ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወጥተው ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ከሶስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከጉዞአቸው ፡ መድረሻ ፡ ተቃረቡ ። አየሩም ፡ ቀዝቀዝ ፡ እያለ ፡ ሔደ ። ድኔፐር ፡ እንደቀረበ ፡ ተሰማቸው ፤ ወዲያው ፡ ከሰማይ ፡ ጋር ፡ የገጠመ ፡ መስሎ ፡ ከሩቅ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ እየተነፈሰና ፡ እየቀረበ ፡ መጥቶ ፡ በመጨረሻ ፡ የምድሩን ፡ ግማሽ ፡ አልብሶ ፡ ታያቸው ። አንድ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ድኔፐር ፡ የሚቀላቀሉት ፡ ፈጣን ፡ ወንዞች ፡ ኃይል ፡ ጨምረውለት ፡ እንደሞገደኛ ፡ ባህር ፡

እየደነፋ ፡ በሰፊው ፡ ይፈሳል ፤ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በመሃሉ ፡ ያሉት ፡ ደሴቶች ፡ ውኃውን ፡ ስለሚገፉት ፡ ከደሴቶቹ ፡ የሚሸሸውን ፡ ውኃ ፡ የሚያግደው ፡ ገደል ፡ ወይም ፡ ጉብታ ፡ ስለሌለ ፡ የበለጠ ፡ ሰፊ ፡ ሆኖ ፡ ከወሰኑ ፡ አልፎ ፡ ይንጣለላል ። ኮዛኮቹ ፡ ከፈረሶቻቸው ፡ ወርደው ፡ በአንድ ፡ ጀልባ ፡ ከተሳፈሩ ፡ በኋላ ፡ ሶስት ፡ ሰዓት ፡ ተጉዘው ፡ ዘላኑ ፡ ሴች ፡ ከሚገኝበት ፡ ከሆርቲጸ ፡ ደሴት ፡ ወደብ ፡ ደረሱ ።

ወደቡ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ከባለጀልባዎች ፡ ጋር ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር ። ኮዛኮቻችን ፡ የፈረሶቻቸውን ፡ መቀነቻ ፡ አጠበቁ ። ታራስ ፡ ቀበቶውን ፡ አጥብቆ ፡ ጢሙን ፡ በኩራት ፡ እየዳሰሰ ፡ ይጀነን ፡ ጀመር ። ጕልማሳ ፡ ልጆቹም ፡ ሽብር ፡ በተቀላቀለው ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ አለባበሳቸውንና ፡ ትጥቃቸውን ፡ አስተካከሉ ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ ተነስተው ፡ ከሴቹ ፡ ግማሽ ፡ ቬርስት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ወደሚገኝ ፡ አንድ ፡ የገጠር ፡ ሰፈር ፡ አመሩ ። ከሰፈሩ ፡ ሲደርሱም ፡ ሃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ አንጠረኞች ፡ በየስፍራው ፡ ብረት ፡ ሲቀጠቅጡ ፡ የመዶሻቸው ፡ ድምጽ ፡ ጆሮአቸውን ፡ አደነቆረው ። ክንዳማ ፡ የሆኑ ፡ ፋቂዎች ፡ በመንገዱ ፡ ዳር ፡ በየበረንዳው ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተቀምጠው ፡ የበሬ ፡ ቆዳ ፡ ይወጥራሉ ። ነጋዴዎች ፡ ከፊታቸው ፡ ብረታ ፡ ብረትና ፡ የባሩድ ፡ እቃ ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ደርድረው ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ። እዚህ ፡ አንድ ፡ አርመን ፡ ዋጋቸው ፡ ውድ ፡ የሆነ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቆቹን ፡ ሰቅሎአል ። እዚያ ፡ አንድ ፡ ታታር ፡ የተከተፈ ፡ የበግ ፡ ሥጋ ፡ በሊጥ ፡ እየጠቀለለ ፡ ይጠብሳል ። አንድ ፡ አይሁድ ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ቮድካ ፡ ከበርሚል ፡ ይቀዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ያዩት ፡ ሰው ፡ እጅና ፡ እግሮቹ ፡ ተዘረጋግተው ፡ ተንጋሎ ፡ መሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ጭው ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ የወሰደውን ፡ የዛፖሮዥያዊ ፡ ኮዛክ ፡ ነው ። ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ ሳያደንቅ ፡ ለማለፍ ፡ አልቻለም ።



«እንዴት ፡ ግሩም ፡ ትይንት ፡ ነው! እንዴት ፡ ያለ ፡ የወንድነት ፡ መልክ ፡ አለው!» ብሎ ፡ በአድናቆት ፡ ጮኸ ።

በእውነትም ፡ ትይንቱ ፡ የጀግንነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ትይንት ፡ ነበር ። መሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ የተዘረጋው ፡ ኮዛክ ፡ የተጎነጎነው ፡ ጐፈሬው ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ይሆናል ፤ ሰፊውን ፡ ሱሪውን ፡ ከአማረ ፡ ቀይ ፡ ጨርቅ ፡ መሰፋቱን ፡ በመናቅና ፡ ከምንም ፡ ባለመቁጠር ፡ በጥቁር ፡ ዘይት ፡ አበላሽቶታል ።

ቡልባ ፡ ይህን ፡ ኮዛክ ፡ ከልቡ ፡ ካደነቀው ፡ በኋላ ፡ በሞያተኞች ፡ በተጣበበ ፡ ቀጭን ፡ መንገድ ፡ ጉዞውን ፡ ይቀጥላል ። የሴቹ ፡ ባልደረቦች ፡ ከመተኮስና ፡ ጦር ፡ ከመሰንዘር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ስለማያውቁ ፡ የሚያለብሱዋቸውና ፡ የሚመግቡዋቸው ፡ ከየዘሩ ፡ የተጠራቀሙት ፡ እነዚህ ፡ ሞያተኞች ፡ ነበሩ ።

በመጨረሻ ፡ ይህን ፡ ሰፈር ፡ አልፈው ፡ ሳር ፡ ክዳን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ታታሮች ፡ ልማድ ፡ ቆዳ ፡ ክዳን ፡ ያሏቸውን ፡ የኮዛክ ፡ ጐጆዎች ፡ ፈንጠር ፡ ፈንጠር ፡ ብለው ፡ ያዩሉ ። በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ባለፉት ፡ ሰፈር ፡ እንዳዩት ፡ ያለ ፡ ባለአጥር ፡ ከበሩም ፡ ላይ ፡ ጥላ ፡ የሚሆን ፡ በረንዳ ፡ ያለው ፡ ቤት ፡ አይታይም ። አንዳንዶቹ ፡ የኮዛኮቹ ፡ ጐጆዎች ፡ ብቻ ፡ በዙሪያቸው ፡ መድፍ ፡ ተጠምዶአል ። አጭር ፡ ሆኖ ፡ የተሠራና ፡ በምንም ፡ ዘበኛ ፡ ያልተጠበቀ ፡ በእንጨትና ፡ በአፈር ፡ ክምር ፡ የተሠራ ፡ ምሽግ ፡ ለግድ ፡ የለሽነት ፡ ድፍረትና ፡ ለጥንቃቄ ፡ ማነስ ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ጥቂቶች ፡ ጠብደል ፡ ኮዛኮች ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻቸውን ፡ እንደጐረሱ ፡ መሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ መንገደኞቹ ፡ ሲያልፉ ፡ በችለተኝነት ፡ ከመመልከት ፡ በቀር ፡ አልተሸበሩም ። ታራስና ፡ ልጆቹ ፡ «እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ጐበዝ!» ብለው ፡ በጥንቃቄ ፡ በመካከላቸው ፡ ሲያልፉ ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ «እንዴት ፡ ዋላችሁ!» በማለት ፡ መለሱላቸው ። በየስፍራው ፡ ተሰብ

ሰበው ፡ የቆሙት ፡ ሰዎች ፡ በጦር ፡ ሜዳና ፡ በማናቸውም ፡ የጀብዱ ፡ ሞያ ፡ የተፈተኑ ፡ ለመሆናቸው ፡ የጠየመው ፡ ፊታቸው ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ሴቹ ፡ ማለት ፡ ይሄ ፡ ነው! እንደ ፡ አንበሳ ፡ ኩሩና ፡ ጠንካራ ፡ የሆኑት ፡ የወንዶች ፡ ሰፈር ፡ ይህ ፡ ነው! ነፃነትና ፡ ኮዛካዊነት ፡ በሞላው ፡ ኡክሬይን ፡ የሚፈሰው ፡ ከዚህ ፡ ፈልቆ ፡ ነው!

መንገደኞቹ ፡ ራዳ ፡ የሚባለው ፡ የኮዛኮች ፡ ሸንጎ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከሚሰበሰብበት ፡ ሰፊ ፡ አደባባይ ፡ ደረሱ ። በዚያ ፡ አደባባይ ፡ አንድ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ በአፉ ፡ በተደፋ ፡ ትልቅ ፡ በርሚል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሸሚዙን ፡ አውልቆ ፡ ቀዳዳውን ፡ ይጠቅማል ። እልፍ ፡ ሲሉ ፡ ሙዚቀኞች ፡ ተሰብስበው ፡ በመሃላቸው ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ሲጨፍር ፡ ተመለከቱ ። ወጣቱ ፡ ጨፋሪ ፡ እየደጋገመ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ። «ሙዚቃውን ፡ ፈጠን ፡ አድርጉት ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ፎማ ፡ እነዚህን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከቮድካው ፡ አትንፈጋቸው!» ፎማ ፡ የተባለው ፡ ኮዛክም ፡ በትልቅ ፡ ዋንጫ ፡ ቮድካ ፡ እየቀዳ ፡ ለሚመጣው ፡ ሁሉ ፡ ይሰጣል ። በወጣቱ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ዙሪያ ፡ አራት ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሸብረክ ፡ ቀና ፡ እያሉና ፡ እንደ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ እየተሽከረከሩ ፡ ይጨፍራሉ ። በጭፈራቸው ፡ መሬቱን ፡ ሲረግጡትም ፡ ሩቅ ፡ ድረስ ፡ ይሰማል ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ጭፈራው ፡ ከሁሉ ፡ የፈጠነና ፡ ጩኸቱም ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ነበር ። የተጎነጎነው ፡ ጸጉሩ ፡ በነፋሱ ፡ ይውለበለባል ፤ ጡንቻማ ፡ ደረቱ ፡ ባዶ ፡ ሲሆን ፡ የለበሰው ፡ ከበግ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራ ፡ ሞቃት ፡ ኮት ፡ ብቻ ፡ ስለነበር ፡ ከሰውነቱ ፡ የሚወርደው ፡ ላብ ፡ በባልዲ ፡ የሚቀዳ ፡ ይመስላል ። ይህን ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «ኮትህን ፡ አውልቀው ፤ በሙቀት ፡ ቀለጥህ ፡ አይደለም ፡ እንዴ !» አለው ፤ ዛፖሮዥያኑ ፡ «የለም ፡ አልችልም ፡» በማለት ፡ ጮኸ ፡ መለሰ ። «ለምን?» «የለም ፡ ተፈጥሮዬ ፡ ነው ፤ አውልቄ ፡ የምጥለውን ፡ ነገር ፡



ሁሉ ፡ ቮድካ ፡ ነው ፡ የምገዛበት!» በውነትም ፡ ጎልማሳው ፡ ቆብም ፡ በኮፍታኑ ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ ጨርቅም ፡ እንዲሁም ፡ ያጌጠ ፡ ባለጥልፍ ፡ መሃረብ ፡ አልነበረውም ። ሁሉም ፡ እንደተለመደው ፡ ሔደዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዘፈኑ ፡ ቦታ ፡ ሕዝቡ ፡ እየበረከተ ፡ ሔደ ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በጭፈራው ፡ ተካፋይ ፡ ሆኑ ። ከተመልካቾቹ ፡ መካከል ፡ ይህን ፡ አስደናቂ ፡ ጭፈራ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የማይነሸጠው ፡ አልነበረም ። ጭፈራው ፡ ከታላቆቹ ፡ መሥራቾቹ ፡ ባገኘው ፡ ስም ፡ ኮዛቾክ ፡ የሚባለው ፡ ጭፈራ ፡ ነው ።

«ምነው ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ ባልሆንኩ ፡ ኖሮ ፡ እኔም ፡ ከጭፈራው ፡ በገባሁ ፡ ነበር!» አለ ፡ ታራስ ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ በጀብዱ ፡ ሞያቸው ፡ በሴቹ ፡ በሞላ ፡ የሚከበሩት ፡ የተጎነጎነው ፡ ጠጉራቸው ፡ የሸበተ ፡ ጠና ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ ብቅ ፡ ይሉ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ታራስ ፡ የሚያውቃቸውን ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ። «አንተ ፡ ነህ ፡ እንዴ ፡ ፔቼሪጺ! እንደምነህ ፡ ኮዞሉፕ!» «ምን ፡ እግር ፡ አመጣህ ፡ ታራስ?» «አንተ ፡ ደግሞ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ ዶሎቶ?» «እንደምነህ ፡ ኪርዱግ! እንደምነህ ፡ ጉስትይ! እንደገና ፡ እንገናኛለን ፡ ብዬ ፡ አላሰብኩም ፡ ነበር ፡ ሬሚኝ!» እያለ ፡ ታራስ ፡ ከነዚህ ፡ ከሩሲያ ፡ መስክ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ጀግኖች ፡ ጋር ፡ ተሳስሞ ፡ ጥያቄ ፡ መጠየቅ ፡ ሲቀጥል ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ያዳምጡት ፡ ነበር ። «ካስያን ፡ እንዴት ፡ ነው? ቦሮዳቭካ ፡ የት ፡ አለ? ኮሎፔርስ? ፔድስቶክ ፡ እንደምነው?» ነገር ፡ ግን ፡ ታራስ ፡ ለጥያቄዎቹ ፡ ያገኘው ፡ መልስ ፡ ቦሮዳቭካ ፡ በቶሎፓን ፡ ተሰቀለ ፤ ኮሎፔር ፡ ከነነፍሱ ፡ እንዳለ ፡ ቆዳው ፡ ተገፍፎ ፡ በኪዚኪርሜን ፡ አቅራቢያ ፡ ሞተ ፤ የፔድስቶክ ፡ ጭንቅላት ፡ በጨው ፡ ታጅሎ ፡ በቶፉ ፡ ወደ ፡ ኮንስታንቲኖፖል ፡ ተልኳል ፡ የሚሉ ፡ መርዶዎች ፡ ነበሩ ። «አዬ ፡ ጉድ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ጥሩ ፡ ኮዛኮች ፡ ነበሩ!» ብሎ ፡ ተከዘ ።

## ምዕራፍ ፤ ሶስት ።

ታራስ ፡ ቡልባና ፡ ልጆቹ ፣ አንድ ፡ ሳምንት ፣ ያህል ፡ አልፎአቸዋል ። አስታጥና ፡ አንድሬይ ፣ በጦር ፡ ትምህርት ፡ ያጠፉት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አጭር ፡ ነበር ። በመሠረቱ ፡ ሴቹ ፣ በጦር ፡ ትምህርት ፡ ረገድ ፡ ለመቸገርና ፡ ጊዜውን ፡ ሊያጠፉ ፡ አይፈቅድም ። የድርጅቱ ፡ ጐልማሶች ፡ የሚሰለጥኑትና ፡ ጦር ፡ የሚለምዱት ፡ በዋናው ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ለዚህም ፡ ሲባል ፡ ኮዛኮቹ ፡ አዘውትረው ፡ ጦርነት ፡ እንደገጠሙ ፡ ነው ። ለኢላማ ፡ ተኩስ ፡ ከመለማመድ ፡ አልፎ ፡ አልፎም ፡ ከፈረስ ፡ እሽቅድድምና ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ አውሬ ፡ ከማባረር ፡ በቀር ፡ ለኮዛኮች ፡ ሌላውን ፡ የጦር ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ ማጥናት ፡ የሚሰለችና ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ሲሆን ፡ ዋናው ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያቸው ፡ መደሰትና ፡ መጨፈር ፡ ነው ።

ሴቹ ፡ ያልተለመደና ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ የጭፈራና ፡ የፈንጠዝያ ፡ ስፍራ ፡ ነበር ። አንዳንዶቹ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ጊዜ ፡ ሲያሳልፉ ፡ ጥቂቶች ፡ ደግሞ ፡ ንግድ ፡ ሲሞክሩ ፡ አብዛኞቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ግን ፡ የዘረፉዋቸው ፡ ንብረቶች ፡ ከነሱ ፡ አልፈው ፡ በነጋዴዎች ፡ እጅ ፡ እስኪገቡና ፡ ገንዘባቸው ፡ ከኪሳቸው ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ከጡት ፡ አንስቶ ፡ እስከማታ ፡ ድረስ ፡ በመፈንጠዝ ፡ ነው ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉት ። ፈንጠዝያቸው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ለዛ ፡ ነበረው ። ስብሰባቸውና ፡ ድግሳቸው ፡ ኃዘናቸውን ፡ በመጠጥ ፡ ለመሸፈን ፡ እንደሚጥሩ ፡ ሰዎች ፡ ያለ ፡ ሳይሆን ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ የእውነተኛ ፡ ደስታ ፡ ድግሥ ፡ ነው ። በዚያ ፡ የፈንጠዝያ ፡ ስብሰባ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማናቸውንም ፡ ችግሩን ፡ ከኋላ ፡ አራግፎ ፡ መምጣት ፡ አለበት ፡ በጠቅላላው ፡ ዋናው ፡ ዓላማው ፡ ያለፈውን ፡ ሕይወቱን ፡ ሁሉ ፡ እንዳልነበረ ፡ አድርጐ ፡ በመጣል ፤ ከላይ ፡ ከተንጣለለው ፡ ሰማይና ፡



ከውስጣዊ ፡ የሕይወት ፡ ደስታቸው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ከሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ ወደ ፡ ነፃው ፡ የዘላንነት ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ መግፋት ፡ ነው ። ይህ ፡ ዓላማ ፡ ነው ፡ ያንን ፡ ታላቅ ፡ የፈንጠዝያ ፡ መንፈስ ፡ ያመነጨው ። ያለሥራ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተጋድመው ፡ የሚያወጉትን ፡ ቀልድና ፡ ጨዋታ ፡ ሰምቶ ፡ ሳይስቁ ፡ ለማለፍ ፡ እጅግ ፡ አዳጋች ፡ ነው ። አንድ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ በስካርና ፡ በፈንጠዝያ ፡ ቢሆንም ፡ ፈንጠዝያው ፡ በመጠጥ ፡ ቤት ፡ እንደሚገኘው ፡ ያለ ፡ የውሸት ፡ ደስታ ፡ የሚሰጥ ፡ አልነበረም ። የኮዛኮች ፡ ኑሮ ፡ በአንድ ፡ ትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ እንደተመደቡ ፡ ተማሪዎች ፡ የተሳሰረ ፡ የጓደኝነትና ፡ የኅብረት ፡ ኑሮ ፡ ነው ። ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በትምህርት ፡ ክፍል ፡ ተጐልቶ ፡ የአስተማሪውን ፡ ወሬ ፡ ሲያዳምጡ ፡ በመዋል ፡ ፈንታ ፡ ኮዛኮቹ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ፈረስ ፡ ጭነው ፡ ለወረራ ፡ ሲዘምቱ ፡ መታየታቸው ፡ ነው ። በትምህርት ፡ ቤታቸው ፡ ኳስ ፡ በሚጫወቱበት ፡ ሜዳ ፡ ምትክ ፡ አንድ ፡ ፈጣን ፡ ታታር ፡ ወይም ፡ ባለአረንጓዴ ፡ ጥምጥም ፡ ቱርክ ፡ ድንገት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ሰልሎት ፡ የሚሔድ ፡ ከድፍረት ፡ የተነሳ ፡ ዘብ ፡ ያልቆመበት ፡ ጠረፍ ፡ ነው ፡ ያላቸው ። በአንድ ፡ በኩልም ፡ ደግሞ ፡ ጐልማሶቹ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ የተሰበሰቡት ፡ ያለፈቃዳቸው ፡ እየተገደዱ ፡ ሲሆን ፡ እዚህ ፡ የመጡት ፡ ግን ፡ ከእናት ፡ ከአባታቸው ፡ ቤት ፡ እየኮበለሉ ፡ እውነተኛውን ፡ የጀግንነት ፡ ኑሮ ፡ በመምረጥ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ስፍራ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ በጀግንነት ፡ ባሕሪያቸው ፡ መሠረት ፡ በኪሳቸው ፡ አንዲት ፡ ኮፔክ ፡ እንኳን ፡ የማያስቀምጡና ፡ ሃብት ፡ ለማከማቸት ፡ የማይጥሩ ፡ ናቸው ። በነዚህ ፡ ጐልማሶች ፡ መካከል ፡ የተማሪ ፡ ቤትን ፡ አለንጋ ፡ በመሰልቸት ፡ ሲኮበልሉ ፡ ከፊደላት ፡ አንዲት ፡ ቀለም ፡ እንኳን ፡ ሳይጨብጡ ፡ የመጡ ፡ ሲኖሩ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ስለሆራስ ፤ ስለሲዘሮና ፡ ስለሮማውያን ፡ ሪፑብሊክ ፡ ታሪክ ፡ የሚ

ያውቁ ፡ የተማሩ ፡ ናቸው ። ኋላ ፡ በፖላንድ ፡ ንጉሥ ፡ አርማ ፡ ሥር ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያገኙ ፡ የጦር ፡ መኮንኖችና ፡ እንዲሁም ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ውለን ፡ ክብራችን ፡ ከጠበቅን ፡ የየትም ፡ ወገን ፡ ብንሆን ፡ ግድ ፡ የለም ፡ በሚል ፡ ዓላማ ፡ የሚመሩ ፡ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ በነዚሁ ፡ በኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ነበሩ ። ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ ሴች ፡ ደርሰን ፡ የጀግና ፡ መኳንንትነት ፡ ደርሰናል ፡ ለማለት ፡ ብቻ ፡ የመጡ ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ማን ፡ የሌለ ፡ አለ? ይህ ፡ የዘመኑ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ነበር ። የወርቅ ፡ ጽዋዎች ፣ የከበሩ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅና ፡ የወርቅ ፡ ሳንቲሞችም ፡ እንዲሁም ፡ ጦርነት ፡ ወዳዶች ፡ በዚህ ፡ ስፈር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቦታ ፡ አያጡም ። ስፍራ ፡ የማይገኝላቸው ፡ ለሴት ፡ ወዳዶች ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አንዲት ፡ ሴት ፡ ከሴች ፡ ዳርቻ ፡ እንኳን ፡ ደርሳ ፡ አታውቅም ። አስታጥና ፡ አንድሬይ ፡ ወደ ፡ ሴቹ ፡ ሲገቡ ፡ ከአዩዋቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ እነማናችሁ ፡ ከየትስ ፡ መጣችሁ ፡ በማለት ፡ ስማቸውን ፡ እንኳን ፡ የጠየቀ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ስላልነበር ፡ ገረማቸው ። አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ ሁናቴአቸው ፡ ሲታይ ፡ ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ ተለይተውት ፡ ወደ ፡ ቆዩት ፡ ቤታቸው ፡ ተመልሰው ፡ የሚገቡ ፡ እንጂ ፡ ለሰፈሩ ፡ እንግዳ ፡ አይመስሉም ። አዲስ ፡ መጪው ፡ መምጣቱን ፡ የሚገልጸው ፡ ለኮሼቮይ ፡ አታማኑ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ግንኙነታቸውም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ።

«እንኳን ፡ ደህና ፡ መጣህ ፡ ወዳጄ! በክርስቶስ ፡ ታምናለህ?»

«እምናለሁ ፡» ይላል ፡ አዲስ ፡ መጪው ።

«በሶስቱ ፡ ሰላሶችስ ፡ ታምናለህ?»

«አዎ ፣ እምናለሁ ።»

«ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትስማለህ?»

«አዎ ።»

«እስቲ ፡ ስታማትብ ፡ እንይህ ።»

አዲስ ፡ መጪውም ፡ ያማትባል ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኮሼቮይው ፡ «መልካም ፣ ሒድና ፡ የመረጥከውን ፡ ጕጆ ፡ ውሰድ ፡» ይልና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ተፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በሴቹ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ጾምና ፡ ሱባኤን ፡ በፍጹም ፡ የማይሞክሩ ፡ ቢሆኑም ፡ በአንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰብስበው ፡ እየጸለዩ ፣ ይህንኑም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመጠበቅ ፡ እስከመጨረሻው ፡ ጠብታ ፡ ደማቸውን ፡ ለማፍሰስ ፡ ዝግጁ ፡ ነበሩ ። ዛፖሮዥያኖቹ ፡ እጃቸው ፡ ከኪሳቸው ፡ የሚያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ያለክርክር ፡ የሚያፈሱ ፡ ስለነበሩ ፡ አንዳንድ ፡ አይሁዶች ፣ አርመኖችና ፡ ታታሮች ፡ በሴቹ ፡ ዳር ፡ ሰፍረው ፡ ይነግዳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ ብልጥ ፡ ነጋዴዎች ፡ መጨረሻቸው ፡ ዘወትር ፡ የጭንቅ ፡ ኑሮ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ገንዘባቸውን ፡ አባክነው ፡ ሲጨርሱ ፡ የነጋዴዎቹን ፡ መደብር ፡ እየሰባበሩ ፡ የፈለጉትም ፡ ሁሉ ፡ በዘረፋ ፡ ይወስዳሉ ።

ሴቹ ፡ ስልሳ ፡ መንደሮች ፡ ሲገኙበት ፡ እያንዳንዱም ፡ መንደር ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ነፃ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ያለና ፡ ከአንድ ፡ የአዳሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው ። ማንም ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ለማበጀት ፡ ፍላጐት ፡ አልነበረውም ። ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ባትኮ ፡ (አባት ፡) ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ በመንደሩ ፡ አለቃ ፡ እጅ ፡ ነው ። የገንዘብ ፣ የልብስ ፣ የምግብ ፣ የሚነደው ፡ እንጨት ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ አላፊው ፡ ይኸው ፡ ባትኮ ፡ ነው ። ገንዘባቸውን ፡ እንዲያስቀምጥላቸው ፡ ለሱ ፡ ይሰጡታል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ መንደረተኞቹ ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ የሚጣሉበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ የጠቡ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ወደ ፡ ዱላ ፡ ይደርስና ፡ የተጣሉት ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ እስኪያሸንፍ ፡ ድረስ ፡ ተቀጣቅጠው ፡ በመጨረሻው ፡ ሁሉም ፡ ያለቂም ፡ አብረው ፡ እየፈነጠዙ ፡ ጠቡ ፡ በዚህ ፡ ይፈጸማል ። በዚህ ፡ በዚህ ፡ ሴቹ ፡ ጐልማሶችን ፡ የሚማርክ ፡ ብዙ ፡ መልክ ፡ ነበረው ።

እስታጥና ፡ አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ የደስታና ፡ የፈንጠዝያ ፡ ውቅያኖስ ፡ በሙሉ ፡ የወጣትነት ፡ ልባቸው ፡ ገብተው ፡ ተደባለቁና ፡ የአባታቸውን ፡ ቤት ፤ ተማሪ ፡ ቤታቸውን ፡ ሌላውንም ፡ ቀድሞ ፡ በአእምሮአቸው ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ወዲያው ፡ ረስተው ፡ አዲሱን ፡ ኑሮአቸውን ፡ ይከታተሉ ፡ ጀመር ። እዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አስደሰታቸው ፤ ረብሻው ፡ ቀላሉ ፡ አስተዳደርና ፡ ሕግጋቱ ፡ አስደሳች ፡ ሆነው ፡ ታዩዋቸው ። ሕግጋቱ ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ቢታይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ላለ ፡ ነፃ ፡ ሪፑብሊክ ፡ አለመጠን ፡ ጥብቅ ፡ ደንቦች ፡ ነበሩ ። ለምሳሌ ፡ ሲሰርቅ ፡ የተገኘ ፡ ኮዛክ ፡ ስርቆቱ ፡ ምንም ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆን ፡ ለጠቅላለው ፡ የኮዛካዊነት ፡ ክብር ፡ አሳፋሪ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚገመት ፡ የሃፍረት ፡ ምሰሶ ፡ ከሚባል ፡ አንድ ፡ ግንድ ፡ ጋር ፡ ይታሰርና ፡ ከጐኑ ፡ አንድ ፡ ከንተሮ ፡ ተጋድሞ ፡ አላፊው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከንተሮውን ፡ እያነሳ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ይቀጠቅጠዋል ። እዳውን ፡ አልከፈለም ፡ ያለ ፡ ኮዛክ ፡ ሲገኝ ፡ ከመድፍ ፡ ጋር ፡ በሰንሰለት ፡ ይታሰርና ፡ አንዱ ፡ ጓደኛው ፡ እዳውን ፡ ከፍሎ ፡ ካላስፈታው ፡ በቀር ፡ እዚያው ፡ እንደታሰረ ፡ ይቀራል ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ አንድሬይን ፡ ያስደነቀው ፡ በነፍስ ፡ ገዳይ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመው ፡ ቅጣት ፡ ነው ። አንድሬይ ፡ ዓይኑ ፡ እያየ ፡ ጉድጓድ ፡ ተቆፍሮ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩ ፡ ጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ከነነፍሱ ፡ ተጥሎ ፡ የሚቹን ፡ ሬሳ ፡ የያዘውም ፡ ሳጥን ፡ እዚያው ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮ ፡ ሁለቱም ፡ አብረው ፡ ሲቀበሩ ፡ ተመለከተ ። ከነሕይወቱ ፡ ከሬሳ ፡ ሳጥን ፡ ጋር ፡ የተቀበረው ፡ ሰው ፡ በሃሳቡ ፡ እየመጣ ፡ አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ አሰቃቂ ፡ ፍርድ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮው ፡ ታውኮ ፡ ነበር ።

በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ጐልማሶች ፡ በኮዛኮቹ ፡ መካከል ፡ መልካም ፡ ስፍራ ፡ ለመያዝ ፡ በቁ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከመንደረተኛ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ጋር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡



ጠቅላላው ፡ ሰፈር ፡ በሙሉ ፡ ድርጅት ፡ ሲነሳ ፡ አብረው ፡ በፈረስ ፡ እየወጡ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ አእዋፍና ፡ የሜዳ ፡ እንስሳት ፡ በማደን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኩሬዎችና ፡ ወደ ፡ ወንዞች ፡ እየሔዱ ፡ ለመንደራቸው ፡ ምግብ ፡ ለማከማቸት ፡ አሣ ፡ በማጥመድ ፡ የሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኑ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ የኮዛክነት ፡ ችሎታቸውን ፡ ለመፈተን ፡ በቂ ፡ ባይሆንም ፡ በእድለኝነትና ፡ በድፍረታቸው ፡ የተነሳ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጐልማሶች ፡ የበለጡ ፡ ሆነው ፡ ይታዩ ፡ ጀመር ። ደፋርና ፡ አነጣጣሪ ፡ ተኳሾች ፡ ነበሩ ። የድኔፐርን ፡ ወንዝ ፡ ፈረሰኛውን ፡ ውኃ ፡ ታግሎ ፡ ማቋረጥ ፡ ከኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉብዝና ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ሁለቱ ፡ ጐልማሶች ፡ ይህንኑ ፡ ፈተና ፡ በሚገባ ፡ በማለፍ ፡ የውሃ ፡ ዋና ፡ ችሎታቸውን ፡ አስመሰከሩ ።

ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ግን ፡ ለልጆቹ ፡ ያሰበላቸው ፡ ሌላ ፡ ዓላማ ፡ ነበረው ። በሚያሳልፉት ፡ የስንፍና ፡ ኑሮ ፡ መንፈሱ ፡ ስለታወከ ፡ ለእውነተኛ ፡ የጀብዱ ፡ ሞያ ፡ ይጓጓ ፡ ጀመር ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ መላውን ፡ የሴች ፡ ሰፈር ፡ ለዘመቻ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያነሳሳው ፡ ብዙ ፡ ሲያሰላስል ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኮሼቮይው ፡ ሔዶ ፤

«ታዲያስ ፡ ኮሼቮይ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ለዘመቻ ፡ የምንሰለፍበት ፡ ጊዜ ፡ አልደረሰምን?» ሲል ፡ በቀጥታ ፡ ጠየቀው ።

ኮሼቮዩም ፡ በአፉ ፡ የያዘውን ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻ ፡ አውጥቶ ፡ «ምንም ፡ የምንዘምትበት ፡ ስፍራ ፡ የለም ፡» አለው ።

«እንዴት ፡ የለም? በታታሮች ፡ ወይም ፡ በቱርኮች ፡ ላይ ፡ ልንዘምት ፡ እንችላለን!»

«በቱርኮችም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በታታሮችም ፡ ላይ ፡ ልንዘምት ፡ አንችልም ፡» አለና ፡ ኮሼቮዩ ፡ እንደገና ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻውን ፡ ነከሰ ።

«ለምን ፡ አንችልም ?»

«ለሱልጣኑ ፣ የሰላም ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ ገብተናል ።»

«ይህ ፣ እንዴት ፣ ይሆናል? እሱ ፣ የማያምን ፣ ነው ፤ የማያምኑትንም ፣ ሁሉ ፣ እንድንቀጣ ፣ አምላክና ፣ ቅዱስ ፣ ትእዛዙ ፣ ይፈቅዱልናል ።»

«የለም ፤ መብት ፣ የለንም ፤ በኃይማኖታችን ፣ ምለን ፣ ቃል ፣ ኪዳን ፣ ባንገባ ፣ ኖሮ ፣ እርግጥ ፣ በተቻለ ፣ ነበር ። አሁን ፣ ግን ፣ በፍጹም ፣ አንችልም ።»

«ለምን ፣ አንችልም? መብት ፣ የለንም ፣ ማለትህ ፣ ምን ፣ ማለትህ ፣ ነው? እኔ ፣ ገና ፣ ጦር ፣ ያልቀመሱ ፣ ሁለት ፣ ወጣት ፣ ልጆቼን ፣ ይገዬ ፣ መጥቼአለሁ ፤ አንተ ፣ ደግሞ ፣ ለዘመቻ ፣ መብት ፣ የለም ፣ ትላለህ ። ዛፖሮዥያኖች ፣ ሊዋጉ ፣ አይችሉም ፣ ማለትህ ፣ ነው?»

«ምንም ፣ ማድረግ ፣ አይቻልም ፣ የተወሰነው ፣ ይህ ፣ ነው ።»

«ታድያ ፣ የኮዛክ ፣ ጉልበት ፣ በከንቱ ፣ ሊጠፋ ፣ ይገባል? አንድ ፣ ወንድ ፣ ለክርስቲያንና ፣ ለሃገሩ ፣ ምንም ፣ ዋጋ ፣ ያለው ፣ ሞያ ፣ ሳይሠራ ፣ እንደውሻ ፣ ይሙት ፣ ሊባል ፣ ነው? ታድያ ፣ መኖራችን ፣ ለምን ፣ ይሆን? ንገረኝ ፣ ለምን ፣ ይሆን? አዋቂ ፣ ሰው ፣ ነህ ፤ ኮሼቮይ ፣ ለመሆን ፣ ያለእውቀትህ ፣ በከንቱ ፣ አልተመረጥክም ። እንግዲያው ፣ በል ፣ እስቲ ፣ ለምን ፣ እንደምንኖር ፣ ንገረኝ?»

ኮሼቮዩ ፣ ለጥያቄው ፣ ምንም ፣ መልስ ፣ አልሰጠው ፤ ከተናገረው ፣ የማይዛባ ፣ ኮዛክ ፣ ነበር ። ለትንሽ ፣ ጊዜ ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ ከቆየ ፣ በኋላ ፣ «የሆነው ፣ ሆኖ ፣ ምንም ፣ ጦርነት ፣ አይደረግም ፡» አለ ።

«ጦርነት ፣ አይደረግም ፣ አልከኝ?» አለና ፣ ታራስ ፣ ዳግመኛ ፣ ጠየቀው ።

«የለም ።»

«ታድያ ፣ ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ማሰብም ፣ ከንቱ ፣ ነው ፣ ማለትህ ፣ ነው?»



«አዎ ፣ ምንም ፣ ጥቅም ፣ የለውም ።»

በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ቡልባ ፣ በልቡ ፣ «ቆይ ፣ አሳይሃለሁ ፣ አንተ ፣ የሰይጣን ፣ ልጅ!» አለና ፣ ከዚያን ፣ ቀን ፣ ጀምሮ ፣ ኮሼቮዩን ፣ ሊበቀለው ፣ ወሰነ ።

ቡልባ ፣ ብዙ ፣ ጓደኞቹን ፣ ሰብስቦ ፣ ከአነጋገራቸው ፣ በኋላ ፣ መጠጥ ፣ በሰፊው ፣ ሲያጠጣቸው ፣ ሞቅ ፣ ያላቸው ፣ ኮዛኮቹ ፣ ራዳውን ፣ ለመሰብሰብ ፣ የሚመታው ፣ ነጋሪት ፣ ወዳለበት ፣ አደባባይ ፣ ተግተልትለው ፣ ሔዱ ። እዚያም ፣ ሲደርሱ ፣ ነጋሪት ፣ መቺው ፣ የመምቻውን ፣ እንጨት ፣ ይዞት ፣ ሔዶ ፣ ስለነበር ፣ ሁሉም ፣ ያገኙትን ፣ ቁራጭ ፣ እንጨት ፣ እያነሱ ፣ ነጋሪቱን ፣ ይደበድቡ ፣ ጀመር ። የነጋሪቱን ፣ ድምጽ ፣ በመስማት ፣ ከሁሉ ፣ በፊት ፣ ወደ ፣ አደባባዩ ፣ የመጣው ፣ ነጋሪት ፣ መቺው ፣ ራሱ ፣ ሲሆን ፣ እሱም ፣ ቁመተ ፣ ረጅም ፣ አንድ ፣ ዓይና ፣ ኮዛክ ፣ ነበር ። ያንኑ ፣ አንዱን ፣ ዓይኑንም ፣ እንቅልፍ ፣ ተጭኖት ፣ ይጨናበሳል ።

«የማን ፣ ደፋር ፣ ነው ፣ ነጋሪቱን ፣ የሚመታ?» አለና ፣ ጮኸ ።

በስካር ፣ ሞቅ ፣ ያላቸው ፣ ሽማግሌዎቹ ፣ ኮዛኮቹም ፤ «ዝም ፣ በል! ዱላህን ፣ ያዝና ፣ እንደታዘዝህው ፣ ነጋሪቱን ፣ መምታት ፣ ነው ፣ ያለብህ ፡» አሉት ። ነጋሪት ፣ መቺው ፣ እንዲህ ፣ ባለው ፣ ሰዓት ፣ መከራከር ፣ የሚያስከትለውን ፣ ነገር ፣ በደንብ ፣ ስለሚያውቅ ፣ በኪሱ ፣ የያዘውን ፣ አጭር ፣ የነጋሪት ፣ መምቻ ፣ እንደታዘዘው ፣ አወጣ ። ነጋሪቱም ፣ ሲጒስም ፣ ዛፖሮዥያኖቹ ፣ ከቀፎ ፣ እንደሚወጣ ፣ ንብ ፣ እየተግተለተሉ ፣ ወጥተው ፣ በአደባባዩ ፣ ዙሪያ ፣ ተሰለፉ ። በመጨረሻም ፣ ኮሼቮዩ ፤ ዳኛው ፤ ኤሳውሉና ፣ ሌሎቹም ፣ ሹማምንት ፣ መጥተው ፣ ቆባቸውን ፣ እያወለቁ ፣ በዙሪያቸው ፣ እጆቻቸውን ፣ በኩራት ፣ አጣምረው ፣ ለቆሙት ፣ ኮዛኮች ፣ ለጥ ፣ ብለው ፣ እጅ ፣ ነሱ ።

ወዲያው ፣ ኮሼቮዩ ፤ «የዚህ ፣ ስብሰባ ፣ ምክንያት ፣ ምን

ድነው? ፍላጐታችሁ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ወዳጆቼ?» በማለት ፡ ሲጠይቅ ፡ ጫጫታና ፡ ስድብ ፡ ዝም ፡ አሰኘው ።

«የስልጣን ፡ በትርህን ፡ አስቀምጥ! አሁኑኑ ፡ አስረክብ ፡ አንት ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! ከእንግዲህ ፡ አንፈልግህም!» እያሉ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ይጮኹ ፡ ጀመር ። አንዳንዶቹ ፡ ሞቅ ፡ ያላላቸው ፡ ኮዛኮች ፡ በዚህ ፡ ሃሳብ ፡ አልተስማሙም ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፡ የሰከረውም ፡ ያልሰከረውም ፡ ይንጫጫ ፡ ጀመር ።

ኮሼቮዩ ፡ ሊናገር ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የተቆጣው ፡ በፈቃዱ ፡ አዳሪ ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተደጋግሞ ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ ፡ ደብድቦ ፡ ሊገድለው ፡ እንደሚችል ፡ ስለሚያውቅ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሳና ፡ የሥልጣን ፡ ምልክት ፡ በትሩን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አጋድሞ ፡ ከሕዝቡ ፡ ተቀላቀለ ።

የቀሩት ፡ ሹማምንትም ፡ «ክቡራን ፡ ሆይ ፤ እኛም ፡ ሥልጣናችንን ፡ እንድናስረክብ ፡ ትፈልጋላችሁን?» ብለው ፡ በመጠየቅ ፡ ሁሉም ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ለማስረከብ ፡ ተዘጋጁ ።

ሕዝቡ ፡ ግን ፡ «የለም ፤ እናንተስ ፡ ቀጥሉ ፤ ኮሼቮዩ ፡ ከባልቴት ፡ ሴት ፡ የማይሻል ፡ ስለሆነ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማስወጣት ፡ ?ፈለግነው ። ኮሼቮይ ፡ እንዲሆን ፡ የምንፈልገው ፡ አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ወንድ ፡ ነው ።» እያሉ ፡ ጮኹ ።

«አሁን ፡ ኮሼቮይ ፡ እንዲሆን ፡ ማንን ፡ ትመርጣላችሁ?»

«ኩኩቤንኮን ፡ ምረጡ!» የሚል ፡ ድምጽ ፡ ከአንድ ፡ ወገን ፡ ይሰማል ።

በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ «ኩኩቤንኮን ፡ አንፈልግም ። እሱ ፡ የእናቱ ፡ ወተት ፡ ከአፉ ፡ ያልደረቀ ፡ ገና ፡ ሕፃን ፡ ነው!» እያሉ ፡ ይጮኻሉ ።

«ሺሎ ፡ ኮሼቮይ ፡ ይሁን ፡ ሺሎን ፡ ምረጡ!»

«የለም ፡ ሺሎ ፡ ክፉ ፡ ወስላታ ፡ ነው ። ይህ ፡ የውሻ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ታታር ፡ ሌባ ፡ ሆኖ ፡ ምን ፡ ኮዛክ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል! ለካራሙ ፡ ሺሎ ፡ ገሃነብ ፡ ይግባ!»



«ቦሮዳትይ! ቦሮዳትይን ፡ ኮሼቮያችን ፡ እናድርግ!»

«ቦሮዳትይን ፡ አንፈልግም ፤ ወዲያ ፡ ገደል ፡ ይግባ!»

ታራስ ፡ ቡልባ ፡ በበኩሉ ፡ እየዞረ ፡ «ለኪርዲያጋ ፡ ጩኹ!» እያለ ፡ ይመክር ፡ ነበር ።

ሕዝቡም ፡ «ኪርዲያጋ! ኪርዲያጋ!» እያለ ፡ ጩኸቱን ፡ ቀጠለ ።

«ቦሮዳትይ! ቦሮዳትይ!»

«ኪርዲያጋ! ኪርዲያጋ!»

«ሺሎ!»

«ሺሎ ፡ ገደል ፡ ይግባ!»

«ኪርዲያጋ!»

ተመራጮቹ ፡ ሰዎች ፡ ከውስጥ ፡ ሆነው ፡ የሚጐትጐቱ ፡ እንዳይመስልባቸው ፡ ስማቸው ፡ ሲጠራ ፡ ወዲያው ፡ ከሕዝቡ ፡ ፈንጠር ፡ እያሉ ፡ ቆሙ ።

«ኪርዲያጋ! ኪርዲያጋ!» የሚለው ፡ ጩኸት ፡ እየገነነ ፡ ሔደ ።

«ቦሮዳትይ!» የሚል ፡ ድምጽም ፡ ይሰማል ።

በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ተመራጮች ፡ ደጋፊዎች ፡ መካከል ፡ የተፈጠረውን ፡ ክርክር ፡ ለመወሰን ፡ ወዲያው ፡ በመራጮቹ ፡ መካከል ፡ ዱላ ፡ ተነሳና ፡ በቡጢ ፡ ከተቀጣቀጡ ፡ በኋላ ፡ የኪርዲያጋ ፡ ወገን ፡ ድል ፡ አደረገ ።

«ሒዱና ፡ ኪርዲያጋን ፡ አምጡት!» ሲባል ፡ ስድስት ፡ የሚሆኑ ፡ ኮዛኮች ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ቮድካ ፡ ጠጥተው ፡ ስለነበር ፡ መራመድ ፡ አቅቶአቸው ፡ እየተወላገዱ ፡ የመመረጡን ፡ ዜና ፡ ለኪርዲያጋ ፡ ለመንገር ፡ ሔዱ ።

ጠና ፡ ያለው ፡ ብልጥ ፡ ኮዛክ ፡ ኪርዲያጋ ፡ ስለሚደረገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማያውቅ ፡ መስሎ ፡ ጐጆው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

«ምን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ ወዳጆቼ?» ሲል ፡ ጠየቃቸው ።

«ና ፤ ኮሼቮይ ፡ እንድትሆን ፡ ተመርጠሃል ።» አሉት ።

«ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፡ ወዳጆቼ! እንዲህ ፡ ያለው ፡ ክብር ፡ ለኔ ፡ ይበዛብኛል ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ብሎ ፡ ኮሼቮይ! ምነው ፡ በሠራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ፡ እንዴ?» እያለ ፡ ተግደረደረ ።

«ና ፡ ነው ፡ እኮ ፡ የምልህ!» አለና ፡ አንዱ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ጮኸበት ።

ሌሎች ፡ ሁለቱ ፡ ደግሞ ፡ ብብትና ፡ ብብቱን ፡ ይዘው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለመከራከር ፡ ቢሞክር ፡ «ምን ፡ ይጐትትሃል ፡ አንተ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! የተሰጠህን ፡ ክብር ፡ መቀበል ፡ ነው ፡ አንት ፡ ውሻ!» በማለት ፡ እየሰደቡ ፡ በርግጫና ፡ በጉሽም ፡ እየጐሻሸሙ ፡ ጐትተው ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ወሰዱት ።

በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ ኪርዲያጋ ፡ አደባባዩን ፡ ከበው ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ቀረበ ።

አቅራቢዎቹም ፡ «ታድያስ ፡ ጐበዝ ፡ ይህ ፡ ኮዛክ ፡ ኮሼቮይ ፡ እንዲሆን ፡ ሁላችሁም ፡ ተቀብላችሁታል? » ብለው ፡ ጠየቁ ።

ሕዝቡም ፡ «ተስማምተናል!» በማለት ፡ ሜዳው ፡ እስኪያስተጋባ ፡ ድረስ ፡ ጮኸ ።

ከሹማምንቱ ፡ አንዱ ፡ የሥልጣን ፡ ምልክት ፡ የሆነውን ፡ በትር ፡ አነሳና ፡ ለአዲሱ ፡ ኮሼቮይ ፡ አበረከተ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኪርዲያጋ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ አልቀበልም ፡ በማለት ፡ ተግደረደረ ። ሹሙ ፡ እንደገና ፡ አበረከተው ። ኪርዲያጋም ፡ አሁንም ፡ እምቢ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ለሶስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲያቀርብለት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ተቀበለ ። ሥልጣኑን ፡ መረከቡ ፡ ሲረጋገጥ ፡ በዚያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ጮኹ ። ሜዳውም ፡ ጮኸታቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ አስተጋባ ። ከዚያ ፡ ጢማቸውና ፡ ጠጉራቸው ፡ የሸበተ ፡ ሽማግሌ ፡ ኮዛኮች ፡ ከሕዝቡ ፡ ነጠል ፡ ብለው ፡ ወጡና ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በዝናብ ፡ የረጠበውን ፡ ጭቃ ፡ አፍሰው ፡ በኪርዲያጋ ፡ ራስ ፡



ላይ ፡ አስቀመጡ ። ጭቃውም ፡ ከጭንቅላቱ ፡ ተንጠፍጥፎ ፡ በጢሙና ፡ በጉንጮቹ ፡ ላይ ፡ እየወረደ ፡ ፊቱን ፡ አለበሰው ። ኪርዲያጋ ፡ ግን ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፡ ስለሰጡት ፡ ክብር ፡ ኮዛኮቹን ፡ አመሰገናቸው ።

በዚህ ፡ መሠረት ፡ የጫጫታ ፡ ምርጫ ፡ ተፈጸመ ። በምርጫው ፡ ውጤት ፡ ከቡልባ ፡ ይበልጥ ፡ የተደሰተ ፡ መኖሩን ፡ እንጃ ። ቡልባ ፡ በቀድሞው ፡ ኮሼቮይ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ቂም ፡ ከመበቀሉም ፡ በላይ ፡ ኪርዲያጋ ፡ በባሕርም ፡ በምድር ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ወታደራዊ ፡ ልፋትን ፡ አብሮት ፡ የተቀበለ ፡ የጥንት ፡ ጓደኛው ፡ ስለነበር ፡ በመመረጡ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ። ወዲያው ፡ ሕዝቡ ፡ ምርጫውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለፈንጠዝያ ፡ ተበታተነና ፡ አስታፕና ፡ አንድሬይ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አይተውት ፡ የማያውቁ ፡ ታላቅ ፡ የፈንጠዝያ ፡ ሁከት ፡ ተመለከቱ ። የመጠጥ ፡ ቤቶች ፡ እየተበረበሩ ፡ ቮድካና ፡ ሌላውም ፡ መጠጥ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፈልበት ፡ ተዘረፈ ። ባለመደብሮቹም ፡ ሕይወታቸውን ፡ ስለአተረፉ ፡ ብቻ ፡ ከመደሰት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ሊያደርጉ ፡ አልቻሉም ። ኮዛኮቹ ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ወታደራዊ ፡ ዘፈን ፡ ሲዘፍኑ ፡ አደሩ ። ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ዘፋኞች ፡ በየመንገዱ ፡ እየዞሩ ፡ ሲዘፍኑ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ በሴቹ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጡ ፡ መዘምራንም ፡ የዛፖሮዥያኑን ፡ ተግባር ፡ ለመቀደስ ፡ ሲያዜሙ ፡ አደሩ ። በመጨረሻ ፡ መጠጡና ፡ ድካሙ ፡ እነዚህን ፡ ብርቱ ፡ ሰዎች ፡ አደከማቸው ። በየስፍራው ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። እዚህ ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ ተቃቅፎ ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ይወድቃሉ ። እዚያ ፡ ብዙ ፡ ኮዛኮች ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ተደራርበው ፡ ተከምረዋል ። አንዱ ፡ ደግሞ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ የሚተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ይመርጣል ። ከሁሉም ፡ ብርቱ ፡ የሆነው ፡ ጠንካራ ፡ ኮዛክ ፡ አሁንም ፡ ስልት ፡

የሌለው ፡ ዘፈን ፡ እያጉተመተመ ፡ ጥቂት ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ስካሩ ፡ አሸንፎት ፡ ወደቀ ።

አሁን ፡ ሴቹ ፡ በሞላ ፡ እንቅልፍ ፡ ተኛ ።

## ምዕራፍ ፡ አራት ።

በማግሥቱ ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ከአዲሱ ፡ ኮሼቮይ ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ዛፖሮዥያኖቹን ፡ ወደዘመቻ ፡ ለመላክ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ መመካከር ፡ ጀመረ ። ኮሼቮዩ ፡ ብልጥና ፡ ጮሌ ፡ ኮዛክ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ዛፖሮዥያኖችን ፡ ጠንቅቆ ፡ ስለሚያውቅ ፡ እንዲህ ፡ በማለት ፡ ንግግሩን ፡ ጀመረ ፤

«መሃላችንን ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ ልንሰብር ፡ አንችልም ፡ ግን ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ አለ ። መሃላችንን ፡ ሳንሰብር ፡ ዘዴ ፡ እንፈልጋለን ። ሕዝቡ ፡ በእኔ ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሆን ፡ በፈቃዱ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ አድርግ ። ይህን ፡ ለማድረግም ፡ ከማንም ፡ ይልቅ ፡ አንተ ፡ ትሻላለህ ። ከዚያ ፡ እኔና ፡ ሌሎቹ ፡ ሹማምንት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ እንዳላወቅን ፡ ሆነን ፡ ሮጠን ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ እንሔዳለን ።»

ይህን ፡ በተነጋገሩ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነጋሪቱ ፡ መመታት፡ ጀመረ ። ኮዛኮቹ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስካርና ፡ ድካም ፡ ቢሰማቸው ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ተሰበሰቡ ። አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ የኮዛክ ፡ ቆቦች ፡ በአደባባዩ ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ ። «ማን ፡...? ለምን ፡ ...? ምንድነው ፡ ነገሩ?» እያሉ ፡ ያጉረመርሙ ፡ ነበር ። ግን ፡ ማንም ፡ መልስ ፡ አልሰጣቸው ። በመጨረሻ ፡ ከየስፍራው ፤ «የኮዛክ ፡ ጉልበታችን ፡ በከንቱ ፡ ተበላሸ ፤ ጦርነት ፡ የለም! አለቆቻችን ፡ እየሰነፉ ፡ ሔዱ ፤ ዓይኖቻቸውንም ፡ ሞራ ፡ ሸፈነው! በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ጠፋ!» የሚል ፡ የቁጣ ፡ ድምጽ ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ። ሌሎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በመጀመሪያ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ከአዳመጡ ፡ በኋላ ፤ «በእውነትም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ የለም!» በማለት ፡ ሁሉም ፡ ተያይዘው ፡ ማጉረምረም ፡ ቀጠሉ ። ሹማምንቶቹም ፡ ነገሩን ፡ ያላወቁ ፡ መስለው ፡ ሲገረሙ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ኮሼቮይ ፡ ነጠል ፡ ብሎ ፡ «ፍቀዱልኝ ፡ ወንድሞቼ ፡ አንድ ፡ ንግግር ፡ ላድርግ ፡» አለ ።

«በል ፡ ተናገር!»

«የንግግሬ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የተከበራችሁት ፡ ወንድሞቼ ፡ ከኔ ፡ ይበልጥ ፡ ብታውቁት ፡ ብዙ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ከየአይሁዱ ፡ የመጠጥ ፡ መደብርና ፡ እንዲሁም ፡ ከራሳቸው ፡ ወንድሞች ፡ በመበደር ፡ ዕዳ ፡ ስለዋጣቸው ፡ አሁን ፡ ከየትም ፡ ሥፍራ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ በዱቤ ፡ ሊያገኙ ፡ አልቻሉም ። ዳግመኛም ፡ ልገልጽላችሁ ፡ የምፈልገው ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ የማያውቁ ፡ ብዙ ፡ ጐልማሶች ፡ እንዳሉ ፡ ሲሆን ፡ ወዳጆቼ ፡ እናንተም ፡ እንደምታውቁት ፡ ማንም ፡ ወጣት ፡ ያለጦር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። አንድ ፡ ከሃዲ ፡ እንኳን ፡ ያልገደለ ፡ እንዴት ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ሊባል ፡ ይቻላል?»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባ ፤ «መልካም ፡ ይናገራል ፡» ብሎ ፡ አሰበ ።

ኮሼቮይ ፡ ወዲያው ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ፤

«ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ስል ፡ ሰላም ፡ ይፍረስ ፡ ማለቴ ፡ አይምሰላችሁ ፤ እውነቱን ፡ ለመግለጽ ፡ ብቻ ፡ ስል ፡ ነው ። ደግሞስ ፡ ያለንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እስቲ ፡ ተመልከቱት ። በእውነቱ ፡ የሚያሳፍረን ፡ ነው ። ሴቹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እርዳታ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዓመታት ፡ ድርጅት ፡ ሲኖር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ መልኩ ፡ ይቅርና ፡ ከውስጥ ፡ እንኳን ፡ ለሥዕሎቹ ፡ ምንም ፡ ማምጃ ፡ የለውም ። ለሥዕሎቹ ፡ ጠርዝም ፡ ማስጌጫ ፡ ብር ፡ አቅልጦ ፡ ለመሥራት ፡ እንኳን ፡ ማንም ፡ የሞከረ ፡ የለም ። ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አንዳንድ ፡ ኮዛኮች ፡ በኑዛዜ ፡ ካወረሱት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ንብረት ፡ የለውም ። አውራሾቹም ፡ ሃብታቸውን ፡ በሙሉ ፡ በቁማቸው ፡

የጠጡበት ፡ ስለሆኑ ፡ የተናዘዙት ፡ ሃብትም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይደለም ። ይህንንም ፡ ስላችሁ ፡ በከሐዲዎቹ ፡ ላይ ፡ እንዝመትባቸው ፡ ማለቴ ፡ አይደለም ። ለሱልጣኑ ፡ የሰላም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተናል ። ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ስንገባ ፡ በሃይማኖታችን ፡ ምለን ፡ ነውና ፡ ብናፈርሰው ፡ ለነፍሳችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ።»

እዚህ ፡ ላይ ፡ ቡልባ ፤ «የዚህ ፡ ሁሉ ፡ መዘላበድ ፡ ትርጉሙ ፡ ምን ፡ ይሆን?» እያለ ፡ ይገረም ፡ ጀመር ።

«ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ ወንድሞቼ ፤ እኛ ፡ ጦርነቱን ፡ ለመጀመር ፡ አንችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። የጨዋነት ፡ ክብራችን ፡ አይፈቅድልንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአረጀው ፡ አእምሮዬ ፡ እንደሚያሳስበኝ ፡ ጐልማሶቻችንን ፡ በጀልባ ፡ ልከን ፡ የአናቶሊያን ፡ ወደብ ፡ ትንሽ ፡ እንዲያስሱ ፡ ማድረግ ፡ እንችል ፡ ይሆናል ። ታዲያስ ፡ ምን ፡ ይመስላችሁአል ፡ ወንድሞቼ?»

«ምራን ፡ እንሒድ ፡ ምራን!» እያለ ፡ ሕዝቡ ፡ ከሁሉም ፡ ወገን ፡ ተንጫጫ ።

«ለሃይማኖታችን ፡ ስንል ፡ ከንዳችንን ፡ ለመንተራስ ፡ ዝግጁ ፡ ነን!»

ኮሼቮይ ፡ ደነገጠ ፤ የሰላሙ ፡ ስምምነት ፡ እንዲፈርስ ፡ ስለማይፈልግ ፡ ሕዝቡን ፡ በሞላ ፡ ለዘመቻ ፡ ለመቀስቀስ ፡ አላሰበም ፡ ነበር ።

«ሌላ ፡ ንግግር ፡ እንዳደርግ ፡ ፍቀዱልኝ ፡ ወንድሞቼ ፡» ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ «በቃህ! የመጀመሪያውን ፡ ጣዕሙን ፡ ታጠፋዋለህ ፡» እያሉ ፡ ጮሁበት ።

«እንዲህ ፡ ካላችሁ ፡ ይሁን ፤ እሺ ፡ እኔ ፡ እንደፈቃዳችሁ ፡ ታዛዥ ፡ ባርያችሁ ፡ ነኝ ። ማንም ፡ ሰው ፡ እንደሚያውቀው ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚለው ፡ የሕዝብ ፡ ድምጽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምጽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከመላው ፡ ሕዝብ ፡ የተሻለ ፡ ምንም ፡ ሸንጐ ፡ የለም ። ግን ፡ አንድ ፡ ያሰብኩት ፡ ነገር ፡ አለ ። ወንድሞቼ ፤ እንደምታውቁት ፡ ሱልጣኑ ፡ የጐ



ልማሶቻችንን ፡ አነስተኛ ፡ ዘመቻ ፡ ያለቅጣት ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ የሚያልፈው ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ ኃይላችንን ፡ አደርጅተን ፡ ተዘጋጅተን ፡ ልንጠብቀው ፡ ይገባል ፤ ማንንም ፡ የምንፈራበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ የለንም ። ወዲህም ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ በሌለንበት ፡ ታታሮች ፡ ሴቹን ፡ ሊወርሩ ፡ ይችላሉ ። እነዚያ ፡ ውሻ ፡ ቱርኮች ፡ ግን ፡ ጌታቸው ፡ ባለበት ፡ ቤት ፡ ደፍረው ፡ አይመጡም ፤ ሆኖም ፡ ከኋላ ፡ ከኋላ ፡ መናከሳቸው ፡ አይቀርም ። እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ እኛ ፡ አሁን ፡ በቂ ፡ ጀልባ ፡ የለንም ፤ ሁሉንም ፡ የሚያዘምት ፡ በቂ ፡ ባሩድም ፡ ተወቅጦ ፡ አልተዘጋጀም ። እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ግን ፡ ለፍላጐታችሁ ፡ አገልጋይ ፡ ባርያ ፡ እንደመሆኔ ፡ መጠን ፡ የሐሳባችሁን ፡ ደጋፊ ፡ ነኝ ።»

ተንኮለኛው ፡ አታማን ፡ ይህንን ፡ ተናግሮ ፡ ዝም ፡ አለ ። ሕዝቡ ፡ በየፊናው ፡ ተከፋፍሎ ፡ ይመካከር ፡ ጀመረ ። የየመንደሩ ፡ አለቆችም ፡ ራስ ፡ ለራስ ፡ ገጥመው ፡ ሸንጐ ፡ ያዙ ። አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ ወኔአቸውን ፡ ለመግታት ፡ ያልቻሉት ፡ ጥቂቶች ፡ ብቻ ፡ ስለነበሩ ፡ ይህ ፡ ጠቢብ ፡ የሆነ ፡ የጥንቃቄ ፡ ምክር ፡ ጸደቀ ።

ወዲያው ፡ ከድኔፕር ፡ ማዶ ፡ ወዳለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ የመሣሪያና ፡ የንብረት ፡ ማከማቻ ፡ ሰዎች ፡ ተላኩ ። የተማረከው ፡ ንብረትና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በከፊል ፡ የሚቀመጠው ፡ በዚያ ፡ ሥፍራ ፡ በቁጠማው ፡ መካከል ፡ ከውኃው ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ ነበር ። የተላኩት ፡ ሰዎች ፡ ወደዚያ ፡ ሲሔዱ ፡ የቀሩት ፡ ወደ ፡ ጀልባዎቹ ፡ ሔደው ፡ ለዘመቻው ፡ ዝግጅት ፡ ጀመሩ ። ከመቅጽበት ፡ ወደቡ ፡ ሕዝብ ፡ ይርመሰመስበት ፡ ጀመር ። አናጢዎች ፡ መጥረቢያቸውን ፡ እየያዙ ፡ መጡ ። ጸሐይ ፡ ያጠየማቸው ፡ ትከሻማ ፤ ጢማቸው ፡ በሽበት ፡ የገረጣ ፤ ጠና ፡ ያሉ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ሱሪአቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ በመግባት ፡ ጀልባዎቹን ፡ በገመድ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ይጐትቱ ፡ ጀመር ። የቀሩት ፡

የደረቁ ፡ ግንዶችና ፡ አዲስ ፡ የተቆረጡ ፡ ዛፎች ፡ እየገቱተቱ ፡ የተሰነጠቁ ፡ ጀልባዎችን ፡ ማደስ ፡ ያዙ ። ጠና ፡ ያሉትና ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ለወጣቶቹ ፡ ሥራውን ፡ ያሳያሉ ፤ የሥራው ፡ ጫጫታ ፡ ከየሥፍራው ፡ አስተጋባ ።

ወዲያው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ጀልባ ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ እየቀረበ ፡ መጣ ። በውስጡ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ገና ፡ ከሩቁ ፡ እጃቸውን ፡ ያወዛውዙ ፡ ነበር ። ሰዎቹም ፡ የተበጣጠሰ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፤ እንዲያውም ፡ ግማሾቹ ፡ ከሸሚዝና ፡ በአፋቸው ፡ ከያዙት ፡ አጫጭር ፡ የትንባሆ ፡ ማጨሻ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ያልነበራቸው ፡ ኮዛኮች ፡ ናቸው ። የመታረዛቸው ፡ ምክንያትም ፡ አንድ ፡ አደጋ ፡ ደርሶባቸው ፡ ወይም ፡ ልብሳቸውን ፡ ሸጠው ፡ እንደፈነጠዙበት ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ዕድሜው ፡ ወደ ፡ ሃምሳ ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ ትከሻማ ፡ አጭር ፡ ኮዛክ ፡ ከሌሎቹ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ እጁን ፡ እያወዛወዘ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ይጮኻል ። ነገር ፡ ግን ፡ ድምጹ ፡ በሠራተኞቹ ፡ ጫጫታ ፡ ተውጦ ፡ አልተሰማም ።

ጀልባዋ ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ ጠጋ ፡ ስትል ፡ ኮሼቮዩ ፤ «ምን ፡ ወሬ ፡ ይዛችኋል?» ብሎ ፡ ጠየቀ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በወደቡ ፡ ዳር ፡ የነበሩት ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ አቁመው ፡ ቀና ፡ አሉ ።

በጀልባው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጠብደል ፡ ኮዛክ ፤ «መጥፎ ፡ ወሬ!» ሲል ፡ መለሰ ።

«ምንድነው ፡ እሱ?»

«ንግግር ፡ እንዳደርግ ፡ ትፈቅዱልኛላችሁ ፡ ወንድሞቼ?»

«በል ፡ ተናገር!»

«ወይስ ፡ ራዳ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ትፈልጋላችሁ?»

«ተናገር ፡ ሁላችንም ፡ እዚህ ፡ ነን ፡» ተባለና ፡ ሕዝቡ ፡ ከያለበት ፡ ተሰበሰበ ።

«በሄትማንቺና[1] ፡ ውስጥ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ተግባር ፡ አልሰማችሁም?»



«ምንድነው ፡ የተፈጸመው?» አለና ፡ አንድ ፡ የመንደር ፡ አለቃ ፡ ጠየቀው ።

«እንዴታ! ምንም ፡ ነገር ፡ እንዳትሰሙ ፡ ታታሮች ፡ ጆሮአችሁን ፡ ወትፈውታል ፡ መሰለኝ ።»

«በላ ፡ የሆነውን ፡ ንገረን ።»

«እዚያ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ነገሮች ፡ ማንም ፡ ተወልዶ ፡ የተጠመቀ ፡ ሰው ፡ አይቶአቸው ፡ የማያውቅ ፡ ናቸው ።»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝቡ ፡ መሃል ፡ አንዱ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ያለቀ ፡ ኮዛክ ፤ «የሆነውን ፡ ነገር ፡ ንገረን ፡ የውሻ ፡ ልጅ!» አለና ፡ ጮኸ ።

«የተቀደሱት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖቻችን ፡ እንኳ ፡ የኛ ፡ ያልሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ መጥቶአል ።»

«እንዴት ፡ ነው ፡ የኛ ፡ ያልሆኑት?»

«በኪራይ ፡ ለአይሁዶች ፡ ተሰጡ ፤ አይሁዱ ፡ በቅድሚያ ፡ ካልተከፈለው ፡ ቅዳሴ ፡ አይደረግም ።»

«ሰውየው ፡ አብድዋል ፡ መሰለኝ!»

«ደግሞ ፡ የተረገመው ፡ ውሻ ፡ አይሁድ ፡ በተቀደሰው ፡ የፋሲካ ፡ መክለፍታችን ፡ ላይ ፡ ባልጸዳ ፡ እጁ ፡ ምልክት ፡ ካላደረገበት ፡ ሊፈተት ፡ አይችልም ።»

«ይህ ፡ ሰው ፡ ይዋሻል ፡ ወንድሞቼ! ያልጸዳ ፡ አይሁድ ፡ በተቀደሰው ፡ የፋሲካ ፡ መክለፍት ፡ ላይ ፡ እርማውን ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም!»

«አዳምጡኝ! ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ሮማውያን ፡ ቀሳውስት ፡ በኡክሬይን ፡ በሞላ ፡ በጋሪ ፡ ሲጋልቡ ፡ ይታያሉ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ችግሩ ፡ ጋሪያቸው ፡ አይደለም ፤ ጉዱ ፡ በፈረስ ፡ ፈንታ ፡ ለጋሪያቸው ፡ መጉተቻ ፡ እርቶዶክስ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ መጫናቸው ፡ ነው ። አዳምጡኝ! ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። እንደሚወራው ፡ የአይሁድ ፡ ሴቶች ፡ ከኛ ፡ ቀሣውስት ፡ መጐናፀፊያ ፡ እየወሰዱ ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ፡ ሰፍተውታል ፡ ይባላል ። ይኸውላችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ በኡክሬይን ፡ የሚ

ሠራው ፡ ሥራ! ታዲያ ፡ እናንተ ፡ እዚህ ፡ በፈንጠዝያ ፡ ተቀምጣችሁ ፡ ደግሞ ፡ ታታሮች ፡ አስደንግጠዋችኋል ፡ መሰለኝ ። ዓይንም ፡ ጆሮም ፡ እንደሌለው ፡ ድንጋይ ፡ ሆናችሁ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ምንም ፡ አታውቁ ።»

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ያዳምጥ ፡ የነበረው ፡ ኮሼቮይ ፡ «ቆይ ፡ ቆይ!» አለ ።

እንዲህ ፡ ባለው ፡ ሰዓት ፡ በመጀመሪያ ፡ ስሜታቸው ፡ ሳይሸነፉ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በቁጣ ፡ እስኪገነፍሉ ፡ ድረስ ፡ ነገሩን ፡ በአዕምሮአቸው ፡ ማሰላሰል ፡ የሁሉም ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ጠባይ ፡ ነበር ። ኮሼቮዩ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ነገሩን ፡ አሰላስሎ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ «ቆይ ፡ እስቲ ፡ ንገረኝ! እናንተ ፡ ምን ፡ ስታደርጉ ፡ ነው ፡ አባቶቻችሁን ፡ ለአጋንንት ፡ ይሰጣቸውና ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ እናንተ ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ነበር? ጐራዴ ፡ የላችሁም? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ፈቀዳችሁ?»

«የፖሊሾቹ ፡ ቁጥር ፡ አምሳ ፡ ሺ ፡ ሲሆን ፡ እናንተስ ፡ ብትሆኑ ፡ ምን ፡ ልታደርጉ ፡ ኖሮአል? ደግሞ ፡ የእኛንም ፡ ኃጢአት ፡ መደበቅ ፡ አይጠቅምም ፡ ከኛውም ፡ መካከል ፡ የነዚያን ፡ ኃይማኖት ፡ የተቀበሉ ፡ አንዳንድ ፡ ውሾች ፡ አልጠፉም ።»

«ሄትማናችሁና ፡ ኰሎኔሎቻችሁ ፡ የት ፡ ነበሩ?»

«በኰሎኔሎቻችን ፡ ላይ ፡ ከደረሰባቸው ፡ ነገር ፡ እምላክ ፡ ይሰውረን!»

«እንዴት?»

«ሄትማናችን ፡ በብረት ፡ ድስት ፡ ተቀቅሎ ፡ ዋርሶ ፡ ወድቆአል ፤ የኰሎኔሎቻችን ፡ ጭንቅላቶቻቸውና ፡ ክንዶቻቸው ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያያቸው ፡ ከአደባባይ ፡ አደባባይ ፡ ይዞራሉ ። ይህ ፡ ነው ፡ በኰሎኔሎቻችን ፡ ላይ ፡ የደረሰባቸው!»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጀመረ ። ኃይለኛ ፡ ሞገድ ፡ ከመነሣቱ ፡ በፊት ፡ ባሕር ፡ ጸጥ ፡ እንደሚል ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፀጥታ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ንግግር ፡ ሲጀምሩ ፡ ወደቡ ፡ በድምጻቸው ፡ ተናወጸ ።



«እንዴት ፡ አይሁዶች ፡ የክርስቲያን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይከራያሉ! ሮማውያን ፡ ቄሶች ፡ እንዴት ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ለጋሪ ፡ መጐተቻ ፡ ይጭኑአቸዋል! እንዴት! ለነዚህ ፡ ለተረገሙ ፡ ካቶሊኮች ፡ ተብሎ ፡ በሩሲያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል! ኮሎኔሎቻችንና ፡ ሄትማናችንን ፡ እንዲህ ፡ እስኪያደርጉዋቸው ፡ ድረስ! የለም ፡ ይህ ፡ አይሆንም ፡ ይህ ፡ አይደረግም!»

እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ በየሥፍራው ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ።

ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ለንዴታቸው ፡ መንገድ ፡ ሰጡት ። ኃይላቸውም ፡ ተሰማቸው ። አሁን ፡ ስሜታቸው ፡ ቀላል ፡ አዕምሮ ፡ ያለው ፡ የተጨዋች ፡ ሕዝብ ፡ ስሜት ፡ ሳይሆን ፡ የጠንካራ ፡ በቀላሉ ፡ የማይናደዱና ፡ ከተናደዱ ፡ ግን ፡ የማይበርዱ ፡ ጥብቅ ፡ ሰዎች ፡ ስሜት ፡ ነው ።

«አይሁዶችን ፡ በሞላ ፡ መስቀል ፡ ነው ፤ ከቄሶቻችን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ለሴቶቻቸው ፡ ቀሚስ ፡ እንዳይሰፉ ፤ በተቀደሰው ፡ የፋሲካ ፡ መክለፍታችን ፡ ላይም ፡ ምልክታቸውን ፡ እንዳያደርጉ ፡ መቀጣት ፡ አለባቸው! እነዚህን ፡ እርጉሞች ፡ ሰብስቦ ፡ ድኔፕር ፡ መጨመር ፡ ነው!» የሚል ፡ ጩኸት ፡ ከሕዝቡ ፡ መሃል ፡ ተሰማ ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ የተናገራቸው ፡ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ የሁሉንም ፡ ደም ፡ ስለአፈላው ፡ በአቅራቢያው ፡ መንደር ፡ ያሉትን ፡ አይሁዶች ፡ ለመፍጀት ፡ ሁሉም ፡ ገሰገሱ ።

ያልታደሉት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በፍርሃት ፡ ተሸብረው ፡ በባዶ ፡ የቮድካ ፡ በርሚሎች ፤ በየምድጃው ፡ በሴቶቻቸው ፡ ቀሚስ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ተደበቁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የትም ፡ ቢገቡ ፡ ከኮዛኮች ፡ አላመለጡም ።

እንደ ፡ አጣና ፡ ረጅምና ፡ ቀጭን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ አይሁድ ፡ ኮዛኮቹ ፡ በደረሱበት ፡ ጊዜ ፡ ከጓደኞቹ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፡

ብሎ ፡ በፍርሃት ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ «የተከበራችሁ ፡ ጌቶቼ! የተከበራችሁ ፡ መኳንንት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፤ አንዲት ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ እንድናገር ፡ ፍቀዱልኝ! ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያል ሰማችሁት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ እንገልጽላች ኋለን!» አለ ።

ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበው ፡ ሰው ፡ የመከራከሪያ ፡ ንግግ ሩን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሁልጊዜ ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆነው ፡ ቡልባ ፡ «ደግ ፡ ነው ፤ ተውአቸው ፡ ይናገሩ ፡» አለ ።

«የተከበራችሁ ፡ መኳንንት! እንደናንተ ፡ ያሉ ፡ መኳን ንት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታይተው ፡ አያውቁም! እንደናንተ ፡ ያለ ፡ ደግ ፡ መልካምና ፡ ጀግና ፡ ሰው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አልተ ፈጠረም! በዛፖሮዥያን ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ብለን ፡ ክፉ ፡ እና ስባለን? በኡክሬይን ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ የሚይዙት ፡ የኛ ፡ ወገ ኖች ፡ አይደሉም!በፍጹም ፡ አይደሉም! እንዲያውም ፡ አይሁ ዶች ፡ አይደሉም ፤ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ ዲያብሎስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያውቀው ፤ ተወግረው ፡ መጣል ፡ የሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው! እዚህ ፡ ያለነው ፡ ማነኛችንም ፡ ይህንኑ ፡ ነው ፡ የም ንለው ። አደለም ፡ ሽሎማ? እውነት ፡ አደለም ፡ ሽሙል?»

በወገኖቻቸው ፡ መካከል ፡ በፍርሃት ፡ ገርጥተው ፡ የቆ ሙት ፡ ሽሎማና ፡ ሽሙል ፡ «እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ እው ነት ፡ ነው!» ሲሉ ፡ መለሱ ።

ረጅሙም ፡ አይሁድ ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፡ «እኛ ፡ ከጠ ላቶቻችሁ ፡ ጋር ፡ ተባብረን ፡ አናውቅም ። ካቶሊኮቹንም ፡ እንደሆን ፡ ልናውቃቸው ፡ እንኳን ፡ አንፈልግም ፤ ጋኔል ፡ እንቅልፍ ፡ ይንሳቸው! እኛና ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ወንድማማ ች ፡ ማለት ፡ ነን ።»

«ምን! ወንድማማች ፡ ናቸው ፡ ዛፖሮዥያኖች? ይህ ፡ አይደረግም ፤ አንት ፡ የተረገምክ ፡ አይሁድ ! ድኔፐር ፡ ውስ ጥ ፡ እንጨምራቸው ፡ ጉበዝ! እኒህን ፡ እርጉሞች ፡ ሁሉንም ፡



ማስመጥ ፡ ነው!» በማለት ፡ ከኮዛኮቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ጮኸ ፡ ተናገረ ።

ወዲያው ፡ እነዚህን ፡ ቃላት ፡ ሲሰሙ ፡ ሁሉም ፡ አይሁ ዶቹን ፡ እየያዙ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ይጨምሩአቸው ፡ ጀመር ። ከየሥፍራው ፡ የሚዘገንን ፡ ጩኸትና ፡ ጫጫታ ፡ ሲሰማ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ግን ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ የሚፍጨረጨሩትን ፡ አይ ሁዶች ፡ እያዩ ፡ ይስቁ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ አደጋ ፡ ሊያመ ጣ ፡ የቻለው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ንግግር ፡ ያደረገው ፡ አይሁድ ፡ ተይዞ ፡ ከቆመበት ፡ እየጮኸ ፡ ቡልባ ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ተጠም ጥሞ ፡ «ክቡር ፡ ጌታዬ ፤ እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ጌታዬ! ሟቹን ፡ ወንድምን ፡ ዶሮሽን ፡ አውቃቸው ፡ ነበር! ታላቅ ፡ መኳንንት ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቱርኮች ፡ ተማርከው ፡ ሳለ ፡ ገንዘብ ፡ ከፍለው ፡ እንዲወጡ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ ከፍየላቸው ፡ ነበር ፡» አለ ።

«ወንድሜን ፡ ታውቀዋለህ?» አለና ፡ ታራስ ፡ ጠየቀው ።

«አዎ ፡ አውቃቸዋለሁ! በጣም ፡ ቸር ፡ መኳንንት ፡ ነበሩ ።»

«ለመሆኑ ፡ ስምህ ፡ ማን ፡ ይባላል?»

«ያንኬል ።»

«ደግ ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ ታራስ ፡ ጥቂት ፡ በነገሩ ፡ ከአሰ በ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኮዛኮች ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ «ይህን ፡ አይሁድ ፡ ለመስቀል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ጊዜ ፡ አናጣም ፤ ለጊዜው ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡» አላቸው ።

ከዚያ ፡ ታራስ ፡ ተከታዮቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በሠረገላዎቻቸው ፡ አጠገብ ፡ ከቆሙበት ፡ ሥፍራ ፡ ሔዶ ፡ አይሁዱን ፤ «በል ፡ እዚህ ፡ ሠረገላው ፡ ሥር ፡ ግባና ፡ እንዳትንቀሳቀስ ፤ እናንተም ፡ ጠብቁት ፡» ብሎ ፡ ካዘዘ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ ሔደ ።

አሁን ፡ ሁናቴው ፡ ስለተለወጠ ፡ ዘመቻው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ፈረሶችና ፡ ሠረገላዎች ፡ እንደሚያስ ፈልጉ ፡ በመገንዘብ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በውኃው ፡ ዳር ፡ ጀልባ ፡

ማዘጋጀቱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡ መሰብሰብ ፡ ጀምሮአል ። ወጣቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ አንድነት ፡ በሽማግሌዎቹና ፡ በአለቆቹ ፡ ምክር ፡ መሠረት ፡ ተስማምቶ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፖላንድ ፡ ለመዝመትና ፡ በኃይማኖታቸው ፡ እንዲሁም ፡ በኮዛክ ፡ ክብር ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ለመበቀል ፡ ከተሞቹን ፡ ሁሉ ፡ ለመዝረፍ ፤ ሰብልና ፡ መንደሮችንም ፡ ለማቃጠል ፡ ወስነው ፡ ተነሡ ። በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ ታጥቀው ፡ ለዘመቻው ፡ ተዘጋጁ ። ኮሼቮዩ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ የአንድ ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ ሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ ሽቁጥቁጥና ፡ ዓይነ ፡ አፋር ፡ ሰው ፡ መምሰሉ ፡ ቀርቶ ፡ አሁን ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ መሪአቸው ፡ ሆነ ። ትእዛዝ ፡ በሚሰጥበትም ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ እንደልብ ፡ አዳሪዎችና ፡ ጨዋታ ፡ ወዳድ ፡ ሰዎች ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ሊመለከቱት ፡ እንኳን ፡ ባለመድፈር ፡ በአክብሮት ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ያዳምጡ ፡ ነበር ። ኮሼቮዩ ፡ በብዙ ፡ የጦር ፡ ሜዳዎች ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ የተፈተነ ፡ የበሰለ ፡ ኮዛክ ፡ ስለነበር ፡ ትእዛዙን ፡ ሲያስተላልፍ ፡ ያለመርበትበት ፡ በእርጋታ ፡ ነበር ።

«ድርጅታችሁን ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ እንድትመረምሩ ፡ ያስፈልጋል ። ስረገላዎቻችሁንና ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎቻችሁን ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምራችሁ ፡ ዝግጁ ፡ መሆናቸውን ፡ አረጋግጡ ። ብዙ ፡ ልብስ ፡ እንዳትሸከሙ ፤ አንዳንድ ፡ ሸሚዝና ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሱሪ ፡ ብቻ ፡ ያዙ ። ለምግብም ፡ አንድ ፡ ቶፋ ፡ የገንፎ ፡ ዱቄትና ፡ አንድ ፡ ቶፋ ፡ የተፈጨ ፡ በቆሎ ፡ ይበቃል ። ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳይሸከም ። አስፈላጊው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሠረገላው ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። እያንዳንዱ ፡ ኮዛክ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ፈረስ ፡ መጫን ፡ አለበት ፤ ደግሞ ፡ ወንዞችን ፡ ለመሻገርና ፡ ለሌላም ፡ ክፉ ፡ ሥፍራዎች ፡ የሚሆኑን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ጥንድ ፡ ያህል ፡ ሠረገላ ፡ ጐታች ፡ በሬዎች ፡ ያስፈልጉናል ። ደግሞ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ አጥብቄ ፡ የምጠይቃችሁ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንድትጠብቁ ፡ ነው ። በዘረፋ ፡ ሲቀናቸው ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ ከፈይና ፡ የከበሩ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ለእግራቸው ፡ መጠቅለያ ፡ የሚቀዳድዱ ፡ ከመሃላችሁ ፡ አንዳንድ ፡ ጐልማሶች ፡ እንዳሉ ፡ አውቃለሁ ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የሰይጣን ፡ ልማድ ፡ ተውት ። እንድያውም ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቁን ፡ ችላ ፡ ብላችሁ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ብርና ፡ ይህንን ፡ የመሳሰለው ፡ ሃብት ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሆነ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ፈልጉ ፤ ደግሞ ፡ በዘመቻ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰክሮ ፡ ቢታይ ፡ ክፉ ፡ ቅጣት ፡ እንደሚደርስበት ፡ አስቀድሜ ፡ እነግራችኋለሁ ። በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ አለ ፡ የሚባል ፡ ታላቅ ፡ ጀግናም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ከአንዱ ፡ ሠረገላ ፡ ጋር ፡ አንገቱን ፡ እንደውሻ ፡ አሳስሬ ፡ በጥይት ፡ ተመቶ ፡ እዚያው ፡ የውሻ ፡ ሞት ፡ ይሞታል ። ሬሣውም ፡ እንኳን ፡ ሳይቀበር ፡ ለአሞሮች ፡ ይጣላል ። በዘመቻ ፡ ላይ ፡ የሚሰክር ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ቀብር ፡ አይገባውም ። እናንተ ፡ ጐልማሶች ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ጠና ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝ ፡ መቀበል ፡ አለባችሁ ። ሰውነታችሁን ፡ አንዱ ፡ ላይ ፡ ጥይት ፡ ቢጨርፋችሁ ፡ ወይም ፡ የጐራዴ ፡ ስለት ፡ ቢጭራችሁ ፡ ከምንም ፡ አትቁጠሩት ፤ ትንሽ ፡ ባሩድ ፡ በአንድ ፡ መለኪያ ፡ ቮድካ ፡ በጥብጣችሁ ፡ ጅው ፡ አድርጋችሁ ፡ ስትጠጡት ፡ ደህና ፡ ትሆናላችሁ ። ትኩሳትም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ሕመም ፡ አይሰማችሁም ። ቁስሉም ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ካልሆነ ፡ ትንሽ ፡ አፈር ፡ በምራቃችሁ ፡ ለውሳችሁ ፡ ስትደመድሙበት ፡ ይደርቃል ። በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ጐበዝ ፤ ወደየሥራችሁ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ አትጣደፉ ፤ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ በጥንቃቄ ፡ መሥራት ፡ ነው!»

ኮሼቮዩ ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ከመጨረሱ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ በፍጥነት ፡ ወደየሥራቸው ፡ ተሰማሩ ። በሠፈሩ ፡ ውስጥ ፡ መጠጥ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ታይቶ ፡ እንደማያውቅ ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ሰካራም ፡ አይታይም ።

አንዳንዶቹ ፡ የሠረገላቸውን ፡ መሽከርከሪያ ፡ ሲያጠብቁና ፡ ሲለውጡ ፤ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ ጓዝ ፡ የጦር ፡ መሣ

ሪያቸውን ፡ ሲጭኑ ፡ የቀሩት ፡ ፈረሶችና ፡ በሮች ፡ ለጭነት ፡
እየነዱ ፡ አመጡ ። የፈረሶች ፡ ኮቴ ፤ የሚፈተኑ ፡ ጠመንጃ
ዎች ፡ ጩኸት ፤ የሚሳሉ ፡ ጐራዴዎች ፡ ኳኳታ ፤ በሬዎች ፡
ሲያገሱና ፡ ሠረገላዎቹም ፡ ሲንቀሳቀሱ ፡ ከየሥፍራው ፡ ይሰማ ፡
ጀመር ። ወዲያው ፡ የኮዛኮቹ ፡ የጦር ፡ ድርጅት ፡ በሜዳው ፡
ላይ ፡ አተርትሮ ፡ ተዘረጋ ። የዚህንም ፡ ሠራዊት ፡ ሰልፍ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ከጫፍ ፡ እጫፍ ፡ ሮጦ ፡ ለመድረስ ፡ ቢሞክር ፡
በጣም ፡ አድካሚ ፡ መንገድ ፡ እንደሚሆንበት ፡ አይጠረጠ
ርም ።

ከእንጨት ፡ በተሠራው ፡ በትንሹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ቄሱ ፡ የመሰናበቻ ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡
ጠበል ፡ ረጩ ። እያንዳንዱም ፡ ኮዛክ ፡ መስቀል ፡ እየተሣለመ ፡
አለፈ ። ጦሩ ፡ ከሠፈሩ ፡ ወጥቶ ፡ ሲሔድ ፡ ዘማቾቹ ፡ ሁሉ ፡ ዘ
ወር ፡ ብለው ፡ ተመለከቱና ፡ «ደህና ፡ ሁኚ ፡ እናታችን! እግ
ዚአብሔር ፡ ከክፉ ፡ ይጠብቅሽ!» ብለው ፡ ጉዞአቸውን ፡
ቀጠሉ ።

ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ከጦሩ ፡ ሠፈር ፡ ውጭ ፡ ባለው ፡ መንደር ፡
ሲያልፍ ፡ እሱ ፡ ያዳነው ፡ አይሁድ ፡ ያንኬል ፡ በአንድ ፡ እፍታ ፡
መደብር ፡ አቁሞ ፡ ለዘማች ፡ ወታደር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሸ
ቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ዳቦ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ሲሸጥ ፡ ተመለከተው ።
ታራስም ፡ «አይሁዶች ፡ ምን ፡ ያሉ ፡ ሰይጣኖች ፡ ናቸው!»
ብሎ ፡ እየተገረመ ፡ ፈረሱን ፡ ወደሱ ፡ ኮልኩሎ ፤ «አንተ ፡
ሞኝ ፡ እዚህ ፡ ተጐልተህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ? በጥይት ፡ መመ
ታት ፡ አምሮሃል?» አለው ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ያንኬል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምሥጢር ፡ እንደ
ሚናገር ፡ ሰው ፡ ሺክክ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቡልባ ፡ ተጠጋና ፡ እን
ዲህ ፡ አለው ፤

«ጌታዬ ፡ ብቻ ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገሩ ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡
የኔም ፡ ሠረገላ ፡ ከኮዛኮች ፡ ሠረገላ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ነው ፡ ያለ
ው ፤ ስለዚህ ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡



ሁሉ ፡ ማናቸው ፡ አይሁድ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ እሸ
ጣለሁ!»

ታራስ ፡ ቡልባ ፡ በአይሁዶች ፡ የነጋዴነት ፡ መንፈስ ፡
እየተገረመ ፡ ወደ ፡ ሠልፉ ፡ ተመለሰ ።

## ምዕራፍ ፡ አምስት ።

ወዲያው ፡ ደቡብ ፡ ምእራብ ፡ ፖላንድ ፡ በፍርሃት ፡ ይ
ሸበር ፡ ጀመር ። «ዛፖሮዥያኖች! ዛፖሮዥያኖች ፡ ሊመጡ ፡
ነው!» የሚል ፡ ወሬ ፡ በየሥፍራው ፡ ተነዛ ። ሸሽተው ፡ ለማ
ምለጥ ፡ የቻሉ ፡ ሁሉ ፡ ተሰደዱ ፤ ነገ ፡ ታታሮች ፡ ለሚያፈ
ራርሱት ፡ ምን ፡ አለፋን ፡ በማለት ፡ ምሽግ ፡ ወይም ፡ የረባ ፡
ሕንጻ ፡ ሳይሠራ ፡ የጣር ፡ ጐጆ ፡ ብቻ ፡ በሚታይበት ፡ በዚያ ፡
የግድ ፡ የለሽ ፡ ዘመን ፡ እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡
ቀላል ፡ ንብረቱን ፡ እየፈታ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሥነ ፡
ሥርዓት ፡ በሌለው ፡ ስደት ፡ ተበታተነ ፤ አንዱ ፡ ማረሻና ፡
በሬውን ፡ በፈረስና ፡ በጠመንጃ ፡ ለውጦ ፡ በቀበሌው ፡ ወደሚ
ገኘው ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ሲገባ ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ የሚችለውን ፡
ንብረቱን ፡ ተሸክሞ ፡ ከብቶቹን ፡ እየነዳ ፡ ሸሽቶ ፡ ይደበ
ቃል ። ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ወራ
ሪዎቹን ፡ ለመቋቋም ፡ ከተሰለፉ ፡ በኋላ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ግን ፡
ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሽሽት ፡ ይበታተኑ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ዛፖ
ሮዥያኖች ፡ በመባል ፡ የሚጠራው ፡ ጦር ፡ ወዳድና ፡ ኃይ
ለኛ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ድርጅት ፡ ያነ
ሰው ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ ውስጡን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጦር ፡ ስልት ፡
ድርጅት ፡ እንዳለው ፡ ማንም ፡ ያውቅ ፡ ነበር ። በፈረስ ፡ ላይ ፡
የተቀመጡት ፡ ኮዛኮች ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ጭነት ፡ እንዳይከ
ብዳቸውና ፡ እንዳይሞቃቸው ፡ በጣም ፡ ይጠነቀቃሉ ። ከሠረ
ገላዎች ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፡ የሚሔዱት ፡ እግረኞችም ፡ ጉዞአቸው ፡
የረጋ ፡ ነው ። መላው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ቀኑን ፡ በየጫካ

ውና ፡ ጭር ፡ ባለው ፡ መስክ ፡ እያሳለፈ ፡ ሌሊት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚጓዘው ። የጠላትን ፡ ሁናቴ ፡ የሚያጣሩ ፡ ሰላዮች ፡ ሁልጊዜ ፡ ከጦሩ ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ይላካሉ ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ካልታሰበው ፡ ሥፍራ ፡ ድንገት ፡ ከተፍ ፡ እያሉ ፡ የረገጡትን ፡ ቀበሌ ፡ ሁሉ ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ሸፍነውት ፡ ያልፉ ፡ ነበር ። መንደሮችን ፡ ያቃጥላሉ ፤ የቀንድ ፡ ከብቶችና ፡ ፈረሶች ፡ ተዘርፈው ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ይነዳቸዋል ፡ ወይም ፡ እዛው ፡ ይታረዳሉ ። ዘመቻቸው ፡ ከእውነተኛ ፡ ዘመቻ ፡ ይልቅ ፡ የደም ፡ ድግስ ፡ ነበር ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ። በዚያ ፡ የአረመኔ ፡ ዘመን ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ የረገጡትን ፡ ምድር ፡ መመልከት ፡ በጣም ፡ የሚዘገንን ፡ ነገር ፡ ነበር ። የተገደሉ ፡ ሕፃናት ፤ ጡታቸው ፡ የተቆረጠ ፡ ሴቶች ፤ የባታቸው ፡ ቆዳ ፡ የተገፈፈና ፡ የተለቀቁ ፡ ምርኮኞች ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ ኮዛኮች ፡ ቂማቸውን ፡ ይወጡ ፡ ጀመር ።

የኮዛኮቹን ፡ መምጣት ፡ የሰሙ ፡ የአንድ ፡ ገዳም ፡ አለቃ ፡ በመንግሥትና ፡ በእነሱ ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ አለመኖሩንና ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የሚፈጽሙትም ፡ የወረራ ፡ ተግባር ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ መልዕክት ፡ የሚያደርሱ ፡ ሁለት ፡ መነኮሳት ፡ ላኩ ።

ለመልዕክቱም ፡ መልስ ፡ የኮዛኮች ፡ ኮሼቮይ ፤ «የገዳሙን ፡ አለቃ ፡ ምንም ፡ አይስጉ ፡ በሉዋቸው ፤ ኮዛኮች ፡ ለትንባሆአቸው ፡ የሚሆን ፡ እሳት ፡ ከማንደድ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አይሠሩም ፡» በማለት ፡ መልስ ፡ ላከላቸው ።

ወዲያው ፡ ብዙ ፡ ሳይቆይ ፡ ያ ፡ የሚያምር ፡ ትልቅ ፡ ገዳም ፡ በእሣት ፡ ተያይዞ ፡ እንደጧፍ ፡ ይንቀለቀል ፡ ጀመር ።

በቀበሌው ፡ የተመደቡት ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ ያድኑናል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ በሚጣልባቸው ፡ ከተሞች ፡ መነኮሣት ፤ አይሁዶችና ፡ ሴቶች ፡ ከአንዱ ፡ ሥፍራ ፡ ተሰደው ፡ እየጐረፉ ፡ ሲገቡ ፡ ሥፍራ ፡ አልበቃቸው ፡ አለ ። አንዳንድ ፡



ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ከመንግሥት ፡ ተልከው ፡ ይመጡና ፡ እነሱም ፡ ወይ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ማግኘት ፡ ያቅታቸዋል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ተገናኝተው ፡ ገና ፡ ውጊያው ፡ ከመጀመሩ ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሰው ፡ በፈጣን ፡ ፈረሶቻቸው ፡ ይፈረጥጣሉ ። በአለፉ ፡ የጦር ፡ ሜዳዎች ፡ ሰፊ ፡ ዝና ፡ ካገኙ ፡ የንጉሡ ፡ የጦር ፡ መኳንኖች ፡ መካከል ፡ ኮዛኮቹን ፡ ጠንክረው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ለመቋቋም ፡ ያስቡ ፡ አንዳንድ ፡ ቆራጥ ፡ ጀግኖች ፡ ነበሩ ።

እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ወጣቶቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ዘረፋውንና ፡ ሌላውን ፡ ነገር ፡ ችላ ፡ በማለት ፡ ችሎታቸውን ፡ ለታላላቆቻቸው ፡ ለማሳየት ፡ ብቻ ፡ ሲሉ ፡ በአማረው ፡ ሰንጋው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ የካባው ፡ ዘርፍ ፡ በነፋስ ፡ ከሚውለበለበው ፡ ኩሩና ፡ ጅንን ፡ የፖሊሽ ፡ ወታደር ፡ ጋር ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ይገጥሙ ፡ ነበር ። የጦርነትን ፡ ጥበብ ፡ መማር ፡ ለወጣቶቹ ፡ ኮዛኮች ፡ እንደ ፡ ጨዋታ ፡ ነው ። ገና ፡ ከአሁኑ ፡ ብዙ ፡ የፈረስ ፡ እቃዎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ጐራዴዎችና ፡ ጠመንጃዎች ፡ ማርከዋል ። በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እነዚህ ፡ ወጣቶች ፡ በሰለው ፡ ሙሉ ፡ ሰው ፡ ሆኑ ። የህጻንነት ፡ ልስላሴ ፡ ይታይበት ፡ የነበረው ፡ ፊታቸው ፡ አሁን ፡ የጠነከረና ፡ ኮስታራ ፡ ሆነ ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ከዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ጀግኖች ፡ ኮዛኮች ፡ መካከል ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ስለያዙለት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ። አስታፕ ፡ ለጦር ፡ ሜዳ ፡ በተለይ ፡ የተፈጠረ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ገና ፡ በሃያ ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ የአሳየው ፡ እርጋታና ፡ የጦር ፡ ሞያ ፡ ወደፊት ፡ መሪ ፡ እንደሚሆን ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ።

«ገና ፡ ወደፊት ፡ ጥሩ ፡ ኮሎኔል ፡ ይወጣዋል ፤ ወደፊት ፡ ከገዛ ፡ ባትኩው ፡ እንኳን ፡ የበለጠ ፡ ነው ፡ የሚሆነው ፡» እያለ ፡ ታራስ ፡ በደስታ ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

አንድሬይን ፡ ደግሞ ፡ ስለት ፡ ለስለት ፡ ሲጋጭና ፡ የጥይትም ፡ ጩኸት ፡ እንደ ፡ ሙዚቃ ፡ ሆኖ ፡ ይማርከው ፡ ነበር ።

የራሱንም ፡ ሆነ ፡ የጠላቱን ፡ ኃይል ፡ አስቀድሞ ፡ ማመዛዘን ፡ በፍጹም ፡ አይችልም ። በጦርነት ፡ ደስታ ፡ ከመዋጡ ፡ የተነሳ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ እውር ፡ ይሆናል ። አእምሮው ፡ እሳት ፡ እንደሚነድበት ፡ ሲሆንና ፡ የሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዓይኖቹ ፡ ላይ ፡ ሲዞር ፡ የሰው ፡ ጭንቅላት ፡ ተቆርጦ ፡ ሲሽከረከር ፡ ፈረሶች ፡ ሲወድቁ ፡ እርሳስ ፡ በጆሮው ፡ እያፏጨ ፡ ጐራዴ ፡ ከፊቱ ፡ እያብለጨለጨ ፡ በጦሩ ፡ መሃል ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየሰነዘረ ፡ ሲያልፍ ፡ ከመደሰት ፡ በቀር ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ የሚሰነዘሩትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ከምንም ፡ አይቆጥራቸውም ። አንድሬይ ፡ ውጊያ ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ ማናቸውም ፡ የረጋና ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ከማይሞክረው ፡ አደገኛ ፡ ስፍራ ፡ እየገባ ፡ ብዙ ፡ ጀብዱ ፡ ሲፈጽም ፡ አባቱ ፡ እያየው ፡ ይደነቅ ፡ ነበር ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ልጁን ፡ በአድናቆት ፡ ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡ «እግዚአብሔር ፡ ይጠብቀው ፡ እንጂ ፡ ጥሩ ፡ ወታደር ፡ ይወጣዋል! ከኦስታፕ ፡ እኩል ፡ አይሆንም ፡ ግን ፡ ጥሩ ፡ ወታደር ፡ የሚሆን ፡ ነው!» ይል ፡ ነበር።

ብዙ ፡ ከበርቴ ፡ ሰዎችና ፡ ብዙ ፡ ሃብት ፡ ይገኝበታል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ስለተሰማ ፡ የኮዛኮች ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ዱብኖ ፡ ከተማ ፡ ለመጓዝ ፡ አሰበ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ከከተማው ፡ ደረሱ ። የከተማው ፡ ኑዋሪዎች ፡ ጠላታቸው ፡ እቤታቸው ፡ እስኪገባ ፡ ከመመልከት ፡ ይልቅ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተከላክለው ፡ በከተማቸው ፡ አደባባይና ፡ በየመንገዱ ፡ ለመሞት ፡ ቆርጠው ፡ ነበር ። የከተማው ፡ ዙሪያ ፡ በከፍተኛ ፡ የአፈር ፡ ዙሪያ ፡ ተመሽጐ ፡ አል ። በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውም ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ የአለበትን ፡ ግዴታ ፡ የተገነዘበ ፡ ጠንካራ ፡ ድርጅት ፡ ነበር ። ኮዛኮቹ ፡ ምሽጉን ፡ ጥሶ ፡ ለመግባት ፡ ቢሞክሩ ፡ ከባድ ፡ ተኩስ ፡ ወረደባቸው ። የከተማው ፡ ኑዋሪዎች ፡ በምሽጉ ፡ ጀርባ ፡ ተሰብስበው ፡ ከተማቸውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ለመጠበቅ ፡ መቁረጣቸው ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ። ሴ



ቶቹ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ በዚህ ፡ የተከላካይነት ፡ ውጊያ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ድንጊያ ፤ በርሚል ፤ ያገኙትን ፡ እቃ ፡ ሁሉ ፡ እያነሱ ፡ ከመወርወራቸውም ፡ በላይ ፡ በዓይናቸው ፡ እየገባ ፡ ማየት ፡ እንዲከለክላቸው ፡ አሸዋ ፡ እያፈሱ ፡ በኮዛኮቹ ፡ ላይ ፡ ይበትኑ ፡ ጀመር ። ኮዛኮቹ ፡ መሽጐ ፡ ከተቀመጠ ፡ ጠላት ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ አይወዱም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ኮሼቮይ ፡ ጦሩ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፤ «ግድ ፡ የላችሁም ፡ ወንድሞቼ ፡ ለጊዜው ፡ እናፈግፍግ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንዳቸውም ፡ እንኳን ፡ ከዚች ፡ ከተማ ፡ የወጡ ፡ እንደሆነ ፡ ክርስቲያንነቴ ፡ ቀርቶ ፡ የተረገመ ፡ ታታር ፡ በላችሁ ፡ ጥሩኝ ። ዝም ፡ በሏቸው ፡ እነዚህ ፡ ውሾች ፡ እዛው ፡ በርሃብ ፡ ይለቁ!» አለ ።

የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ከተማውን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ እንዳይፈታ ፡ ያህል ፡ ያካባቢውን ፡ መንደሮች ፡ እህሉንም ፡ ማቃጠል ፡ ጀመረ ። በአንዳንድ ፡ ስፍራም ፡ ባልታጨደው ፡ ሰብል ፡ መሃል ፡ የኮዛኮች ፡ ፈረሶች ፡ እንዲመገቡ ፡ ተለቀቁ ። የከተማው ፡ ህዝብ ፡ ምግቡን ፡ የሚያገኘው ፡ ከገጠሩ ፡ እርሻ ፡ ስለነበር ፡ ሰብሉ ፡ ሲበላሽ ፡ በመመልከቱ ፡ ጭንቅ ፡ ያዘው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሰረገላዎቻቸውን ፡ በሁለት ፡ ረድፍ ፡ ደርድረው ፡ የከተማውን ፡ ዙሪያ ፡ ከከበቡ ፡ በኋላ ፡ በመንደር ፡ ተመድበው ፡ የምርኮ ፡ እቃ ፡ እየተለዋወጡ ፡ በእርጋታ ፡ እየተጫዋወቱ ፡ ተቀመጡ ። በየአንዳንዱ ፡ መንደር ፡ ድንገት ፡ አደጋ ፡ ቢመጣ ፡ የሚያሳይ ፡ ትልቅ ፡ ደመራ ፡ እየነደደ ፡ በእሳቱ ፡ አጠገብም ፡ ንቁ ፡ ዘበኛ ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቅ ፡ ያድራል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ ያለውጊያ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መቀመጥ ፡ እየሰለቻቸው ፡ ሔደ ። ይህንንም ፡ በመመልከት ፡ ኮሼቮዩ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ በማለት ፡ የተመደበላቸው ፡ የመጠጥ ፡ ልክ ፡ እጥፍ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ አድርጐ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ኑሮ ፡ ለኮዛኮቹ ፡ አልጣማቸውም ። በተለ

ይም ፣ ለታራስ ፣ ቡልባ ፣ ልጆች ። እንድሬይማ ፣ መሰልቸቱ ፣
በግልጽ ፣ ይታይበት ፣ ነበር ።

ይህንኑ ፣ በመመልከት ፣ ታራስ ፣ ታናሹን ፣ ልጁን ፣
ጠርቶ ፣ «አንተ ፣ እሳት ፣ ጉረምሳ! ገና ፣ መሪ ፣ የምትሆን ፣
ነህና ፣ ሁሉንም ፣ መቻል ፣ አለብህ ። ጥሩ ፣ ጀግና ፣ የሚባለ
ው ፣ በጦር ፣ ሜዳ ፣ ላይ ፣ ልበ ፣ ሙሉ ፣ የሚሆነው ፣ ሰው ፣
ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ እርጋታንም ፣ የሚችል ፣ ጭምር ፣ ነው ፡»
ሲል ፣ መከረው ።

ነገር ፣ ግን ፣ እሳት ፣ የሆነው ፣ የልጅነት ፣ ዘመንና ፣ የእ
ርጅና ፣ እድሜ ፣ ምን ፣ ጊዜም ፣ አይግባቡም ፤ ጠባያቸው ፣ የተ
ለያየ ፣ ከመሆኑ ፣ የተነሳ ፣ አንዱን ፣ ነገር ፣ የተለያየ ፣ መልክ ፣
ያለው ፣ አድርገው ፣ ነው ፣ የሚመለከቱት ።

ይህ ፣ ሁሉ ፣ ሲሆን ፣ የቡልባ ፣ ክፍለ ፣ ጦር ፣ በቶሽካ
ች ፣ መሪነት ፣ ዋናው ፣ ጦር ፣ ሠራዊት ፣ ካለበት ፣ ሥፍራ ፣ ደ
ረሰ ። ከሱም ፣ ጋር ፣ ሁለት ፣ ኤሳውሎችና ፣ ሌሎችም ፣ የጦር ፣
መኮንኖች ፣ አብረው ፣ ነበሩ ። በጠቅላላው ፣ አዲስ ፣ የመጡ
ት ፣ የቡልባ ፣ ክፍለ ፣ ጦር ፣ ኮዛኮች ፣ አራት ፣ ሺ ፣ ይሆናሉ ።
ከአዲሱ ፣ ጦር ፣ ጋር ፣ የመጡት ፣ ሹማምንት ፣ ለሁለቱም ፣
ለቡልባ ፣ ልጆች ፣ ለየአንዳንዳቸው ፣ ከእናታቸው ፣ የተላከ ፣
ከሲፕረስ ፣ እንጨት ፣ የተሠራ ፣ የቅዱሳን ፣ ምስል ፣ አመጡ
ላቸው ። ሁለቱ ፣ ወንድማማቾች ፣ የተቀደሱትን ፣ ምስሎች ፣
በየአንገታቸው ፣ ካሰሩ ፣ በኋላ ፣ የአሮጊት ፣ እናታቸው ፣ ሃሳ
ብ ፣ በአእምሮአቸው ፣ እየመጣ ፣ ያስጨንቃቸው ፣ ጀመር ።
የላከችው ፣ ስጦታ ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው? ምን ፣ ሚርት ፣ የያ
ዘ ፣ ይሆን? ጠላታቸውን ፣ ድል ፣ እንዲያደርጉና ፣ ሃብት ፣ ሰ
ብስበው ፣ በደስታ ፣ ወደ ፣ ቤታቸው ፣ እንዲመለሱ ፣ ምር
ቃት ፣ ይሆን? ወይስ...? ነገር ፣ ግን ፣ የወደፊቱን ፣ ነገር ፣ የሚ
ያውቅ ፣ የለም ፤ የአንድ ፣ ሰው ፣ የወደፊት ፣ እጣ ፣ በጨፈ ፣
ላይ ፣ እንዳረፈ ፣ የበልግ ፣ ወቅት ፣ ጉም ፣ ያለ ፣ ነው ። በጭ
ጋጉ ፣ ውስጥ ፣ አዕዋፍ ፣ እርስ ፣ በእርስ ፣ ሳይተያዩ ፣ ይበራሉ ፤



ጨልሌው ፣ እርግብዋን ፤ እርግብዋም ፣ ጨልሌውን ፣ ለማየት ፣
ባለመቻል ፣ ምን ፣ ያህል ፣ በሞት ፣ አጠገብ ፣ እንዳሉ ፣ እንዳ
ቸውም ፣ ሳያውቁት ፣ ይተላለፋሉ ።

እስታፕ ፣ ወዲያው ፣ ወደተመደበበት ፣ ተግባር ፣ ተመ
ለሰ ፤ እንድሬይ ፣ ግን ፣ ምክንያቱን ፣ ሳያውቀው ፣ አንድ ፣
ቅር ፣ የሚል ፣ ነገር ፣ ልቡን ፣ አስጨነቀው ። ኮዛኮቹ ፣ እራ
ታቸውን ፣ በልተዋል ፤ ጊዜውም ፣ ከመሸ ፣ ቆይቶአል ። የአ
ማረው ፣ የሃምሌ ፣ ሌሊት ፣ አስደሳች ፣ መልክ ፣ ይዞ ፣ ይታ
ያል ። እንድሬይ ፣ እንዲህ ፣ ባለው ፣ አስደሳች ፣ ሌሊት ፣ ተማ
ርኮ ፣ ወደ ፣ ጎጆው ፣ ለመግባት ፣ ወይም ፣ እንቅልፍ ፣ ለመተ
ኛት ፣ አልቻለም ። ስፍር ፣ ቁጥር ፣ የሌላቸው ፣ ከዋክብት ፣
በሰማዩ ፣ ላይ ፣ ቁልጭ ፣ ብለው ፣ ያንጸባርቃሉ ። ከጠላት ፣
የተዘረፈ ፣ ብዙ ፣ እቃ ፣ የተጫኑ ፣ ሠረገላዎች ፤ በየሜዳው ፣
ይታያሉ ። በሰረገላዎችም ፣ ዙሪያ ፣ ዛፖሮዥያውያን ፣ ተጋ
ድመዋል ። ከረጢት ፣ ባርኔጣ ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ አጠገባቸው ፣
ያለውን ፣ ጓደኛቸውን ፣ ተንተርሰው ፣ የተኙት ፣ ኮዛኮች ፣
አስደናቂ ፣ ትርእይት ፣ ሆነው ፣ የሚታዩ ፣ ነበሩ ። አንድ ፣ ኮ
ዛክ ፣ ሲተኛም ፣ ቀን ፣ የታጠቀው ፣ የዘመቻው ፣ መሣሪያ ፣
ሁሉ ፣ አይለየውም ። ሠረገላ ፣ ጎታች ፣ በሬዎች ፣ በሜዳው ፣
ላይ ፣ ተኝተው ፣ ትልልቅ ፣ ጉብታ ፣ ይመስላሉ ። በየስፍራ
ው ፣ የተኙት ፣ ሰዎች ፣ ኩርፊያ ፣ እያየለ ፣ ሔደ ። ከወደ ፣
መስኩም ፣ በችካል ፣ ታስረው ፣ የቆሙት ፣ ፈረሶች ፣ መታሰ
ራቸውን ፣ በመቃወም ፣ ሲያሽካኩ ፣ ይሰማሉ ። ይህ ፣ ሁሉ ፣
ሲሆን ፣ የተዋበው ፣ የሃምሌ ፣ ሌሊት ፣ ከምን ፣ ጊዜውም ፣
የበለጠ ፣ ውበት ፣ ተጎናጽፎ ፣ ነበር ። ተጨማሪ ፣ ውበት ፣
የሰጡትም ፣ ገና ፣ አመድ ፣ ሆነው ፣ ያልጠፉት ፣ አሁንም ፣
የሚነዱት ፣ ያካባቢው ፣ መንደሮች ፣ ናቸው ። በአንዱ ፣ ስፍ
ራ ፣ የእሳቱ ፣ ነበልባል ፣ በዝግታና ፣ በታላቅ ፣ ግርማ ፣ ወደ ፣
ሰማይ ፣ የሚጓዝ ፣ ይመስላል ። በሌላው ፣ ደግሞ ፣ ነበል
ባሉ ፣ የሚነድ ፣ ነገር ፣ እያጋጠመው ፣ እውሎ ፣ ነፋስ ፣ እንደ

5•

ሚያነሳው ፡ አፈር ፡ ብትን ፡ ብሎ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አንጻር ፡ ይወረወራል ። ነዶ ፡ የከሰለው ፡ የገዳሙ ፡ ህንጻ ፡ ጥቁር ፡ ሆኖ ፡ ቆሞ ፡ በአካባቢው ፡ ነበልባሉ ፡ በደነፋ ፡ ቁጥር ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ መሃል ፡ አንድ ፡ ያልታደለ ፡ አይሁድ ፡ ወይም ፡ መነኩሴ ፡ ከህንጻው ፡ ግድግዳ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ዛፍ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ እሳቱ ፡ ሲለበልበው ፡ ይታያል ። በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ርቀው ፡ የሚበሩ ፡ አዕዋፍ ፡ በአንድ ፡ የነበልባል ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጥቋቁር ፡ መስቀሎች ፡ ይመስላሉ ። የተከበበው ፡ ከተማ ፡ የአንቀላፋ ፡ ይመስላል ። የቤቶቹ ፡ ጣራና ፡ ምሽጉ ፡ በሩቅ ፡ ካለው ፡ ቃጠሎ ፡ በሚደርሳቸው ፡ ውጋጋን ፡ ብዥ ፡ ብዥ ፡ እያሉ ፡ ይታያሉ ።

አንድሬይ ፡ በተደረደሩት ፡ የኮዛክ ፡ ሠረገላዎች ፡ መካከል ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ። ለጥበቃ ፡ የነደዱት ፡ ደመራዎች ፡ ነደው ፡ ሊያልቁ ፡ ተቃርበዋል ። ዘበኞቹም ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶአቸዋል ። አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ ግድየለሽነት ፡ ተገርሞ ፤ «ኃይለኛና ፡ የሚፈራ ፡ ጠላት ፡ በአቅራቢያችን ፡ አለመኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ አሰበ ። በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሠረገላ ፡ ሒዶ ፡ ወጣና ፡ እጆቹን ፡ ተንተርሶ ፡ በጀርባው ፡ ተጋደመ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደው ፡ ስለአልቻለ ፡ ሰማይ ፡ ሰማዩን ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። በከዋክብት ፡ ብርሃን ፡ የሚብለጨለጨው ፡ ሰማይ ፡ ከፊቱ ፡ ተዘርግቶአል ። አየሩ ፡ ንጹሕና ፡ ጣፋጭ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንድሬይ ፡ እንደማናወዝ ፡ እያለ ፡ ስስ ፡ መጋረጃ ፡ ከፊቱ ፡ የተጋረደ ፡ ይመስል ፤ ሰማዩ ፡ ለአንድ ፡ አፍታ ፡ ብዥ ፡ ይልበትና ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ይታየዋል ።

እንዲህ ፡ በሚያናውዝበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ የተደቀነ ፡ መሰለው ። ይህም ፡ ሲነቁ ፡ ወዲያው ፡ የሚጠፋ ፡ ቅዠት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ ዓይኖቹን ፡ ቢገልጥ ፡ በእውነትም ፡ የጠወለገ ፡ ቀጭን ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ አጐንብሶ ፡ ዓይን ፡ ዓይኑን ፡ ሲመለከተው ፡ አየ ። እንደ ፡ ከሰል ፡ የጠቆረ ፡ ረጅም ፡ ያልተበጠረ ፡ ጠጉር ፡ ጠቆር ፡ ካለ ፡ ሻሽ ፡ ዘልቆ ፡ ወርዶ ፡ ይታያል ። የዓይኖቹ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴና ፡ የቀጭኑ ፡ ፊት ፡ የጠወለገ ፡ የሞት ፡ መልክ ፡ ከአንድ ፡ ልዩ ፡ መንፈስ ፡ በቀር ፡ የሌላ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያዳግታል ። አንድሬይ ፡ ሽጉጡን ፡ ጨበጠና ፤ «ማነህ? ክፉ ፡ መንፈስ ፡ እንደሆንህ ፡ ሒድ ፡ ጥፋ ፤ ሕይወት ፡ ያለህ ፡ ሰው ፡ እንደሆንህም ፡ ቀልድህ ፡ ለዛ ፡ ያጣ ፡ ነው ። አሁን ፡ ካልሔድህ ፡ በጥይት ፡ እገድልሃለሁ ፡» አለ ።

ለዚህም ፡ መልስ ፡ ከፊቱ ፡ የቆመው ፡ መንፈስ ፡ ጸጥታን ፡ በመጠየቅ ፡ ጣቱን ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ምልክት ፡ ሰጠው ። አንድሬይም ፡ የቃጣውን ፡ ሽጉጥ ፡ ዝቅ ፡ አደረገና ፡ ይህን ፡ ፍጥረት ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ሲመለከተው ፡ የጠጉሩ ፡ ርዝመት ፤ አንገቱ ፡ እንዲሁም ፡ በከፊል ፡ ራቁት ፡ የሆነው ፡ ደረት ፡ የሴት ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘበ ። ግን ፡ ይቺ ፡ ሴት ፡ የዚህ ፡ አካባቢ ፡ ተወላጅ ፡ አይደለችም ። ፊትዋ ፡ ጠይም ፡ ነው ፤ ሰፊ ፡ የሆኑት ፡ የጉንጭ ፡ አጥንቶቿም ፡ ከጐደጐደው ፡ ጉንጭዋ ፡ ጋር ፡ ሲተያዩ ፡ አብጠው ፡ የሾሉ ፡ ይመስላሉ ። ጠባብ ፡ የሆነው ፡ የዓይኖችዋ ፡ ቅድም ፡ እንደ ፡ ቀስት ፡ ወደላይ ፡ ጠመም ፡ ያለ ፡ ነው ። የሴትዮዋን ፡ መልክ ፡ አተኩሮ ፡ ሲመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያያት ፡ ሴት ፡ እየመሰለችው ፡ ሔደች ። በመጨረሻ ፡ መታገስ ፡ ሲያቅተው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ፤

«ማን ፡ እንደሆንሽ ፡ ንገሪኝ? አንድ ፡ ሥፍራ ፡ ያየሁሽ ፡ ይመስለኛል ።»

«የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በኪየቭ ፡ ከተማ ፡ ነው ።»

«የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡... በኪየቭ ፡ ...» እያለ ፡ አንድሬይ ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ ያሳለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወስ ፡ ሞከረ ፤ ወዲያው ፡ እንደገና ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ከተመለከታት ፡ በኋላ ፡ «የወየወዱ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ደንገጡር ፡ ታታርዋ ፡ ሴትዮ ፡ ነሽ!» ብሎ ፡ በድንገት ፡ ጮኸ ።

ታታርዋም ፡ «ቀስ!» አለችና ፡ በፍርሃት ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡ የአንድሬይን ፡ ጩኸት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሰምቶት ፡ እንደሁ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ትገላመጥ ፡ ጀመር ።

አንድሬይም ፡ ቀስ ፡ ባለ ፡ ሹክሹክታ ፡ «ንገሪኝ ፡ ለምን ፡ መጣሽ? እመቤትሽ ፡ የት ፡ ናት? ለመሆኑ ፡ ደህና ፡ ናት?» አላት ።

«እዚሁ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ያሉት ።»

«እዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ?» አሁንም ፡ አንድሬይ ፡ ልቡ ፡ ካለመጠን ፡ እየመታ ፡ ጮኸ ፡ ሊናገር ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ።

«ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ታደርጋለች?»

«ጌቶችም ፡ እዚሁ ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ የዱብና ፡ ወየወዳ ፡ ከሆኑ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ያልፋቸዋል ።»

«ባል ፡ አግብታለች? ንገሪኝ ፡ እንጂ! ምን ፡ ግራ ፡ የሆንሽ ፡ ፍጥረት ፡ ነሽ! እስዋ ፡ እንዴት ፡ ናት?»

«እመቤቴ ፡ እህል ፡ ከቀመሱ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሆኖአቸዋል ።»

«እንዴት?»

«የከተማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ ከቀመሰ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አልፎታል ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከአፈር ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የሚቀመስ ፡ አላገኘም ።»

አንድሬይ ፡ በድንጋጤ ፡ በድን ፡ ሆነ ።

«እመቤቴ ፡ ከከተማው ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ከዛፖሮዥያኖች ፡ መካከል ፡ እርስዎን ፡ ስለአዩ ፡ ሒጅና ፡ ያንን ፡ መኮንን ፡ ያስታውሰኝ ፡ እንደሁ ፡ ወደኔ ፡ እንዲመጣ ፤ አለዚያም ፡ ባልቴት ፡ እናቴ ፡ ዓይኔ ፡ ሥር ፡ ስትሞት ፡ ከማይ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ እንኳን ፡ ቢሰጥሽ ፡ ይዘሽ ፡ ነይ ። እኔ ፡ ከእስዋ ፡ በፊት ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል ፤ ሒደሽ ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቀሽ ፡ ለምኚው ፤ እሱም ፡ አሮጊት ፡ እናት ፡ ይኖረዋልና ፡ ለሳቸው ፡ ሲል ፡ እንኳን ፡ እህል ፡ ሊሰጠን ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ ወደርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ላኩኝ ።»



የወጣቱ ፡ ኮዛክ ፡ ልብ ፡ በተመሰቃቀሉ ፡ ስሜቶች ፡ ታወከ ።

«ለመሆኑ ፡ አንቺ ፡ እንዴት ፡ ደረስሽ? እንዴት ፡ መጣሽ?»

«በምድር ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የዋሻ ፡ መንገድ ።»

«የዋሻ ፡ መንገድ ፡ አለ?»

«አለ ።»

«የት?»

«አያጋልጡኝ ፡ እንደሆን ፡ ጌታዬ ።»

«ላላጋልጥሽ ፡ በቅዱስ ፡ መስቀል ፡ እምላለሁ?»

«እንግዲያው ፡ እዚያ ፡ ወዲያ ፡ ያሉትን ፡ ቋጥቋጦች ፡ አልፈው ፡ ሸጥዋን ፡ ይሻገሩና ፡ ቁጠማው ፡ እጅብ ፡ ወደአለበት ፡ ሥፍራ ፡ ይሒዱ ።»

«ዋሻው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ያደርሳል?»

«ቀጥታ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ያገባል ።»

«በይ ፡ አሁኑኑ ፡ እንሒድ!»

«መጀመሪያ ፡ ስለክርስቶስና ፡ ስለቅድስት ፡ ማርያም ፡ ብለው ፡ አንዲት ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ!»

«ጥሩ ። ይሰጥሻል ፤ እዚህ ፡ ሠረገላው ፡ ጐን ፡ ቁሚ ፤ እንዲያውም ፡ ገብተሽ ፡ ብትጋደሚ ፡ ይሻላል ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተኝቶአል ፡ ማንም ፡ የሚያየሽ ፡ የለም ። እኔ ፡ አሁኑኑ ፡ እመለሳለሁ ።»

ከዚያ ፡ ዕቃ ፡ ወደተጫነባቸው ፡ ሠረገላዎች ፡ ሔደ ፤ ልቡ ፡ አለመጠን ፡ ይመታ ፡ ነበር ። በአሁኑ ፡ የኮዛክ ፡ ኑሮው ፡ ተገፍቶ ፡ ወድቆ ፡ የነበረው ፡ ያለፈው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ በተራው ፡ የአሁኑን ፡ ነገር ፡ ሸፈነው ። ያቺ ፡ ኩሩ ፡ ሴት ፡ ከጠሊቅ ፡ ባህር ፡ ብቅ ፡ ያለች ፡ መስላ ፡ ከፊቱ ፡ ተደቀነች ፤ የተዋቡት ፡ ክንዶችዋ ፤ ዓይኖችዋ ፤ የሚስቁት ፡ ከንፈሮችዋ ፡ ጥቅልል ፡ ጥቅልል ፡ ብሎ ፡ ደረትዋ ፡ ላይ ፡ የወደቀው ፡ ቡና ፡ ቀለም ፡ ጠጉርዋ ፡ ተሟልቶ ፡ የተፈ

ጠረው ፡ ለጋ ፡ ሰውነትዋ ፡ እንደገና ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ውል ፡ አለ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜው ፡ ለጠየቀው ፡ ኃይለኛ ፡ ስሜት ፡ ሥፍራ ፡ ለቆ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ከአዕምሮው ፡ አልጠፋም ፡ ነበር ። የወጣቱን ፡ ኮዛክ ፡ እንቅልፍ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ ቢያወከው ፡ ኖሮአል! ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ከእንቅልፉ ፡ እየነቃ ፡ ምክንያቱን ፡ ሳያውቀው ፡ ሳይተኛ ፡ ይነጋ ፡ ነበር ።

አሁን ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ሲያመራ ፡ እንደገና ፡ እንደሚያያት ፡ በማሰብ ፡ ብቻ ፡ ልቡ ፡ በኃይል ፡ እየመታ ፡ ጉልበቱም ፡ ተንቀጠቀጠ ። ሠረገላዎቹ ፡ ካሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ሲደርስ ፡ የመጣበትን ፡ ምክንያት ፡ ጨርሶ ፡ ረስቶታል ፤ ለማስታወስም ፡ ግንባሩን ፡ እያሸ ፡ ብዙ ፡ ካሰበ ፡ በኋላ ፡ ያች ፡ ውብ ፡ ወይዘሮ ፡ በረሃብ ፡ ልትሞት ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ቢለው ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ በፍርሃት ፡ ተንቀጠቀጠ ። ከሠረገላዎቹ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ዘሎ ፡ ወጥቶ ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ዳቦ ፡ ታቅፎ ፡ ወጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲያ ፡ ያለው ፡ ዳቦ ፡ ለግድ ፡ የለሹ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ተስማሚ ፡ ቢሆንም ፡ ለለስላሳው ፡ ለእስዋ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንደማይሆን ፡ አመዛዘነ ። ወዲያው ፡ ያን ፡ ቀን ፡ በእራት ፡ ላይ ፡ ለሦስት ፡ ቀን ፡ የሚሆነውን ፡ የገንፎ ፡ እህል ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ አገነፋችሁት ፡ በማለት ፡ ኮሼቮይ ፡ አብሳዮቹን ፡ መቅጣቱ ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ ብዙ ፡ የተረፈ ፡ ገንፎ ፡ እንደሚያገኝ ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኖ ፡ የአባቱን ፡ የገንፎ ፡ ገንቦ ፡ ያዘና ፡ የሠፈሩ ፡ ምግብ ፡ አብሳይ ፡ ወደአለበት ፡ ሥፍራ ፡ ሔደ ። አብሳዩም ፡ አሥር ፡ ገንቦ ፡ በሚይዙ ፡ ትልልቅ ፡ የብረት ፡ ድስቶች ፡ መካከል ፡ ተጋድሞ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶታል ። ብረት ፡ ድስቶቹ ፡ የተጣዱበት ፡ የብረት ፡ ድስቶች ፡ እሳት ፡ ከስሎ ፡ ገና ፡ አሁንም ፡ አልጠፋም ። አንድሬይ ፡ ወደ ፡ ብረት ፡ ድስቶቹ ፡ ተጠግቶ ፡ ቢመለከት ፡ ሁለቱም ፡ ድስቶቹ ፡ ባዶ ፡ ሆነው ፡ ስላያቸው ፡ ደነገጠ ። ያን ፡ ሁሉ ፡ ገንፎ ፡ የጨረሱት ፡ ልዩ ፡ ፍጥረቶች ፡ እንደሆኑ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ። በተለይ ፡ በዚያ ፡ ሠፈር ፡ የተመደቡት ፡ ሰዎች ፡



በሌሎቹ ፡ ከተመደቡት ፡ በቁጥር ፡ ያነሱ ፡ ስለነበሩ ፡ አንድሬይ ፡ በጣም ፡ ተገረመ ። ወደሌሎች ፡ ሠፈሮችም ፡ ሔደ ። ድስቶቹን ፡ ቢፈትሽ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አጣ ። «ዛፖሮዥያኖች ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ናቸው ፤ ትንሽ ፡ ምግብ ፡ ሲኖር ፡ ይበሉታል ፤ ብዙ ፡ ያለ ፡ እንደሆንም ፡ ምንም ፡ አያስተርፉም ፡» የሚባለው ፡ ተረት ፡ ትዝ ፡ አለው ።

እንግዲህ ፡ ምን ፡ ያድርግ? በአባቱ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ በሚገኝ ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ ውስጥ ፡ የገዳሙ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ሲዘረፍ ፡ የተገኘ ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ለስላሳ ፡ የስንዴ ፡ ዳቦ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ሠረገላ ፡ ቢሔድ ፡ ከረጢቱ ፡ እዚያ ፡ የለም ፤ ኦስታፕ ፡ ከረጢቱን ፡ ተንተርሶ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ አካባቢው ፡ ሁሉ ፡ እስኪያስተጋባ ፡ ያንኳርፍ ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ከረጢቱን ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ ያዘና ፡ በኃይል ፡ ሲመነጭቀው ፡ የኦስታፕ ፡ ጭንቅላት ፡ ከመሬቱ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ ። ኦስታፕ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ባንኖ ፡ ዓይኖቹን ፡ ሳይገልጥ ፡ ቁጭ ፡ እንዳለ ፤ «ያዙት ፡ ይህን ፡ የፖሊሽ ፡ ሰይጣን! ፈረሱን ፡ ያዙት! ያዙት!» ብሎ ፡ በኃይል ፡ ጮኸ ።

አንድሬይም ፡ በድንጋጤ ፡ የያዘውን ፡ ከረጢት ፡ በመቃጣት ፡ አንሥቶ ፡ «ዝም ፡ በል ፡ አለዚያ ፡ እገድልሃለሁ!» ብሎ ፡ ጮኸበት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ መግደል ፡ ምንም ፡ አስፈላጊ ፡ አልሆነም ፤ ምክንያቱም ፡ ኦስታፕ ፡ የቅዠት ፡ ንግግሩን ፡ አቆመና ፡ ወደኋላው ፡ ተፈንግሎ ፡ በዙሪያው ፡ ያለው ፡ ሣር ፡ ሁሉ ፡ እስኪንቀጠቀጥ ፡ ድረስ ፡ ማንኳረፍ ፡ ቀጠለ ። የኦስታፕ ፡ ቅዠት ፡ ሌሎች ፡ ኮዛኮችን ፡ ቀስቅሶ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ አንድሬይ ፡ አካባቢውን ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመለከተ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ከአቅራቢያው ፡ አንገቱን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ በእንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ተመልሶ ፡ ሲተኛ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የነቃ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። አንድሬይ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ከረጢቱን ፡ ተሸክሞ ፡

ሔደ ። ታታርዋ ፡ ሴትዮ ፡ በፍርሃት ፡ ትንፋሽዋን ፡ ውጣ ፡ እንደ ፡ ተጋደመች ፡ ነበረች ።

«ነይ ፤ ተነሺ ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተኝቶአል ፤ ምንም ፡ አትፍሪ ። ሁሉንም ፡ መሸከም ፡ ያልቻልኩ ፡ እንደሆን ፡ አንዱን ፡ ዳቦ ፡ ለመያዝ ፡ ትችይ ፡ ይሆን?» አላትና ፡ ከረጢቱን ፡ በትከሻው ፡ ተሸክሞ ፡ እግረ ፡ መንገዱንም ፡ ከአንድ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ዱቄት ፡ የተሞላ ፡ ሌላ ፡ ከረጢት ፡ አንሥቶ ፡ ይዞ ፡ ታታርዋን ፡ ተሸካሚ ፡ ያላትን ፡ ዳቦ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ በክንዱ ፡ አቅፎ ፡ በተኙት ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ መካከል ፡ በድፍረት ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ።

ወጺያው ፡ በሽማግሌው ፡ አባቱ ፡ በታራስ ፡ ቡልባ ፡ አጠገብ ፡ ሲያልፉ ፡ አባትየው ፡ «አንድሬይ!» አለና ፡ ተጣራ ።

አንድሬይም ፡ በድንጋጤ ፡ ልቡ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ቆመና ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ «ምንድነው?» አለ ።

«ሴት ፡ አብራህ ፡ አለች! ቆይ ፡ ስነሣ ፡ በቁምህ ፡ ነው ፡ ቆዳህን ፡ የምገፈው! ሴቶች ፡ ለምንም ፡ አይጠቅሙህ!» አለና ፡ ቡልባ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ የተሸፋፈነችውን ፡ ታታር ፡ በቁጣ ፡ ተመለከታት ።

አንድሬይ ፡ የአባቱን ፡ ፊት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ ፈርቶ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ በድን ፡ እቆመበት ፡ ሥፍራ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ቀና ፡ ቢል ፡ ቡልባ ፡ እጁን ፡ ትራስ ፡ አድርጎ ፡ ወዲያው ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶታል ። አንድሬይ ፡ ከጭንቅ ፡ በመውጣቱ ፡ አማተበ ። ድንጋጤና ፡ ፍርሃቱም ፡ ከአመጣጡ ፡ በበለጠ ፡ ፍጥነት ፡ ለቅቆት ፡ ሔደ ። ታታርዋን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ እንደተሸፋፈነች ፡ ሐውልት ፡ መስላ ፡ ከሩቅ ፡ በሚመጣው ፡ የቃጠሎ ፡ ብርሃን ፡ ዓይኖችዋ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሬሣ ፡ ዓይን ፡ ቁልጭ ፡ ብለው ፡ እየታዩ ፡ ቆማለች ። ወዲያው ፡ የቀሚስዋን ፡ እጅጌ ፡ ጐተት ፡ ሲያደርገው ፡ ተከተለችውና ፡ እየተገላመጡ ፡ አንዲት ፡ ቁልቁለት ፡ ወርደው ፡ በቁጥቋጦ ፡ የተሸፈነች ፡ ጠባብ ፡ ሸጥ ፡ ተሻገሩ ።



ቁልቁለቱን ፡ ከወረዱ ፡ ወዲያ ፡ ከኮዛኮቹ ፡ ሠፈር ፡ ተሰውረው ፡ አይታዩም ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ሲመለከት ፡ ከአቀበቱ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የበቀለው ፡ ሣር ፡ ብቻ ፡ ከሰማዩ ፡ ጋር ፡ የገጠመ ፡ መስሎ ፡ ታየው ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ የሚነፍሰው ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ጐሕ ፡ ሊቀድ ፡ መቃረቡን ፡ አስታወሰው ። በከተማውም ፡ ሆነ ፡ በተወረረው ፡ አካባቢ ፡ አንድም ፡ ዶሮ ፡ ስለአልተረፈ ፡ የዶሮ ፡ ጩኸት ፡ አይሰማም ። ሸጥዋን ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፡ ከፊታቸው ፡ ያገኙት ፡ አቀበት ፡ ከወረዱት ፡ ቁልቁለት ፡ የባሰ ፡ ረጅምና ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነበር ። በዚያ ፡ አቅራቢያ ፡ ያለው ፡ የምሽግ ፡ ግንብ ፡ በጣም ፡ አጭርና ፡ ወታደርም ፡ የማይታይበት ፡ ስለነበር ፡ አቀበቱ ፡ በተፈጥሮው ፡ ለከተማው ፡ ምሽግ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ ይመስላል ፤ ቀጥ ፡ ያለው ፡ አቀበት ፡ በቁጥቋጦና ፡ በአረም ፡ የተሸፈነ ፡ ሲሆን ፡ ከአቀበቱ ፡ መደብና ፡ ከውኃው ፡ መካከል ፡ ረጅም ፡ ሰው ፡ የሚውጥ ፡ ቄጠማ ፡ በቅሎአል ። ከቄጠማው ፡ አለፍ ፡ ብሎ ፡ ቀድሞ ፡ በአታክልት ፡ ዙሪያ ፡ የታጠረ ፡ የፈራረሰ ፡ አጥር ፡ ይታያል ። ከአጥሩም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አታክልቶች ፡ አሉ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሥፍራው ፡ ጨፌና ፡ በውኃ ፡ የተሸፈነ ፡ ስለነበር ፡ ታታርዋ ፡ ጫማዋን ፡ አውልቃና ፡ ቀሚስዋን ፡ ሰብስባ ፡ በባዶ ፡ እግርዋ ፡ በጥንቃቄ ፡ ትራመድ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ቁጥቋጦዎቹን ፡ ገለጥ ፡ ስታደርግ ፡ ጠባብ ፡ የዋሻ ፡ በር ፡ ብቅ ፡ አለ ። ታታርዋ ፡ ቀድማ ፡ ገባች ፤ አንድሬይም ፡ ከነሸክሙ ፡ ለመግባት ፡ ሲል ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ተከተላት ፤ ወዲያው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጨለማ ፡ ዋጣቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ስድስት ።

አንድሬይ ፡ ከረጢቶቹን ፡ እንደተሸከመ ፡ በጨለማው ፡ ዋሻ ፡ ታታርዋን ፡ ተከትሎ ፡ በዳበሣ ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ።

«በቅርቡ ፡ ብርሃን ፡ እናገኛለን ፤ ፋኖሱን ፡ ከአስቀመ
ጥኩበት ፡ ሥፍራ ፡ ደርሰናል ፡» አለችው ።
በእውነትም ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ መንገዳቸውን ፡
ያሳያቸው ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ከአካባቢው ፡ ትንሽ ፡ ሰፋ ፡
ካለ ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ ። ይህ ፡ ሥፍራ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ሳይ
ሆን ፡ አይቀርም ። ምክንያቱም ፡ ከወደ ፡ ጥግ ፡ በኩል ፡ እንደ
መቅደስ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ጠባብ ፡ ጠረጴዛ ፡ ተቀምጦ ፡ ከበላ
ዩም ፡ መልኩ ፡ በጣም ፡ የተበላሸ ፡ የካቶሊኮች ፡ የማርያም ፡
ሥዕል ፡ ተሰቅሎአል ። ትንሽ ፡ የብር ፡ ኩራዝ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ተንጠልጥሎ ፡ በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ ይፈ
ነጥቃል ። ታታርዋ ፡ ጐንበስ ፡ ብላ ፡ እዚያው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡
አስቀምጣው ፡ የነበረውን ፡ ከመዳብ ፡ የተሠራ ፡ ፋኖስ ፡ እን
ስታ ፡ ጠፍቶ ፡ ስለነበር ፡ ከሥዕሉ ፡ መብራት ፡ እሳት ፡ አያያዘ
ች ። ብርሃኑ ፡ እየደመቀ ፡ ሔደ ። ከዚያ ፡ ፊትና ፡ ኋላ ፡ ተከ
ታትለው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ። በጤንነት ፡ የተጠበ
ቀው ፡ የአንድሬይ ፡ የተዋበ ፡ የወጣትነት ፡ መልክና ፡ አብ
ራው ፡ ያለችው ፡ ጓደኛው ፡ የከሣ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልዩ
ነት ፡ ነበረው ። ዋሻው ፡ እየሰፋ ፡ ስለሔደ ፡ አንድሬይ ፡ ቀጥ ፡
ብሎ ፡ ለመቆም ፡ ቻለ ። የዋሻውን ፡ ግድግዳ ፡ በመገረም ፡ እየ
ተመለከተ ፡ ኪዩቭ ፡ ያሉት ፡ የዋሻ ፡ መቃብሮች ፡ ትዝ ፡
አሉት ። እንደ ፡ ኪዩቭ ፡ የዋሻ ፡ መቃብሮች ፡ ሁሉ ፡ እዚህ
ም ፡ በግርግዳው ፡ ላይ ፡ ተቆፍረው ፡ በተሠሩ ፡ መደቦች ፡ ላይ ፡
በአንዳንዶቹ ፡ የሬሣ ፡ ሣጥኖች ፡ ቆመው ፡ ሲታዩ ፡ በሌሎ
ች ፡ ደግሞ ፡ በእርጥበት ፡ የሻገተ ፡ የሰው ፡ አጽም ፡ ተከምሮ
አል ። እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ዋሻ ፡ አንዳንድ ፡ ቅዱሳን ፡ የሆኑ ፡
ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሐዘንና ፡ መከራ ፡ ሸሽተው ፡ በሱ
ባኤ ፡ ሳይቀመጡበት ፡ አልቀሩም ። አንዳንድ ፡ ቦታ ፡ በጣም ፡
ጨለማ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎም ፡ ከእግራቸው ፡ ሥር ፡ ውኃ ፡
ይሰማቸዋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ የጉዞ ፡ ጓደኛው ፡ ድ
ካም ፡ በአረማመድዋ ፡ ይታይ ፡ ስለነበር ፡ እንድታርፍ ፡ መ



ቆም ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። አንዲት ፡ ጉርሻ ፡ ዳቦ ፡ ብትውጥ ፡ ሆድ ፡
ቁርጠት ፡ ሆኖባት ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መራመድ ፡ እያቃታት ፡
ቀጥ ፡ ብላ ፡ ትቆም ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡
የብረት ፡ መዝጊያ ፡ ከፊታቸው ፡ ታያቸው ። «ተመስገን ፡
አምላኬ ፡ ደረስን!» ብላ ፡ ታታርዋ ፡ በሩን ፡ ለማንኳኳት ፡
እጅዋን ፡ ብታነሣ ፡ አቅም ፡ አነሣት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አንድ
ሬይ ፡ ሔደና ፡ በሩን ፡ በኃይል ፡ አንኳኳው ። ከበሩ ፡ አልፎ ፡
ሰፊ ፡ ሥፍራ ፡ መኖሩን ፡ የሚያስረዳ ፡ ቀበሌ ፡ ተሰማ ። ወዲ
ያው ፡ ከአንድ ፡ ከሁለት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ቁልፍ ፡ ሲንኳኳና ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ በደረጃ ፡ ሲወርድ ፡ ተሰማ ። በመጨረሻ ፡ በሩ ፡
ተከፈተና ፡ በአንድ ፡ እጁ ፡ ሻማ ፡ በሌላው ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡
ቁልፍ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ በጠባብ ፡ የመተላለፊያ ፡
ደረጃ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አገኙ ። በኮዛኮች ፡ መካከል ፡ እጅግ ፡ ከመ
ጠላታቸው ፡ የተነሣ ፡ ከአይሁዶች ፡ የባሰ ፡ የጭካኔ ፡ ፍርድ ፡
ከሚፈጸምባቸው ፡ የካቶሊክ ፡ መነኮሣት ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡
ይህ ፡ መነኩሴ ፡ እፊቱ ፡ ቆሞ ፡ ሲመለከት ፡ አንድሬይ ፡ ሳ
ያስበው ፡ ደሙ ፡ ፈላ ። መነኩሴውም ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ኮዛ
ክ ፡ በማየቱ ፡ ደንግጦ ፡ ሳለ ፡ ታታርዋ ፡ በሹክሹክታ ፡ ስታ
ነጋግረው ፡ ልቡ ፡ ረጋ ። ወዲያው ፡ በሩን ፡ ቆልፎ ፡ በደረ
ጃው ፡ አሳለፋቸውና ፡ በጨለማው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡
ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ መሆናቸውን ፡ አወቁ ። ረጃጅም ፡ ሻ
ማዎች ፡ በሚበሩበት ፡ በአንዱ ፡ መቅደስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
አንድ ፡ ቄስ ፡ ተንበርክከው ፡ በለሰለሰ ፡ ድምጽ ፡ ጸሎት ፡
ያደርሳሉ ። ከቄሱም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡
ሁለት ፡ ወጣት ፡ ዲያቆኖች ፡ መአጠንት ፡ ይዘው ፡ ተንበርክ
ከዋል ። ቄሱ ፡ የሚያደርሱት ፡ ፀሎት ፡ አንድ ፡ አምላካዊ ፡
ተአምር ፡ ወርዶ ፡ ከተማው ፡ እንዲድን ፤ ምሽጉ ፡ እንዲጠ
ነክር ፤ ሕዝቡም ፡ በደረሰበት ፡ ምድራዊ ፡ ክፉ ፡ ዕድል ፡ ትእ
ግስት ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚለማመን ፡ ፀሎት ፡ ነበር ። ጥቂት ፡
ሴቶች ፡ ተንበርክከው ፡ ከድካማቸውም ፡ የተነሣ ፡ እፊታ

ቸው ፡ ያሉትን ፡ የወንበር ፡ ድጋፎች ፡ ተደግፈዋል ። አንዳ
ንድ ፡ ወንዶችም ፡ የሕንፃውን ፡ ምሰሶዎች ፡ እየተደገፉ ፡ በሐ
ዘን ፡ ተክዘው ፡ ተንበርክከዋል ። ከመቅደሱ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡
ቀለም ፡ የተቀባ ፡ የመስኮት ፡ መስተዋት ፡ የጐህ ፡ ብርሃን ፡
ገብቶ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አዳራሽ ፡ ፈገግ ፡ አለ ። በሚገ
ባውም ፡ ጮራ ፡ ዲያቆናቱ ፡ ከያዙት ፡ መእጠንት ፡ የሚወ
ጣው ፡ የእጣን ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ቀለማት ፡ ይዞ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ከቆመበት ፡ ጨ
ለማ ፡ ሥፍራ ፡ ሆኖ ፡ የገባው ፡ ብርሃን ፡ ያመጣውን ፡ አስደ
ናቂ ፡ ለውጥ ፡ ተመልክቶ ፡ ተገረመ ። ወዲያው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ግርማ ፡ ያለው ፡ የኦርጋኑ ፡ ድምጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡
ሞላው ። ኦርጋኑም ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ በሚዝገመገምና ፡
ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ በለሰለሰ ፡ ጣፋጭ ፡ ስልት ፡ ከተሰማ ፡ በ
ኋላ ፡ ዝም ፡ ሲል ፡ ቀበሌው ፡ ግን ፡ በሕንፃው ፡ ውስጥ ፡ ሲያ
ስተጋባ ፡ ብዙ ፡ ቆየ ። አንድሬይም ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ቆሞ ፡
በዚህ ፡ ባለታላቅ ፡ ግርማ ፡ ሙዚቃ ፡ ተገረመ ። ወዲያው ፡
ታታርዋ ፡ ልብሱን ፡ ጐተት ፡ አደረገችና ፡ «እንሒድ!» አለ
ችው ። ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያስተውላቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡
አቋርጠው ፡ ወጡና ፡ ውጭ ፡ ካለው ፡ አደባባይ ፡ ደረሱ ። አደ
ባባዩ ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ሲሆን ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ባዶ ፡ ነበር ።
ምናልባት ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ አደባባይ ፡
ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ይገበይ ፡ እንደነበር ፡ የሚያስረዱ ፡ አንዳ
ንድ ፡ የነጋዴ ፡ መደቦች ፡ አሉ ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ በየትም ፡ ሥ
ፍራ ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ፡ የከተማው ፡ መንገድ ፡ ድን
ጊያ ፡ በመነጠፍ ፡ ፈንታ ፡ በአፈር ፡ የተደመደመ ፡ ነው ።
አደባባዩ ፡ ከጭቃ ፡ ወይም ፡ ከድንጋይ ፡ በተሠሩ ፡ ትናን
ሽ ፡ ቤቶች ፡ ተከቦአል ። በአንድ ፡ ወገን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያ
ኑ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ምናልባት ፡ የከተማው ፡ አዳራሽ ፡ ወይም ፡
አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ የያዘ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።
ከሌሎቹ ፡ ቤቶች ፡ ጐልቶ ፡ የሚታይ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ሕንፃ ፡



አለ ። ይህም ፡ ሕንፃ ፡ ባለሁለት ፡ ፎቅ ፡ ሲሆን ፡ በላዩም ፡
በሚገኝ ፡ ተጨማሪ ፡ ደርብ ፡ ዘበኛ ፡ ቆሞአል ። በዘበኛው ፡
መቆሚያ ፡ ጣራ ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ የሰዓት ፡ መልክ ፡ ተቀርጾአል ።
መላው ፡ አደባባይ ፡ የሞተ ፡ ይመስላል ። አንድሬይ ፡ ግን ፡
አንድ ፡ የደከመ ፡ የሚያቃስት ፡ ድምጽ ፡ ተሰማውና ፡ ወደኋ
ላው ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡ አደባባዩን ፡ አቋርጦ ፡ በወዲያኛው ፡ ገጽ ፡
ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ላይ ፡
በድን ፡ መስለው ፡ ተጋድመው ፡ አየ ። ተኝተው ፡ ይሆን ፡ ወይ
ስ ፡ ሞተዋል ፡ በማለት ፡ አተኩሮ ፡ እያየ ፡ ለማጣራት ፡ ሲ
ሞክር ፡ ወዲያው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እግሩን ፡ አደናቀፈው ።
ወደ ፡ ታች ፡ ሲመለከትም ፡ ያደናቀፈው ፡ ነገር ፡ የአንዲት ፡
የአይሁድ ፡ ሴት ፡ ሬሣ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ምንም ፡ እንኳን ፡
የተጐሳቆለው ፡ ፊትዋ ፡ እሁን ፡ ሊያረጋግጥ ፡ ባይችልም ፡
ሴትዮዋ ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ሳትሆን ፡ አልቀረችም ። በራስዋ ፡
ላይ ፡ ቀይ ፡ የሃር ፡ ሻሽ ፡ ታሥሮአል ። በጆሮዎችዋ ፡ ላይ ፡
የሉል ፡ ወይም ፡ የጨሌ ፡ ጌጥ ፡ አንጠልጥላለች ። ጐንዋ ፡
አንድ ፡ ልጅ ፡ ተጋድሞ ፡ ጡትዋን ፡ በእጁ ፡ እንደጨበጠ ፡
ወተት ፡ ሲያጠባት ፡ ጊዜ ፡ በጭንቅ ፡ ብስጭት ፡ ጠምዝዞ ፡
ይዞታል ። ሕፃኑ ፡ ልቅሶውም ፡ ጩኸቱም ፡ አቁሞአል ። ነ
ፍሱ ፡ ላለመውጣትዋ ፡ ምልክት ፡ የሆነው ፡ በእርጋታ ፡ ሲ
ንቀሳቀስ ፡ የሚታየው ፡ ሆዱ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። በአንድ ፡ መንገ
ድ ፡ አጠፍ ፡ ሲሉ ፡ አንድ ፡ እብድ ፡ ሰውየ ፡ አጋጠማቸውና ፡
አንድሬይ ፡ የተሸከመውን ፡ እቃ ፡ በማየት ፡ እብዱ ፡ ሰውየ ፡
«ዳቦ!» ብሎ ፡ ጮኸ ፡ እንደነብር ፡ ጉብ ፡ አለበት ። ነገር ፡
ግን ፡ ጉልበቱ ፡ የእብደቱን ፡ ያህል ፡ ስላልነበር ፡ አንድሬይ ፡
ገፍተር ፡ ሲያደርገው ፡ በጀርባው ፡ ወድቆ ፡ ተዘረጋ ። በዚ
ህን ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ በርኅራኄ ፡ ልቡ ፡ ተነክቶ ፡ አንድ ፡ ዳቦ ፡
ሲጥልለት ፡ ዳቦውን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ አበደ ፡ ውሻ ፡ ተናነ
ቀው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ እህል ፡ አልቀመሰም ፡
ነበርና ፡ ወዲያው ፡ እዚያው ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ ሆድ ፡ ቁር

ጠት ፡ ያስቃየው ፡ ጀመር ። በየደረሱበት ፡ ርሃቡ ፡ ያደረሰ
ውን ፡ አሰቃቂ ፡ ነገር ፡ ያይ ፡ ጀመር ። ብዙዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ስ
ቃያቸውን ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ለመቀበል ፡ ስለ
አልቻሉ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ታምር ፡ ከአየሩ ፡ መድኃኒት ፡
የሚያገኙ ፡ ይመስል ፡ ወደውጭ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ወጥ
ተው ፡ ኖሮአል ። በአንድ ፡ ቤት ፡ ደጃፍ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ባል
ቴት ፡ ተቀምጠው ፡ ሞተው ፡ እንደሁና ፡ እንቅልፍ ፡ ይውሰ
ዳቸው ፡ ለማወቅ ፡ ያዳግታል ። ሆኖም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍ
ተው ፡ የተቀመጡት ፡ ባልቴት ፡ ሳይንቀሳቀሱ ፡ ድርቅ ፡ ከማ
ለታቸው ፡ የተነሣ ፡ ማየት ፡ ወይም ፡ መስማት ፡ እንደማ
ይችሉ ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ከሌላ ፡ ቤት ፡ ጣራ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡
በገመድ ፡ የተንጠለጠለ ፡ አንድ ፡ የተሸማቀቀ ፡ ሬሣ ፡ ይታ
ያል ። ይህ ፡ ያልታደለ ፡ ሰው ፡ የርሃብን ፡ ስቃይ ፡ መቻል ፡
ሲያቅተው ፡ ጊዜ ፡ ሕይወቱን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ማጥፋት ፡ መር
ጦ ፡ በገመድ ፡ ታንቆ ፡ ሞቶአል ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ አሰቃቂ ፡ የርሃብ ፡ ውጤት ፡ በመመል
ከቱ ፡ አንድሬይ ፡ አላስችል ፡ አለውና ፡ ታታርዋን ፡ እንዲ
ህ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ፤

«ሕይወታቸውን ፡ ለማቆየት ፡ ያህል ፡ እንኳን ፡ በእው
ነት ፡ የሚቀምሱት ፡ ነገር ፡ አጥተው ፡ ነው? መቼም ፡ ሰው ፡
ችግር ፡ ሲበዛበት ፡ ያለውን ፡ በልቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ በሕግ ፡
የተከለከሉትን ፡ ፍጥረቶች ፡ እንኳን ፡ መመገብ ፡ አለ
በት ።»

ታታርዋም ፡ «ሁሉም ፡ ተበልቶአል ፤ ያለው ፡ እን
ስሳት ፡ ሁሉ ፡ ለምግብ ፡ ሆኖአል ፤ አንድ ፡ ፈረስ ፡ ወይ ፡
አንድ ፡ ውሻ ፡ አንዲት ፡ አይጥ ፡ እንኳን ፡ በከተማው ፡ ው
ስጥ ፡ አይገኝም ። በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ስንቅ ፡ አከ
ማችተን ፡ አናውቅም ፡ ነበር ። ምግብ ፡ ሁሉ ፡ የሚ
መጣልን ፡ በአካባቢው ፡ ካሉት ፡ መንደሮች ፡ ነው ፡»
አለችው ።



«ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሰቃቂ ፡ ሞት ፡ እየሞታችሁ ፡
አሁንም ፡ ከተማውን ፡ እንደያዛችሁ ፡ ለመቆየት ፡ እንዴት ፡
ታስባላችሁ?»

«አዎ ፤ ወየወዳ ፡ እንኳን ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ባስረከ
ቡ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ትላንት ፡ ጠዋት ፡ በቡድግሮቪ ፡ ያሉት ፡
ኰሎኔል ፡ ከተማው ፡ ለጠላት ፡ እንዳይለቀቅ ፡ በመከልከል ፡
መልዕክት ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ አሞራ ፡ ልከው ፡ እሳቸው ፡ ለእር
ዳታ ፡ ሊደርሱልን ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ የያዙ ፡ ኰሎኔል ፡ በመ
ጠበቅ ፡ ላይ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለገለጹ ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡
ይመጣሉ ፡ ተብለው ፡ ይጠበቃሉ ። ይኸው ፡ አሁን ፡ ከቤቱ ፡
ደረስን ።»

ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ ምናልባት ፡ በኢጣልያ ፡ መሐ
ንዲስ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ አንድሬይ ፡ ገና ፡ ከሩቁ ፡ ተመ
ልክቶ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ቤት ፡ ባለሁለት ፡ ፎቅ ፡ ሲሆን ፡ በተዋ
በ ፡ ጡብ ፡ ድንጋይ ፡ የታነጸ ፡ ነው ። ይህ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅስ
ት ፡ ያጌጠው ፡ ሕንፃ ፡ በበሩ ፡ መድረክ ፡ ወደ ፡ አደባባዩ ፡
የሚያወርድ ፡ ቀለም ፡ ከተቀቡ ፡ ሸክላዎች ፡ የተሠራ ፡ ሰፊ ፡
ደረጃ ፡ ነበረው ። ከደረጃው ፡ ሥር ፡ በአንድ ፡ እጃቸው ፡ ጦራ
ቸውን ፡ ይዘው ፡ በሌላው ፡ ደግሞ ፡ ያቀረቀረውን ፡ እራሳ
ቸውን ፡ የደገፉ ፡ ሁለት ፡ ዘበኞች ፡ ተቀምጠዋል ። ዘበኞቹ ፡
ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ሐውልት ፡ መስለው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። እን
ቅልፍ ፡ የወሰዳቸው ፡ አይመስሉም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዘበኛ ፡ ሆ
ነው ፡ ተቀምጠው ፡ በደረጃው ፡ የሚወጡትን ፡ ሰዎች ፡ ቀና ፡
ብለው ፡ እንኳን ፡ አይመለከቱም ። ከደረጃው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡
የከበረ ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ጦረኛ ፡ አንድ ፡ የጸሎት ፡
መጽሐፍ ፡ ገልጦ ፡ ይዞ ፡ ቆሞአል ። እሱም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ በደ
ከሙት ፡ ዓይኖቹ ፡ ሲመለከታቸው ፡ ታታርዋ ፡ ቀረብ ፡ ብላ ፡
አንድ ፡ ነገር ፡ ነገረችውና ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ጸሎት ፡ መጽ
ሐፉ ፡ አቀረቀረ ። ሰፊ ፡ ከሆነው ፡ ከመጀመሪያው ፡ አዳራሽ ፡
ሲገቡ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ከፖሊሾች ፡ መኳንንት ፡ በማይለየው ፡

6—401

ክብርና ፡ ወግ ፡ መሠረት ፡ ወታደሮች ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬዎችና ፡
ሌሎችም ፡ አሽከሮች ፡ በየስፍራው ፡ ግድግዳውን ፡ ተደግ
ፈው ፡ ተቀምጠው ፡ አዳራሹን ፡ ሞልተውታል ። ነዶ ፡ ያለቀ ፡
ሻማ ፡ ሽታ ፡ ይሸታል ። ሁለት ፡ ሻማዎች ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡
ቁመት ፡ በሚያህል ፡ የሻማ ፡ ማስቀመጫ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡
ምንም ፡ እንኳን ፡ የጠዋቱ ፡ ብርሃን ፡ በመስኮት ፡ ቢገባ ፡ አሁ
ንም ፡ እንደበሩ ፡ ናቸው ።

አንድሬይ ፡ በተዋበ ፡ ቅርጻቅርጽ ፡ የተሠራ ፡ ማንቃ ፡
ወዳለው ፡ ሰፊ ፡ በር ፡ ሲያመራ ፡ ታታርዋ ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡
ጐተተችና ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ያለች ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ በር ፡ አመ
ለከተችው ። በዚችም ፡ በር ፡ አልፈው ፡ ከአንድ ፡ ክፍል ፡ ሲ
ደርሱ ፡ አንድሬይ ፡ ክፍሉን ፡ በመደነቅ ፡ እየተገላመጠ ፡ ያ
ስተውል ፡ ጀመር ። በመስኮቱ ፡ መዝጊያ ፡ ጭላንጭሎች ፡ የሚ
ገባው ፡ ጨረር ፡ ድምቅ ፡ ቀይ ፡ የሆነውን ፡ መጋረጃና ፡ እንዲ
ሁም ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ የተሰቀለ ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ አጉል
ቶ ፡ ያሳያል ። ታታርዋ ፡ አንድሬይን ፡ እዚያው ፡ እንዲ
ቆይ ፡ ምልክት ፡ ሰጠችውና ፡ በሩን ፡ ከፍታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡
ክፍል ፡ ስትገባ ፡ ከወዲያኛው ፡ ክፍል ፡ የሚመጣ ፡ የሻማ ፡
ብርሃን ፡ ታየው ። ወዲያውም ፡ የለሰለሰ ፡ የሹክሹክታ ፡ ድ
ምጽ ፡ ሲሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ተሸበረ ። ገርበብ ፡ ባለው ፡ መዝ
ጊያ ፡ ረጅም ፡ ያማረ ፡ ጠጉር ፡ በትከሻዋ ፡ ላይ ፡ የተንዠረገገ ፡
የአንድ ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ቅርጽ ፡ ታየው ። ወዲያው ፡ ታታ
ርዋ ፡ ተመለሰችና ፡ አስገባችው ። እሱ ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ እን
ደገባና ፡ በሩም ፡ ከኋላው ፡ እንዴት ፡ እንደተዘጋ ፡ በፍጹ
ም ፡ ትዝ ፡ አይለውም ።

በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሻማዎች ፡ ይበራሉ ። በአን
ድ ፡ ሥዕል ፡ አጠገብም ፡ የሚበራ ፡ አንድ ፡ ኩራዝ ፡ አለ ።
በሥዕሉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ለጸሎት ፡ መንበርከኪያ ፡ ደረጃ
ዎች ፡ ያሉት ፡ ረጅም ፡ ጠረጴዛ ፡ ይታያል ። አንድሬይ ፡ እነ
ዚህን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመመልከት ፡ ስሜትም ፡ አልነበ



ረው ። ዘወር ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ሴትዮ ፡ ቆማ ፡ አየ ። ለመራመ
ድ ፡ አስባ ፡ እዚያው ፡ ደርቃ ፡ የቀረች ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ ድ
ንጋይ ፡ የተለወጠች ፡ ትመስላለች ። ወደሱ ፡ ልትዘል ፡ ስትል ፡
ሰውነትዋን ፡ በግድ ፡ ገትታ ፡ ያቆመችው ፡ ስትመስል ፡ እሱ
ም ፡ እንደዚሁ ፡ በመገረም ፡ ደንዝዞ ፡ ከፊትዋ ፡ ቆሞአል ።
አሁን ፡ እንደሚያያት ፡ ሆና ፡ አገኛታለሁ ፡ ብሎ ፡ አላሰ
በም ፡ ነበር ፤ ተለውጣለች ፡ ቀድሞ ፡ ያወቃት ፡ ልጃገረድ ፡
አይደለችም ። አሁን ፡ የቀድሞው ፡ መልኳ ፡ ምንም ፡ አይታ
ይም ። ከቀድሞው ፡ ይልቅ ፡ አሁን ፡ በአጠፊታ ፡ የበለጠች ፡
ቆንጆና ፡ በውበትዋ ፡ የምትማርክ ፡ ሆናለች ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡
በጅምር ፡ እንዳለ ፡ ነገር ፡ ነበረች ፡ አሁን ፡ ግን ፡ አዋቂ ፡ ሠዓ
ሊ ፡ ለመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ በጠቢብ ፡ ብሩሹ ፡ ነካክቶ ፡ ያስ
ተካከላት ፡ ግሩም ፡ ሥዕል ፡ መስላለች ። ቀድሞ ፡ ቀበጥ ፡ ብት
ሆንም ፡ ደስ ፡ የምትል ፡ ልጃገረድ ፡ ነበረች ። አሁን ፡ ግን ፡
ውበትዋ ፡ ያበበ ፡ ሙሉ ፡ ሴት ፡ ናት ። ዓይኖችዋ ፡ በበሰለ ፡
ስሜት ፡ ያበራሉ ። ይህም ፡ እንዲያው ፡ የስሜት ፡ ምልክ
ት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ስሜት ፡ ራሱ ፡ በሙሉ ፡ መልኩ ፡ ነው ።
ገና ፡ ያልደረቀው ፡ የእንባዋ ፡ እርጥበት ፡ ለዓይኖችዋ ፡ ልዩ ፡
መልክ ፡ ሰጥቶት ፡ ይታያል ። ደረትዋ ፤ አንገትዋና ፡ ትከ
ሻዋ ፡ ከሙሉ ፡ ውበት ፡ ልክ ፡ ደርሰዋል ። ቀድሞ ፡ በፊትዋ ፡
ይበተን ፡ የነበረው ፡ በስሱ ፡ ጥቅልል ፡ ጥቅልል ፡ ያለው ፡ ጠ
ጉርዋ ፡ አሁን ፡ በብዛት ፡ አምሮ ፡ ግማሹ ፡ ተጐንጉኖ ፡ የቀ
ረው ፡ በደረትዋ ፡ ወርዶ ፡ እስከ ፡ ጭንዋ ፡ ድረስ ፡ ተንዠ
ርጐዋል ። በጠቅላላው ፡ መላው ፡ መልኳ ፡ ተለውጦአል ።
አእምሮውን ፡ ሲያስጨንቀው ፡ ከኖረው ፡ መልኳ ፡ ተመሳ
ሳይ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ቢፈልግ ፡ አንድም ፡ አላገኘም ። የፊትዋ ፡
መገርጣት ፡ አስደናቂውን ፡ ውበትዋን ፡ ምንም ፡ አላበላሸ
ውም ። እንዲያውም ፡ አስደናቂ ፡ ተጨማሪ ፡ ለዛ ፡ ሰጥቶታል ።
አንድሬይ ፡ በፍጹም ፡ ተማርኮ ፡ እፊትዋ ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ። እሱ
ዋም ፡ የጐልማሳነትን ፡ ሙሉ ፡ ውበት ፡ ተጐናጽፎ ፡ እፊ

ሁ*

ትዋ ፣ የቆመውን ፣ ኮዛክ ፣ በማየትዋ ፣ የተገረመች ፣ ትመስ ላለች ። ሃር ፣ የመሰሉት ፣ ቅንድቦቹ ፣ ቀስት ፣ መስለው ፤ ጸሐይ ፣ የጠገቡት ፣ ጉንጮቹ ፣ የወጣትነት ፣ ወዝ ፣ ይነበ ብባቸዋል ። ገና ፣ የበቀለው ፣ የጕልማሳነት ፣ ጥቁር ፣ ጢሙ ፣ እንደ ፣ ሃር ፣ የለሰለሰ ፣ ነው ።

እንደ ፣ ብር ፣ ቃጨል ፣ የጠራው ፣ ድምጽዋ ፣ እየተን ቀጠቀጠ ፤ «ቸሩ ፣ መኳንንት ፣ ሆይ ፤ ላመሰግንህ ፣ አቅም ፣ ያንሰኛል ። ዋጋህን ፣ ሊከፍልህ ፣ የሚችለው ፣ እምላክ ፣ ብቻ ፣ ነው ። እኔ ፣ አንዲት ፣ ደካማ ፣ ሴት ፣ ነኝ ፣...» አለችውና ፣ ዓይኖቿን ፣ አቀረቀረች ። የተዋበው ፣ ፊቷም ፣ በማቀርቀር ፣ ደፋ ፣ ሲል ፣ የሃፍረት ፣ ቅላት ፣ ለብሶ ፣ ነበር ። አንድሬይ ፣ መናገር ፣ እንኳን ፣ ተሳነው ። በልቡ ፣ የሚያስጨንቀውን ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ ሊገልጽላት ፣ ተመኘ ፤ ግን ፣ አልቻለም ። ምላሱ ፣ እንደታሰረና ፣ ከልሳኑም ፣ ድምጽ ፣ እንደማይወጣ ፣ ተሰማው ። በተማሪ ፣ ቤትና ፣ እንደ ፣ ዘላን ፣ ኑሮ ፣ ባለው ፣ በዘመቻ ፣ ኑሮ ፣ ላደገው ፣ ለእሱ ፣ እንዲህ ፣ ላለው ፣ ንግግር ፣ መልስ ፣ ለመስጠት ፣ የማይቻለው ፣ መሆኑን ፣ በመገንዘብ ፣ የኮዛክነት ፣ ተፈጥሮውን ፣ ረገመ ።

ወዲያው ፣ ታታሩዋ ፣ ገባች ። የመጣውን ፣ ዳቦ ፣ ቆራርጣ ፣ በወርቅ ፣ ሳህን ፣ ላይ ፣ አድርጋ ፣ ለእመቤቷ ፣ አቀረበች ። ውቢቱ ፣ ወይዘሮም ፣ በፊት ፣ ገረድዋን ፤ ከዚያም ፣ ዳቦውን ፣ ከተመለከተች ፣ በኋላ ፣ ወደ ፣ አንድሬይ ፣ ቀና ፣ አለች ። የደረሰባት ፣ ሥቃይና ፣ ልትገልጸው ፣ ያልቻለችው ፣ ስሜት ፣ ሁሉ ፣ በዓይኖቿ ፣ ላይ ፣ ይነበብ ፣ ነበር ። አንድሬይም ፣ ማናቸውንም ፣ ነገር ፣ ከንግግር ፣ ሊረዳው ፣ ከሚችለው ፣ ይበልጥ ፣ ተረዳው ። ወዲያውም ፣ ከልቡ ፣ እየቀለለው ፣ ሄደ ፤ ሰውነቱ ፣ ሁሉ ፣ ከእስራት ፣ እንደተፈታ ፣ ሆኖ ፣ ተሰማው ። በአንድ ፣ ባልታወቀ ፣ እጅ ፣ እንደታሠረ ፣ ሆኖ ፣ የነበረው ፣ ስሜቱ ፣ ሁሉ ፣ ነፃ ፣ ሆኖ ፣ በማይገቱ ፣ ቃላት ፣ እየጐረፈ ፣ ለመውጣት ፣ ጓጓ ። ግን ፣ ወዲያው ፣ ያቺ ፣ ቆንጆ ፣ ልጅ ፣ ድንገት ፣ ወደ ፣ ታታሩዋ ፣ ዘወር ፣ አለችና ፣ «እናቴስ? ለሷም ፣ ውስደሽላታል?» ብላ ፣ ጠየቀች ።

ታታሩዋም ፤ «ተኝተዋል ፣» አለች ።

«አባቴስ?»

«እዎ ፣ ወስጀላቸዋለሁ ። መኰንኑን ፣ ለማመስገን ፣ እኔው ፣ እራሴ ፣ እመጣለሁ ፣ ብለዋል ።»

ከዚያ ፣ ልጅቷ ፣ አንድ ፣ ቁራሽ ፣ ዳቦ ፣ አነሳችና ፣ ሉል ፣ በመሳሰሉት ፣ ጣቶቿ ፣ ሰበር ፣ አድርጋ ፣ ስትጕርስ ፣ አንድሬይ ፣ ይህ ፣ ነው ፣ በማይባል ፣ ደስታ ፣ ተመልቶ ፣ ይመለከታት ፣ ነበር ። ግን ፣ ወዲያው ፣ ያ ፣ በረሃብ ፣ ያበደው ፣ ሰውየ ፣ ቁራሽ ፣ ዳቦ ፣ በመዋጥ ፣ የደረሰበት ፣ ሥቃይ ፣ ትዝ ፣ አለውና ፣ በድንጋጤ ፣ ጠውልጐ ፤ «በቃ! ብዙ ፣ ቀን ፣ እህል ፣ ስላልቀመስሽ ፣ አሁን ፣ ዳቦው ፣ መርዝ ፣ ይሆንብሻል ፣» አለና ፣ እጇዋን ፣ ያዛት ። እሷም ፣ ወዲያው ፣ ዳቦውን ፣ አስቀመጠችና ፣ እንደታዛዥ ፣ ሕፃን ፣ ቀና ፣ ብላ ፣ ዓይን ፣ ዓይኑን ፣ ትመለከተው ፣ ጀመር ። እንዲያ ፣ ባለው ፣ ሰዓት ፣ በእንዲት ፣ ቆንጆ ፣ ወጣት ፣ ዓይኖች ፣ ላይ ፣ ምን ፣ እንደሚነበብና ፣ ዓይኖቿን ፣ የሚመለከተውም ፣ ጕልማሳ ፣ ስሜት ፣ ምን ፣ እንደ ሆን ፣ ለመግለጽ ፣ ምንም ፣ የሥዕል ፣ ቀለማት ፣ ወይም ፣ የንግግር ፣ ቃላት ፣ አይገኙለትም ።

አንድሬይ ፣ ልቡ ፣ ነፍሱም ፣ መላ ፣ ተፈጥሮው ፣ በስሜት ፣ ገንፍሎ ፣ እንዲህ ፣ አላት ፤

«ንግሥት ፣ ሆይ! ምን ፣ የምትሽው ፣ ነገር ፣ አለ? ምን ፣ የሚያሰኝሽ ፣ ነገር ፣ አለ? እኔን ፣ እዝዥኝ! በዚህ ፣ ዓለም ፣ ሊፈጸም ፣ የማይቻል ፣ ተግባር ፣ ፈጽም ፣ ብለሽ ፣ እዝዥኝ! ከሞት ፣ የሚያደርሰኝ ፣ ቢሆንም ፣ እንኳን ፣ አደርገዋለሁ! አዎ ፣ አደርገዋለሁ! ለአንቺ ፣ ሲሉ ፣ መሞት ፣ እጅግ ፣ ጣፋጭ ፣ ሞት ፣ እንደሆነ ፣ በቅዱስ ፣ መስቀል ፣ ስም ፣ እምላለሁ ! የግሌ ፣ የሆኑ ፣ ሶስት ፣ መንደሮች ፣ አሉኝ ። የአባቴ ፣ የፈረስ ፣ መንጋ ፣ ግማሹ ፣ እናቴ ፣ ይዛው ፣ የገባችው ፣ ሃብት ፣ በሙሉ ፣

ከአባቴ ፣ ደብቃ ፣ የምታስቀምጠው ፡ እንኳን ፣ ሳይቀር ፡ ሁሉም ፣ የኔ ፣ ነው! የኔን ፣ ያህል ፣ የጦር ፣ መሣሪያ ፣ ያለው ፡ ማንም ፣ ከዛክ ፣ አይገኝም ። የጐራዴዬ ፣ እጀታ ፣ ብቻ ፣ አንድ ፡ መንጋ ፣ ምርጥ ፣ ፈረሶችና ፣ ሶስት ፣ ሺ ፣ በጐች ፣ ሊገዛልኝ ፡ ይችላል ። ይህን ፣ ሁሉ ፣ ከአንቺ ፡ አፍ ፣ በሚወጣ ፣ አንድ ፡ ቃል ፣ ወይም ፣ በተዋበው ፣ ጥቁር ፡ ቅንድብሽ ፣ ንቅናቄ ፣ ባሕር ፣ ውስጥ ፣ ልጥለው ፤ ላቃጥለው ፡ ዝግጁ ፣ ነኝ! ምናልባት ፡ ንግግሬ ፣ ያለ ፣ ጊዜውና ፣ ያለ ፣ ሥፍራው ፡ የተደረገ ፣ የሞኝ ፣ ንግግር ፣ ይሆናል ። በተማሪ ፣ ቤትና ፣ በዛፖሮዥያኖች ፣ መካከል ፣ ኖሬ ፣ እንደ ፣ ነገሥታት ፣ እንደ ፣ ልዑላንና ፣ እንደ ፡ ጨዋ ፣ መኳንንት ፣ ልናገር ፣ አልችልም ። አንቺ ፣ ከሁላችንም ፣ የተለየሽ ፣ የእግዚአብሔር ፣ ፍጥረት ፣ እንደሆንሽ ፣ አውቃለሁ ። ሌሎች ፣ የጨዋ ፣ ሚስቶችና ፣ ልጆች ፣ ሁሉ ፣ ከአንቺ ፣ በታች ፣ ናቸው ። እኛ ፣ ባሮችሽ ፣ ለመሆን ፣ እንኳን ፣ አንበቃም ። አንቺን ፣ ለማገልገል ፣ የሚገባቸው ፡ የሰማይ ፡ መላዕክት ፣ ብቻ ፣ ናቸው ።»

ልጅቷ ፣ አካላቷ ፣ ሁሉ ፣ ጆሮ ፣ ሆኖ ፣ አንድም ፣ ቃል ፡ ሳያመልጣት ፣ ኃይለኛ ፣ የወጣት ፣ መንፈስ ፣ እንደመስታዋት ፣ የሚያሳየውን ፣ ይህን ፣ ንግግር ፣ ከፍ ፣ ባለ ፣ አድናቆት ፣ ታደምጥ ፣ ነበር ። የተዋበውን ፣ ፊቷን ፣ ወደሱ ፣ ቀና ፡ አድርጋ ፣ ግንባሯ ፣ ላይ ፣ የተበታተነውን ፣ ጸጉርዋን ፣ ወደኋላ ፣ አደረገችና ፣ ብዙ ፣ ስታስተውለው ፣ ቆየች ። ልትናገርም ፣ አስባ ፣ ወዲያው ፣ ይህ ፣ ወጣት ፣ ዛፖሮዥያን ፣ መሆኑንና ፣ አባቱ ፣ ወንድሞቹና ፣ ሃገሩ ፣ ለበቀል ፣ ታጥቀው ፣ የተሰለፉ ፡ መሆናቸውን ፤ ከተማዋን ፣ የከበቧት ፣ ዛፖሮዥያኖች ፣ ጨካኞች ፣ መሆናቸውንና ፣ የከተማው ፣ ኑዋሪዎች ፣ ሁሉ ፣ በአሰቃቂ ፣ የሞት ፣ ጥላ ፣ ሥር ፣ እንዳሉ ፣ በማስታወስ ፣ ምላሷን ፡ ሰበሰበች ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ሳታስበው ፣ በዓይኖቿ ፣ እንባ ፡ ተንቀረዘዘና ፣ በጥልፍ ፣ ያጌጠ ፣ አንድ ፣ የሃር ፣ መሐረብ ፡ አንስታ ፣ ከዓይኗ ፣ ስታስጠጋው ፣ መሐረቡ ፣ ወዲያው ፣ ራ



ሰ ። በሃዘን ፡ ስትንሰቀሰቅም ፡ እሱ ፣ እንዳያያት ፡ መርዘኛ ፣ እባብ ፡ እንደነደፋት ፣ ሁሉ ፣ የተዋበውን ፣ ራሷን ፣ ወደኋላ ፣ ዘንበል ፣ አድርጋ ፣ በረዶ ፣ በመሰሉት ፣ ጥርሶቿም ፣ ከንፈሯን ፡ ነክሳ ፣ ዓይኖቿን ፣ በመሐረቡ ፡ ሸፍና ፡ ብዙ ፣ ቆየች ።

«አንድ ፣ ቃል ፣ ብቻ ፣ እንኳን ፣ ተናግረሽ ፡ ድምጽሽን ፣ ልስማው!» አለና ፣ አንድሬይ ፣ ለስላሳውን ፣ እጅዋን ፣ በእጁ ፡ ጨበጠ ። በዚህን ፣ ጊዜም ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፡ የሚያንገበግብ ፡ እሳት ፣ በደም ፣ ሥሩ ፣ ሁሉ ፣ ተሰራጭቶ ፣ እጅዋን ፣ ጠበቅ ፣ አድርጎ ፣ ጨበጠው ።

እሷ ፣ ግን ፣ መሐረቡን ፣ ከፊቷ ፣ ሳታነሳ ፤ ሳትንቀሳቀስ ፣ ዝም ፣ አለች ።

«ለምን ፣ ተከዝሽ? ንገሪኝ ፤ ለምንድን ፣ ነው ፣ ያዘንሽው?» አላት ።

በዚህን ፣ ጊዜ ፣ መሐረቡን ፣ ከፊቷ ፣ አንስታ ፣ ዓይኖቿ ፣ ላይ ፣ የተበተነውን ፣ ረጅም ፣ ጸጉሯን ፣ ወደ ፣ ጐን ፣ መለስ ፣ አደረገችና ፤ ቀስ ፣ ባለ ፣ ድምጽ ፤ ሃዘን ፣ የተመላ ፣ ንግግር ፣ ጀመረች ፤

«በዕውነት ፣ እኔ ፣ ሊታዘንልኝ ፣ የሚገባ ፣ ፍጥረት ፣ አይደለሁምን? የወለደችኝስ ፣ እናቴ ፣ ምንኛ ፣ ልታዝን ፣ ይገባታል ፣ ተፈጥሮዬ ፣ ሁሉ ፣ መሪር ፣ ነው ። ወይ ፣ ክፉ ፣ ዕድሌ! ያለርኅራኄ ፣ የምታሰቃየኝ ፣ አንተ ፣ አይደለህምን? ወይ ፣ ክፉ ፣ ዕድሌ! ከፍተኛ ፣ መኳንንት ፤ ሃብታም ፣ ጨዋዎች ፤ የውጭ ፣ መንግሥታት ፣ ባላባቶች ፣ አንተው ፣ አምጥተህ ፡ ከእግሬ ፣ ሥር ፣ ጣልህልኝ! ሁሉም ፡ ወደዱኝ ። ከነሱም ፣ ማንኛቸውንም ፣ ወደድሁህ ፣ ብለው ፣ ታላቅ ፣ ክብር ፣ አድርጎ ፣ በቆጠረው ፣ ነበር ። ትንሽ ፣ ምልክትም ፣ ባሳየው ፣ ኖሮ ፤ ከነሱ ፣ መካከል ፣ በትውልድም ፣ በውበትም ፣ የላቀው ፣ አንዱ ፣ የኑሮ ፣ ጓደኛዬ ፣ በሆነ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ጨካኙ ፡ ዕድሌ ፣ ልቤን ፣ ከሃገራችን ፣ ስመጥሩ ፣ መኳንንት ፡ ሳይሆን ፡ በአንድ ፣ እንግዳ ፣ ሰው ፤ በጠላታችን ፣ እንዲማረክ ፡ አደረ

ግኸው ። ምን ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቼ ፡ ይሆን ፤ ቅድስት ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ሆይ! ምን ፡ ኃጢአት ፡ ምን ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ብሠራ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በጭካኔ ፡ የፈረድሽብኝ? ጊዜዬን ፡ ሁሉ ፡ በተትረፈረፈ ፡ የሃብት ፡ ኑሮ ፡ አሳለፍሁት ። ማለፊያ ፡ ምግቦችና ፡ ጣፋጭ ፡ ወይኖች ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ነበሩ ። ታዲያ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለምን ፡ ኖሩዋል? መጨረሻው ፡ ምን ፡ ሊሆን? በመንግሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የመጨረሻው ፡ መናጢ ፡ ድሃ ፡ እንኳን ፡ የማይሞተውን ፡ አሰቃቂ ፡ ሞት ፡ እንድሞት ፡ ነው? ደግሞ ፡ ይኸው ፡ አሰቃቂው ፡ መጨረሻዬ ፡ ሳያንሰኝ ፤ ሃያ ፡ ጊዜ ፡ ተደጋግሞም ፡ ቢሆን ፡ በሥቃይ ፡ ልሞትላቸው ፡ የምመኘውን ፡ አባትና ፡ እናቴን ፡ ከኔ ፡ ቀድመው ፡ በሥቃይ ፡ ሲሞቱ ፡ ልመለከት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሳይበቃ ፡ ቀርቶ ፡ ይኸው ፡ ተጨማሪ ፡ ሥቃይ ፡ ደረሰብኝ ። በዚች ፡ በመጨረሻዬ ፡ ሰዓት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሕልሜ ፡ እንኳን ፡ ታይቶኝ ፡ የማያውቅ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ ለመስማትና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ ለማየት ፡ በቅቼ ፡ በንግግሩ ፡ ልቤ ፡ እንዲጨነቅና ፡ መሪሩ ፡ ዕጣዬ ፡ የባሰ ፡ መሪር ፡ እንዲሆን ፡ ሆንሁ ። አሟሟቴ ፡ የበለጠ ፡ መሪር ፡ ሞት ፡ እንዲሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጸጸት ፡ ደረሰብኝ ። ስሞትም ፤ ክፉው ፡ ዕድሌ ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ እረግምሃለሁ ። የተቀደስሽ ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ሆይ ፡ ኃጢአቴን ፡ ይቅር ፡ በይኝና ፡ አንቺንም ፡ እንዲሁ ፡ እረግምሻለሁ!»

ይህንን ፡ ተናግራ ፡ ዝም ፡ ስትል ፡ የመጨነቅና ፡ የተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ መልክ ፡ ፊቷን ፡ አለበሰው ። በሃዘን ፡ ከተኮሰተሩት ፡ ቅንድቦቿና ፡ ከአቀረቀሩት ፡ ዓይኖቿ ፡ ጀምሮ ፡ በደማም ፡ ጉንጮቿ ፡ ላይ ፡ እስከሚወርዱት ፡ የእንባ ፡ ዘለላዎች ፡ ድረስ ፡ ጠቅላላው ፡ ገጽዋ ፤ «ከእንግዲህ ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ አይገኝም!» የሚል ፡ ቃል ፡ የተጻፈባቸው ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤

«እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ ተሰምቶ ፡ አይታወቅም! በፍጹም ፡ ሊሆን ፡ አይችልም! የሴቶች ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡



የሆነች ፡ ቆንጆ ፡ የተፈጠረችው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ቅድስት ፡ አድርጐ ፡ እንዲሰግድላት ፡ ሲሆን ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ መሪር ፡ ዕድል ፡ ልትሠቃይ ፡ አትችልም! የለም ፤ አትሞችም! በትውልዴና ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በምወዳቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ እምላለሁ ፤ በፍጹም ፡ አትሞችም! ግን ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ይህንን ፡ ጨካኝ ፡ ዕድል ፡ ኃይልና ፡ ድፍረት ፡ ወይም ፡ ጸሎት ፡ ሊያሸንፈው ፡ ካልቻለ ፡ አብረን ፡ እንሞታለን ፤ ከአንቺም ፡ ቀድሜ ፡ እኔ ፤ እፊትሽ ፤ ከተዋቡት ፡ እግሮችሽ ፡ ሥር ፡ እሞታለሁ ። ሊነጥለን ፡ የሚችለው ፡ ሞት ፡ ብቻ ፡ ነው ።»

እሷም ፡ የተዋበውን ፡ አንገቷን ፡ በእርጋታ ፡ እየነቀነቀች ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፤

«መኰንኔ ፡ ሆይ ፤ እኔንንም ፡ እራስህንም ፡ አታታልል ። እምነትህንና ፡ ያለብህን ፡ ግዴታ ፡ ስለማውቅ ፡ ልትወደኝ ፡ እንደማትችል ፡ በሃዘን ፡ ተገንዝቤያለሁ ። እኛ ፡ ጠላቶችህ ፡ ስንሆን ፤ አባትና ፡ ወገኖችህ ፡ ሃገርህም ፡ ይበልጡብሃል ።»

አንድሬይ ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀና ፡ እንደ ፡ ረጅም ፡ ምሰሶ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፤ «ታዲያ ፡ አባቴ ፤ ወገኖቼ ፤ ሃገሬስ ፡ ለእኔ ፡ ምኖቼ ፡ ናቸው? ምርጫ ፡ ከመጣ ፤ ምንም ፡ ነገር ፤ ማንንም ፡ ሰው ፡ ለማወቅ ፡ አልፈልግም! ማንንም!» አለና ፡ በተለመደው ፡ የኰዛኮች ፡ የቆራጥነት ፡ አነጋገርና ፡ ድምጽ፤ «ኡክሬይን ፡ የኔ ፡ ሃገር ፡ ናት ፡ የሚል ፡ ማን ፡ ነው? ሃገሬ ፡ እንድትሆን ፡ ማን ፡ ነው ፡ የሰጠኝ? ሃገር ፡ ማለት ፡ ልባችን ፡ የሚጓጓለትና ፡ ከሁሉ ፡ አብልጠን ፡ የምንወደው ፡ ነገር ፡ ነው ። አንቺ ፡ …አዎ ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፡ የኔ ፡ ሃገር! እንዲህ ፡ ያለችውን ፡ ሃገር ፡ በሕይወት ፡ እስካለሁ ፡ ድረስ ፡ በልቤ ፡ ተሸክሜያት ፡ እኖራለሁ ። ሊነጥቀኝ ፡ ቢሞክርም ፡ ማናቸውንም ፡ ኰዛክ ፡ እቋቋመዋለሁ! ለዚች ፡ ሃገር ፡ ያለኝን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ልፈታ ፡ ሃብቴንም ፡ ልበትን ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ!» አለ ።

ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ደርቃ ፡ የተዋበች ፡ ሃውልት ፡ መስላ ፡ ከተመለከተችው ፡ በኋላ ፡ እንባዋ ፡ ይረግፍ ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ ዘልላ ፡ አንገቱን ፡ በረዶ ፡ በመሰሉት ፡ ክንዶቿ ፡ አቅፋ ፡ ጮኻ ፡ ተንሰቀሰቀች ።

ልክ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ከውጭ ፤ ራቅ ፡ ያለ ፡ የጫጫታና ፡ የጡሩምባ ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ ። ለአንድሬይ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ አልተሰማውም ። ለእሱ ፡ የሚሰማው ፤ የተዋቡት ፡ ከንፈሮቿና ፡ ሞቃት ፡ ትንፋሿ ፤ ጉንጩን ፡ የሚነካው ፡ እንባዋ ፤ ፊቱን ፡ ያለበሰው ፡ ሐር ፡ የመሰለው ፡ ጸጉሩዋ ፡ መዓዛ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ታታሩዋ ፡ ገረድ ፤ «ዳንን! ዳንን!» በማለት ፡ በደስታ ፡ እየጮኸች ፡ ገባችና ፤ «ወታደሮቻችን ፡ ከተማ ፡ ገብተዋል ። እህልና ፡ እንዲሁም ፡ የተማረኩ ፡ ዛፖሮዥያዎችን ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡» አለች ።

ነገር ፡ ግን ፡ የተቃቀፉት ፡ ልጂቱና ፡ ጐልማሳው ፤ የማን ፡ ወታደሮች ፡ ከተማ ፡ እንደገቡ ፤ ምንስ ፡ ይዘው ፡ እንደመጡ ፤ የተማረኩት ፡ ዛፖሮዥያውያኖችስ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በፍጹም ፡ አላዳመጡም ። አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በማይገኝ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ተውጦ ፡ ጉንጩን ፡ የሚነካኩትን ፡ ጣፋጭ ፡ ከንፈሮች ፡ ይስም ፡ ጀመር ። እሷም ፡ መልሳ ፡ ትስመው ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ሁለቱንም ፡ የተሰማቸው ፡ ስሜት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

ኮዛኩ ፡ ከእንግዲህ ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ነው! ከኮዛክ ፡ መኳንንትነት ፡ ኮበለለ! ከእንግዲህ ፡ ዛፖሮዥዬን ፤ የአባቱን ፡ መንደሮች ፤ የእምላኩንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አያይም! ኡክሬይንም ፡ ሊጠብቋት ፡ ከታጠቁት ፡ ልጆቿ ፡ ሁሉ ፡ የላቀውን ፡ ጀግና ፡ ልጅዋን ፡ ከእንግዲህ ፡ አታየውም ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ከሸበተው ፡ ጸጉሩ ፡ አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ነጭቶ ፡ እንዲህ ፡ የሚያሳፍረውን ፡ ልጁን ፡ የወለደበትን ፡ ቀን ፡ ይረግማል ።



## ምዕራፍ ፡ ሰባት ።

ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ የዛፖሮዥያንን ፡ ሠፈር ፡ መላው ። በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ወታደሮቹ ፡ እንዴት ፡ አልፈው ፡ ከከተማው ፡ እንደገቡ ፡ ማንም ፡ ሊያውቅ ፡ አልቻለም ። በኋላ ፡ ግን ፡ በከተማው ፡ የስርቆሽ ፡ በር ፡ ሠፍሮ ፡ የነበረው ፡ የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ጥምብዝ ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ ስለነበር ፡ አንዳቸውም ፡ ሳይሰሙ ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ደርሰው ፤ ግማሻቸውን ፡ ገድለው ፡ የተረፉትን ፡ ማርከው ፡ መሄዳቸው ፡ ታወቀ ። ጫጫታውን ፡ የሰሙ ፡ የጐረቤት ፡ ሰፈር ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ መሳሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ሲነሱ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ ገብተው ፡ ኖሮ ፡ ያለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተሯሩጠው ፡ የተከተሉትንም ፡ እንቅልፍ ፡ ያልለቀቃቸው ፡ ኮዛኮች ፡ የወታደሮቹ ፡ የደጀን ፡ ጦር ፡ ተታኩሶ ፡ መለሳቸው ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮይው ፡ ሁሉም ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አዝዞ ፡ ሁሉም ፡ ተሰበሰቡና ፡ ባርኔጣቸውን ፡ አውልቀው ፡ ዙሪያውን ፡ በጸጥታ ፡ ሲቆሙ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ የደረሰውን ፡ አያችሁ ፡ ወንድሞቼ ። ስካር ፡ ምን ፡ እንዳደረሰ ፡ ተመለከታችሁ! ጠላት ፡ እንዴት ፡ እንዳሳፈረን ፡ ይኸው ፡ አያችሁ ። ሁልጊዜ ፡ ይኸው ፡ ናችሁ! የሚሰጣችሁ ፡ ቮድካ ፡ ትንሽ ፡ በርከት ፡ ካለላችሁ ፡ ትጋቱ ፡ ትጋቱና ፡ የክርስቲያን ፡ ወታደሮች ፡ ጠላት ፡ ሱሪያችሁን ፡ መጐተት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊታችሁ ፡ ላይ ፡ ቢያነጥሰባችሁም ፡ አትሰሙትም!»

ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋታቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቆሙ ። የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፤

«ቆይ ፡ እስቲ ፡ ባትኮ! ምንም ፡ እንኳን ፡ ኮሼቮይው ፡ ሲናገር ፡ ማቋረጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ቢሆንም ፤ ጉዳዩ ፡ አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ባለመሆኑ ፡ ልናገር ፡ ይገባኛል ። ይህን ፡ የክርስ

ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ደርቃ ፡ የተዋበች ፡ ሃውልት ፡ መስላ ፡ ከተመለከተችው ፡ በኋላ ፡ እንባዋ ፡ ይረግፍ ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ ዘልላ ፡ አንገቱን ፡ በረዶ ፡ በመሰሉት ፡ ክንዶቿ ፡ አቅፋ ፡ ጮኻ ፡ ተንሰቀሰቀች ።

ልክ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ከውጭ ፤ ራቅ ፡ ያለ ፡ የጫጫታና ፡ የጡሩምባ ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ ። ለአንድሬይ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ አልተሰማውም ። ለእሱ ፡ የሚሰማው ፤ የተዋቡት ፡ ከንፈሮቿና ፡ ሞቃት ፡ ትንፋሿ ፤ ጉንጩን ፡ የሚነካው ፡ እንባዋ ፤ ፊቱን ፡ ያለበሰው ፡ ሐር ፡ የመሰለው ፡ ጸጉሩዋ ፡ መዓዛ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ታታሪዋ ፡ ገረድ ፤ «ዳንን! ዳንን!» በማለት ፡ በደስታ ፡ እየጮኸች ፡ ገባችና ፤ «ወታደሮቻችን ፡ ከተማ ፡ ገብተዋል ። እህልና ፡ እንዲሁም ፡ የተማረኩ ፡ ዛፖሮዥያኖችን ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡» አለች ።

ነገር ፡ ግን ፡ የተቃቀፉት ፡ ልጂቱና ፡ ጐልማሳው ፤ የማን ፡ ወታደሮች ፡ ከተማ ፡ እንደገቡ ፤ ምንስ ፡ ይዘው ፡ እንደመጡ ፤ የተማረኩት ፡ ዛፖሮዥያውያኖችስ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በፍጹም ፡ አላዳመጡም ። አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በማይገኝ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ተውጦ ፡ ጉንጩን ፡ የሚነካኩትን ፡ ጣፋጭ ፡ ከንፈሮች ፡ ይስም ፡ ጀመር ። እሷም ፡ መልሳ ፡ ትስመው ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ሁለቱንም ፡ የተሰማቸው ፡ ስሜት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

ኮዛኩ ፡ ከእንግዲህ ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ነው! ከኮዛክ ፡ መኳንንትነት ፡ ኮበለለ! ከእንግዲህ ፡ ዛፖሮዥዬን ፤ የአባቱን ፡ መንደሮች ፤ የአምላኩንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አያይም! ኡክሬይንም ፡ ሊጠብቋት ፡ ከታጠቁት ፡ ልጆቿ ፡ ሁሉ ፡ የላቀውን ፡ ጀግና ፡ ልጅዋን ፡ ከእንግዲህ ፡ አታየውም ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ከሸበተው ፡ ጸጉሩ ፡ አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ነጭቶ ፡ እንዲህ ፡ የሚያሳፍረውን ፡ ልጁን ፡ የወለደበትን ፡ ቀን ፡ ይረግማል ።





ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ የዛፖሮዥያንን ፡ ሠፈር ፡ መላው ። በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ወታደሮቹ ፡ እንዴት ፡ አልፈው ፡ ከከተማው ፡ እንደገቡ ፡ ማንም ፡ ሊያውቅ ፡ አልቻለም ። በኋላ ፡ ግን ፡ በከተማው ፡ የስርቆሽ ፡ በር ፡ ሠፍሮ ፡ የነበረው ፡ የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ጥምብዝ ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ ስለነበር ፡ አንዳቸውም ፡ ሳይሰሙ ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ደርሰው ፤ ግማሸቻቸውን ፡ ገድለው ፡ የተረፉትን ፡ ማርከው ፡ መሄዳቸው ፡ ታወቀ ። ጫጫታውን ፡ የሰሙ ፡ የጐረቤት ፡ ሰፈር ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ መሳሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ሲነሱ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ ገብተው ፡ ኖሮ ፡ ያለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተሯሩጠው ፡ የተከተሉትንም ፡ እንቅልፍ ፡ ያልለቀቃቸው ፡ ኮዛኮች ፡ የወታደሮቹ ፡ የደጀን ፡ ጦር ፡ ተታኩሶ ፡ መለሳቸው ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮይው ፡ ሁሉም ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አዘዞ ፡ ሁሉም ፡ ተሰበሰቡና ፡ ባርኔጣቸውን ፡ አውልቀው ፡ ዙሪያውን ፡ በጸጥታ ፡ ሲቆሙ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ የደረሰውን ፡ አያችሁ ፡ ወንድሞቼ ። ስካር ፡ ምን ፡ እንዳደረሰ ፡ ተመለከታችሁ! ጠላት ፡ እንዴት ፡ እንዳሳፈረን ፡ ይኸው ፡ አያችሁ ። ሁልጊዜ ፡ ይኸው ፡ ናችሁ! የሚሰጣችሁ ፡ ቮድካ ፡ ትንሽ ፡ በርከት ፡ ካለላችሁ ፡ ትጋቱ ፡ ትጋቱና ፡ የክርስቲያን ፡ ወታደሮች ፡ ጠላት ፡ ሱሪያችሁን ፡ መጐተት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊታችሁ ፡ ላይ ፡ ቢያነጥስባችሁም ፡ አትሰሙትም!»

ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋታቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቆሙ ። የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፤

«ቆይ ፡ እስቲ ፡ ባትኮ! ምንም ፡ እንኳን ፡ ኮሼቮይው ፡ ሲናገር ፡ ማቋረጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ቢሆንም ፤ ጉዳዩ ፡ አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ባለመሆኑ ፡ ልናገር ፡ ይገባኛል ። ይህን ፡ የክርስ

ቲያን ፡ ጦር ፡ ስትወቅስ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ አልተከተልህም ። በዘመቻ ፡ ላይ ፡ እያሉ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ሲዋጉ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ጠንካራ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ እንደተመደቡ ፡ ሰክረው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሞት ፡ የሚገባቸው ፡ ጥፋተኞች ፡ በሆኑ ፡ ነበር ። እኛ ፡ ግን ፡ በከንቱ ፡ ተጐልተን ፡ ወይም ፡ በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ስንንቀዋለል ፡ ነው ፡ የሰነበትነው ። ወይ ፡ አልጾምን ፡ ወይ ፡ ሌላ ፡ የክርስቲያን ፡ ሙያ ፡ አልሠራን ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በከንቱ ፡ ተጐልቶ ፡ ከመጠጣትና ፡ ከመስከር ፡ እንዴት ፡ ይወሰናል? በዚህ ፡ ምንም ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ። ይልቅስ ፡ አሁን ፡ ባላሰቡ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ለማምለጥ ፡ እንደማይችሉ ፡ እናሳያቸው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ቀጥቅጠን ፡ ድል ፡ አድርገናቸዋል ። አሁንም ፡ ያንዳቸው ፡ ህይወት ፡ እንኳን ፡ እንዳይተርፍ ፡ አድርገን ፡ እንቀጥቅጣቸው ።»

የመንደሩ ፡ አለቃ ፡ ንግግር ፡ ኮዛኮቹን ፡ ሁሉ ፡ አስደሰታቸው ። አቀርቅሮ ፡ የነበረው ፡ ራሳቸው ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ብዙዎቹም ፤ «ኩኩቤንኮ ፡ መልካም ፡ ተናገረ!» በማለት ፡ አደነቁ ።

ከኮሼቮይው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ የነበረው ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፤ «ታዲያስ ፡ ኮሼቮይ? ኩኩቤንኮ ፡ እውነቱን ፡ የተናገረ ፡ይመስላል ። ታዲያ ፡ ለዚህ ፡ ምን ፡ ትመለሳለህ?» አለው ።

ኮሼቮይውም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«በእውነቱ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልጅ ፡ የወለደ ፡ አባት ፡ የታደለ ፡ ነው! የነቀፌታ ፡ ቃል ፡ ለመሰንዘር ፡ አዋቂነት ፡ አያስፈልገውም ። ነገር ፡ ግን ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ያለን ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ በማሳዘን ፡ ፈንታ ፡ የሚያነቃቃና ፡ የሚያደፋፍር ፡ ቃል ፡ ለመናገር ፡ ታላቅ ፡ ጥበብን ፡ ይጠይቃል ። እኔም ፡ ራሴ ፡ የሚያበረታታችሁ ፡ ቃል ፡ ለመናገር ፡ አስቤ ፡ ነበር ። ግን ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ፈጥኖ ፡ በማሰብ ፡ ተናገረው ።»



በዚህን ፡ ጊዜ ፡ «ኮሼቮይውም ፡ መልካም ፡ ተናገረ!» የሚል ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ድምጽ ፡ አስተጋባ ።

ጠና ፡ ያሉት ፡ ሽበቶ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ በዝግታ ፡ «መልካም ፡ ተናገረ ፡ » አሉ ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮይው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ፤

«አሁን ፡ አዳምጡኝ ፡ ወዳጆቼ! ሰይጣን ፡ ይያዘውና ፤ ይህን ፡ ምሽግ ፡ ለመያዝ ፤ ጀርመኖች ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ተንጠላጥሎ ፡ ወይም ፡ ሰርስሮ ፡ መግባት ፡ የኮዛክ ፡ ሞያ ፡ አይደለም ። በግምት ፡ ለመረዳት ፡ እንደምንችለው ፡ ጠላቶቻችን ፡ወደ ፡ ከተማው ፡ ሲገቡ ፡ ብዙ ፡ ሠረገላ ፡ ስላልነበራቸው ፡ በቂ ፡ ስንቅና ፡ ጓዝ ፡ አልያዙም ፡ ማለት ፡ ነው ። በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሰዎችም ፡ በጣም ፡ ስለተራቡ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ አፍታ ፡ ነው ፡ የሚጨርሱት ። በሳር ፡ ረገድ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ከቅዱሳናቸው ፡ አንዱ ፡ ከሰማይ ፡ ድርቆሽ ፡ ካልጣለላቸው ፡ በቀር ፡ ፈረሶቻቸው ፡ ምንም ፡ የሚቀምሱት ፡ የላቸውም ። ይህንኑም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ። ቄሶቻቸው ፡ ከመላስኝነት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ የላቸውም ፡... የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ጠላቶቻችን ፡ ምሽጋቸውን ፡ ትተው ፡ መውጣታቸው ፡ አይቀርም ። ስለዚህ ፡ በሶስት ፡ ተከፈሉና ፡ በሶስቱ ፡ የከተማው ፡ በሮች ፡ ተሰለፉ ። የአምስት ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ በዋናው ፡ በር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፤ በቀሩት ፡ በሁለቱ ፡ ደግሞ ፡ በያንዳንዳቸው ፡ የሶስት ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ይሰለፍ ። የዲያድኪቭና ፡ የኮርሰን ፡ መንደሮች ፡ ለደፈጣ ፡ ይዘጋጁ ። ኮሎኔል ፡ ታራስም ፡ ክፍለ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ያደፍጣል ። የቲታሬቭካና ፡ የቲሞገሼቭካ ፡ መንደሮች ፡ ተጠባባቂ ፡ ጦር ፡ በመሆን ፡ ከጓዛችን ፡ በስተቀኝ ፡ ይሰለፋሉ ። የሽቸርቢኖቭና ፡ የላይኛው ፡ እስቴብሊኪቭ ፡ መንደሮችም ፡ እንዲሁ ፡ በጓዙ ፡ በስተግራ ፡ ይሰለፋሉ ። ከዚያ ፡ ክመካከላችን ፡ አነጋገር ፡ የሚ

ያውቁ ፡ ደፋሮች ፡ ወጥተው ፡ ጠላትን ፡ በንግግር ፡ ያበሳጩ፤ ፖሊሶች ፡ በተፈጥሮ ፡ ቅል ፡ ራሶች ፡ ስለሆኑ ፡ ስድባችሁን ፡ አይችሉምና ፡ ዛሬውኑ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ከምሽጋቸው ፡ ሳይወጡ ፡ አይቀሩም ። የሰፈር ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ሰፈራችሁን ፡ መቆጣጠር ፡ አለባችሁ ። ሰው ፡ የጐደለበት ፡ እንዳለ ፡ ከፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ከተረፉት ፡ ሰዎች ፡ ወስዶ ፡ ይሙላ ። ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ተቆጣጥራችሁ ፡ አጠናቅቁ ። አእምሮውን ፡ ቀለል ፡ እንዲለው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ዳቦና ፡ አንድ ፡ መለኪያ ፡ ቮድካ ፡ ስጡ ። ብቻ ፡ የትናንቱ ፡ ምግብ ፡ ሲታሰብ ፡ የማንም ፡ ሆድ ፡ የጐደለ ፡ አይመስለኝም ። እንዲያውም ፡ እውነት ፡ ለመናገር ፡ እንደትናንቱ ፡ አበላላችሁ ፡ ሳትፈነዱ ፡ ማደራችሁ ፡ ገርሞኛል ። ደግሞ ፡ የመጨረሻ ፡ ትእዛዜን ፡ አዳምጡ ። አንድ ፡ አይሁድ ፡ የመጠጥ ፡ ነጋዴ ፡ አንዲት ፡ መለኪያ ፡ ቮድካ ፡ እንኳን ፡ ለአንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሲሸጥ ፡ ቢገኝ ፡ የአሳማ ፡ ጆሮ ፡ ግንባሩ ፡ ላይ ፡ በምስማር ፡ መትቼ ፡ ቁልቁል ፡ ነው ፡ የምሰቅለው ። አሁን ፡ ወንድሞቼ ፡ ወደየሥራችሁ!»

ኮሼቮይው ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ሲያበቃ ፣ ቆባቸውን ፡ እንዳወለቁ ፡ እጅ ፡ ነስተውት ፡ ወደየሠረገላቸውና ፡ ወደየሰፈራቸው ፡ ተሰማሩ ። ርቀው ፡ እስኪሔዱም ፡ ድረስ ፡ ቆባቸውን ፡ መልሰውን ፡ አላደረጉም ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ ዝግጅታቸውን ፡ ጀመሩ ። ጐራዴያቸውንና ፡ ሰይፋቸውን ፡ አሰናዱ ። ባሩድም ፡ ከከረጢት ፡ እያወጡ ፡ የባሩድ ፡ ቀንዳቸውን ፡ ሞሉ ። ፈረሶቻቸውን ፡ መርጠው ፡ ሠረገላዎቻቸውንም ፡ አደራጁ ።

ታራስ ፡ ወደ ፡ ክፍለ ፡ ጦሩ ፡ ሲሄድ ፡ መንገዱን ፡ ሁሉ ፡ አንድሬይ ፡ የት ፡ እንደጠፋ ፡ ያሰላስል ፡ ነበር ። እንደሌሎቹ ፡ ከመንቃቱ ፡ በፊት ፡ ታስሮ ፡ ተማርኮ ፡ ይሆን? ግን ፡ ይህ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። አንድሬይ ፡ በሕይወቱ ፡ እንዳለ ፡ የሚማረክ ፡ ሰው ፡ አይደለም ። ደግሞ ፡ ሞቷል ፡ እንዳይባል ፡ ከሞቱት ፡ ኮዛኮች ፡ መሃል ፡ ሬሳው ፡ አልተገኘም ። ታራስ ፡



ከጦሩ ፡ ሰፈር ፡ ሲደርስ ፡ በሃሳብ ፡ ከመዋጡ ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስሙን ፡ ሲጠራው ፡ አልሰማም ፡ ነበር ።

በመጨረሻም ፡ ከእንቅልፍ ፡ እንደነቃ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፣ «ማን ፡ ነው ፡ የሚፈልገኝ?» ሲል ፡ አይሁዱ ፡ ያንኬል ፡ ከፊቱ ፡ ቆሞ ፡ አገኘ ።

አይሁዱም ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ እንዳሰበ ፡ ሁሉ ፡ እየተርበተበተ ፡ «ክቡር ፡ ኮሎኔል! ክቡር ፡ ኰሎኔል! ከተማ ፡ ደርሼ ፡ ነው ፡ የመጣሁ ፣ ክቡር ፡ ኮሎኔል!» አለ ።

ታራስ ፡ ይህ ፡ አይሁድ ፡ ከተማው ፡ ገብቶ ፡ ለመውጣት ፡ እንዴት ፡ እንደቻለ ፡ በማድነቅ ፡ እየተመለከተ ፣ «ምን ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ የወሰደህ?» አለው ።

«ይኸው ፡ አሁን ፡ እነግረዎታለሁ ። ይኸውልዎ ፡ በአነጋግ ፡ ላይ ፡ ኮዛኮች ፡ ተኩስ ፡ ጀምረው ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ጩኸት ፡ ስሰማ ፡ ወዲያው ፡ ጨርቄን ፡ አንጠልጥየ ፡ ለማጥለቅ ፡ እንኳን ፡ ሳልዘገይ ፡ የተኩሱን ፡ ምክንያት ፡ ለማጣራት ፡ ሮጥሁና ፡ ልክ ፡ ከከተማው ፡ በር ፡ ስደርስ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ወታደሮች ፡ ሲገቡ ፡ አገኘሁ ። በወታደሮቹም ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ኮርኔት ፡ ጋሌንዶዊችን ፡ አየኋቸው ። እኚህ ፡ ሰው ፡ የማውቃቸው ፡ መኳንንት ፡ ሲሆኑ ፣ በአለፉት ፡ ሶስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ቼርቮኔጽ ፡ ብድር ፡ አለባቸው ። ስለዚህ ፡ ብድሬን ፡ የምጠይቅ ፡ በመምሰል ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ከተማ ፡ ገባሁ ።»

«እንዴት? ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ገብተህ ፡ ደግሞ ፡ ብድር ፡ ለማስከፈል ፡ ፈለግህ? እሱም ፡ እዚያው ፡ እንደውሻ ፡ እንድትሰቀል ፡ ሳያደርግ ፡ ቀረ?» አለው ፡ ቡልባ ።

«እንዴታ! ሊሰቅሉኝማ ፡ ፈለጉ ። አሽከሮቻቸውም ፡ ወዲያው ፡ ገመዱን ፡ አንገቴ ፡ ላይ ፡ አግብተውት ፡ ነበር ። ግን ፡ ጌትዮውን ፡ ነፍሴን ፡ እንዲያተርፏት ፡ በመለመን ፡ ያለባቸውን ፡ ብድር ፡ እስከፈለጉት ፡ ጊዜ ፡ እንዲያቆዩት ፣ ደግሞ ፡ ሌሎቹ ፡ መኳንንት ፡ ያለባቸውን ፡ ብድር ፡ ካስከፈሉኝ ፡ ተጨ

ማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እሰጥዎታለሁ ፡ ብዬ ፡ ለመንኳቸው ። ክቡር ፡ ኮርኔቱ ፣ ብዙ ፡ መንደሮች ፣ አራት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ እንዲሁም ፡ እስከ ፡ እሽክሎቭ ፡ የሚደርስ ፡ ሰፊ ፡ መሬት ፡ ይኑራቸው ፡ እንጂ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ ከአንድ ፡ ኮዛክ ፡ አይሻሉም ። አንድ ፡ ቼርቮኔጽ ፡ እንኳን ፡ በኪሳቸው ፡ አይገኝም! አሁንም ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የብሬስሎቭ ፡ አይሁዶች ፡ ባይሰጧቸው ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ለመዝመቻ ፡ እንኳን ፡ ምንም ፡ ባላገኙ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ከምክር ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባ ፡ ቀሩት ፡...»

«ታዲያ ፡ ከተማ ፡ ሄደህ ፡ ምን ፡ አደረግህ? ከኛ ፡ ሰዎች ፡ ያየኸው ፡ አለ?»

«አዎ ፡ በደንብ ፡ አይቻለሁ! ብዙ ፡ የኛ ፡ ሰዎች ፡ እዚያ ፡ አሉ ። ኢሳክ ፣ ራሁም ፣ ሳሙኤል ፣ ሃይቫሎህ ፡ ደግሞ ፡ ወለድ ፡ እግድ ፡ ያዡ ፡ አይሁድ ፡...»

«ውሾቹን ፡ እዚያው ፡ ሰይጣን ፡ ይውሰዳቸው! ስለአይሁድ ፡ ዘሮችህ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ግድ ፡ አለኝ! እኔ ፡ የጠየቅሁህ ፡ ስለኛ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ነው!» አለና ፡ ታራስ ፡ በቁጣ ፡ ጮኸበት ።

«አይ ፣ እኔ ፡ የኛን ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ አላየሁም ። ጌታዬ ፡ አንድሬይን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያየኋቸው ።»

«አንድሬይን ፡ አየኸው! በልኮ ፡ ንገረኝ ፡ አንተ ፡ አይሁድ ፣ የት ፡ ነው ፡ ያየኸው? በእስር ፡ ቤት? በጓድጓድ ፡ ውስጥ? ተዋርዶና ፡ ታሥሮ ፡ ነው?»

«ጌታዬ ፡ አንድሬይን ፡ ለማሰር ፡ ማን ፡ ይደፍራል! አሁን ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ታላቅ ፡ መኳንንት ፡ ሆነዋል ። ኧረግ ፡ በእግዚአብሔር ፣ ላውቃቸው ፡ እንኳን ፡ አልቻልሁም! ትከሻቸው ፡ ወርቅ ፡ ብቻ ፣ ደረታቸው ፡ ወርቅ ፡ ብቻ ፣ ጥሩራቸው ፡ ወርቅ ፡ የጦር ፡ ትጥቃቸው ፡ ሁሉ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ልክ ፡ እንደመስከረም ፡ ጸሐይ ፡ በወርቅ ፡ ያንጸባርቃሉ ። ደግሞ ፡ ወየወዱ ፡ ምርጥ ፡ ፈረሳቸውን ፡ ሰጥተዋቸዋል ። ፈረሱ ፡ ብቻ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ቼርቮኔጽ ፡ የሚያወጣ ፡ ነው!»



ቡልባ ፡ ግራ ፡ ገባው ።

«ለምንድን ፡ ነው ፡ ይህን ፡ የባዕድ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ የለበሰው?»

«የበለጠ ፡ ስለሚያምር ፡ ነዋ ። ደግሞ ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላሉ ። ሌሎችም ፡ አብረዋቸው ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላሉ ። እሳቸው ፡ ያስተምሯቸዋል ፣ እነሱም ፡ ያስተምሯቸዋል ። ልክ ፡ ሃብታም ፡ የፖሊሽ ፡ መኰንን ፡ ሆነዋል!»

«ይህን ፡ እንዲያደርግ ፡ ማን ፡ አስገደደው?»

«እኔ ፡ ማንም ፡ አስገደዳቸው ፡ አላልሁም ። በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ወደነሱ ፡ መሔዳቸውን ፡ ጌታዬ ፡ አያውቁም ፡ እንዴ?»

«ማን ፡ ነው ፡ በፈቃዱ ፡ የሔደው?»

«ጌታዬ ፡ አንድሬይ ፡ ናቸዋ!»

«ወዴት ፡ ነው ፡ የሔደው?»

«ወደነሱ ፡ ወገን ፡ ነዋ ። አሁን ፡ በቃ ፡ በፍጹም ፡ የነሱ ፡ ሰው ፡ ሆነዋል ።»

«ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የአሳማ ፡ ጆሮ!»

«እንዴት ፡ ልዋሽ ፡ እችላለሁ! ውሸት ፡ የምናገረው ፡ እኔ ፡ ሞኝ ፡ ነኝ ፡ እንዴ! በነፍሴ ፡ ቆርጬ ፡ እዋሻለሁ ፡ ይመስለዎታል! ለአንድ ፡ ጌታ ፡ ውሸት ፡ የሚናገር ፡ አይሁድ ፡ እንደውሻ ፡ መስቀሉን ፡ አጣሁት ፡ እንዴ!»

«እንግዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ኃይማኖትና ፡ አገሩን ፡ ሸጧል ፡ ማለት ፡ ነው?»

«እኔ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሸጠዋል ፡ አላልሁም ። እኔ ፡ ወደነሱ ፡ ወገን ፡ መሔዳቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተናገርሁት ። »

«ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የተረገምህ ፡ አይሁድ! በክርስቲያኖች ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ተሠርቶ ፡ አያውቅም! ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ልክስክስ ፡ ውሻ!»

«እንዲያው ፣ ዋሽቼ ፡ እንደሆን ፡ በቤቴ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ሳር ፡ ይብቀልበት! እውነት ፡ ዋሽቼ ፡ እንደሆን ፣ በአባቴ ፣

በእናቴ ፣ በአማቴ ፣ በአባቴ ፡ አባት ፣ በእናቴም ፡ አባት ፡ መቃብሮች ፡ ላይ ፡ አላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ምራቁን ፡ ይትፋበት! እንዲያውም ፡ ጌታዬ ፡ ከፈቀዱ ፡ ወደነሱ ፡ ወገን ፡ የሔዱ በትንም ፡ ምክንያት ፡ እንግረዎታለሁ ።»

«ለምን ፡ ሔደ?»

«ወየወዱ ፡ እጅግ ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አለቻቸው ፡… አቤት ፡ አምላኬ! እንዴት ፡ ቆንጆ ፡ ናት!»

እዚህ ፡ ላይ ፡ አይሁዱ ፡ እጆቹን ፡ በመዘርጋት ፣ ዓይኖቹን ፡ በማፍጠጥ ፣ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የሚጣፍጥ ፡ ነገር ፡ እንዲቀምስ ፡ ሁሉ ፡ አፉን ፡ በማጣጣም ፡ ስለውበቷ ፡ ለመግለጽ ፡ ሞከረ ።

«በልኮ ፣ ታዲያስ ፡ ምን ፡ ሆነ?» አለው ፡ ቡልባ ።

«በቃ ፣ ለእሷ ፡ ሲሉ ፡ ወደነሱ ፡ ወገን ፡ ሔዱ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ፍቅር ፡ ከያዘው ፡ ውኃ ፡ እንደተነከረ ፡ የሜማ ፡ ቆዳ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደፈለጉት ፡ ይተጣጠፋል ።»

ቡልባ ፡ በሃሳብ ፡ ተዋጠ ። የሴት ፡ ኃይሏ ፡ ታላቅ ፡ መሆኑና ፡ ብዙ ፡ ኃይለኛ ፡ ሰዎችንም ፡ አሸንፋ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንደመራች ፡ ትዝ ፡ አለው ። አንድሬይም ፡ በተፈጥሮው ፡ በሴት ፡ ውበት ፡ በቶሎ ፡ የሚማረክ ፡ መሆኑንም ፡ አስታወሰ ። ይህን ፡ ሲያሰላስል ፡ ከቆመበት ፡ መሬት ፡ የተተከለ ፡ ይመስል ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ብዙ ፡ ቆየ ።

አይሁዱም ፣ «ይስሙኝ ፡ ጌታዬ ፣ ሁሉንም ፡ ልንገርዎ ፡» አለና ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ፣

«ወዲያው ፡ ጩኸቱን ፡ እንደሰማሁና ፡ ወታደሮቹ ፡ የከተማውን ፡ በር ፡ ሲገቡ ፡ ሳይ ፣ ድንገት ፡ ያስፈልገኝ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ አንድ ፡ የሉል ፡ ጌጥ ፡ ያዝሁና ፡ ሮጥሁ ። መቼም ፡ በከተማው ፡ ወይዛዝርት ፡ አሉና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሚበሉት ፡ ባይኖራቸው ፡ ሉሉን ፡ እንደሚገዙኝ ፡ አውቅ ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ የኮርኔቱ ፡ አሽከሮች ፡ ወዲያው ፡ እንደለቀቁኝ ፣ ሉሉን ፡ ለመሸጥ ፡ ወደ ፡ ወየወዱ ፡ ግቢ ፡ ሮጥሁኝና ፡ እዚያው ፡ ያገኘኋት ፡ አንዲት ፡ ታታር ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ነገረችኝ ። ‘ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሲሸሹ ፡ ሠርግ ፡ ይደረጋል ። ጌታዬ ፡ አንድሬይ ፡ ዛፖሮዥያኖቹን ፡ ለማባረር ፡ ቃል ፡ ገብተዋል ፡’ አለችኝ ።»



«ታዲያ ፡ ያን ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ ፡ እዚያው ፡ አልገደልኸውም?» አለና ፡ ቡልባ ፡ ጮኸ ።

«ለምን ፡ ይገደላሉ? በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ነው ፡ የሄዱት ። ምን ፡ ጥፋት ፡ አጠፉ? እዚያ ፡ የሚሻላቸው ፡ ሆኖ ፡ አገኙትና ፡ ሄዱ ።»

«ታዲያ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተያያችሁ?»

«እንዴታ! አየኋቸው ፡ እንጂ! አቤት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ባለግርማ ፡ ጀግና ! ከሁሉም ፡ የላቁ ፡ ባለግርማ ፡ ሞገሥ! ደግሞ ፡ ወዲያው ፡ አወቁኝ ፣ እግዚአብሔር ፡ ይባርካቸው ። ቀረብ ፡ ስላቸውም ፡ እንዲህ ፡ አሉኝ ፡…»

«ምን ፡ አለህ?»

«መጀመሪያ ፡ በጣታቸው ፡ ጠሩኝና ፡ ‘ያንኬል!’ አሉኝ ። እኔም ፣ ‘ጌታዬ ፡ አንድሬይ!’ አልኋቸው ። ‘ያንኬል ፣ ለአባቴ ፡ ንገረው ፣ ለወንድሜ ፡ ንገረው ፣ ለኮዛኮች ፡ ንገራቸው ፣ ለዛፖሮዥያን ፡ ሁሉ ፣ ለሁሉም ፡ ንገር ። ከእንግዲህ ፡ አባቴ ፡ አባቴ ፡ አይደለም ፣ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ አይደለም ፣ ጓደኞቼም ፡ ጓደኞቼ ፡ አይደሉም ። ሁሉንም ፡ እወጋቸዋለሁ! ከያንዳንዳቸው ፡ ጋር ፡ እዋጋለሁ!’ አሉኝ ።»

«ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንት ፡ ከሃዲ ፡ ይሁዳ! ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንት ፡ ውሻ! ክርስቶስን ፡ የሰቀልኸው ፡ አንተው ፡ ነህ! አንት ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተረገምህ ፡ ሰው! እገድልሃለሁ ፡ አንት ፡ ሰይጣን! በል ፡ ከፊቴ ፡ ጥፋ ፡ ወይ ፡ እዚህ ፡ ቆመህ ፡ሙት!» አለና ፡ ቡልባ ፡ በቁጣ ፡ ጮኾ ፡ ጐራዴውን ፡ መዘዘ ።

የደነገጠው ፡ አይሁድም ፡ ወዲያው ፡ ሩጫ ፡ ጀምሮ ፡ ቀጫጭን ፡ እግሮቹ ፡ የቻሉትን ፡ ያህል ፡ ይበር ፡ ጀመር ። ምንም ፡

እንኳን ፡ ታራስ ፡ ቁጣውን ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለመወጣት ፡ ስላልፈለገ ፡ ባይከተለውም  አይሁዱ ፡ ተገላምጦ ፡ እንኳን ፡ ሳያይ ፡ የኮዛኮቹን ፡ ሰፈር ፡ አቋርጦ ፡ በመስኩም ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ሮጠ ።

ቡልባ ፡ አሁን ፡ ሲያስታውስ ፤ ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ አንድሬይን ፡ ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ በሰፈሩ ፡ መሃል ፡ ሲጓዝ ፡ እንዳየው ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የገዛ ፡ ልጁ ፡ ሃይማኖቱንና ፡ ነፍሱን ፡ ሸጦ ፡ እንዲህ ፡ ካለ ፡ ውርደት ፡ ይደርሳል ፡ ብሎ ፡ ባያምንም ፡ የሸበተውን ፡ ራሱን ፡ በትካዜ ፡ አቀረቀረ ።

በመጨረሻ ፡ ጦሩን ፡ ወደ ፡ ደፈጣ ፡ መራና ፡ እሱም ፡ አብሮ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ብቻ ፡ ኮዛኮች ፡ ሳያቋርጡት ፡ በተረፈው ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ተሰወረ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ፈረሰኞችና ፡ እግረኞች ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ወደ ፡ ሶስቱ ፡ የከተማው ፡ በሮች ፡ በሚወስዱት ፡ መንገዶች ፡ ተጉዞው ፡ ቀርበዋል ። አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ተከታትለው ፡ የየመንደሩ ፡ የጦር ፡ ክፍሎች ፡ ይጓዙ ፡ ጀመር ። ኡማን ፤ ፖፖቪች ፤ ካኔቭ ፤ እስቴብሊኪቭ ፤ ኔዛማይ ፤ ጉርጉዝ ፤ ቲታሬቭካ ፤ ቲሞዜቭካ ፤ የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ብቻ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ተሰልፈዋል ። የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ ቮድካቸውን ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ ጠጥተው ፡ በዚሁ ፡ በመጠጣቸው ፡ መልካም ፡ እድላቸውን ፡ አጥፍተውታል ። አንዳንዶቹ ፡ ከታሠሩ ፡ በኋላ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ እንዳሉ ፡ ሲነቁ ፤ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ እዚያው ፡ እንደተኙ ፡ በመሞት ፡ ሳይነቁ ፡ ቀርተዋል ። አለቃቸው ፡ ህሊብ ፡ ራሱ ፡ ሱሪ ፡ እንኳን ፡ ሳያጠልቅ ፡ ሃሪቁን ፡ በጠላት ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የነቃው ።

በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የጠላት ፡ ንቅናቄ ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ። ሁሉም ፡ ከምሽጉ ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ ተሰልፈው ፡ ለኮዛኮች ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ትርኢት ፡ ሆነው ፡ ታዩ ። የፖሊሽ ፡ መኳንንት ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ የበለጠ ፡ ያማረ ፡ እየሆኑ ፡ በምሽጉ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ።



እንደበረዶ ፡ በነጣ ፡ ላባ ፡ ያጌጡት ፡ የነሃስ ፡ ጥሩሮቻቸው ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ጸሐዮች ፡ ያበሩ ፡ ጀመር ። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ከጫፋቸው ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ የታጠፉ ፡ ቀለማቸው ፡ ቀላ ፡ ያሉ ፡ ወይም ፡ ሰመያዊ ፡ ቀላል ፡ ቆቦች ፡ አድርገው ፡ በወርቀዘቦ ፡ ወይም ፡ በጥልፍ ፡ ያጌጠ ፡ ኮት ፡ ለብሰዋል ። ብዙዎቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ በወጣበት ፡ ጌጥ ፡ ያጌጡ ፡ ጐራዴዎችና ፡ ጠበንጃዎች ፡ ይዘዋል ። ሌላም ፡ ብዙ ፡ ጌጣጌጥና ፡ የወግ ፡ እቃ ፡ በትጥቃቸው ፡ ይታያል ። የቡድዣክ ፡ ኮሎኔል ፡ ባለ ወርቀዘቦ ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ አድርጎ ፡ ከሁሉም ፡ ግንባር ፡ ተጀንኖ ፡ ቆሟል ። ኮሎኔሉ ፡ ግዙፍ ፡ ሰው ፡ ነበር ። በአካባቢው ፡ ካሉት ፡ ሁሉ ፡ በቁመትም ፡ ሆነ ፡ በውፍረት ፡ የበለጠ ፡ ሲሆን ፡ ለክብሩ ፡ የሚገባውና ፡ ውድ ፡ የሆነው ፡ ኮቱ ፡ በጭንቅ ፡ የያዘው ፡ ይመስላል ። በሌሎቹ ፡ በሮች ፡ አንፃር ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ኮሎኔል ፡ ቆሟል ። ይህኛው ፡ ኮሎኔል ፡ በሰውነቱ ፡ ትንሽና ፡ ድርቅ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ጓሳ ፡ ከሚመስሉት ፡ ቅንድቦቹ ፡ ሥር ፡ ያሉት ፡ ጥቃቅን ፡ ዓይኖቹ ፡ በንቃት ፡ ይቁለጨለጫሉ ። ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ በቅልጥፍና ፡ እየዞረ ፡ በደረቅ ፡ እጁ ፡ በማመልከት ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በአካል ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆንም ፡ በጦር ፡ ስልት ፡ ተሰጥኦ ፡ እንዳለው ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ከእሱ ፡ ብዙም ፡ ሳይርቅ ፤ አንድ ፡ ረጅምና ፡ ለግላጋ ፡ ኮርኔት ፡ ቆሟል ። ኮርኔቱ ፡ ችፍግ ፡ ያለ ፡ ጺም ፡ ሲኖረው ፡ ጠንካራ ፡ መጠጥና ፡ ፈንጠዝያ ፡ ለመውደዱ ፡ ምልክት ፡ የሆነ ፡ ደም ፡ የመሰለ ፡ ቅላት ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይታያል ። ከሱም ፡ ጀርባ ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፡ ይታያሉ ። እነዚህ ፡ መኳንንት ፡ በገንዘባቸው ፡ ወይም ፡ ከንጉሡ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ባገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከዘር ፡ ዘር ፡ በወረደላቸው ፡ በአባቶቻቸው ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ እቃ ፡ ለአይሁዶች ፡ በመሸጥ ፡ ባገኙት ፡ ገንዘብ ፡ የታጠቁ ፡ ነበሩ ። በዚያ ፡ የነበሩት ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ከየስፍራው ፡ የተጠራቀሙ ፡ ናቸው ። አንዳንዶቹ ፡ ለመጠጥ ፡ መግዣ ፡ እንኳን ፡ የሚሆን ፡ ገን

ዞብ ፤ የላቸውም ። ሆኖም ፡ ሁሉም ፡ ለጦርነት ፡ ለብሰውና ፡ ታጥቀው ፡ ተዘጋጅተዋል ።

የኮዛኮች ፡ ጦር ፡ ከምሽጉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በጸጥታ ፡ ቆሞአል ። በልብሳቸው ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ የወርቅ ፡ ምልክት ፡ አይታይም ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ በአንዳንዶቹ ፡ ጐራዴዎች ፡ እጀታና ፡ በጠመንጃቸው ፡ ላይ ፡ የጌጥ ፡ ሥራ ፡ ሲያብለጨልጭ ፡ ይታያል ። ኮዛኮች ፡ በጌጥ ፡ ያሸበረቀ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ አይወዱም ። የጨርቅ ፡ ልብሶቻቸውም ፡ ሆኑ ፡ የብረት ፡ ልብሶቻቸው ፡ ጌጥ ፡ የሌላቸው ፡ ልሙጥ ፡ ናቸው ። ጫፍ ፡ ጫፋቸው ፡ ቀይ ፡ የሆኑት ፡ የበግ ፡ ቆዳ ፡ ቆቦቻቸው ፡ ሜዳውን ፡ አልብሰውት ፡ ይታያሉ ።

ከዛፖሮዥያኖቹ ፡ ሰልፍ ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ኮዛኮች ፡ በፈረስ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ለየት ፡ ብለው ፡ ወጡ ። እኒህ ፡ ኮዛኮች ፡ አንዱ ፡ ወጣት ፡ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡ ጠና ፡ ያለ ፡ ሲሆኑ ፡ ሁለቱም ፡ በአነጋገር ፡ ቅልጥፍናቸው ፡ የታወቁ ፡ በጦር ፡ ሞያም ፡ የማይነቀፉ ፡ አህሪም ፡ ናሽና ፡ ሚኪታ ፡ ጐሎኮፕቴንኮ ፡ የሚባሉ ፡ ነበሩ ። ከነዚህ ፡ ከሁለቱም ፡ ኋላ ፡ ዴሚድ ፡ ፖፖቪች ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ተከትሏቸዋል ። ፖፖቪች ፡ በሴቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የኖረ ፡ ሲሆን ፡ በአድሪአኖፖል ፡ የተዋጋና ፡ በሕይወቱ ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ፈተና ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ነበር ። ተማርኮ ፡ በእሳት ፡ ሊቃጠል ፡ ሲል ፡ ጸጉሩና ፡ ጢሙ ፡ ከተንጫረረ ፡ በኋላ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ሴቹ ፡ መጥቶ ፡ አሁን ፡ ጸጉሩም ፡ ጢሙም ፡ አድጐለታል ። እሱም ፡ እንደቀሩት ፡ እንደሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ በአንደበቱ ፡ ተመርጦ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ተከትሏቸው ፡ የሄደው ። ወዲያው ፡ እነዚህ ፡ የተመረጡት ፡ ኮዛኮች ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለማበሳጨት ፡ ዘለፋቸውን ፡ ጀመሩ ።

«አሃ! የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ቀይ ፡ ኮት ፡ ልብሶአል ፡ ግን ፡ ውስጣቸው ፡ ቢታይ ፡ ሃሞታቸው ፡ ነጭ ፡ ነው!»

ከምሽጉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ወፍራሙ ፡ ኮሎኔልም ፤ «ቆይ ፡ አሳያችኋለሁ! ሁላችሁንም ፡ በሰንሰለት ፡ ነው ፡ እማስራችሁ ፡



ጠመንጃዎቻችሁንና ፡ ፈረሶቻችሁን ፡ አስረክቡ ፡ እናንት ፡ ገባሮች! ጓደኞቻችሁን ፡ እንዴት ፡ እንደአሰርኋቸው ፡ አላያችሁም?» አለና ፡ ወደ ፡ ተከታዮቹ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ «እስቲ ፡ እንዲያዩአቸው ፡ ኮዛኮቹን ፡ እዚህ ፡ አቅርቧቸው!» አለ ።

ኮዛኮቹ ፡ በገመድ ፡ እንደታሰሩ ፡ መጥተው ፡ ምሽጉ ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ። የመንደር ፡ አለቃቸው ፡ ህሊብ ፡ ሱሪ ፡ እንኳን ፡ ሳይኖረው ፡ ራቁቱን ፡ ከፊታቸው ፡ ቆሞአል ። ከእንቅልፉ ፡ ሳይነቃ ፡ እንደውሻ ፡ ተይዞ ፡ በመታሰሩና ፡ እንዲሁም ፡ ራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ በወገኖቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በመታየቱ ፡ አፍሮ ፡ አንገቱን ፡ አቀረቀረ ። ጸጉሩ ፡ ሌሊቱን ፡ ሽብቶ ፡ አድሮአል ።

«አይዞህ ፡ ህሊብ! እናድንሃለን!» አሉና ፡ ከታች ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ ጮኹ ።

ቦሮዳትይ ፡ የተባለው ፡ የመንደር ፡ አለቃ ፡ «አይዞህ ፡ ጓዴ! ራቁትህን ፡ መማረክህ ፡ የአንተ ፡ ጥፋት ፡ አይደለም ። በማንም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ የአጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ አንድ ፡ ልብስ ፡ እንኳን ፡ ሳያለብሱህ ፡ ለማፌዣ ፡ ስለአመጡህ ፡ ሊያፍሩ ፡ የሚገባቸው ፡ እነሱ ፡ ነበሩ ፡» በማለት ፡ ጓደኛውን ፡ አጽናናው ።

ጐሎኮፕቴንኮ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተ ፡ «እንቅልፍ ፡ ከወሰዳቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ጐበዝ ፡ ወታደሮች ፡ ናችሁ!» አለ ።

ከላይ ፡ ያሉትም ፡ «ቆዩ ፡ ቁንጮአችሁን ፡ ነው ፡ የምንቆርጥላችሁ ፡» እያሉ ፡ ጮኹ ።

«እስቲ ፡ ሲያደርጉት ፡ እናያለን!» አለ ፡ ፖፖቪች ፡ ወዲያው ፡ በኮርቻው ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ግን ፡ እኮ ፡ አይሆንም ፡ አይባልም ፤ ምናልባት ፡ ፖሊሾቹ ፡ የሚሉት ፡ እውነት ፡ ይሆናል ። እዚያ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ቅርጫት ፡ ሆድ ፡ መሪነት ፡ በእውነትም ፡ ደህና ፡ ሊከላከሉ ፡ ይችላሉ ።»

ኮዛኮቹም ፡ ፖፖቪች ፡ አንድ ፡ ቀልድ ፡ እንዳዘጋጀ ፡ ተገንዝበው ፤ «እንዴት ፡ ነው ፡ ደህና ፡ ሊከላከሉ ፡ የሚችሉት?» ብለው ፡ ጠየቁት ።

ፖፖቪችም ፡ «ምክንያቱም ፡ ቀፈታሙ ፡ ኮሎኔል ፡ መሪ ፡ ከሆነ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ከኋላው ፡ ተከልሎ ፡ እኛ ፡ የምንወረውረው ፡ ጦር ፡ ከሱ ፡ ቦርጭ ፡ አልፎ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ሊያገኝ ፡ ስለማይችል ፡ ነው ፡» ሲል ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ሳቁ ። ብዙዎቹም ፡ የፖፖቪችን ፡ አንደበት ፡ በማድነቅ ፡ ንግግር ፡ ጀምረው ፡ ነበር ። ግን ፡ የጀመሩትን ፡ ንግግር ፡ ለመጨረስ ፡ እንኳን ፡ ጊዜ ፡ አላገኙም ።

ፖሊሾቹ ፡ ይህንን ፡ ዘለፋ ፡ ለመታገስ ፡ ስላልቻሉ ፡ ኮሎኔሉ ፡ ለውጊያ ፡ ምልክት ፡ ሲሰጥ ፡ የኮዛኮቹ ፡ ኮሼቮይ ፡ ስለአየ ፤ «ዘወር ፡ በሉ ፡ ከምሽጉ ፡ ሥር ፡ ዘወር ፡ በሉ!» ብሎ ፡ ጮኸ ።

ኮዛኮቹ ፡ ከምሽጉ ፡ ሥር ፡ መለስ ፡ ከማለታቸው ፡ ፖሊሾቹ ፡ ከላይ ፡ ሆነው ፡ ተኩስ ፡ ያዘንቡባቸው ፡ ጀመር ። በምሽጉ ፡ ላይ ፡ ጥድፊያ ፡ ሆነ ፤ ሽበቶው ፡ ወየወዳ ፡ ራሳቸው ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ብቅ ፡ አሉ ። የግንቡ ፡ በሮች ፡ ተከፍተው ፤ ብዙ ፡ ጌጥ ፡ ያጌጡ ፡ ልብሶች ፡ የለበሰ ፡ ወታደሮች ፡ እየጎረፉ ፡ ወጡ ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ ወታደሮች ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በያዘ ፡ የጦር ፡ ሰልፍ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሲወጡ ፡ በመጨረሻም ፡ እንደየግል ፡ ፍላጐታቸው ፡ የለበሱና ፡ የታጠቁት ፡ ከፍተኛ ፡ መኳንንት ፡ መጡ ። መኳንንቱ ፡ ከተራው ፡ ወታደራቸው ፡ ጋር ፡ መደባለቅን ፡ አይፈቅዱም ፡ ነበር ። የሚያዙት ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ የሌላቸው ፡ መኳንንትም ፡ ከገባሮቻቸውና ፡ ከቤት ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ተሰለፉ ። ከመኳንንቱ ፡ ጀርባ ፡ እንደገና ፡ ሌላ ፡ የወታደሮች ፡ ሰልፍ ፡ ተከትሎአል ። ከዚያ ፡ ኮርኔቱ ፡ ቀጠለ ። ከሱም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ የወታደሮች ፡ ሰልፍ ፤ ከዚያም ፡ ወፍራሙ ፡ ኮሎኔል ፡ ሲያልፍ ፡ ትንሹ ፡ ኮሎኔል ፡ የደጀኑን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ከኋላ ፡ ተከትሎአል ።



የኮዛኮቹ ፡ ኮሼቮይ ፡ እየጮኸ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥ ፡ ጀመር ። «እንዳይደራጁ ፡ ጊዜ ፡ አትስጡአቸው! የሁሉም ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ አንድነት ፡ ሆናችሁ ፡ ተዋጉ! ሌሎቹን ፡ በሮች ፡ ተውአቸው! የትታሬቭ ፡ መንደር ፡ ቀኝ ፡ አዝማቹን ፡ ውጋ! የዲያድኪቭ ፡ መንደር ፡ ግራ ፡ አዝማቹን ፡ ውጋ! ኩኩቤንኮና ፡ ፓሊቮዳ ፡ ከኋላቸው ፡ ጥመዱ ! ሰልፋቸውን ፡ አበላሹ! በታትኗቸው!»

ኮዛኮቹ ፡ ከሁሉም ፡ ወገን ፡ በመውጋት ፡ የፖሊሾቹን ፡ ሰልፍ ፡ በታትነው ፡ ከመሃላቸው ፡ ተቀላቀሉ ። ለጠላታቸው ፡ የጥይት ፡ መተኮሻ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ አልሰጡትም ፤ ጦርና ፡ ጐራዴ ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ። ከጠላት ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ ስለነበር ፡ እያንዳንዱ ፡ ኮዛክ ፡ ሞያውን ፡ ለማሳየት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ሆነለት ። ዴሚድ ፡ ፖፖቪች ፡ ሶስት ፡ ተራ ፡ ወታደሮች ፡ ገድሎ ፡ እንዲሁም ፡ ሁለት ፡ ከፍተኛ ፡ መኳንንት ፡ ከፈረሳቸው ፡ ሲጥል ፤ «ጥሩ ፡ ፈረሶች! ሁልጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ፈረሶች ፡ ስመኝ ፡ ነበር!» አለና ፡ ፈረሶቹን ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡ ነድቶ ፡ እዚያ ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ እንዲጠብቁለት ፡ ተናገረ ። ይህን ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ከፈረሳቸው ፡ የጣላቸው ፡ መኳንንት ፡ ዘንድ ፡ ሔዶ ፡ አንዱን ፡ ወዲያው ፡ ገደለው ። አንደኛውን ፡ ደግሞ ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ ጐራዴውንና ፡ ከኪሱ ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ወርቅ ፡ ከገፈፈው ፡ በኋላ ፤ አንገቱን ፡ በገመድ ፡ ጠልፎ ፡ የገመዱን ፡ ጫፍ ፡ ከኮርቻው ፡ ጋር ፡ አሰረና ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ እየጐተተ ፡ ወሰደው ።

ኮቢታ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ጥሩ ፡ ወጣት ፡ ኮዛክ ፡ ከአንድ ፡ የፖሊሽ ፡ ጐበዝ ፡ ጦረኛ ፡ ጋር ፡ ተጋጥመው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ፡ ቆዩ ። ወዲያው ፡ ኮዛኩ ፡ በፖሊሹ ፡ ላይ ፡ አየለበትና ፡ ጥሎ ፡ በሰላ ፡ የቱርክ ፡ ጮቤው ፡ ደረቱን ፡ ወጋው ። ግን ፡ ኮዛኩም ፡ አልቀረለትም ፡ ወዲያው ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ጆሮ ፡ ግንዱን ፡ ብሎ ፡ ጣለው ። ተኳሹም ፡ ከሁሉም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጨዋና ፡ ከሁሉም ፡ ያማረ ፡ መኮንን ፡ ነበር ። በታላቅ ፡ ግር

ማ ፡ በሃመር ፡ ፈረሱ ፡ ሆኖ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተወረ
ወረ ፡ ብዙ ፡ ልዑላዊ ፡ ሞያ ፡ ፈጸመ ። ሁለቱን ፡ ኮዛኮች ፡ በጐ
ራዴ ፡ ሰነጠቃቸው ። ፌዮዶር ፡ ኮርዥ ፡ የተባለውን ፡ ጥሩ ፡
ኮዛክ ፡ መጀመሪያ ፡ ፈረሱን ፡ በጥይት ፡ ጥሎ ፡ በኋላ ፡ እሱን ፡
በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የብዙዎችን ፡ አን
ገትና ፡ ክንድ ፡ የቆራረጠው ፡ ይህ ፡ መኮንን ፡ አሁን ፡ ኮዛ
ኩን ፡ ኮቢታን ፡ ጀሮ ፡ ግንዱን ፡ በጥይት ፡ መትቶ ፡ ገደለው ።

የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
አይቶ ፡ ስለነበር ፡ «ከዚህ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ጉልበቴን ፡
መፈተን ፡ ያለብኝ!» ብሎ ፡ ጮኸ ። ወዲያው ፡ ፈረሱን ፡ ኮ
ለኮለና ፡ ከኋላው ፡ ጋልቦ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ ሲ
ጮኽ ፡ በአቅራቢያው ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አንቀጠ
ቀጣቸው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የፖሊሹ ፡ መኮንን ፡ ዞሮ ፡ ጠላ
ቱን ፡ ለመግጠም ፡ ሲል ፡ ፈረሱ ፡ በጩኸቱ ፡ ደንብሮ ፡ ስለ
አስቸገረው ፡ ገና ፡ ከመዞሩ ፡ የኩኩቤንኮ ፡ ጥይት ፡ ትከሻውን ፡
መታና ፡ ከፈረሱ ፡ አውርዶ ፡ ጣለው ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡
ልቡ ፡ ሳይሸነፍ ፡ ጠላቱን ፡ ለመምታት ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ። ግን ፡
ክንዱ ፡ ዝሎ ፡ ጐራዴውን ፡ ማንሳት ፡ እንኳን ፡ አልቻለም ።
በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ሰይፉን ፡ አወጣና ፡ በተከፈተው ፡
በጠላቱ ፡ አፍ ፡ ጨመረው ። ሰይፉም ፡ የዚያን ፡ መኮንን ፡ እ
ንደ ፡ ስኳር ፡ የነጡ ፡ ሁለት ፡ ጥርሶች ፡ ሰብሮ ፤ ምላሱን ፡ ለሁ
ለት ፡ ሰንጥቆ ፤ አንገቱን ፡ አነካከተና ፡ አልፎ ፡ መሬት ፡ ውስ
ጥ ፡ ተሰካ ። መኮንኑን ፡ ከቀዝቃዛው ፡ መሬት ፡ ጋር ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ሰፋው ። በወንዝ ፡ ዳር ፡ እንደበቀለ ፡ ጽጌረዳ ፡ የቀ
ላው ፡ ልዑላዊ ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ምንጭ ፡ እየገነፈለ ፡ በወር
ቀዘቦ ፡ የተዘመዘመውን ፡ ቢጫ ፡ ኮቱን ፡ በከለው ። ኩኩቤ
ንኮ ፡ የገደለውን ፡ መኮንን ፡ ትቶ ፡ ወደሌላ ፡ ዞረና ፡ ከው
ጊያው ፡ ተደባለቀ ።

የኡማን ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ቦሮዳትይ ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡
ስለነበር ፤ «ይህን ፡ ያህል ፡ ሃብት ፡ የተሸከመ ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡



ለምን ፡ ሳይማርከው ፡ ሄደ! እኔ ፡ ራሴ ፡ ሰባት ፡ መኳንንት ፡
በእጄ ፡ ገድያለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንዳቸውም ፡ ላይ ፡ እንዲ
ህ ፡ ያለ ፡ የከበረ ፡ ትጥቅ ፡ አላየሁም ፡» አለና ፡ ወደ ፡ ኩኩ
ቤንኮ ፡ ግዳይ ፡ ሄደ ።

ቦሮዳትይ ፡ በስስት ፡ ተታለለና ፡ የከበረውን ፡ የጦር ፡ ትጥ
ቅ ፡ ለመፍታት ፡ ጐንበስ ፡ አለ ። ወዲያው ፡ አንድ ፡ በአል
ማዝ ፡ ያጌጠ ፡ የቱርክ ፡ ጩቤ ፡ ከሬሳው ፡ ላይ ፡ አንስቶ ፤
እንዲሁም ፡ ወርቅ ፡ የያዘ ፡ ከረጢት ፡ ከቀበቶው ፡ ፈታ ፤
ከዚያም ፡ ያማረ ፡ መሃረብ ፤ ብዙ ፡ ብር ፤ እንዲሁም ፡ ለፍ
ቅር ፡ መታሰቢያ ፡ የተሰጠ ፡ የሴት ፡ ጸጉር ፡ ቁራጭ ፡ የያዘ ፡
ቦርሳ ፡ ሲያወልቅ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከፈረሱ ፡ አውርዶ ፡ በጐ
ራዴ ፡ መትቶ ፡ የተወውን ፡ አፍንጫ ፡ ቀይ ፡ ኮርኔት ፡ ከኋ
ላው ፡ ሲመጣበት ፡ አላየውም ። ኮርኔቱ ፡ ጐራዴውን ፡ ባለ ፡
ኃይሉ ፡ አንስቶ ፡ በአጐነበሰው ፡ በቦሮዳትይ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡
አሳረፈው ። የኮዛኩ ፡ ስስት ፡ ምንም ፡ አልጠቀመውም ፤ አን
ገቱ ፡ ተቀንጥሶ ፡ ተወረወረ ፤ ቀሪ ፡ አካሉም ፡ ያለ ፡ ጭን
ቅላት ፡ ሲወድቅ ፡ ያካባቢውን ፡ ምድር ፡ በደም ፡ አቀላው ።
የኮዛክ ፡ ነፍሱም ፡ በራ ፡ ሔደች ። ኮርኔቱ ፡ የኮዛኩን ፡ አን
ገት ፡ በቁንጮው ፡ አንጠልጥሎ ፡ ኮርቻው ፡ ላይ ፡ ሊያስረ
ው ፡ ሲል ፡ ክፉ ፡ ደም ፡ መላሽ ፡ ከተፍ ፡ አለበት ።

ንስር ፡ አሞራ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ አንዣብቦ ፡ በሚያድ
ነው ፡ አውሬ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ ትክል ፡ እንደሚልበት ፡ ሁሉ ፡
የታራስ ፡ ቡልባ ፡ ልጅ ፡ የአስታፕ ፡ ገመድ ፡ ሸምቀቆ ፡ በኮ
ርኔቱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አንዣበበና ፡ በአንገቱ ፡ ጥልቅ ፡ አለ ። ሸ
ምቀቆው ፡ በጉሮሮው ፡ ላይ ፡ እየጠበቀ ፡ ሲሔድ ፡ የኮርኔቱ ፡
ፊት ፡ ጠወለገ ፤ ሽጉጡን ፡ አውጥቶ ፡ ለመተኮስ ፡ ቢሞክር ፡
እጁ ፡ ሊያነጣጥርለት ፡ ስላልቻለ ፡ ጥይቱ ፡ ባክኖ ፡ ቀረ ።
ከዚያ ፡ ኮርኔቱ ፡ ለምርኮኛ ፡ ማሠሪያ ፡ በኮርቻው ፡ ላይ ፡
ይዞት ፡ የነበረውን ፡ ገመድ ፡ አስታፕ ፡ ፈታና ፡ ኮርኔቱን ፡
እጅና ፡ እግሩን ፡ አስሮ ፡ የገመዱንም ፡ ጫፍ ፡ ከራሱ ፡ ኮርቻ ፡

ጋር ፡ አሰረና ፡ የኡማን ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ ሁሉ ፡ ለአለ
ቃቸው ፡ የመጨረሻ ፡ ክብር ፡ የሚደረገውን ፡ በቀል ፡ እንዲ
መለከቱ ፡ እየተጣራ ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ ይጐትተው ፡ ጀመር ።

የኡማን ፡ ኮዛኮች ፡ አለቃቸው ፡ መሞቱን ፡ እንደሰሙ ፡
ውጊያውን ፡ ትተው ፡ ሬሳውን ፡ ለማግኘት ፡ ሮጡና ፡ ወዲ
ያው ፡ ሳይዘገዩም ፡ ለአለቅነት ፡ ማንን ፡ እንደሚመርጡ ፡ ይመ
ካከሩ ፡ ጀመር ። በመጨረሻ ፡ ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ተስ
ማሙ ። «ለምን ፡ በከንቱ ፡ እንከራከራለን? ከወጣቱ ፡ ከኦስ
ታፕ ፡ ቡልባ ፡ የተሻለ ፡ አለቃ ፡ አናገኝም ፤ እርግጥ ፡ ነው ፡
በእድሜ ፡ ከሁላችን ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሽማግሌ ፡
አእምሮ ፡ ነው ፡ የያዘው ፡» ተባባሉና ፡ ኦስታፕን ፡ ለመም
ረጥ ፡ ወሰኑ ።

ኦስታፕም ፡ በልጅነቱ ፡ ምክንያት ፡ ሥልጣኑን ፡ አል
ቀበልም ፡ ሳይል ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ መግ
ደርደር ፡ አስፈላጊ ፡ አለመሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ባርኔጣውን ፡
አውልቆ ፡ ስለተሰጠው ፡ ክብር ፡ ኮዛክ ፡ ጓደኞቹን ፡ አመስግኖ ፡
ወዲያው ፡ ወደ ፡ ውጊያው ፡ መራቸውና ፡ አለቅነት ፡ የመረ
ጡት ፡ በከንቱ ፡ አለመሆኑን ፡ በሞያ ፡ ገለጸላቸው ።

ፖሊሾቹ ፡ ውጊያው ፡ ከወዲያ ፡ ወገን ፡ ሲያይልባቸው ፡
ጊዜ ፡ እንደገና ፡ ተደራጅተው ፡ ለመዋጋት ፡ ወደኋላ ፡ በሩ
ጫ ፡ ሸሹ ። ትንሹ ፡ ኮሎኔል ፡ በተጠባባቂነት ፡ ለብቻ ፡ የቆ
የውን ፡ የደጀን ፡ ጦር ፡ ለውጊያ ፡ ሲያዝዝ ፡ ጦሩም ፡ ወዲያው ፡
ተኩስ ፡ ከፈተና ፡ በኮዛኮቹ ፡ ላይ ፡ ጥይት ፡ አወረደባቸው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ጥይቱ ፡ ዓይናቸው ፡ ፈጥጦ ፡ ውጊያውን ፡ የሚ
ያስተውሉትን ፡ የኮዛክ ፡ በሬዎች ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ሰው ፡
አልነካም ። በሬዎቹ ፡ በፍርሃት ፡ እየጮኹ ፡ ወደ ፡ ኮዛኮች ፡ ሰ
ፈር ፡ ዞረው ፡ ሠረገላዎችን ፡ እየሰባበሩና ፡ ብዙም ፡ ሰው ፡ በእ
ግራቸው ፡ እየረጋገጡ ፡ ፈረጠጡ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፡
ክፍለ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ካደፈጠበት ፡ ቦታ ፡ ወጣና ፡ የበሬዎ
ቹን ፡ መንገድ ፡ ዘጋባቸው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የደነበሩት ፡ በሬ



ዎች ፡ የታራስ ፡ ሰዎች ፡ ስላስደነገጧቸው ፡ ወደ ፡ ፖሊሾች ፡
ጦር ፡ ዞረው ፡ ፈረሰኞችን ፡ እየጣሉ ፡ እየረጋገጡ ፡ በታተኗ
ቸው ።

ዛፖሮዥያኖቹም ፡ «ጐሽ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ በሬዎቻ
ችን! በዘመቻ ፡ ላይ ፡ አገለገላችሁን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በጦር ፡
ሜዳ ፡ ረዳችሁ!» ብለው ፡ ጮኸው ፡ ጠላታቸውን ፡ በኃይል ፡
ይጣደፉ ፡ ጀመር ።

ከጠላት ፡ ጦር ፡ ብዙዎቹ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ሞቱ ። ብዙ ፡
ኮዛኮችም ፡ ሞያቸውን ፡ አሳዩ ። ፖሊሾቹ ፡ እንዳልሆነላቸው ፡
ስለተገነዘቡ ፡ የከተማው ፡ በር ፡ እንዲከፈት ፡ አስደረጉና ፡
አጧራ ፡ የለበሱት ፡ የደከሙ ፡ ፈረሰኞች ፡ እንደበግ ፡ ተግ
ተልትለው ፡ ገቡ ። አንዳንድ ፡ ኮዛኮች ፡ በማባረር ፡ ተከትሏ
ቸው ፡ ነበር ። ኦስታፕ ፡ ግን ፡ «ከግንቡ ፡ ራቁ! ጥሩ ፡ አይ
ደለም ፡ አትቅረቡ ፤ ወንድሞቼ !» ብሎ ፡ በመጮኽ ፡ የኡ
ማንን ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ አስቀራቸው ። እውነትም ፡ ደህና ፡
ኃይቶት ፡ ኖሮአል ። በግንቡ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የጠላት ፡ ወታደ
ሮች ፡ ተኩስ ፡ ስለከፈቱባቸው ፡ ግንቡን ፡ የቀረቡት ፡ ኮዛ
ኮች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው ። ወዲያው ፡ ኮሼቮዩ ፡ ጋልቦ ፡
መጣና ፤ «እንዲህ ፡ ነው ፡ አለቃ ፡ ማለት ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ ከመ
ሾሙ ፡ መንደሩን ፡ ልክ ፡ እንደነባር ፡ ሆኖ ፡ ይመራል!» በማ
ለት ፡ ኦስታፕን ፡ አመሰገነው ። ሽማግሌው ፡ ቡልባ ፡ ይህ ፡
የተባለው ፡ አለቃ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡
ኦስታፕ ፡ በኡማን ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡
ተቀምጦ ፡ ተመለከተ ። «ይኸውላችሁ ፡ ወንድ ፡ ማለት!»
አለና ፡ ታራስ ፡ በአድናቆት ፡ ልጁን ፡ ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡
እጅግ ፡ ተደስቶ ፡ ልጁን ፡ ስለመረጡለት ፡ የኡማንን ፡ ኮዛኮ
ች ፡ አመሰገናቸው ።

ኮዛኮቹ ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ለመመለስ ፡ ሲያስቡ ፡ ፖ
ሊሾቹ ፡ በከተማው ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ብቅ ፡ አሉ ።
ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የቀድሞው ፡ ጌጥ ፡ ሁሉ ፡ ተበላሽቷል ።

ብዙ ፡ ያጌጡ ፡ ልብሶች ፡ በደም ፡ ተበክለዋል ፤ የሚያምሩትን ፡
የነሃስ ፡ ጥሩሮችም ፡ አቧራ ፡ ሸፍኖአቸዋል ።

ከግንቡ ፡ ሥር ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፤ «ታድያስ ፡ እንደ
ፎከራችሁት ፡ አሰራችሁን ፡ እንዴ?» እያሉ ፡ ጮኹ ። ወፍ
ራሙ ፡ ኮሎኔልም ፡ በእጁ ፡ የያዘውን ፡ ገመድ ፡ እያወዛወዘ ፡
የቀድሞ ፡ ዛቻውን ፡ በመድገም ፡ «ቆይ ፡ አሳያችኋለሁ!» ብሎ ፡
በቁጣ ፡ ጮኸ ። በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ አቧራ ፡ የለበ
ሱና ፡ የደከሙ ፡ ጠረኞች ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ መዛታ
ቸውን ፡ ቀጠሉ ። አንዳንድ ፡ ንዴተኞችም ፡ ስድብ ፡ ይለዋ
ወጡ ፡ ነበር ።

በመጨረሻ ፡ ሁሉም ፡ ረጋ ፡ አሉ ። አንዳንዶቹ ፡ በው
ጊያ ፡ ደክመው ፡ ለማረፍ ፡ ጋደም ፡ ሲሉ ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡
ቁስላቸው ፡ ላይ ፡ አፈር ፡ እየነሰነሱ ፡ ከጠላት ፡ ሬሳ ፡ በሚቀ
ዱት ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ጨርቅ ፡ ይጠቀልሉ ፡ ጀመር ።
አንዳንድ ፡ በፍጹም ፡ ያልደከሙ ፡ ግን ፡ የሞቱትን ፡ ቀብር ፡
ያዘጋጁ ፡ ጀመር ። ጉድጓዱ ፡ በጐራዴና ፡ በአንካሴ ፡ እየተ
ቆፈረ ፡ አፈሩንም ፡ በቆባቸውና ፡ በኮታቸው ፡ እያወጡ ፡ የወ
ደቁት ፡ ኮዛኮች ፡ ሬሳ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተጋድሞ ፡ ጨካ
ኞች ፡ አሞሮች ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ እንዳያነቁሩት ፡ አፈር ፡
ለበሰ ። የፖሊሾች ፡ ሬሳ ፡ ግን ፡ ተሰብስቦ ፡ በደንባሪ ፡ ፈረሶ
ች ፡ ጭራ ፡ ላይ ፡ ከታሰረ ፡ በኋላ ፡ ፈረሶቹን ፡ አስደንብረው ፡
በሜዳው ፡ ለቀቋቸው ። ፈረሶቹም ፡ በአቧራ ፡ የተለወሱትን ፡
የፖሊሾቹን ፡ ሬሳዎች ፡ እየጐተቱ ፡ በዳገት ፤ በቁልቁለት ፤
በጉድጓድና ፡ በወንዞችም ፡ አልፈው ፡ እየጋለቡ ፡ ጠፉ ።

ከዚያ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ወደ ፡ እራት ፡ ተሰማሩ ። ሌሊቱንም ፡
በውጊያው ፡ ላይ ፡ ስለደረሰባቸው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሲ
ወያዩ ፡ ቆዩ ። የያንዳንዳቸው ፡ የጦር ፡ ሞያ ፡ ሲነሳና ፡ ሲወራ ፡
ብዙ ፡ አመሹ ። ታራስም ፡ አንድሬይ ፡ ከጠላት ፡ ጦር ፡ ጋር ፡
ስላለመኖሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያሰላስል ፡ አመሸ ። ያ ፡ ይሁዳ ፡ በገ
ዛ ፡ ወገኖቹ ፡ ላይ ፡ ለመሰለፍ ፡ አፍሮ ፡ ቀርቶ ፡ ይሆን ፡ ወይስ ፡



አንድሬይ ፡ እንዲሁ ፡ ተማርኮ ፡ ተወስዶ ፡ አይሁዱ ፡ ያን
ኪል ፡ ዋሽቶ ፡ ይሆን? ግን ፡ ወዲያው ፡ የአንድሬይ ፡ ልብ ፡ በአ
ንድ ፡ ሴት ፡ ቃል ፡ ቶሎ ፡ እንደሚወላውል ፡ አስታውሶ ፡ ታ
ራስ ፡ በኃዘን ፡ ተዋጠ ። ወጥመድ ፡ ባገባችው ፡ ፖሊሽ ፡ ሴት ፡
ላይም ፡ በቀሉን ፡ ለመወጣት ፡ ማለ ። ቢሆንለት ፡ ይህን ፡
መሃላውን ፡ ከመፈጸም ፡ የሚመለስ ፡ አይደለም ። ቢያገኛት ፡
ውበትዋንም ፡ ባልተመለከተ ፡ ነበር ። የተዋበውን ፡ ጸጉር
ዋን ፡ አስሮ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲያዩዋት ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡
እንደሚጐትታት ፡ አይጠረጠርም ። በተራራ ፡ ላይ ፡ እንዳ
ለ ፡ ንጹህ ፡ በረዶ ፡ የነጡት ፡ ጡቶችዋና ፡ ትከሻዋ ፡ በሜዳ
ው ፡ ላይ ፡ ሲንገላቱ ፡ በደምና ፡ በአቧራ ፡ በተለወሱ ፡ ነበር ።
ያን ፡ የተዋበ ፡ ለጋ ፡ አካልዋን ፡ ቆራርጦ ፡ በጣለው ፡ ነበር ።
ግን ፡ ቡልባ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለነገ ፡ ምን ፡ እንዳሰበ ፡ ሊያ
ውቅ ፡ አይችልም ። በመጨረሻ ፡ እናወዘውና ፡ እንቅልፍ ፡
ወሰደው ።

ኮዛኮቹ ፡ አሁንም ፡ ያወጋሉ ። ንቁዎቹ ፡ ዘበኞችም ፡ ሌሊ
ቱን ፡ ሙሉ ፡ ለዘብ ፡ ጥበቃ ፡ በነደዱት ፡ ደመራዎች ፡ አጠ
ገብ ፡ ቆመው ፡ በትጋት ፡ ይጠብቃሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ስምንት ።

ገና ፡ ጀንበር ፡ ከፍ ፡ ሳትል ፡ ዛፖሮዢያኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ለም
ክር ፡ ተሰበሰቡ ። ኮዛኮቹ ፡ ሴቹን ፡ ለቀው ፡ በዘመቱበት ፡ ታታ
ሮች ፡ መጥተው ፡ ሰፈሩን ፡ ዘርፈው ፡ የተከማቸውን ፡ ሃብት ፡
ሁሉ ፡ በዝብዘው ፡ በዚያ ፡ የነበሩትን ፡ ኮዛኮች ፡ ሁሉ ፡ ገድ
ለውና ፡ ማርከው ፡ የከብትና ፡ የፈረሶችን ፡ መንጋም ፡ እየነዱ ፡
በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፔሬኮፕ ፡ ሔደዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ተሰማ ።
ማክሲም ፡ ጐሎዱኻ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ብቻ ፡ ከመን
ገድ ፡ ሚርዛውን ፡ ገድሎ ፡ ከታታሮች ፡ አምልጦ ፡ የታታር ፡
ልብስ ፡ ለብሶና ፡ በታታር ፡ ፈረስ ፡ እየጋለበ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡

ተኩልና ፡ ሁለት ፡ ሌሊት ፡ ተጉዞ ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ዱብኖ ፡
ከተማ ፡ አጠገብ ፡ መስፈራቸውን ፡ ስለሰማ ፡ ከሰፈራቸው ፡
ደረሰ ። እንደደረሰም ፡ የሆነውን ፡ ጉዳት ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡
አመጣጡ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ኮዛኮቹ ፡ እንደተለመደው ፡
አለመጠን ፡ ጠጥተው ፡ በስካር ፡ እንዳሉ ፡ ተይዘው ፡ እንደ
ሆነ ፤ ታታሮቹም ፡ የተደበቀውን ፡ የጦር ፡ ሰራዊቱን ፡ ሃብት ፡
እንዴት ፡ እንዳገኙት ፡ ለማስረዳት ፡ አልቻለም ። በድካም ፡
ጉልበቱ ፡ ዝሎ ፡ ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ አብጦ ፡ ፊቱም ፡ በነፋ
ስ ፡ ተጠብሶና ፡ ተላልጦ ፡ ስለነበር ፡ ወዲያው ፡ እንደደረሰ ፡
እንቅልፍ ፡ ወሰደው ።

እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ዘራፊዎቹን ፡ ተከታትሎ ፡ መያ
ዝ ፡ በኮዛኮቹ ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ነበር ። አለዚያ ፡ ግን ፡
እስረኞቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በእስያ ፡ ማይነር ፤ በስማርነና ፡ ወይም ፡
በክሪት ፡ ደሴት ፡ ወደሚገኙት ፡ የባርያ ፡ ገበያዎች ፡ ይላ
ካሉ ። አሁን ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ለምክር ፡ የተሰበሰቡት ፡ ለ
ዚሁ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ስብሰባ ፡ የመጡት ፡ ከአለቆቻቸው ፡
ትእዛዝ ፡ ለመቀበል ፡ ሳይሆን ፡ በእኩልነት ፡ እርስ ፡ በእር
ሳቸው ፡ ለመመካከር ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉም ፡ ቆባቸውን ፡ ሳያ
ወልቁ ፡ ቆሙ ።

«ሽማግሌዎች ፡ በመጀመርያ ፡ ምክራቸውን ፡ ይስጡ!»
እያሉ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሲጮሁ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ «ኮሼቮይ ፡
ምክርህን ፡ ስጠን!» ይሉ ፡ ጀመር ።

ኮሼቮዩም ፡ ቆቡን ፡ አውልቆ ፡ እንደ ፡ አለቃቸው ፡ ሳ
ይሆን ፡ እንደ ፡ ጓደኛቸው ፡ ሆኖ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ስለሰጡት ፡ ክብር ፡
በትህትና ፡ ካመሰገናቸው ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ምክር ፡ ለመስጠት ፡ ከኔ ፡ ይበልጥ ፡ አዋቂዎችና ፡
የበሰሉ ፡ ሰዎች ፡ በመካከላችን ፡ ይገኛሉ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የመ
ናገሩን ፡ ክብር ፡ ለኔ ፡ ከሰጣችሁኝ ፡ ምክሬ ፡ ይህ ፡ ነው ።
የታታሮችን ፡ ነገር ፡ ሁላችሁም ፡ ስለምታውቁት ፡ አሁን ፡
ምንም ፡ ጊዜ ፡ ሳናባክን ፡ ብንከተላቸው ፡ ይሻላል ። ታታ



ሮች ፡ እኛን ፡ አይጠብቁንም ፤ የዘረፉትን ፡ ሃብት ፡ ሁሉ ፡ ወዲ
ያው ፡ በታትነው ፡ ያጠፉትና ፡ ምልክት ፡ እንኳን ፡ አናገ
ኝም ። ፖሊሾቹ ፡ አሁን ፡ ኮዛኮች ፡ ማን ፡ እንደሆንን ፡ ተገ
ንዝበውታል ፤ በሃይማኖታችን ፡ ላይ ፡ የተፈጸመውን ፡ በደል ፡
በተቻለን ፡ ተበቅለነዋል ። ይህ ፡ የተራበ ፡ ከተማም ፡ ምንም ፡
የሚጠቅመን ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ የኔ ፡ ምክር ፡ ዘራፊዎ
ቹን ፡ ተከትለን ፡ እንድንሔድ ፡ ነው ።»

«እንሒድ !» እያሉ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጮሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ ታራስ ፡ ቡልባ
ን ፡ አላስደሰቱትም ። ሽበት ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያደረገባቸውን ፡
ቅፍግ ፡ ያለ ፡ ቅንድቦቹ ፡ ኮስትሮ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«የለም ፡ ምክርህን ፡ ጥሩ ፡ ምክር ፡ አይደለም ፤ እንዲ
ህ ፡ ልትል ፡ አይገባም ፤ እንደሚመስለኝ ፡ ተማርከው ፡ እዚ
ህ ፡ በፖሊሾች ፡ እጅ ፡ ያሉትን ፡ ጓደኞቻችንን ፡ ረስተሃቸ
ዋል ። ተቀዳሚውንና ፡ የተቀደሰውን ፡ የጓደኝነት ፡ ሕግ ፡
ጥሰን ፡ ኮዛክ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዋና ፡ ዋና
ዎቹ ፡ የኡክሬይን ፡ ሩሲያውያን ፡ መኳንንት ፡ ላይ ፡ እንደ
ደረሰው ፡ ሁሉ ፡ በቁማቸው ፡ ተሰቃይተውና ፡ ተቆራርጠው ፡
እንዲቀሩ ፡ የፈለግህ ፡ ትመስላለህ ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ዓይ
ነት ፡ ሰዎች ፡ እንባላለን ፡ እስቲ ፡ ልጠይቅህ? ጓደኛው ፡ በባ
ዕድ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ወድቆ ፡ እንዲቀር ፡ ትቶ ፡ የሚ
ሔድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ኮዛክ ፡ ነው? የኮዛክነት ፡ ክብራች
ሁን ፡ መጠበቅ ፡ ከተዋችሁና ፡ መሰደብን ፡ ከፈለጋችሁ ፡ እኔ
ን ፡ ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፡ እኔ ፡ ብቻዬንም ፡ ቢሆን ፡ እዚሁ ፡
እቀራለሁ!»

ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ሃሳባቸው ፡ ወለወለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኮሼቮዩ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ጀግናው ፡ ኮሎኔል ፡ ሆይ ፤ በታታሮች ፡ እጅም ፡ ጓደ
ኞቻችን ፡ መኖራቸውንና ፡ እኛ ፡ ካልደረስንላቸው ፡ ለእድ
ሜ ፡ ልክ ፡ ባርነት ፡ ለከሃዲዎች ፡ እንደሚሸጡ ፡ ይህም ፡ ከ

ማናቸውም ፡ ከፉ ፡ ሞት ፡ የባሰ ፡ እድል ፡ መሆኑን ፡ ረስተኸው ፡ ይሆን? በክርስቲያን ፡ ደማችን ፡ ያፈራነውን ፡ ሃብት ፡ ዘርፈው ፡ መውሰዳቸውን ፡ ረስተኸዋልን?»

ኮዛኮቹ ፡ የሁለቱን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ንግግር ፡ እያሰላሰሉ ፡ የሚናገሩት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ሁሉም ፡ በስማቸውና ፡ በክብራቸው ፡ እንከን ፡ እንዲደርስበት ፡ አልፈለጉም ። ከዚያ ፡ በዛፖሮዥያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ የሁሉ ፡ ታላቅ ፡ የሆነው ፡ ካሲያን ፡ ቦቭዲዩግ ፡ ምክር ፡ ለመስጠት ፡ ቀረበ ። ይህ ፡ ሰው ፡ በኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ የተከበረና ፡ ሁለት ፡ ጊዜም ፡ ኮሼቮይ ፡ ሆኖ ፡ የተመረጠ ፡ ነው ። በጦር ፡ ሜዳም ፡ እንደ ፡ ማናቸውም ፡ ጐበዝ ፡ ኮዛክ ፡ በጊዜው ፡ ብዙ ፡ ሞያ ፡ ሠርቶአል ። አሁን ፡ ግን ፡ ስለአረጀ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ተካፋይነቱን ፡ ትቶ ፡ ምክርም ፡ መስጠት ፡ ስለማይፈልግ ፡ በኮዛኮቹ ፡ መሃል ፡ ተጋድሞ ፡ ስለጦርነትና ፡ ስለጀብዱ ፡ ሲወራ ፡ ማዳመጥ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አይናገርም ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተደረጉት ፡ ዘመቻዎች ፡ ከሰፈር ፡ አልወጣም ፡ ነበር ። በአሁኑ ፡ ዘመቻ ፡ ግን ፡ ሽማግሌው ፡ ኮዛክ ፡ ወኔው ፡ አላስችል ፡ ስላለው ፡ «የሆነው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብሬአችሁ ፡ እሄዳለሁ ፡ ለኮዛክነት ፡ ክብር ፡ ገና ፡ ሳላገለግል ፡ አልቀርም!» ብሎ ፡ መጣ ።

አሁን ፡ ምክር ፡ ለመስጠት ፡ ሲነሳ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጸጥ ፡ አሉ ፤ ሲናገር ፡ ከሰሙት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፎአል ። ቦቭዲዩግ ፡ ምን ፡ እንደሚል ፡ ለመስማት ፡ ሁሉም ፡ ጓጉ ።

እሱም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ንግግሩን ፡ ጀመረ ፤

«ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፡ ሆይ ፤ ምክሬን ፡ የምሰጥበት ፡ ጊዜው ፡ እነሆ ፡ ደረሰ ። ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ የሽማግሌ ፡ ቃሌን ፡ አዳምጡኝ ። የኮሼቮዩ ፡ ንግግር ፡ በእውነትም ፡ የአዋቂ ፡ ንግግር ፡ ነው ። የጦር ፡ ሠራዊቱንና ፡ ሃብቱንም ፡ የመጠበቅ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ የኮዛኮች ፡ መሪ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የተናገረው ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ይህ ፡ ነው ፡ የመጀመሪያ ፡ ንግግሬ ፤ ሁለተኛው ፡ ንግግሬ ፡ ደግሞ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። ኮሎኔል ፡ ታራስ ፡ የተናገረው ፡ ቃልም ፡ ታላቅ ፡ እውነትን ፡ የተመረኮዘ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ረጅም ፡ እድሜ ፡ ይስጠው ። ለኡክሬይንም ፡ እንደሱ ፡ ያሉ ፡ ኮሎኔሎች ፡ አያሳጣት! የኮዛኮች ፡ ተቀዳሚ ፡ ተግባርና ፡ ክብር ፡ ለጓደኞቻቸው ፡ ታማኝ ፡ ሆነው ፡ መገኘት ፡ ነው ። በዚህ ፡ በረጅሙ ፡ እድሜዬ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ጓደኛውን ፡ ሲከዳ ፡ ሰምቼ ፡ አላውቅም ። እዚህ ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮችና ፡ ከሴቹም ፡ የተማረኩት ፡ ሁሉም ፡ ጓደኞቻችን ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ የቁጥራቸው ፡ ማነስ ፡ ወይም ፡ መብዛት ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም ። ሁሉም ፡ ጓደኞቻችንና ፡ ሁሉም ፡ የምንወዳቸው ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ምክሬ ፡ ይህ ፡ ነው ። በታታሮች ፡ እጅ ፡ ያሉት ፡ እስረኞች ፡ ይበልጡብናል ፡ የሚሉ ፡ ታታሮቹን ፡ ይከተሉ ፤ በፖሊሾቹ ፡ እጅ ፡ ያሉት ፡ እስረኞች ፡ ይበልጡብናል ፡ የሚሉም ፡ እዚሁ ፡ ይቅሩ ። ታታሮቹን ፡ ተከትለው ፡ የሚዘምቱትን ፡ ኮሼቮዩ ፡ ይምራ ። የሚቀሩት ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ ኮሼቮይ ፡ ይምረጡ ። ደግሞ ፡ የሽማግሌ ፡ ምክሬን ፡ ብታዳምጡኝ ፡ ለቀሪዎቹ ፡ ኮሼቮይ ፡ ለመሆን ፡ ከታራስ ፡ ቡልባ ፡ የተሻለ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይገኝም ። በጉብዝና ፡ ማናችንም ፡ ብንሆን ፡ እሱን ፡ አናክልም!»

ቦቭዲዩግ ፡ ይህን ፡ ተናገረና ፡ ዝም ፡ አለ ። ኮዛኮቹም ፡ ከዚህ ፡ ሽማግሌ ፡ ኮዛክ ፡ በቀረበው ፡ ምክር ፡ ተደሰቱ ። ሁሉም ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እየወረወሩ ፡ «ተባረክ ፡ ባትኮ! ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ኖረህ ፡ በመጨረሻ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ተናገርክ! ለኮዛክነት ፡ ክብር ፡ ገና ፡ አገለግላለሁ ፡ በማለት ፡ የሰጠኸው ፡ ቃል ፡ በከንቱ ፡ አልቀረም!» እያሉ ፡ ጮሁ ።

«ታዲያ ፡ ሁላችሁም ፡ በዚህ ፡ ተስማምታችኋል?» ሲል ፡ ኮሼቮዩ ፡ ጠየቀ ።

ኮዛኮቹም ፡ «አዎ ፡ ተስማምተናል!» ብለው ፡ ጮሁ ።

«እንግዲያው ፡ ሸንጎው ፡ ተፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው?»

«አዎ ፡ ተፈጸመ ።»

«እንግዲያው ፡ ልጆቼ ፡ ትእዛዜን ፡ አዳምጡ!» አለና ፡
ኮሼቮዩ ፡ ቆቡን ፡ አድርጎ ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ቆመ ። ዛፖሮ
ዥያኖቹም ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ ሲናገር ፡ እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፡
ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ቆሙ ።
ኮሼቮዩ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«አሁን ፡ ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፡ ተከፋፈሉ! ለመሔ
ድ ፡ የምትፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፤ ለመቅረት ፡ የምትፈ
ልጉ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ተለዩ! የአንድ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡
አብዛኛው ፡ የመንደሩ ፡ ጦር ፡ ወደሔደበት ፡ ይደባለቃል ።
ቀሪው ፡ አነስተኛው ፡ የዚያ ፡ መንደር ፡ ጦርም ፡ ከሌላ ፡ መን
ደር ፡ ጋር ፡ ይደባለቃል ።»

ወዲያው ፡ እንደታዘዙት ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ተከፍለው ፡
ቆሙ ። እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ በቁጥር ፡
ምንም ፡ አልተበላለጡም ። ለመቅረት ፡ የፈለጉት ፡ አብዛ
ኛው ፡ ኔዛማይ ፡ መንደር ፡ የኡማንና ፡ የካኔቨ ፡ መንደሮች ፡
በሙሉ ፡ እንዲሁም ፡ ከፖፖቪች ፡ ከስቴብሊኮቭና ፡ ከቲሞ
ሼቭካ ፡ መንደሮች ፡ አብዛኞቹ ፡ ናቸው ። የቀሩት ፡ ታታሮቹ
ን ፡ ተከትሎ ፡ ለመዝመት ፡ መረጡ ። በሁለቱም ፡ ወገን ፡
ብዙ ፡ ጀግናና ፡ ብርቱ ፡ ኮዛኮች ፡ ነበሩ ። ታታሮቹን ፡ ተከት
ሎ ፡ ለመሔድ ፡ ከመረጡት ፡ ውስጥ ፡ ቼሬቫቲ ፡ ፖኮቲፖሌ ፡
ሌሚሽ ፡ እንዲሁም ፡ ኾማ ፡ ፕሮኮፖቪች ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።
ዴሚድ ፡ ፖፖቪችም ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ብዙ ፡ ለመቆየት ፡
የማይችል ፡ ቅብጥብጥ ፡ ኮዛክ ፡ ስለነበር ፡ ከነሱው ፡ ጋር ፡
ለመሄድ ፡ ተነስቶአል ። ከፖሊሾች ፡ ጋር ፡ ጦርነቱን ፡ አይቶ
አልና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከታታሮች ፡ ጋር ፡ ለመሞካከር ፡ ፈለገ ።
ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ጀግናና ፡ ባለዝና ፡ ኮዛኮችም ፡ እንዲሁም ፡ ከአለ
ቆች ፡ መካከል ፡ ኖስትዩጋን ፡ ፖክሪሽካ ፤ ኔቬሊችኪ ፡ ከታታ
ሮች ፡ ጋር ፡ ገጥመው ፡ ጉራዴና ፡ ጡንቻቸውን ፡ ለመሞ
ከር ፡ ፈቅደው ፡ ተነሱ ። ከሚቀሩት ፡ ኮዛኮች ፡ መካከልም ፡



ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ ነበሩ ። የጦር ፡ አለቆች ፡ የሆኑ ፡ ዴሚትሮ
ቬች ፤ ኩኩቤንኮ ፤ ቬርቲኽቪስት ፤ ባላባን ፤ አስታፕ ፡ ቡል
ባና ፡ ሌሎችም ፡ ባለዝና ፡ ኮዛኮች ፡ እነ ፡ ቮቭቱዜንኮ ፤ ቼሬ
ቪቼንኮ ፤ እስቴፋን ፡ ጉስካ ፤ ኦኽሪም ፡ ጉስካ ፤ ሚኮላ ፡ ጉስቲ
ይ ፤ ዛዶሮዥኒይ ፤ ሜቴሊትሳ ፤ ኢቫን ፡ ዛክሩቲጉባ ፤ ሞሲይ ፡
ሺሎ ፤ ዴክቲያሬንኮ ፤ ሲዶሬንኮ ፤ ፒሳሬንኮ ፤ ሁለተኛው ፡
ፒሳሬንኮ ፤ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ሶስተኛ ፡ ፒሳሬንኮ ፤ ሌሎችም ፡
ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ኮዛኮች ፡ እዚያው ፡ ቀርተው ፡ ከፖሊሾች ፡ ጋር ፡
ለመዋጋት ፡ ቆረጡ ። ሁሉም ፡ በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ የተጓዙና ፡
የዘመቱ ፡ ናቸው ። በአናቶሊያ ፡ ወደቦች ፤ በክራይሚአ ፡ ጨ
ፌና ፡ መስኮች ፤ ከድኔፐር ፡ ከሚቀላቀሉት ፡ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡
ወንዞችም ፤ ያልተጓዙበትና ፡ ያልደረሱበት ፡ ሥፍራ ፡ አልነ
በረም ። ሞልዳቪያን ፤ ዋላኺያንና ፡ የቱርክንም ፡ አገር ፡ ጐብ
ኝተዋል ። በኮዛክ ፡ ጀልባዎቻቸው ፡ በጥቁር ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡
እየተጓዙ ፡ ሃምሳ ፡ ጀልባ ፡ ሆነው ፡ ብዙ ፡ የከበሩና ፡ ታላላቅ ፡
መርከቦችን ፡ እየወጉ ፡ ብዙ ፡ የቱርክ ፡ መርከቦች ፡ አስም
ጠዋል ። በጊዜያቸው ፤ ብዙ ፤ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ባሩድ ፡ የተኮ
ሱ ፡ ናቸው ። ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ደጋግመው ፤ ውድ ፡ ዋጋ ፡
ያላቸው ፡ የሐርና ፡ የከፋይ ፡ ጨርቆችን ፡ ለእግራቸው ፡ ገን
ባሌ ፡ ቀድደዋል ። ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜም ፡ ደጋግመው ፡ በቀ
በቷቸው ፡ የተንጠለጠሉትን ፡ ከረጢቶች ፡ በወርቅ ፡ ሞል
ተው ፡ ነበር ። በመጠጥና ፡ በፈንጠዝያ ፡ ያጠፉትም ፡ ገንዘ
ብ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተብሎ ፡ ሊታወቅ ፡ ያዳግታል ። በሌላ ፡
ሰው ፡ እጅ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እነሱ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ የሚያ
ባክኑት ፡ ሃብት ፡ ለዕድሜ ፡ ልክ ፡ መተዳደሪያ ፡ በበቃ ፡ ነበር ።
እነሱ ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ እየጋበዙ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ እንዲደሰ
ት ፡ ዛፋኝ ፡ ሙዚቀኞች ፡ እየቀጠሩ ፡ በዕውነተኛው ፡ የኮ
ዛክ ፡ ባሕል ፡ አባከኑት ። አሁንም ፡ እንኳን ፡ አንዳንዶቹ ፡
ምንም ፡ ቅርስ ፡ የላቸውም ። ድንገት ፡ በሌለንበት ፡ ወራሪ ፡
የመጣ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ በድኔፐር ፡ ደሴቶች ፡ በቄጠ

ማ ፡ መካከል ፡ የቀበሩዋቸውን ፡ የብር ፡ ጽዋዎች ፣ የወርቅ ፡ ድሪና ፡ አልቦዎች ፡ ታታሮቹ ፡ ለማግኘት ፡ ያዳግታቸዋል ። ራሳቸው ፡ ኮዛኮቹ ፡ እንኳን ፡ ሃብታቸውን ፡ የቀበሩበትን ፡ ሥፍራ ፡ መዘንጋት ፡ ጀምረዋል ። ለታማኝ ፡ ጓደኞቻቸውና ፡ ለክርስቲያንነት ፡ ሃይማኖት ፡ ሲሉ ፡ እዚህ ፡ ቀርተው ፡ ፖሊሾቹን ፡ ለመበቀል ፡ የቆረጡት ፡ ኮዛኮች ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ።

ሽማግሌው ፡ ኮዛክ ፡ ቦቭዲዩግም ፡ አብሯቸው ፡ ለመቅረት ፡ ወስኖ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፣

«ታታሮቹን ፡ ለማባረር ፡ ዕድሜዬ ፡ አይፈቅድልኝም ። ስለዚህ ፡ ዕውነተኛ ፡ የኮዛክ ፡ ሞት ፡ ለመሞት ፡ የምችልበት ፡ ሥፍራ ፡ እዚህ ፡ ነው ። የመሞቻዬ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ለተቀደሰው ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ስዋጋ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ እንድሞት ፡ ዘወትር ፡ ለአምላክ ፡ ስፀልይ ፡ ነበር ። ይኸው ፡ ፀሎቴ ፡ ሠመረልኝ ። ለአንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ኮዛክ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የክብር ፡ ሞት ፡ በየትም ፡ አይገኝም ።»

ሁሉም ፡ በየመንደር ፡ የጦር ፡ ክፍላቸው ፡ ተከፋፍለው ፡ በሁለት ፡ መሥመር ፡ ከተሰለፉ ፡ በኋላ ፡ ኮሼቮይው ፣ በመካከላቸው ፡ እየሄደ ፣ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፣ ሁሉም ፡ ወገን ፡ ተደስቷልን?» አላቸው ።

ኮዛኮቹም ፣ «ሁላችንም ፡ ተደስተናል ፣ ባትኮ!» ብለው ፡ ጮኹ ።

«በሉ ፡ እንግዲያው ፡ ተሳሳሙና ፡ ተሰነባበቱ ። ከእንግዲህ ፡ መገናኘታችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያውቀው ። በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ መሪያችሁን ፡ አዳምጡ ፣ የኮዛክነት ፡ ክብራችሁ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ፈጽሙ ።»

ከዚያ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ተሳሳሙ ። መጀመሪያ ፡ አለቆቹ ፡ ጉንጭ ፡ ለጉንጭ ፡ ተሳስመው ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ መጨባበጥ ፡ ጀመሩ ። ሁለት ፡ አለቆች ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡



ተጨባብጠው ፡ ሲቆሙ ፣ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፣ «እንደገና ፡ እንገናኝ ፡ ይሆን ፡ ወንድሜ ፡ መኳንንት?» ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ ሳይፈልጉ ፡ አልቀሩም ። ግን ፡ ይህ ፡ በሽበቶ ፡ ራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ በሃሳብ ፡ ይጉላላ ፡ እንጂ ፡ አንዳቸውም ፡ ገልፀው ፡ አልተናገሩትም ። በአለቆቹ ፡ ዙሪያ ፡ ሌሎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ሁሉ ፡ ይሰነባበቱ ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ ያለባቸውን ፡ ከባድ ፡ ተግባር ፡ ቢገነዘቡትም ፡ ፖሊሾቹ ፡ መከፋፈላቸውን ፡ እንዳያውቁባቸው ፡ በማለት ፣ ከመጨለሙ ፡ በፊት ፡ እንዳይለያዩ ፡ ወሰኑ ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ በጊዜ ፡ ራት ፡ ለመብላት ፡ ወደየሰፈራቸው ፡ ሄዱ ።

ከራት ፡ በኋላ ፡ መንገደኞቹ ፡ ያለ ፡ ስጋት ፡ ለመተኛት ፡ ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ሆነ ፡ እንደታያቸው ፡ ሁሉ ፣ ወዲያው ፡ ተኝተው ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰዳቸው ። ፀሐይ ፡ እስክትጠልቅ ፡ ድረስ ፡ ተኙ ። ፀሐይ ፡ ጠልቃ ፡ ሲጨልምም ፣ ተነሱና ፡ ሠረገላዎቻቸውን ፡ ዘይት ፡ ማጠጣትና ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀመሩ ፣ ሁሉም ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፣ ሁሉም ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ ቀሪዎቹን ፡ ጓደኞቻቸውን ፡ ተሰናበቱና ፡ በዝግታ ፡ ሠረገላዎቹን ፡ ተከትለው ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ። ፈረሰኞቹ ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፣ ቀስ ፡ ብለው ፡ በማኮብኮብ ፡ እርምጃ ፡ እየተጓዙ ፡ አንድም ፡ ጫጫታ ፡ ወይም ፡ ፉጨት ፡ ሳይሰማ ፡ ሁሉም ፡ በጨለማው ፡ ተሠወሩ ። ከፈረሶቹ ፡ ኮቴና ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በቂ ፡ ዘይት ፡ ሳያገኙ ፡ ከቀሩ ፡ የሠረገላ ፡ መሽከርከሪያዎች ፡ ድምጽ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ አይሰማም ፡ ነበር ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ መንገደኞቹ ፡ በጨለማው ፡ ተውጠው ፡ ባይታዩም ፣ ቀሪዎቹ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ እጃቸውን ፡ ሲያወዛወዙላቸው ፡ ቆዩ ። ወዲያው ፡ ቀሪዎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ወደየሥፍራቸው ፡ ተመልሰው ፡ በከዋክብት ፡ ብርሃን ፡ አካባቢውን ፡ ሲመለከቱ ፣ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሠረገላዎች ፡ እኩሌታ ፡ መሄዱንና ፡ እንዲሁም ፣ ብዙዎቹ ፡ ጓደ

ኞቻቸው ፡ ከመካከላቸው ፡ አለመኖራቸውን ፡ ተገንዝበው ፤ ልባቸው ፡ አዘነ ። ደስተኛው ፡ መንፈሳቸውም ፡ ተከዞ ፤ በሃሳብ ፡ ተውጠው ፡ አንገታቸውን ፡ ደፉ ።

ታራስ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ማዘናቸውንና ፡ ለጐበዝ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ትካዜ ፤ አንገታቸውን ፡ እንደቀለሰው ፡ ተመለከተ ። ነገር ፡ ግን ፡ በፊት ፡ ከጓደኞቻቸው ፡ የመለየቱን ፡ ሃዘን ፡ ይላመዱትና ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ተደስቶ ፡ የበለጠ ፡ ብርታት ፡ እንዲያገኝ ፡ በኮዛክ ፡ የጦር ፡ ጩኸት ፡ አነቃቃቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጠባይ ፡ ለሰፊውና ፡ ለኃያሉ ፡ የስላቭ ፡ ተፈጥሮ ፡ ብቻ ፡ የታደለ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የስላቭ ፡ ተፈጥሮ ፡ ከሌሎች ፡ ሲነፃፀር ፡ በባህርና ፡ በጐጭ ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ያህል ፡ የላቀ ፡ ነው ። ጊዜው ፡ ሞገዳማ ፡ ሲሆን ፡ እንደነጐድጓድ ፡ እያገሳ ፤ ደካማ ፡ ወንዞች ፡ የማይችሉትን ፡ ተራራ ፡ የሚያህል ፡ ማዕበል ፡ ያነሳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ነፋስ ፡ ሳያናውፀው ፡ ፀጥ ፡ ብሎ ፡ በረጋ ፡ ጊዜ ፡ ከማናቸውም ፡ ወንዝ ፡ ይበልጥ ፡ ጠርቶ ፡ ሲንጣለል ፡ ለዓይን ፡ የማይጠገብ ፡ ደስታ ፡ ነው ።

ታራስ ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ የቆመውን ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ እንዲያራግፉ ፡ አሽከሮቹን ፡ አዘዘ ። ይህ ፡ ሠረገላ ፡ ከሌሎቹ ፡ የኮዛኮች ፡ ጓዝ ፡ ተሸካሚዎች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ትልቅና ፡ ጠንካራ ፡ ነበር ። ትልልቅ ፡ ተሽከርካሪዎቹም ፡ በእጥፍ ፡ ብረት ፡ የተጠረዙ ፡ ናቸው ። ሠረገላው ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ተጭኖ ፡ ጭነቱም ፡ ጠንካራ ፡ የበሬ ፡ ቆዳ ፡ ለብሶ ፡ ዘይት ፡ በጠጣ ፡ ገመድ ፡ ተቀርቅቦአል ። የተጫነው ፡ ጭነት ፡ በቡልባ ፡ እቃ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የኖረ ፡ በበርሚል ፡ ያለ ፡ መልካም ፡ የበሰለ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ነበር ። ቡልባ ፡ ይህን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ያመጣው ፡ ድንገት ፡ ታላቅ ፡ አጋጣሚ ፡ ቢደርስ ፡ የኮዛኮቹን ፡ ወኔ ፡ ለመቀስቀስ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ እንዲቀርብ ፡ አስቦ ፡ ነው ። አሽከሮቹ ፡ የኮሎኔሉን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰሙ ፡ ፈጥነው ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ሔዱና ፡ በጐራዴያቸው ፡ ወፍራሙን ፡



ገመድ ፡ ቆራርጠው ፡ ጠንካራውን ፡ ቆዳም ፡ ቀዳደው ፡ የወይን ፡ ጠጁን ፡ በርሚሎች ፡ አወረዱ ።

ከዚያ ፡ ቡልባ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ሁሉንም ፡ ጠጡ ፤ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያገኛችሁትን ፡ መጠጫ ፡ ይዛችሁት ፤ ጭልፋ ፡ ወይም ፡ የፈረስ ፡ ማጠጫ ፤ ባልዲ ፡ ወይም ፡ ዋንጫ ፤ እኒህም ፡ እንኳን ፡ ባይኖራችሁ ፡ እፍኛችሁን ፡ አቅርቡ!»

ኮዛኮቹም ፡ አንዳቸውም ፡ ሳይቀሩ ፡ ያገኙትን ፡ መጠጫ ፡ ይዘው ፤ የሌላቸውም ፡ እፍኛቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ቀረቡ ። የቡልባ ፡ አሽከሮችም ፡ በመካከላቸው ፡ ገብተው ፡ የወይን ፡ ጠጁን ፡ ይቀዱ ፡ ጀመር ። ግን ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ እንዲጠጡ ፡ እሱ ፡ ምልክት ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ መጠጣት ፡ እንዳይጀምር ፡ ቡልባ ፡ አዘዘ ። እሱ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ አስቀድሞ ፡ አስቦአል ። መልካም ፡ የበሰለ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ኃይለኛ ፡ ቢሆንና ፡ የሰውንም ፡ መንፈስ ፡ ለማነቃቃት ፡ ቢችል ፡ በሚጠጣበት ፡ ሰዓት ፡ በደንብ ፡ የተመረጡ ፡ ቃላት ፡ ከተጨመሩ ፡ የወይን ፡ ጠጁ ፡ ኃይልም ፡ ሆነ ፡ የሰዎቹ ፡ ወኔ ፡ አጠፌታ ፡ እንደሚሆን ፡ ታራስ ፡ በደንብ ፡ ያውቃል ።

ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

«ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፤ አሁን ፡ የጋበዝኳችሁ ፡ መሪአችሁ ፡ እንድሆን ፡ ስለመረጣችሁኝ ፡ አይደለም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ለኔ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የአሁኑ ፡ ግብዣ ፡ ምክንያት ፡ እሱ ፡ አይደለም ። ከጓደኞቻችንም ፡ በመለየት ፡ የተነሳ ፡ አይምሰላችሁ ። ሁለቱም ፡ ነገሮች ፡ ቢሆኑ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለግብዣው ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ በሆኑ ፡ ነበር ። ግን ፡ የአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም ። ከፊታችን ፡ የተደቀነው ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ድካምና ፡ ታላቅ ፡ የኮዛክ ፡ ጀግንነት ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው! ስለዚህ ፡ ጓደኞቼ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ ለተቀደሰው ፡ የኦርቶዶክስ ፡

ሃይማኖት ፡ እንጠጣ! በመላው ፡ ዓለም ፡ ተስፋፍቶ ፡ በየትም ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ እንዲኖርና፡ ከሃዲዎች ፡ ሁሉ ፡ ክርስትናን ፡ እንዲቀበሉ ፡ በመመኘት ፡ እንጠጣ! ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ለሴቹ ፡ እንጠጣ! ከሃዲዎችን ፡ ለማስጨነቅ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ እንዲጸና ፡ በየዓመቱም ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ የላቀ ፡ ጀግኖች ፡ ተዋጊዎች ፡ ለማሰለፍ ፡ እንዲችል ፡ እንጠጣ! ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ለኛ ፡ ለራሳችን ፡ ጀግንነት ፡ እንጠጣ! የልጅ ፡ ልጆቻችንና ፡ የነሱም ፡ ልጆች ፡ ቀድሞ ፡ ወንድምነትን ፡ የማይክዱና ፡ የተቸገሩ ፡ ጓደኞቻቸውን ፡ የማያጋልጡ ፡ ጀግኖች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ እያሉ ፡ እንዲያስታውሱን ፡ ይሁን! በሉ ፡ ለሃይማኖታችን ፡ ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፤ ለሃይማኖታችን ፡ በሉ ፡ ለሃይማኖታችን!»

«ለሃይማኖታችን!» ብለው ፡ በመጮህ ፡ ወጣት ፡ ሽማግሌው ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ለሃይማኖታቸው ፡ ጠጡ ።

«ለሴቹ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ጽዋውን ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ አነሳ ።

«ለሴቹ!» ሲል ፡ የኮዛኮቹ ፡ ጩኸት ፡ አስተጋባ ።

ኮዛኮቹ ፡ ለሴቹ ፡ ሰላምታቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ ድምጻቸው ፡ መስኩን ፡ ሁሉ ፡ አቋርጦ ፡ ሩቅ ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

«የመጨረሻ ፡ ጽዋችንን ፡ ወንድሞቼ ፡ ለእኛ ፡ ጀግንነትና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ስንል ፡ እንጠጣ!» አለ ፡ ቡልባ ።

ኮዛኮቹ ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ለጀግንነታቸውና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የመጨረሻ ፡ ጽዋቸው ፡ አንስተው ፡ ጠጡ ።

ጽዋቸው ፡ ባዶ ፡ ሆኖአል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ አሁንም ፡ እጃቸውን ፡ እንዳነሱ ፡ ቆሙ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከመጠጡ ፡ የተነሳ ፡ በዓይኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ ቢታይም ፡ ውስጡን ፡ ጥልቅ ፡ ሃሳብ ፡ ገብቶአቸው ፡ ነበር ። አሁን ፡ በሃ



ሳባቸው ፡ የሚያሰላስሉት ፡ በውጊያው ፡ ስለሚደርሳቸው ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ አይደለም ። እድል ፡ አግኝተው ፡ ወርቅ ፤ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ መሣሪያዎች ፤ በጥልፍ ፡ ያጌጡ ፡ ልብሶችና ፡ የሴርካሲያን ፡ ፈረሶች ፡ ለመማረክ ፡ ስለሚችሉት ፡ ሰዎችም ፡ አይደለም ። በረጅም ፡ ተራራ ፡ ቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሰፊውን ፡ ባህር ፡ ነጥብ ፡ ከመሳሰሉ ፡ ጀልባዎቹና ፡ መርከቦቹ ፡ ጋር ፡ ዳር ፡ ዳሩም ፡ አሻንጉሊት ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ ከተማዎችና ፡ ሳር ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ጫካዎችን ፡ እንደሚመለከት ፡ ንስር ፡ አሞራ ፡ እነሱም ፡ ሜዳውን ፡ አገር ፡ እየተመለከቱ ፡ በሃሳባቸው ፡ የሚያሰላስሉትም ፡ የወደፊት ፡ እድላቸውን ፡ ነበር ። ሜዳው ፡ ሁሉ ፡ ደማቸውን ፡ ጠጥቶ ፡ አጥንታቸውን ፡ ለብሶ ፡ የሠረገላ ፤ የጦርና ፡ የጐራዴ ፡ ስብርባሪም ፡ በየሥፍራው ፡ ተበታትኖ ፡ የሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ። ጭንቅላታቸው ፡ ደም ፡ ከተጋገረበት ፡ ጉንጉን ፡ ጐፈሬአቸው ፡ ጋር ፡ በየሜዳው ፡ ይዘራል ። አሞሮችም ፡ እየወረዱ ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ጭረው ፡ ፈልፍለው ፡ ያወጧቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ አጥንት ፡ የተዘራበት ፡ የዚያ ፡ የሞት ፡ ሰፈር ፡ ዝና ፡ ታላቅ ፡ ይሆናል! ከጀብዶአቸው ፡ አንዱም ፡ ቢሆን ፡ አይረሳም ። የኮዛክ ፡ ጀግንነት ፡ ከጠመንጃ ፡ አፈሙዝ ፡ በኖ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ባሩድ ፡ የሚጠፋ ፡ አይደለም ። ሽበቶው ፡ ጢሙ ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ የራሱ ፡ ሽበት ፡ ሻሽ ፡ የመሰለ ፡ ሽማግሌ ፡ ባንዱራ ፡ መቼ ፡ ዝናቸውን ፡ የሚያነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ። ጀግንነታቸውም ፡ በዓለም ፡ ይነዛል ። ከነሱ ፡ ኋላ ፡ የሚወለዱት ፡ ሁሉ ፡ ስለነሱ ፡ ያወራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ዘጠኝ ።

ከዛፖሮዢያኖቹ ፡ መካከል ፡ ገሚሱ ፡ ጦር ፡ ታታሮቹን ፡ ለመከተል ፡ መሄዱን ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ያወቀ ፡ አልነበረም ። በከተማው ፡ አዳራሽ ፡ ህንፃ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የቆ

ሙት ፣ ዘበኞች ፤ ግማሾቹ ፣ ሠረገላዎች ፤ ወደ ፣ ሜካው ፣ መነ
ዳታቸውን ፣ ተመልክተዋል ። ግን ፣ ኮዛኮቹ ፣ የደፈጣ ፣ ውጊያ ፣
አቅደው ፣ ይሆናል ፣ በማለት ፣ አሰቡ ። የፈረንሳዊው ፣ መሐ
ንዲስ ፣ ግምትም ፣ ይኸው ፣ ነበር ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ ሲሆን ፣ ኮሼ
ቮይው ፣ የተናገረው ፣ ቃል ፣ በከንቱ ፣ አልቀረም ፤ ከተማው ፣
እንደገና ፣ በምግብ ፣ ችግር ፣ ተጨንቋል ። በቀድሞ ፣ ዘመናት ፣
እንደተለመደው ፣ ሁሉ ፤ ወታደሮቹ ፣ ሰንቃቸውን ፣ በሚገባ ፣
አልመጠኑትም ። ከምሽጉ ፣ ወጥተው ፣ አደጋ ፣ በመጣል ፣
ያገኙትን ፣ ምግብ ፣ ለመዝረፍ ፣ ሞክረው ፣ ነበር ። ግን ፣
እነዚህ ፣ ምሽግ ፣ ለቅቀው ፣ የወጡ ፣ ደፋሮች ፤ ግማሾቹ ፣ ወዲ
ያው ፣ በኮዛኮቹ ፣ ተጨፍጭፈው ፣ ሲያልቁ ፣ የተረፉትም ፣ ባዶ ፣
እጃቸውን ፣ ተመለሱ ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ አጋጣሚ ፣ ለአ
ይሁዶች ፣ ተመቻቸውና ፣ ማናቸውንም ፣ ነገር ፣ ዘርዝረው ፣
ተናገሩ ። ዛፖሮዢያኖቹ ፣ ወዴት ፣ እንደሄዱና ፣ ለምንስ ፣
እንደሄዱ ፤ መሪዎቻቸው ፣ እነማን ፣ እንደሆኑ ፤ የመንደሮ
ቹና ፣ የሰዎቹ ፣ ቁጥር ፤ የቀሩትስ ፣ እነማን ፣ እንደሆኑ ፤ ሃሳ
ባቸው ፣ ምን ፣ እንደሆነ ፤ በጠቅላላው ፣ በአጭር ፣ ጊዜ ፣ ው
ስጥ ፣ ሁሉም ፣ ነገር ፣ በከተማው ፣ ታወቀ ። ኮሎኔሎቹ ፣ በዚ
ህ ፣ ወሬ ፣ ተበረታቱና ፣ ለውጊያ ፣ ተዘጋጁ ። ታራስም ፣ የከ
ተማውን ፣ መራወጥ ፣ በማዳመጥ ፣ ነቃና ፣ በፍጥነት ፣ እር
ምጃ ፣ ወሰደ ። ወዲያው ፣ ትዕዛዝ ፣ ሰጠና ፣ የየመንደሩ ፣ ጦር ፣
በሶስት ፣ ቦታ ፣ ሠረገላዎቹን ፣ በዙሪያው ፣ መክቶ ፣ እንዲ
መሽግ ፣ አደረገ ። የሁለት ፣ መንደር ፣ ጦር ፣ ለደፈጣ ፣ ውጊ
ያ ፣ ተመደበና ፣ እንዲሁም ፣ ለጠላት ፣ ፈረሰኞች ፣ መሰና
ክል ፣ እንዲሆን ፣ ሹል ፣ እንጨቶች ፤ የጠበንጃና ፣ የጦር ፣ ሰባ
ሪዎች ፣ በሜዳው ፣ ላይ ፣ ተቸከሉ ። ሁሉም ፣ ነገር ፣ እንደ
ፍላጐቱ ፣ ከተዘጋጀ ፣ በኋላ ፣ ታራስ ፣ ለኮዛኮቹ ፣ ንግግር ፣ አደ
ረገ ። የንግግሩ ፣ ዓላማ ፣ የኮዛኮቹን ፣ ወኔ ፣ ለመቀስቀስ ፣ ወ
ይም ፣ ለማበረታታት ፣ የታቀደ ፣ አልነበረም ። ወኔያቸው ፣
አስቀድሞም ፣ እንደተቀሰቀሰ ፣ ታራስ ፣ አልዘነጋም ። ነገር ፣



ግን ፣ በልቡ ፣ ያለውን ፣ ለማውጣትና ፣ እንዲቀልለው ፣ ሲል ፣
እንዲህ ፣ አላቸው ፤

«መኳንንት ፣ ሆይ ፤ ስለጓደኝነታችንና ፣ ስለወንድማማ
ችነታችን ፣ ልገልጽላችሁ ፣ እፈልጋለሁ ። ሃገራችን ፣ በሌሎ
ች ፣ መንግሥታት ፣ ዘንድ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ግምት ፣
እንደነበራት ፣ ከአባቶቻችሁና ፣ ከአያቶቻችሁ ፣ ሰምታች
ሁታል ። ሃገራችን ፣ በግሪኮች ፣ ዘንድ ፣ የታወቀች ፣ ነበረች ፤
ኮንስታንቲኖፕልንም ፣ ታስገብር ፣ ነበር ። ከተሞቻችን ፣
ሃብታም ፣ ነበሩ ። የራሳችን ፣ ቤተ ፣ መቅደሶችና ፣ እንዲሁ
ም ፣ ካቶሊካውያን ፣ ከሃዲዎች ፣ ሳይሆኑ ፣ እውነተኛ ፣ የሩ
ሲያዊ ፣ ደም ፣ ያላቸው ፣ የራሳችን ፣ ልዑላኖች ፣ ነበሩን ።
ይህንን ፣ ሁሉ ፣ ተገፈፍን ። ሁሉም ፣ ጠፋ ። እንደሙት ፣ ል
ጆች ፣ እኛው ፣ ብቻ ፣ ቀረን ። ሃገራችንም ፣ ኃያል ፣ ባሏ ፣
እንደሞተባት ፣ ሴት ፣ ብቻዋን ፣ ቀረች ። እንዲህ ፣ ባለውም ፣
ጊዜ ፣ ጓደኞቼ ፣ ሆይ ፣ እኛ ፣ በወንድማማችነት ፣ ተሳስረን ፣
ለመቆም ፣ በቃን ። ከጓደኝነት ፣ የሚበልጥ ፣ የተቀደሰ ፣ ዝም
ድና ፣ አይገኝም ። ጓደኝነታችንም ፣ የተመሰረተው ፣ በዚህ ፣
ላይ ፣ ነው ። አባት ፣ ልጁን ፣ ይወዳል ፤ እናት ፣ ልጁዋን ፣
ትወዳለች ። ልጅም ፣ እናትና ፣ አባቱን ፣ ይወዳል ። ግን ፣ ይህ ፣
ሌላ ፣ ነገር ፣ ነው ። እንስሳትም ፣ እንኳን ፣ ልጆቻቸውን ፣
ይወዳሉ ። የደም ፣ ሳይሆን ፣ የመንፈስን ፣ ፍቅርና ፣ ዝምድ
ና ፣ የሚያውቀው ፣ ግን ፣ ሰው ፣ ብቻ ፣ ነው ። ወንድማማችነ
ት ፣ በሌሎች ፣ ሃገሮችም ፣ አለ ። ነገር ፣ ግን ፣ በእኛ ፣ በሩሲ
ያውያን ፣ ምድር ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ ያህል ፣ በየትም ፣ አይገ
ኝም ። ብዙዎቻችሁ ፣ በባዕድ ፣ ሃገሮች ፣ ብዙ ፣ አመታት ፣
አሳልፋችኋል ። በዚያም ፣ እንደናንተው ፣ ያሉ ፣ የእግዚአ
ብሔር ፣ ፍጡር ፣ ሰዎችን ፣ አግኝታችሁ ፣ እንደዘመድ ፣ ተወ
ያይታችኋል ። ነገር ፣ ግን ፣ እነዚህ ፣ ሰዎች ፣ በንግግራቸው ፣
ጠቢብ ፣ ይሁኑ ፣ እንጂ ፣ የልብን ፣ ገልጾ ፣ በመወያየት ፣ ረገድ ፣
ከእናንተ ፣ የተለዩ ፣ ናቸው ። በተፈጥሮ ፣ ሰው ፣ መሆናቸው ፣

ቢታወቅም ፤ እንደናንተ ፡ ፍጹም ፡ የሰውነት ፡ ጠባይ ፡ የላ
ቸውም! የለም ፤ ወንድሞቼ ፤ እንደ ፡ ሩሲያውያን ፡ ከልብ ፡
የሚያፈቅር ፤ በአዕምሮ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሙሉ ፡ አካሉ ፤
አምላክ ፡ በሰጠው ፡ ተፈጥሮ ፡ ሁሉ ፡ የሚያፈቅር ፡...» እዚ
ህ ፡ ላይ ፡ ታራስ ፡ ሽበቶ ፡ ራሱን ፡ ነቅንቀና ፡ እንደገና ፡ ንግግ
ሩን ፡ ቀጠለ ። «እንዲያ ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ የሚያውቅ ፡ ማን
ም ፡ የለም!በሃገራችን ፡ አንዳንድ ፡ የከፋት ፡ መንፈሶች ፡ እን
ደተመሠረቱ ፡ አውቃለሁ ። ለስንዴና ፡ ለድርቆሽ ፡ ክምራ
ቸው ፤ ለፈረስ ፡ መንጋቸውና ፡ እንዲሁም ፡ በበርሚል ፡ ለታ
ሸገው ፡ ጠጃቸው ፡ ብቻ ፡ የሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። የሚያ
ስጠላ ፡ የባዕድ ፡ ልብስ ፡ አጥልቀው ፡ የእናት ፡ የአባታቸውን ፡
ቋንቋም ፡ ንቀው ፡ ትተውት ፡ የሃገር ፡ ልጅ ፡ ከሃገር ፡ ልጅ ፡
ጋር ፡ መነጋገሩ ፡ ቀርቷል ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ የሃገር ፡ ልጅ ፡
የሃገሩን ፡ ልጅ ፡ በገበያ ፡ እንደሚሸጥ ፡ ከብት ፡ ይሸጠው ፡
ጀመር ። አንድ ፡ የባዕድ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ በቢጫ ፡ ጫማ
ው ፡ በእርግጫ ፡ የሚመታቸው ፡ የፖላንድ ፡ ሹም ፡ ለእነሱ ፡
ከወንድማማችነት ፡ በልጦባቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡
ወራዶች ፡ መካከል ፡ የመጨረሻው ፡ ወራዳም ፡ እንኳን ፡ ቢሆ
ን ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ በውርደት ፡ ቢሸቆጠቆጥና ፡ መሬት ፡
ቢልስ ፡ ትንሽ ፡ የሩሲያዊ ፡ ስሜት ፡ ቅንጣት ፡ አያጣም ። ይ
ህም ፡ ስሜቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይገነፍልና ፡ ፀጉሩን ፡ እየነጨ ፡
ህይወቱን ፡ በመርገም ፡ ከሃፍረቱ ፡ ለመንፃት ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡
የሚሠቃይበት ፡ ቀን ፡ ይመጣል ። በሩሲያዊ ፡ ምድራችን ፡
ላይ ፡ ጓደኝነት ፡ ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉም ፡ ይገን
ዘቡት! በሞት ፡ ረገድ ፡ የሆነ ፡ እንደሆንም ፤ እኛ ፡ አሁን ፡
የተሰለፍንለትን ፡ አሟሟት ፡ ከእነሱ ፡ አንዳቸውም ፡ አያገ
ኙትም! አንዳቸውም! ከአይጥ ፡ ልብ ፡ የማይሻለው ፡ ልባ
ቸው ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አሟሟት ፡ አይፈቅድላቸውም!»

እነሆ ፡ የኮዛኮች ፡ መሪ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ። ንግግሩን ፡
ከጨረሰም ፡ በኋላ ፡ በኮዛክ ፡ ጀብዱ ፡ የሸበተውን ፡ ራሱን ፡



በትካዜ ፡ ያነቃንቅ ፡ ነበር ። እዚያ ፡ የቆሙት ፡ ሁሉ ፡ በአነጋ
ገሩ ፡ ልባቸው ፡ ተነካ ። ጠና ፡ ጠና ፡ ያሉት ፡ መኳንንት ፡ አን
ገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ በእርጋታ ፡ ቆመው ፡ ዓይናቸው፡ እንባ ፡
እያቀረረ ፡ በእጅጌያቸው ፡ ይጠርጉ ፡ ጀመር ። ታራስ ፡ የተ
ናገራቸው ፡ ቃላት ፡ በጉብዝና ፡ ልፋትና ፡ ችግር ፡ በኖሩት ፡
የበሰሉ ፡ ሰዎችም ፡ ሆነ ፡ የኑሮን ፡ ችግር ፡ ገና ፡ ሳይቀም
ሱ ፡ ጉብዝናን ፡ የአባት ፡ ቅርስ ፡ አድርገው ፡ በድፍረት ፡ በሚ
መኙት፡ ጐልማሶች ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ያን ፡ አስደ
ሳች ፡ የጀግና ፡ ወኔ ፡ ቀሰቀሱት ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የጠላት ፡ ሰልፍ ፡ ከከተማው ፡ መው
ጣት ፡ ጀምሯል ። ነጋሪት ፡ እየተጐሰመ ፤ መለከት ፡ እየተ
ነፋ ፡ የጠላት ፡ መኳንንት ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ በሌላቸው ፡ ገባሮ
ቻቸው ፡ ታጅበው ፡ እየጋለቡ ፡ ወጡ ። ወዲያው ፡ ወፍራሙ ፡
ኮሎኔል ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰጠና ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ሰይፋ
ቸውን ፡ እያወናጨፉ ፡ ጠበንጃቸውን ፡ ደግነው ፡ ወደ ፡ ኮዛ
ኮቹ ፡ ገሰገሱ ።

ኮዛኮቹም ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ለጠበንጃ ፡ ተኩስ ፡ ሲቀር
ቡላቸው ፡ ያለማቋረጥ ፡ እያከታተሉ ፡ እሩምታ ፡ ይተኩሱ ፡
ጀመር ። ተኩሱም ፡ መስክና ፡ ኮረብታዎችን ፡ አልፎ ፡ ሩቅ ፡
አገር ፡ ድረስ ፡ እንደነጐድጓድ ፡ አስተጋባ ። አካባቢው ፡ ሁሉ ፡
በጢስ ፡ ታፈነ ። ኮዛኮቹ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳያቋርጡ ፡
ተኩሳቸውን ፡ ቀጠሉ ። ከኋላ ፡ ያሉት ፡ እፊት ፡ ላሉት ፡ እያ
ቀባበሉላቸው ፡ አከታትለው ፡ ሲተኩሱ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ዘ
ዴውን ፡ ስላላወቁ ፡ ሳያቀባብሉ ፡ እንዴት ፡ አከታትለው ፡
ይተኩሳሉ ፡ በማለት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ሁለቱንም ፡ ወገን ፡
የባሩድ ፡ ጢስ ፡ አፍኗቸው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይታይም ። አን
ድ ፡ በአንድ ፡ ከመካከላቸው ፡ እየተነጠሉ ፡ የሚወድቁትንም ፡
ወታደሮች ፡ ለማየት ፡ አልቻሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ፖሊሾቹ ፡
የሚወርድባቸው ፡ ተኩስ ፡ ማየሉንና ፡ የሁናቴውንም ፡ መከ
ፋት ፡ ተገንዝበው ፡ ከጢሱ ፡ አፈና ፡ ለመውጣት ፡ አፈግፍ

ስቴፓን ፣ ጉዝካ ፣ ትልቁን ፣ መድፍ ፣ ለመማረክ ፣ መቃረባ
ቸውን ፣ ተመለከተና ፣ ኮዛኮቹን ፣ አስከትሎ ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣
የጦር ፣ ግንባር ፣ አመራ ። የኔዛማይ ፣ ኮዛኮች ፣ በሄዱበት ፣
ሥፍራ ፣ ሁሉ ፣ የፖሊሾቹን ፣ ሬሣ ፣ እየረፈረፉት ፣ ያልፉ ፣ ጀ
መር ። የእነሱም ፣ ሰልፍ ፣ እየሳሳ ፣ ሄደ ። በሠረገላዎቹ ፣ አጠ
ገብ ፣ ቮቭቱዜንኮ ፣ ጠንክሮ ፣ ይዋጋል ። ከግንባር ፣ ቼሬቪቼ
ንኮ ፣ ራቅ ፣ ብሎም ፤ ዴግቲያሬንኮ ፤ ከእሱም ፣ ኋላ ፣ የመን
ደር ፣ ጦር ፣ መሪው ፣ ቬርቲኽቪስት ፣ ይዋጋሉ ። ዴግቲያሬ
ንኮ ፣ ሁለት ፣ መኳንንት ፣ በጦር ፣ ወግቶ ፣ ገድሎ ፣ ከሶስተ
ኛው ፣ ጋር ፣ ገጥሟል ። ይህም ፣ ሶስተኛው ፣ መኰንን ፣ የከ
በረ ፣ የጦር ፣ ልብስ ፣ የለበሰ ፣ ቀልጣፋ ፣ ሰው ፣ ከመሆኑም ፣
በላይ ፣ ሃምሳ ፣ የሚሆኑ ፣ አሽከሮች ፣ አጅበውታል ። ወዲያ
ው ፣ ዴግቲያሬንኮን ፣ አጣድፎ ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ ጣለውና ፣
ጐራዴውን ፣ በራሱ ፣ ላይ ፣ እያወዛወዘ ፤ «እናንት ፣ የኮዛክ ፣
ውሾች ፤ አንዳችሁም ፣ ከእኔ ፣ ለመቋቋም ፣ አትደፍሩም!»
አለና ፣ ጮኸ ።

በዚህን ፣ ጊዜ ፤ «ይኸው ፣ እኔ ፣ አለሁ!» አለና ፣ ሞሲ
ይ ፣ ሺሎ ፣ ፊንጠር ፣ ብሎ ፣ ወጣ ። ሺሎ ፣ ከአንድ ፣ ሁለት ፣
ጊዜ ፣ በባህር ፣ ላይ ፣ የጦር ፣ አዝማች ፣ የሆነና ፣ ብዙ ፣ ዓይ
ነት ፣ ችግር ፣ የቀመሰ ፣ ኮዛክ ፣ ነው ። አንድ ፣ ጊዜ ፣ በትሬ
ቢዞንድ ፣ አቅራቢያ ፣ ከነተከታዮቹ ፣ ቱርኮች ፣ ማርከውት ፣
ሁሉንም ፣ ባሪያ ፣ አድርገው ፣ ብዙ ፣ ሳምንት ፣ ምግብና ፣ ውሃ ፣
ከልክለው ፣ ሲያሰቃዩዋቸው ፣ ምርኮኞቹም ፣ የኦርቶዶክስ ፣
ሃይማኖታቸውን ፣ ከመሻር ፣ ስቃይ ፣ መቀበሉ ፣ ይሻላል ፣ በማ
ለት ፣ ሁሉንም ፣ ቻሉ ። መሪያቸው ፣ ሞሲይ ፣ ሺሎ ፣ ግን ፣
ስቃዩን ፣ አልቻለውም ። የተቀደሰውን ፣ ሃይማኖቱን ፣ አፍ
ርሶ ፣ ያን ፣ የተረገመ ፣ የእስላም ፣ ጥምጥም ፣ በኃጢአተኛው ፣
ራሱ ፣ ላይ ፣ ጠመጠመና ፣ በፓሻው ፣ ተወድዶ ፣ ዕምነት ፣
ከተጣለበት ፣ በኋላ ፣ የእሥር ፣ ቤቱ ፣ ቁልፍ ፣ ያዥና ፣ የባሮቹ ፣
አለቃ ፣ ሆነ ። እስረኞቹ ፣ ባሮችም ፣ ከመካከላቸው ፣ አንዱ ፣



ሃይማኖቱን ፣ ከዶ ፣ ወደ ፣ ጨካኝ ፣ ገዥዎቻቸው ፣ ሲያዘነ
ብል ፣ ከፋቱ ፣ ከማናቸውም ፣ አረመኔ ፣ የባሰ ፣ መሆኑን ፣ ስለ
ሚያውቁ ፣ እጅግ ፣ አዘኑ ። በዕውነትም ፣ ሞሲይ ፣ ሺሎ ፣ እ
ጅግ ፣ ከፋባቸው ። በአዲስ ፣ ሰንሰለት ፣ ከግንድ ፣ ጋር ፣ አስሮ ፣
እስከ ፣ አጥንት ፣ ድረስ ፣ በሚገሽልጥ ፣ አለንጋ ፣ ያለ ፣ ርኅ
ራኄ ፣ ይገርፋቸው ፣ ጀመር ። ቱርኮቹም ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ አሽ
ከር ፣ በማግኘታቸው ፣ ከመደሰታቸው ፣ የተነሳ ፣ ደንባቸውን ፣
ዘነጉና ፣ ፊንጠዝያ ፣ በማድረግ ፣ መጠጥ ፣ ጠጥተው ፣ ሰከሩ ።
በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ሺሎ ፣ ስልሳ ፣ አራቱንም ፣ የእስረኞቹን ፣ የ
ሰንሰለት ፣ ቁልፍ ፣ ወስዶና ፣ ሰንሰለታቸውን ፣ እየፈታ ፣ ጐራ
ዴ ፣ ይዘው ፣ ቱርኮቹን ፣ እንዲቀራርጡ ፣ ለያንዳንዳቸው ፣
የሰንሰለታቸውን ፣ ቁልፍ ፣ ሰጣቸው ። በዚያን ፣ ጊዜ ፣ ኮዛኮ
ቹ ፣ የዘረፉት ፣ ሃብት ፣ እጅግ ፣ ብዙ ፣ ነበር ። በጀግንነት ፣
ወደ ፣ እናት ፣ ሃገራቸው ፣ ከተመለሱም ፣ በኋላ ፣ ዘፋኞች ፣
የሞሲይ ፣ ሺሎን ፣ ጀግንነት ፣ እያነሱ ፣ ለብዙ ፣ ጊዜ ፣ ሲያሞ
ግሱት ፣ ኖረዋል ። እንደ ፣ ችሎታው ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ ኮሼ
ቮይ ፣ ሆኖ ፣ በተመረጠ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ጠባዩ ፣ ግራ ፣
የገባ ፣ ነው ። አንድ ፣ ጊዜ ፣ አስደናቂ ፣ መልካም ፣ ተግባር ፣
ይፈጽምና ፣ ወዲያው ፣ ደግሞ ፣ ሲወሰልት ፣ ይታያል ። ያለ
ውን ፣ ሃብት ፣ ሁሉ ፣ በመጠጥና ፣ በፊንጠዝያ ፣ ጨርሶ ፣ ከየ
ሰው ፣ ከመበደሩም ፣ በላይ ፣ እንደ ፣ ተራ ፣ ሌባ ፣ የመስረቅ ፣
አመል ፣ አደረበት ። አንድ ፣ ቀን ፣ በሌሊት ፣ ሙሉ ፣ የኮዛክ ፣
መሣሪያ ፣ ከሌላ ፣ መንደር ፣ ወስዶ ፣ ለመጠጥ ፣ ነጋዴው ፣
ሸጠና ፣ በዚህም ፣ ወራዳ ፣ ሥራው ፣ የተነሳ ፤ በገበያ ፣ መሃል ፣
ከግንድ ፣ ጋር ፣ ታሥሮ ፣ አላፊ ፣ አግዳሚው ፣ ሁሉ ፣ እንዲ
ቀጠቅጠው ፣ አጠገቡ ፣ ዱላ ፣ ተቀመጠ ። ነገር ፣ ግን ፣ የአለ
ፈውን ፣ የጀግንነት ፣ ሞያውን ፣ በማስታወስ ፣ አንድም ፣ ዛፖ
ሮዥያን ፣ ያን ፣ ዱላ ፣ አላነሳበትም ። ሞሲይ ፣ ሺሎ ፣ የተባለ
ው ፣ ኮዛክ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ ነበር ።

«እናንት ፣ ልክስክስ ፣ ውሾች ፤ እናንተን ፣ ለማሸነፍ ፣

የሚችሉ ፣ ብዙ ፣ ጀግኖች ፣ አሉን!» ብሎ ፣ ጮኸና ፣ ሺሎ ፣
ወደ ፣ ጠላቱ ፣ ገሰገሰ ።

ከዚያ ፣ ሁለቱ ፣ ብቻ ፣ ለብቻ ፣ ገጠሙና ፣ የብረት ፣ ልብ
ሳቸው ፣ እስቲሰረጐድ ፣ ድረስ ፣ በሰይፍ ፣ ይቀጣቀጡ ፣ ጀ
መር ። የፖላንዱ ፣ ጦረኛ ፣ የሺሎን ፣ የብረት ፣ ልብስ ፣
ሰንጥቆ ፣ ስጋውን ፣ አገኘውና ፣ የኮዛኩ ፣ ልብሶ ፣ በደም ፣ ተነ
ከረ ። ነገር ፣ ግን ፣ ሺሎ ፣ ቁስሉን ፣ ከምንም ፣ ሳይቆጥረው ፣
ቀጭንና ፣ ጠምዛዛ ፣ ክንዱን ፣ ከፍ ፣ አድርጐ ፣ በመሰንዘር ፣
ጠላቱን ፣ ኃይለኛ ፣ በትር ፣ መታው ። ፖሊሹም ፣ የራስ ፣ ጥ
ሩሩ ፣ ተሰባብሮ ፣ ተበታተነና ፣ ዝልፍልፍ ፣ ብሎ ፣ ወደቀ ።
ሺሎም ፣ የወደቀውን ፣ ጠላቱን ፣ በሰይፍ ፣ ይቆራርጠው ፣
ጀመር ። ነገር ፣ ግን ፣ የወደቀውን ፣ ጠላቱን ፣ በንዴት ፣ ከመ
ጨፍጨፍ ፣ ይልቅ ፣ ዘወር ፣ ብሎ ፣ ቢመለከት ፣ በተሻለው ፣
ነበር ። ኮዛኩ ፣ ዞሮ ፣ ለመመልከት ፣ ከመቻሉ ፣ በፊት ፣ ከወ
ደቀው ፣ ጠላቱ ፣ አሽከሮች ፣ አንዱ ፣ ደረሰና ፣ አንገቱ ፣ ላይ ፣
ጩቤ ፣ ሰካበት ። ሺሎም ፣ ዘወር ፣ ቢል ፣ የወጋው ፣ ጠላቱ ፣
በባሩዱ ፣ ጢስ ፣ ማሃል ፣ ተሰውሮ ፣ ከዓይኑ ፣ ጠፋ ። በዚህን ፣
ጊዜ ፣ የተወጋውን ፣ አንገቱን ፣ በእጁ ፣ ያዘና ፣ ተንገዳግዶ ፣
ወደቀ ። ወዲያው ፣ ለጓደኞቹ ፤ «ደህና ፣ ሁኑ ፣ መኳንንት ፣
ወንድሞቼ ፤ ጓደኞቼ! የተቀደሰችው ፣ የሩሲያ ፣ ምድር ፣ ለዘ
ለዓለም ፣ ተከብራ ፣ ትኑር!» አለና ፣ ዓይኖቹን ፣ ከደነ ። የኮዛ
ክ ፣ ነፍሱም ፣ ከስጋው ፣ ተለይታ ፣ በረረች ።

በሌላ ፣ ሥፍራ ፣ ዛዶሮዥኒይ ፣ ከነሰዎቹ ፣ በጦሩ ፣ ማሃል ፣
ይገሰግሳል ፤ ቬርቲኸቪስት ፣ የፖሊሾቹን ፣ ሰልፍ ፣ እ
የበታተነ ፣ ሲያልፍ ፤ ባላባንም ፣ ከዋናው ፣ ውጊያ ፣ ማሃል ፣
ዘልሎ ፣ ገባ ።

በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ታራስ ፤ «ታዲያስ ፣ ወንድሞቼ! በባሩድ ፣
ቀንዳችሁ ፣ ገና ፣ ባሩድ ፣ አለን? የኮዛክ ፣ ኃይል ፣ ገና ፣ አልደ
ከመምን? ኮዛኮች ፣ ድል ፣ አልሆኑምን?» አለና ፣ የጦር ፣ መሪ
ዎቹን ፣ ጠየቀ ።



እነሱም ፤ «በባሩድ ፣ ቀንዳችን ፣ ገና ፣ ባሩድ ፣ አለ ፣ ባት
ኮ! የኮዛክ ፣ ኃይል ፣ ገና ፣ አልደከመም! ኮዛኮች ፣ ድል ፣ አይ
ሆኑም!» አሉ ።

ወዲያው ፣ ኮዛኮቹ ፣ እንደገና ፣ በአጥቂነት ፣ ገሰገሱና ፣
የጠላትን ፣ ሰልፍ ፣ ግራ ፣ አጋቡት ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ትንሹ ፣
ኮሎኔል ፣ በየመስኩ ፣ የተበታተኑትን ፣ ሰዎቹን ፣ ለመሰብሰብ ፣
ስምንት ፣ ሰንደቅ ፣ አላማዎች ፣ እንዲተከሉ ፣ አዘዘ ። ፖሊ
ሾቹም ፣ በሰንደቅ ፣ አላማዎቹ ፣ ዙሪያ ፣ ተሰበሰቡ ። ነገር ፣
ግን ፣ ገና ፣ ሳይደራጁ ፣ ኩኩቤንኮ ፣ የኔዛማይን ፣ መንደር ፣
ኮዛኮች ፣ አስከትሎ ፣ ገስገሰና ፣ ከማሃላቸው ፣ ገብቶ ፣ ወፍ
ራሙን ፣ ኮሎኔል ፣ እሱው ፣ እራሱ ፣ ገጠመው ። ኰሎኔሉም ፣
ኩኩቤንኮን ፣ ለመቋቋም ፣ ስላልቻለ ፣ ፈረሱን ፣ አዙሮ ፣ ጋለ
በና ፣ ሸሸ ። ኩኩቤንኮም ፣ ተከትሎት ፣ ጋለበና ፣ እያባረረ ፣
ከጦር ፣ ሰራዊቱ ፣ ለየው ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ በሌላ ፣ ግንባር ፣
የነበረው ፣ ስቴፓን ፣ ጉዝካ ፣ ይህን ፣ ሲመለከት ፤ ኮሎኔሉን ፣
ከፊት ፣ ቀድሞ ፣ ለማቋረጥ ፤ የመጥለፊያ ፣ ገመዱን ፣ አዘጋ
ጅቶ ፣ ሽምጥ ፣ ጋለበ ። ሲደርስም ፣ ገመዱን ፣ ወርውሮ ፣ በኮ
ሎኔሉ ፣ አንገት ፣ አጠለቀው ። የኮሎኔሉ ፣ ፊት ፣ ወዲያው ፣
ደም ፣ መሰለና ፣ ገመዱን ፣ ለመበጠስ ፣ በሁለት ፣ እጁ ፣ ሲታ
ገል ፣ ጉዝካ ፣ በኃይል ፣ ጐተተና ፣ ከፈረሱ ፣ አውርዶ ፣ ጣለው ።
ሲወድቅም ፣ ለመሰናክል ፣ የተቸከለ ፣ ችካል ፣ በሆዱ ፣ ተሻ
ጠበትና ፣ እዚያው ፣ ከመሬት ፣ ተጣብቆ ፣ ቀረ ። ነገር ፣ ግን ፣
ጉዝካም ፣ የተሻለ ፣ ዕድል ፣ አላገኘም ። ምን ፣ ጊዜ ፣ እንደደ
ረሱበት ፣ ሳይታወቅ ፤ አራት ፣ ፖሊሾች ፣ ስቴፓን ፣ ጉዝካን ፣
በአራት ፣ ጦር ፣ ወግተው ፣ በአየር ፣ ላይ ፣ አንጠለጠሉት ።
ጉዝካም ፣ በአራት ፣ ጦር ፣ ተወግቶ ፣ እንደተንጠለጠለ ፤ «ጠ
ላቶቻችን ፣ ድምጥማጣቸው ፣ ይጥፋ! ሩሲያ ፣ ምድራችን ፣ ለዘ
ለዓለም ፣ ትኑር!» በማለት ፣ የመጨረሻ ፣ ቃሉን ፣ ተናገረ ።

በጦር ፣ ግንባር ፣ በስተጐን ፣ ሜቴሊትሳ ፤ ፖሊሾቹን ፣ እያ
ከታተለ ፣ ራስ ፣ ራሳቸውን ፣ ይቀጠቅጣል ። በሌላ ፣ ወገን ፣

9—401

ደግሞ ፥ ኔቬሊችኪይ ፡ ከነተከታዮቹ ፡ እየገሰገሰ ፡ ይዋጋል ። በሰረገላዎቹ ፡ አጠገብ ፡ ዛክሩቲጉባ ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ያተራምሰዋል ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ በሚታዩት ፡ ሠረገላዎችም ፡ አጠገብ ፡ ሶስተኛው ፡ ፒሳሬንኮ ፡ ብቻውን ፡ አንድ ፡ ጓድ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ ይከላከላል ። ከእሱ ፡ አልፎ ፡ ባሉት ፡ ሠረገላዎች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ገፍተው ፡ መጥተው ፡ በሠረገላዎቹ ፡ ላይ ፡ እየወጡ ፡ መዋጋት ፡ ጀምረዋል ።

የጦር ፡ መሪያቸው ፡ ታራስ ፤ ፊት ፡ ፊታቸው ፡ እየጋለበ ፤ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ! በባሩድ ፡ ቀንዳችሁ ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለን? የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመምን? ኮዛኮች ፡ ድል ፡ አልሆኑምን?» አላቸው ።

«በባሩድ ፡ ቀንዳችን ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለ ፤ ባትኮ! የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመም! ኮዛኮች ፡ ድል ፡ አይሆኑም!» አሉት ።

ቦቭዲዩግ ፡ ከልቡ ፡ ሥር ፡ በጥይት ፡ ተመትቶ ፡ ከሠረገላው ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ ወድቋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ ትንፋሹ ፤ «ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በመለየቴ ፡ አላዝንም ። ሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተወሰነ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ። የሩሲያ ፡ ምድር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር!» አለና ፡ ነፍሱ ፡ ቀድሞ ፡ ላለፉት ፡ ሌሎች ፡ ሽማግሎች ፡ በሩሲያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ጀብዱና ፡ ለተቀደሰው ፡ ሃይማኖት ፡ ስለሚደረገው ፡ መስዋዕትነት ፡ ለመንገር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በረረች ።

ወዲያው ፡ ከእሱ ፡ ቀጥሎ ፡ የመንደር ፡ ጦር ፡ አለቃው ፡ ባላባን ፡ ወደቀ ። ሲወድቅም ፤ በጦር ፡ በጥይትና ፡ በጐራዴ ፡ ሶስት ፡ ቦታ ፡ ተመትቶ ፡ ነበር ። ባላባን ፡ ከዋናዎቹ ፡ የኮዛክ ፡ ጀግኖች ፡ አንዱ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በብዙ ፡ የባህር ፡ ዘመቻዎች ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ሞያ ፡ ሠርቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ የሚደነቅለት ፡ በአናቶሊያ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ የፈጸመው ፡ ወረራ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ባላባንና ፡ ተከታዮቹ ፡ ብዙ ፡ የቱርክ ፡ ሃብት ፡ ዘርፈው ፡ ሲመለሱ ፡ ክፉ ፡ ዕድል ፡ አጋጠማቸው ። የቱርኮች ፡ መርከብ ፡ ደርሶ ፡ በመድፍ ፡ ከጀልባዎቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ግማሹን ፡ ገለበጠባቸውና ፡ ብዙ ፡ ኮዛኮችም ፡ ሰመጡ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ባላባንና ፡ ተከታዮቹ ፡ ነፋስ ፡ እየገፋ ፡ እንዲረዳቸው ፡ ሰፋፊ ፡ የኮዛክ ፡ ሱሪያቸውን ፡ ቀድደው ፡ በጀልባዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ወጥረው ፡ አሠሩና ፡ በመድፍ ፡ ፍላጻ ፡ የተሰነጣጠቁትን ፡ ጀልባዎች ፡ ጠጋግነው ፤ በቀን ፡ እንዳይታዩ ፡ ሌሊት ፡ በመጓዝ ፡ እጅግ ፡ ፈጣኑን ፡ የቱርክ ፡ መርከብ ፡ አመለጡት ። ኮዛኮቹ ፡ ሕይወታቸውን ፡ አድነው ፡ ማምለጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በኪየቭ ፡ ላለው ፡ የሜዢጐርስክ ፡ ገዳም ፡ አለቃና ፡ እንዲሁም ፡ በዛፖሮዥዬ ፡ ለቅድስት ፡ ድንግል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ ያጌጠ ፡ ስጦታ ፡ አመጡ ። ይህንንም ፡ የኮዛኮቹን ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ በማሞገስ ፡ ዘፋኞች ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በዘፈን ፡ ሲያነሱት ፡ ኖረዋል ። አሁን ፡ ባላባን ፡ በሞት ፡ ስቃይ ፡ ተይዞ ፡ አንገቱን ፡ ደፋና ፡ በቀስታ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ «መኳንንት ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ መልካም ፡ የተቀደሰ ፡ ሞት ፡ መሞቴ ፡ ነው ። ሰባት ፡ ቆርጬ ፤ ዘጠኝ ፡ ወግቼ ፡ ጥያለሁ ። ብዙዎችንም ፡ በፈረሴ ፡ ደቅድቄ ፡ ጥያለሁ ። በጥይት ፡ የገደልኋቸውንማ ፡ ቁጥራቸውንም ፡ አላስታውሰው ። ሩሲያ ፡ ምድራችን ፡ ለዘለዓለም ፡ አሸብርቃ ፡ ትኑር!» ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ ነፍሱ ፡ በርራ ፡ ሄደች ።

የኮዛኮች ፡ የጀግንነት ፡ አበባ ፡ እየባከነ ፡ ሄደ! ኩኩቤንኮ ፡ ተከብቧል ። ከኔዛማይ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ የተረፉት ፡ ተከታዮቹም ፡ ሰባት ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፡ ኃይላቸው ፡ እየደከመ ፡ ሄዷል ። የኩኩቤንኮ ፡ ልብስ ፡ በደም ፡ ርሷል ።

ታራስ ፡ ራሱ ፡ ይህን ፡ ተመለከተና ፡ ሊረዳው ፡ ፈጥኖ ፡ ሄደ ። ግን ፡ አልደረሰለትም ። ታራስና ፡ ሌሎችም ፡ ኮዛኮች ፡ ለእርዳታ ፡ ደርሰው ፡ የከበቡትን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ከማባረራቸው ፡ በፊት ፤ ኩኩቤንኮ ፡ ከልቡ ፡ ሥር ፡ በጦር ፡

ተወግቶ ፡ ወደቀ ። የወጣት ፡ ደሙም ፡ ደንበኛኑ ፡ የተሰበረ ፡ መልካም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ መስሎ ፡ ይጐርፍ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ ኮዛኮች ፡ ተመለከተና ፤ «ጓደኞቼ ፡ ሆይ ፤ እያያችሁኝ ፡ በመሞቴ ፡ አምላክን ፡ አመሰግነዋለሁ ። ከእኛ ፡ በኋላ ፡ የሚፈጠሩት ፤ ከእኛ ፡ የበለጡ ፡ ጀግኖች ፡ እንዲሆኑ ፡ ያድርግልን ። በክርስቶስ ፡ የተወደደችው ፡ የሩሲያ ፡ ምድራችንም ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደተዋበች ፡ ትኑር!» ብሎ ፤ ወጣት ፡ ነፍሱ ፡ ተለይታው ፡ በረረች ። መላዕክትም ፡ ታቅፈው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወሰዷት ። በሰማይም ፡ ክርስቶስ ፤ «ና ፡ በቀኝ ፡ ጐኔ ፡ ተቀመጥ ፡ ኩኩቤንኮ! እነሆ ፡ አንተ ፡ ጓደኞችህን ፡ አልከዳህም ፤ ወራዳ ፡ ተግባርም ፡ አልፈጸምህም ። ቤተ ፡ መቅደሴን ፡ ተከላክለህ ፡ ጠብቀሃታልና ፤ ና ፡ ወደኔ!» ይለዋል ።

የኩኩቤንኮ ፡ ሞት ፡ ሁሉንም ፡ አሳዘናቸው ። የኮዛኮች ፡ ሠልፍ ፡ እየሳሳ ፡ ሄደ ። ብዙ ፤ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ ወድቀዋል ። ሆኖም ፡ አሁንም ፡ ሳያፈገፍጉ ፡ ሥፍራቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ናቸው ።

ታራስ ፡ የተረፉትን ፡ ሰዎች ፡ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ! በባሩድ ፡ ቀንዳችሁ ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለን? ጐራዴያችሁ ፡ ገና ፡ አልደነዘምን? የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመምን?» አላቸው ።

እነሱም ፤ «ገና ፡ በቂ ፡ ባሩድ ፡ አለን ፤ ባትኮ! ጐራዴያችንም ፡ ገና ፡ ስለት ፡ ነው! የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመም! ኮዛኮች ፡ አያፈገፍጉም!» ሲሉ ፡ መለሱለት ።

ከዚያ ፤ ምንም ፡ ሰው ፡ የተቀነሰባቸው ፡ ሳይመስል ፡ እንደገና ፡ ወደፊት ፡ ገሠገሡ ። ከመንደር ፡ ጦር ፡ አዛዦች ፡ ውስጥ ፡ የተረፉት ፡ ሦስት ፤ ብቻ ፡ ናቸው ። በየሥፍራው ፡ ደም ፡ ይጐርፋል ። የኮዛኮቹና ፡ የጠላቶቻቸው ፡ ሬሣ ፡ ተነባብሮ ፡ ተከምሮ ፡ ከሰው ፡ ቁመት ፡ በላይ ፡ ሆኗል ። ታራስ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፤ ገና ፡ ካሁኑ ፡ ጆቢራዎች ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ያንዣብባሉ ። አቤት ፡ ዛሬ ፡ ያጋጠማቸው ፡ ድግሥ!



ኮዛኮቹ ፡ ወደፊት ፡ ገሥግሠው ፡ ሲዋጉ ፡ ሜቴሊትሲያን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ አንጠለጠሉት ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሁለተኛው ፡ ፒሳሬንኮ ፡ አንገቱ ፡ በጐራዴ ፡ ተቆርጦ ፡ ተሽከረከረ ። ኦኽሪም ፡ ጉስካ ፡ አራት ፡ ቦታ ፡ ተመትቶ ፡ ወደቀ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «አሁን ፡ ነው ፡ እንግዲህ!» አለና ፡ መሐረቡን ፡ አወዛወዘ ። ኦስታፕም ፡ ምልክቱን ፡ አየና ፤ ካደፈጠበት ፡ ቦታ ፡ ተመድርሮ ፡ ወጥቶ ፡ ፖሊሾቹን ፡ እያጣደፈ ፡ መሰናክል ፡ እንዲሆን ፡ ተብሎ ፡ ጋሬጣና ፡ የጦር ፡ ስብርባሪ ፡ ወደተቸከለበት ፡ ሥፍራ ፡ ነዷቸው ። እዚያ ፡ ሲደርሱም ፡ ፈረሶቻቸው ፡ እየተደናቀፉ ፡ ሲወድቁ ፤ ሰዎቹም ፡ እየወረዱ ፡ ይከሰከሱ ፡ ጀመር ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከሠረገላዎቹ ፡ ጀርባ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ያደፈጡት ፡ የኮርሱኝ ፡ ኮዛኮች ፤ ጠላቶቻቸው ፡ ለጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ መቅረባቸውን ፡ ተመለከቱና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የጥይት ፡ በረዶ ፡ አረገፉባቸው ። ፖሊሾቹ ፡ ከመሸበር ፡ የተነሣ ፡ የሚያደርጉት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። በዚህም ፡ ኮዛኮቹ ፡ ተበረታቱና ፤ «ድሉ ፡ የኛ ፡ ነው!» እያሉ ፡ ከያለበት ፡ ይጮሁ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ መለከት ፡ እየነፉ ፡ የድል ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማቸውን ፡ ዘረጉ ። ፖሊሾቹ ፡ በሽብር ፡ እየተሩዋሩዋጡ ፡ መሸሸጊያ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ።

ታራስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ በር ፡ ተመለከተና ፤ «የለም ፤ ድሉ ፡ የኛ ፡ አይደለም!» አለ ። በዕውነትም ፡ አልተሳሳተም ። የከተማው ፡ በር ፡ ተከፍቶ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ ፡ ጀግኖች ፡ ያሉበት ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ገሥግሦ ፡ ወጣ ። ጦረኞቹ ፡ የተቀመጡዋቸው ፡ ፈረሶች ፡ ትልልቅና ፡ ፈጣን ፡ ነበሩ ። በመልኩም ፡ በጀብዱም ፡ ከሁሉ ፡ የላቀ ፡ መኳንንት ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ቀድሞ ፡ ይጋልባል ። ከነሐስ ፡ ጥሩሩ ፡ ዘልቆ ፡ የወረደው ፡ ጥቁር ፡ ፀጉሩ ፡ በነፋስ ፡ ይውለበለባል ። እጅግ ፡ በተዋቡ ፡ ቆንጆ ፡ ጣቶች ፡ የተጠለፈ ፡ ያማረ ፡ መሐረብ ፡ በክንዱ ፡ ላይ ፡ አስሯል ። ታራስ ፡ ይህ ፡ መኰንን ፡ አንድሬይ ፡

መሆኑን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ በመገረም ፡ ደነዘዘ ። አንድሬይ ፡ በክንዱ ፡ ላይ ፡ ለታሠረለት ፡ ማስታወሻ ፡ ተገቢ ፡ ጀግና ፡ መሆኑን ፡ ለማስመስከር ፡ እንደ ፡ አዳኝ ፡ ውሻ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ቅልጥፍና ፡ ከውጊያው ፡ ማሃል ፡ ገብቶ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ያተራምሰው ፡ ጀመር ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፤ አንድሬይ ፡ ከፊቱ ፡ ያሉትን ፡ ሁሉ ፡ በጐራዴ ፡ እየጨፈጨፈ ፡ ሲበታትናቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አላስችል ፡ ብሎት ፤ «እንዴት! ጓደኞችህ? ጓደኞችህን ፡ ትገድላለህ ፤ አንት ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ?» አለና ፡ ጮኸ ። አንድሬይ ፡ ግን ፡ ከፊቱ ፡ ያሉት ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፤ ጠላት ፡ ይሁኑ ፡ ወይም ፡ ወዳጅ ፡ አይታዩትም ። ለእሱ ፡ የሚታየው ፤ የሃር ፡ ጉንጉን ፡ የመሰለ ፡ ረጅም ፡ ጐፈሬ ፤ እንደበረዶ ፡ የነጣ ፡ አንገትና ፡ ደረት ፤ በጠቅላላው ፡ ለፍቅርና ፡ ለመሳም ፡ የተፈጠረ ፡ የአንዲት ፡ ቆንጆ ፡ አካል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይታየውም ።

«ስሙኝ ፡ ልጆቼ! እንደምንም ፡ በሉና ፡ ወደዚያ ፡ ጫካ ፡ አምጡልኝ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ለኮዛኮቹ ፡ ጮኾ ፡ ተናገረ ። ወዲያው ፡ ከመቅጽበት ፡ ፈጣን ፡ ጋላቢ ፡ የተባሉ ፡ ሠላሳ ፡ ኮዛኮች ፡ ትዕዛዙን ፡ ለመፈጸም ፡ ጋልበው ፡ ሄዱ ። እንደሄዱም ፡ ከጠላት ፡ ፈረሰኞች ፡ ግንባር ፡ ቀደሞቹን ፡ ከሌላው ፡ ጦር ፡ ቆርጠው ፡ ለይተው ፡ ጥቂት ፡ ከወጓቸው ፡ በኋላ ፡ ጐሎኮፒቴንኮ ፡ አውቆ ፡ ለማናደድ ፡ ሲል ፡ የአንድሬይን ፡ ጀርባ ፡ በጐራዴ ፡ ጥፌ ፡ ችብ ፡ አደረገውና ፡ ኮዛኮቹ ፡ በሞላ ፡ ዞረው ፡ በአስደናቂው ፡ የኮዛክ ፡ ፍጥነት ፡ ጋልበው ፡ ሸሹ ። አንድሬይ ፡ እጅግ ፡ ተናደደ! በደም ፡ ሥሮቹ ፡ ሁሉ ፡ ያለው ፡ የወጣት ፡ ደሙ ፡ ይፈላ ፡ ጀመር! ወዲያው ፡ ፈረሱን ፡ ኮለኮለና ፡ ኮዛኮቹን ፡ ተከትሎ ፡ ሽምጥ ፡ ጋለበ ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ ዞሮ ፡ ወደኋላው ፡ አልተመለከተም ። በእሱ ፡ ፍጥነት ፡ ልክ ፡ ሊከተሉት ፡ የቻሉት ፡ ሐያ ፡ የሚሆኑ ፡ ፈረሰኞች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ፡ አላወቀም ። ኮዛኮቹ ፡ እንደጋለቡ ፡ ሄደው ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ዘወር ፡ አሉ ። አንድሬይም ፡ እነሱን ፡ ተከትሎ ፡



እየጋለበ ፡ ጐሎኮፒቴንኮን ፡ ሊደርስበት ፡ ሲል ፤ አንድ ፡ ጠንካራ ፡ እጅ ፡ የፈረሱን ፡ ልጓም ፡ ለቀም ፡ አድርጐ ፡ ያዘበት ። ወዲያው ፡ አንድሬይ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ታራስ ፡ ከፊቱ ፡ ቆሞ ፡ አየ! በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ ተንቀጠቀጠ ፤ ፊቱም ፡ በአንድ ፡ አፍታ ፡ ጠወለገ ።

በተማሪ ፡ ቤት ፡ ጓደኛው ፡ በማስመሪያ ፡ መትቶት ፡ የሮጠ ፡ ልጅ ፤ የመታውን ፡ ጓደኛውን ፡ ሲያባርር ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ ከአስተማሪው ፡ ጋር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ንዴቱን ፡ ውጦ ፡ በድንጋጤ ፡ እንደሚቆም ፡ ሁሉ ፡ የአንድሬይም ፡ ንዴት ፡ ከመቅጽበት ፡ ጠፋና ፤ ከፊቱ ፡ የቆመው ፡ የሚያስፈራው ፡ አባቱ ፡ ብቻ ፡ ታየው ።

ታራስ ፡ የልጁን ፡ ዓይን ፡ ዓይኑን ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተ ፤ «በል ፤ አሁን ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ እናድርግ?» አለው ። አንድሬይ ፡ ግን ፡ ምን ፡ እንደሚመልስ ፡ ስላላወቀ ፡ ዓይኖቹን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ ዝም ፡ አለ ።

«ታዲያስ ፡ ልጄ ፤ ፖሊሾቹ ፡ ጠቀሙህ?»

አንድሬይ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠም ።

«እንዴት ፡ ሃይማኖትህን ፡ ትክዳለህ? እንዴት ፡ ጓደኞችህን ፡ ትክዳለህ? በል ፡ እንግዲህ ፤ ከፈረስህ ፡ ውረድ!» አለው ፡ ታራስ ።

አንድሬይም ፡ እንደ ፡ ታዛዥ ፡ ሕፃን ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ከታራስ ፡ ፊት ፡ ቆመ ።

«በል ፡ ሳትንቀሳቀስ ፡ ቀጥ ፡ ብለህ ፡ ቁም! እኔው ፡ ወለድሁህ ፤ እኔው ፡ እገድልሃለሁ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ያነገተውን ፡ ጠበንጃ ፡ አወለቀ ።

አንድሬይ ፡ አመድ ፡ መስሎ ፡ ገርጥቶ ፡ ቆመ ። እንደቆመም ፡ አንድ ፡ ስም ፡ በመጥራት ፡ ከንፈሮቹ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ተንቀሳቀሱ ። የጠራው ፤ የሃገሩን ፡ ስም ፤ የእናቱን ፡ ስም ፤ ወይም ፡ የወንድሞቹን ፡ ስም ፡ አይደለም ። የዚያችን ፡ የፖላንድ ፡ ቆንጆ ፡ ስም ፡ ነው ። ወዲያው ፡ ታራስ ፡ ተኮሰ ።

በስለት ፡ እንደተመታ ፡ አገዳ ፡ አንገቱን ፡ ዘንበል ፡ አድርጐ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍስ ፤ አንድሬይ ፡ ሣሩ ፡ ላይ ፡ ሽብልል ፡ አለ ።

የገዛ ፡ ልጁ ፡ ገዳይ ፤ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ቆሞ ፡ በድኑን ፡ አካል ፡ ተመለከተው ። ከሞተ ፡ በኋላም ፡ እንኳን ፡ የተዋበ ፡ ጐልማሳ ፡ ነበር ። ከአጭር ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የሕይወትን ፡ ኃይልና ፡ ግርማ ፡ የተጐናጸፈው ፤ የማንንም ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ የሚማርክ ፡ ቆንጆው ፡ የወንድ ፡ መልኩ ፡ አሁንም ፡ እንደተዋበ ፡ ነው ።

«እንዴት ፡ ያለ፡ ኮዛክ ፡ ይሆን ፡ ነበር! ቁመቱ ፡ ሎጋ ፤ ቅንድቡ ፡ ጥቁር ፤ መልኩ ፡ ገራም ፤ በውጊያ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ክንደ ፡ ጠንካራ! ታዲያ ፡ አሁን ፡ በከንቱ ፡ ተቀጨ ። እንደ ፡ ልክስክስ ፡ ውሻ ፤ በውርደት ፡ ተቀጨ!» አለ ፡ ታራስ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኦስታፕ ፡ ጋልቦ ፡ መጣና ፤ «ባትኮ ፤ ምንድን ፡ ነው ፡ ያደረግኸው? አንተ ፡ ነህ ፡ የገደልኸው?» አለና ፡ ጠየቀው ።

ታራስም ፡ ራሱን ፡ በመነቅነቅ ፡ መለሰለት ።

እስታፕ ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ የጋረዳቸውን ፡ የወንድሙን ፡ ዓይኖች ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተና ፡ በሐዘን ፡ ተዋጠ ። ወዲያው ፡ አባቱን ፤ «ባትኮ ፤ ጠላቶቻችን ፡ እንዲያዋርዱት ፡ ወይም ፡ አሞራ ፡ እንዳይበላው ፡ በክብር ፡ እንቅበረው ፡» አለው ።

ታራስም ፤ «እኛም ፡ ሳንረዳቸው ፡ እነሱው ፡ ይቀብሩታል ። ብዙ ፡ የሚያለቅሱለትና ፡ የሚያዝኑለትም ፡ ሞልተዋል ፡» አለ ።

ሆኖም ፡ ለአንድ ፡ ሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ቆሞ ፡ እዚኸው ፡ ወድቆ ፡ ተኩላ ፡ ይብላው ፡ ወይስ ፡ ስለጀግንነቱ ፡ የክብር ፡ ቀብር ፡ ይደረግለት? እያለ ፡ ሲያሰላስል ፤ ወዲያው ፡ ጐሎኮፒቴንኮ ፡ ወደሱ ፡ እየጋለበ ፡ ሲመጣ ፡ አየ ።

«ወዮልን ፤ ኮሎኔል! ፖሊሾቹ ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ ለእርዳታ ፡ ደርሶላቸው ፡ ጠንክረዋል!»



ጐሎኮፒቴንኮ ፡ ይህን ፡ ከመናገሩ ፤ ቮቭቱዜንኮ ፡ ጋልቦ ፡ ደረሰ ።

«ወዮልን ፡ ኮሎኔል! አዲስ ፡ ጉልበት ፡ ጦር ፡ መጥቶብናል!»

ቮቭቱዜንኮ ፡ ይህን ፡ ከመናገሩ ፡ ፒሳሬንኮ ፡ በእግሩ ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ፡ «ባትኮ ፡ የት ፡ ነው ፡ ያለህ? ኮዛኮች ፡ ይፈልጉሃል ። የጦር ፡ አለቃው ፡ ኔቪሊችኪይ ፡ እንዲሁም ፡ ዛዶሮዥኒይና ፡ ቼሬቪቼንኮ ፡ ሞተዋል! ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮች ፡ አንተን ፡ ሳናይ ፡ አንሞትም ፡ ብለው ፡ ጸንተው ፡ ቆመዋል ። በመሞቻቸው ፡ ሰዓት ፡ አንተ ፡ እንድታያቸው ፡ ይፈልጋሉ ፡» አለ ።

«ፈረስህ ፡ ላይ ፡ ውጣ ፤ እስታፕ!» አለና ፡ ታራስ ፡ በዚች ፡ በመጨረሻዋ ፡ የሞት ፡ ሰዓት ፡ ኮዛኮቹን ፡ ሊያያቸውና ፡ እነሱም ፡ የጦር ፡ መሪያቸውን ፡ እንዲያዩት ፡ ወደነሱ ፡ ለመሄድ ፡ ተጣድፎ ፡ ተነሳ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እነታራስ ፡ ከነበሩበት ፡ ጫካ ፡ ጋልበው ፡ ከመውጣታቸው ፡ በፊት ፤ ጦርና ፡ ጐራዴ ፡ የያዙ ፡ የጠላት ፡ ፈረሰኞች ፡ የጫካውን ፡ ዙሪያ ፡ ከብበው ፡ በየዛፎቹ ፡ መካከል ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ ።

«ኦስታፕ! እስታፕ! አይዞህ ፡ በርታ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ጐራዴውን ፡ መዝዞ ፡ ወዲህም ፡ ወዲያም ፡ ይሰነዝር ፡ ጀመር ።

ስድስት ፡ ፈረሰኞች ፡ ተመድርፈው ፡ ወደ ፡ ኦስታፕ ፡ ገሰገሱ ። ግን ፡ ክፉ ፡ ዕጣ ፡ ወደቀባቸው ። ያንዱ ፡ አንገት ፡ ወዲያው ፡ ተሽከርክሮ ፡ በረረ ። ሌላው ፡ ፈረሱን ፡ እገታለሁ ፡ ሲል ፡ ወርዶ ፡ በጭንቅላቱ ፡ ተከሰከሰ ። ሶስተኛው ፡ ደግሞ ፡ ደረቱ ፡ በጦር ፡ ተበሳ ። አራተኛው ፡ ፈረሱ ፡ በጥይት ፡ ተመታና ፡ አገርግሮ ፡ ሲወድቅ ፡ ከሥር ፡ አድርጐ ፡ ጨፈለቀው ።

«እንዲያ ፡ ነው ፤ ልጄ! ጐሽ ፡ እንዲያ ፡ ነው ፤ አስታፕ! እኔም ፡ እንዲሁ ፡ እሠራላቸዋለሁ!» ብሎ ፡ ጮኸና ፤ ታራስ ፡ ጠላቶቹን ፡ መጨፈጭፍ ፡ ቀጠለ ። ዓይኑን ፡ ከአስታፕ ፡ ላይ ፡

ሳይነቅል ፡ ጕራዴውን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየሰነዘረ ፡ በከበቡት ፡ ጠላቶቹ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያሳርፈው ፡ ጀመር ። ወዲያው ፤ ስምንት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አስታጥን ፡ ሲከብቡት ፡ አየና ፤ «አስታጥ! አስታጥ! አይዞህ ፡ ጠንክር!» እያለ ፡ ሲያበረታታው ፤ አስታጥ ፡ ግን ፡ በቁጥር ፡ ስላየሉበት ፡ ሊቋቋማቸው ፡ አልቻለም ።

ወዲያው ፡ ገመድ ፡ ወርውረው ፡ አንገቱን ፡ ጠልፉትና ፡ ተብትበው ፡ አሥረው ፡ ወሰዱት ።

ታራስ ፤ «አስታጥ! ወይኔ ፡ አስታጥ! አስታጥ!» እያለ ፡ ከፊቱ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ሁሉ ፡ እየጨፈጨፈ ፤ ለልጁ ፡ ለመድረስ ፡ ይጥር ፡ ጀመር ።

ግን ፡ ወዲያው ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ በአንድ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሲመታ ፡ ተሰማው ። የሚያየው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚዞር ፡ የሚሽከረከር ፡ መሰለው ። ለአጭር ፡ ጊዜ ፤ የሰው ፡ ጭንቅላት ፤ ጦር ፤ ጢስና ፡ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ተዘበራርቆ ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ዞረበት ። ከዚያ ፡ ጭጋግ ፡ እንደጋረደው ፡ ሁሉ ፡ ብዥ ፡ አለበት ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ወርካ ፡ ጅው ፡ ብሎ ፡ ወደቀና ፡ ዓይኖቹን ፡ ከባድ ፡ ጉም ፡ ሸፈናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ አሥር ።

ታራስ ፡ ከከባድ ፡ ስካር ፡ በኋላ ፡ ከእንቅልፍ ፡ ነቅቶ ፡ ጠፍቶ ፡ የነበረውን ፡ አዕምሮውን ፡ እንዳገኘ ፡ ሰው ፡ ያለበት ፡ አካባቢ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፤ «እንዴት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ የተኛሁት!» አለ ። እጅና ፡ እግሩ ፡ በድካም ፡ ዝሎ ፡ ተሳስሯል ። እንግዳ ፡ የሆነ ፡ ክፍል ፡ ጣራና ፡ ግድግዳ ፡ ድብዝዝ ፡ ብሎ ፡ በፊቱ ፡ እንደሚሽከረከር ፡ ሁሉ ፡ ብዥ ፡ ብዥ ፡ አለበት ። በመጨረሻ ፡ አጠገቡ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ትንፋሹን ፡ ሲያዳምጥ ፡ የቆየውን ፡ ቶቭካችን ፡ አየው ።

ቶቭካችም ፡ በልቡ ፤ አዎ ፤ እንዲያውም ፡ ለዘለዓለም ፡



ተኝተህ ፡ ልትቀር ፡ ነበር!» ብሎ ፡ አሰበና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳይናገር ፡ ታራስ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንዲጋደም ፡ በምልክት ፡ አሳየው ።

ታራስ ፡ ግን ፤ «ንገረኝ ፡ እንጂ ፤ ለመሆኑ ፡ የት ፡ ነው ፡ ያለሁት?» አለና ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወስ ፡ ይሞክር ፡ ጀመር ።

ጓደኛውም ፤ «እርፈህ ፡ ተኛ! ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ? የሥራ ፡ አካላትህ ፡ እንደተቆራረጠ ፡ አትመለከትም? አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳልቆም ፡ አንተን ፡ ይዤ ፡ ስጋልብ ፡ ይኸው ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀኔ ፡ ነው ። አንተም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ ስንመጣ ፡ ትኩሳት ፡ ተነስቶብህ ፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ ስትቀባጅር ፡ ነበር ። በፀጥታ ፡ ስትተኛ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜህ ፡ ነው ። ስለዚህ ፤ ኋላ ፡ ስቃይ ፡ እንዳይደርስብህ ፡ እርፈህ ፡ ብትተኛ ፡ ይሻልሃል ፡» አለና ፡ ተቆጣው ።

ታራስ ፡ አሁንም ፡ ምን ፡ እንደደረሰበት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ለማስታወስ ፡ መሞከሩን ፡ አልተወም ።

«አዎ ፤ ተከብቤ ፤ ፖሊሾች ፡ ሊማርኩኝ ፡ እንደነበር ፡ ትዝ ፡ ይለኛል! ያንን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ጥሶ ፡ ለመውጣት ፡ ምንም ፡ ዘዴ ፡ አልነበረኝም!» አለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቶቭካች ፤ ተንኮለኛ ፡ ህፃን ፡ እያስቸገራት ፡ ትዕግሥቷ ፡ እንዳለቀ ፡ሞግዚት ፡ በቁጣ ፡ ጮኾ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«ዝም ፡ በል ፡ ነው ፡ የምልህ ፤ አንት ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! እንዴት ፡ እንዳመለጥህ ፡ ማወቁ ፡ ምን ፡ ይጠቅምሃል? ዋናው ፡ ነገር ፡ ማምለጥህ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ማወቅ ፡ የሚገባህ ፤ የማይከዱህ ፡ ሰዎች ፡ መኖራቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው! ገና ፡ ረጅም ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ሌሊት ፡ መጓዝ ፡ አለብን ፤ ለመሆኑ ፡ እንደተራ ፡ ኮዛክ ፡ የምትፈለግ ፡ መሰሎሃል? የለም ፤ እጅህን ፡ ይዞ ፡ ለሚሰጣቸው ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ጉርሻ ፡ አውጀዋል ።»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «እስታፕስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ?» ብሎ ፡ ጮኸና ፡ እስታፕ ፡ እሱው ፡ እያየው ፡ ተይዞ ፡ እንደታሠረና ፡ አሁንም ፡ በፖሊሾች ፡ እጅ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ ለመነሳት ፡ ይፍጨረጨር ፡ ጀመር ።

የሽማግሌ ፡ ልቡ ፡ በሐዘን ፡ ተጨበጠ ። ቁስሉ ፡ የታሰረበትን ፡ ከየሥፍራው ፡ መነጫጭቆ ፡ ወረወረው ። ሊናገርም ፡ ሞከረ ። ግን ፡ ትኩሳትና ፡ ቅዠት ፡ ተነሳበትና ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ይቀባጅር ፡ ጀመር ። ታማኙ ፡ ጓደኛው ፡ በንዴት ፡ እየተሳደበ ፡ ቆሞ ፡ ይመለከተዋል ። ወዲያው ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ ያዘና ፡ እንደ ፡ ህፃን ፡ ጨብጦ ፡ ቁስሉን ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ካሰረለት ፡ በኋላ ፡ በጀንዲ ፡ ጠቅልሎ ፡ ከኮርቻው ፡ ጋር ፡ በገመድ ፡ ጠፍር ፡ አስሮት ፡ እሱም ፡ ተፈናጥጦ ፡ ይዞት ፡ ጋለበ ።

«ብትሞትም ፡ ብትቆምም ፡ እዚያው ፡ አደርስሃለሁ! ፖሊሾች ፡ በኮዛክ ፡ አጽምና ፡ ደምህ ፡ እያፌዙ ፡ ሰውነትህን ፡ ቆራርጠው ፡ እንዲጥሉህ ፡ አልፈቅድላቸውም ። አሞራ ፡ ዓይንህን ፡ ቢያነቁረውም ፤ የሃገራችን ፡ መስክ ፡ አሞራ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ከፖላንድ ፡ ምድር ፡ የሚነሳ ፡ አሞራ ፡ አይሆንም ። ሞትህም ፡ ቆምህም ፤ ኡክሬይን ፡ አደርስሃለሁ!» አለና ፡ ታማኙ ፡ ጓደኛ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ጋልቦ ፡ ታራስን ፡ አሁንም ፡ ያው ፡ እንደ ፡ በድን ፡ እንደሆነ ፡ ከዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፡ አደረሰው ። እዚያም ፡ ያለመሰልቸት ፡ በቅጠላ ፡ ቅጠልና ፡ በቅባት ፡ መድሃኒት ፡ እያከመ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ አንዲት ፡ አይሁዳዊት ፡ መድሃኒት ፡ አዋቂ ፡ ሴት ፡ ፈልጎ ፡ አምጥቶ ፡ እሷም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡ መድሃኒት ፡ እየቀመመች ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ካጠጣችው ፡ በኋላ ፡ ታራስ ፡ ማገገም ፡ ጀመረ ። የመድሃኒቱ ፡ ኃይል ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ የጸናው ፡ የእሱ ፡ የራሱ ፡ የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ ረድቶት ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ተኩል ፡ ጊዜ ፡ ቁስሉ ፡ ሁሉ ፡ ድኖ ፡ ቆሞ ፡ ለመሄድ ፡ ቻለ ። ምን ፡ ያህል ፡ ከባድ ፡ ቁስል ፡ ቆስሎ ፡ እንደነበር ፡ ምልክት ፡



ሆኖ ፡ የሚያስረዳው ፡ በጐራዴ ፡ ተመትቶ ፡ የዳነው ፡ የቁስሉ ፡ ለምጥ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።ነገር ፡ ግን ፡ ትካዜና ፡ ሐዘን ፡ እንደተጫነው ፡ ይታይበት ፡ ጀመር ። ግንባሩ ፡ ዘወትር ፡ እንደ ተኮፋተረ ፡ ነው ። አካባቢውን ፡ ሲመለከት ፤ በሴቹ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተለውጧል ። የቀድሞ ፡ ጓደኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ሞተዋል ። ለተቀደሰው ፡ የሃይማኖትና ፡ የወንድማማችነት ፡ ዓላማ ፡ ከተሰለፉት ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ እንኳን ፡ አልተረፈም ። ታታሮቹን ፡ ተከታትለው ፡ ከኮሼቮይው ፡ ጋር ፡ የዘመቱትም ፡ ከጠፉ ፡ ቆይተዋል ። አንዳንዶቹ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፤ አንዳንዶቹም ፡ ምግብና ፡ ውኃ ፡ በሌለበት ፡ በክሪሚያ ፡ የጨው ፡ ባህር ፡ ረግረግ ፤ አንዳንዶቹም ፡ ተማርከውና ፡ ተዋርደው ፡ ቀልጠው ፡ ቀርተዋል ። የቀድሞው ፡ ኮሼቮይና ፡ ሌሎቹም ፡ የታራስ ፡ የጥንት ፡ ጓደኞች ፡ አሁን ፡ የለም ። በጊዜያቸው ፡ ጠንካራ ፡ የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ በነበሩት ፡ ጀግኖች ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ አረም ፡ በቅሎባቸዋል ። ለታራስ ፡ ያለፈው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንዳንድ ፡ ድብልቅልቅ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ድግስ ፡ ሆኖ ፡ ታየው ። በድግሱም ፡ ላይ ፡ ተጋባዦች ፡ እንግዶችና ፡ አሽከሮች ፡ ሰሃንና ፡ ድስቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰባብረው ፤ አንድ ፡ ጠብታ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንኳን ፡ ሳይተርፍ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ብርጭቆዎችና ፡ ጻዋዎች ፡ ዘርፈው ፤ በመጨረሻ ፡ ጌትዮው ፤ «ምነው ፡ ይህ ፡ ድግስ ፡ ባልተደገሰ ፡ ኖሮ ፡» ብሎ ፡ ይፀፀታል ።

በሠፈሩ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ታራስን ፡ ለማጽናናትና ፡ ለማስደሰት ፡ ቢደክሙ ፡ ምንም ፡ አልሆነላቸውም ። ሸበቶና ፡ ረጅም ፡ ጢም ፡ ያላቸው ፡ ባንዱራ ፡ መችዎችም ፡ ሁለትና ፡ ሶስት ፡ ሆነው ፡ እየመጡ ፡ የኮዛክ ፡ ጀግንነቱን ፡ ለማሞገስ ፡ ቢሞክሩ ፡ ከንቱ ፡ ልፋት ፡ ሆነባቸው ። ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ በቀዘቀዘ ፡ አስተያየት ፡ እየተመለከተ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ፊቱ ፡ መሪር ፡ ሃዘን ፡ ይጐናፀፍና ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፤ «ወይ ፡ ልጄ! ልጄ ፡ እስታፕ!» እያለ ፡ ይተክዛል ።

ዛፖሮዥያኖች ፡ ለዘረፉ ፡ ባህር ፡ አቋርጠው ፡ ዘመቱ ።
ሁለት ፡ መቶ ፡ ጀልባዎች ፡ በድኔፐር ፡ ወጥተው ፡ ዘለቁና ፡
የእስያ ፡ ማይነርን ፡ ወደቦች ፡ ለእሳትና ፡ ለጐራዴ ፡ ዳረጓ
ቸው ። የጨፈጨፉት ፡ የእስላም ፡ ሕዝብም ፡ የራስ ፡ ጥምጥ
ም ፡ ደም ፡ በጠጣው ፡ መስክ ፡ ተበታትኖና ፡ በውሃው  ዳር
ም ፡ ሲንሳፈፍ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። እስያ ፡ ማይነር ፡ ብዙ ፡  ሰ
ፋፊ ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ሱሪዎችና ፡ ጥቋቁር ፡ የኮዛክ ፡ አለንጋ ፡
የጨበጡ ፡ ጠያይም ፡ እጆች ፡ ተመለከተች ። ዛፖሮዥያኖ
ቹ ፡ በየጓሮው ፡ የወይኑን ፡ ፍሬ ፡ ጨርሰው ፡ አትክልቱን ፡
መንጣጥረው ፡ አጠፉት ። በየመስጊዱ ፡ የፈረሶቻቸው ፡ ፋን
ድያ ፡ ተከመረበት ። የከበሩ ፡ የፔርሺያ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቆ
ችን ፡ እየቀዳደዱ ፡ ድግ ፡ አደረጓቸው ። ብዙ ፡ ዘመን ፡ ካለ
ፈም ፡ በኋላ ፡ አሜሞር ፡ የዛፖሮዥያን ፡ የትንባሆ ፡ ማጨ
ሻቸው ፡ በየመስኩ ፡ ወድቆ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። ሃገሩን ፡ አውከ
ውና ፡ ዘርፈው ፡ በደስታ ፡ ተመልሰው ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ። በጀል
ባዎቻቸው ፡ ሲጓዙም ፤ ባለአሥር ፡ መድፍ ፡ የቱርክ ፡ መር
ከብ ፡ ደረሰባቸውና ፡ በአንድ ፡ እሩምታ ፡ ተኩስ ፡ ትናንሽ ፡
ጀልባዎቻቸውን ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ በታተነባቸው ። ከነሱም ፡
ሲሶ ፡ የሚሆኑት ፡ እዚያው ፡ ሰምጠው ፡ ሲቀሩ ፤ ሌሎቹ ፡ ግን ፡
ተረዳድተው ፡ ሶስት ፡ እንስራ ፡ ሙሉ ፡ ወርቅ ፡ እንደጫኑ ፡
ከድኔፐር ፡ ወደብ ፡ ደረሱ ። ነገር ፡ ግን ፡ ታራስ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
ከምንም ፡ አልቆጠረውም ። እንደሚያድን ፡ ሁሉ ፡ መስኩን ፡
አቋርጦ ፡ ሩቅ ፡ ይሄድና ፡ አንድም ፡ ጥይት ፡ ሳይተኩስ ፡ ይመ
ለሳል ። ለአደን ፡ ብሎ ፡ በሚወጣበት ፡ ሰዓት ፡ ጠበንጃውን ፡
መሬት ፡ ላይ ፡ አጋድሞ ፡ በትካዜ ፡ ይጨበጥና ፡ ከባህሩ ፡ ዳር ፡
ተቀምጦ ፤ «ልጄ ፡ ኦስታፕ! ወይ ፡ ልጄ ፤ ኦስታፕ!» እያለ ፡
በመደጋገም ፡ ሲተክዝ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ይጐለታል ። ከፊቱ ፡
ጥቁር ፡ ባህር ፡ ተንጣልሎ ፡ ያንፀባርቃል ። የባህር ፡ አሞሮች ፡
ራቅ ፡ ባሉ ፡ ቄጠማዎች ፡ መካከል ፡ ይጯጯሃሉ ። የታራስ ፡



ነጭ ፡ ጢም ፡ እንደ ፡ ብር ፡ ይብለጨለጫል ። እንባውም ፡ ከዓ
ይኖቹ ፡ እየተንኳለለ ፡ ይወርዳል ።

ወደ ፡ ኋላ ፡ ታራስ ፡ ይህንን ፡ መሪር ፡ ሃዘንና ፡ ትካዜ ፡
በፍጹም ፡ አልቻለውም ።

«የሆነው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ሄጄ ፡ የደረሰበትን ፡ ሁናቴ ፡
ማወቅ ፡ አለብኝ ። በሕይወት ፡ አለ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ መቃብ
ር ፡ ውስጥ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ሞቶ ፡ ቀባሪ ፡ አጥቶ ፡ ወድቆ ፡
ይሆን? የመጣው ፡ ይምጣ ፡ እንጂ ፡ ሄጄ ፡ ማወቅ ፡ አለብኝ!»
አለና ፡ አሰበ ።

ወዲያው ፡ በአንድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ሙሉ ፡ የዘመቻ ፡
ትጥቁን ፡ ታጥቆና ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ዑማን ፡ ደረሰ ። እዚያ
ም ፡ እንደደረሰ ፡ መስኮቶቹ ፡ በጢስ ፡ ጠቁረው ፤ ጣራውም ፡
ተቀዳድዶ ፡ የወፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ወደሆነ ፡ ቆሻሻ ፡ ጐጆ ፡ አመ
ራ ። ከጐጆው ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ጥራጊና ፡ ቆሻሻ ፡ ተከምሯል ።
ከመስኮቶቹ ፡ በአንዱ ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ ቀለማቸው ፡ በተበላሸ ፡
ሉሎች ፡ ያጌጠ ፡ ሻሽ ፡ ያሰረች ፡ አይሁዳዊት ፡ ራስ ፡ ብቅ ፡ አለ ።

ታራስ ፡ ከፈረሱ ፡ ወረደና ፡ የልጓሙን ፡ ጠፍር ፡ ከበሩ ፡
በተሰካ ፡ ቆልማማ ፡ ብረት ፡ ላይ ፡ እያሠረ ፤ «ባልሽ ፡ አለ?»
አለና ፡ ጠየቀ ።

«እቤት ፡ ነው ፡» አለችና ፡ አይሁዷ ፡ በፍጥነት ፡ ለፈ
ረሱ ፡ በቆና ፡ ስንዴ ፤ ለመኮንኑም ፡ አንድ ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡
ይዛ ፡ ቀረበች ።

«ታዲያስ ፤ አይሁድሽ ፡ የት ፡ ነው?» አላት ፡ ታራስ ።

«በወዲያኛው ፡ ክፍል ፡ ጸሎት ፡ ያደርሳል ፡» አለችና ፡
ቡልባ ፡ ጠላውን ፡ ሲጠጣ ፤ አይሁዷ ፡ ሰላምታ ፡ በማቅረብና ፡
መልካም ፡ ጤና ፡ በመመኘት ፡ በትህትና ፡ ትሽቆጠቆጥ ፡ ጀ
መር ።

«እዚህ ፡ ቆይና ፡ ለፈረሴ ፡ እህልና ፡ ውሃ ፡ ስጭው ። እኔ ፡
ከባልሽ ፡ ጋር ፡ ጉዳይ ፡ ስላለኝ ፡ ገብቼ ፡ ለብቻው ፡ አነጋግረ
ዋለሁ ፡» አለና ፡ ታራስ ፡ ገባ ።

አይሁዱ ፤ ያንኬል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይደለም ። በዚያ ፡ ሥፍራ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ አበዳሪና ፡ ባለ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ተደለድሎ ፤ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የአካባቢውን ፡ መኳንንትና ፡ ሎሌዎቻቸውን ፡ በእጁ ፡ አግብቶ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ይመጠምጣል ። በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አይሁዳዊ ፡ ተግባሩ ፡ በዚያ ፡ ቀበሌ ፡ ሥር ፡ ሰድዷል ። በዚያ ፡ ቀበሌ ፡ በሶስት ፡ ማይል ፡ ዙሪያ ፡ ቢፈለግ ፡ አንድም ፡ ቅጥ ፡ ያለው ፡ ጐጆ ፡ አይገኝም ። ቤቱ ፡ ሁሉ ፡ አርጅቶ ፡ በመፍረስ ፡ ላይ ፡ ነው ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ በመጠጥ ፡ እየባከነ ፤ ከድህነትና ፡ ከቡትቶ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልተረፈም ። በጠቅላላው ፡ ቀበሌው ፡ የዘመቻ ፡ ወይም ፡ የበሽታ ፡ ወረራ ፡ ያጠቃው ፡ ይመስላል ። ያንኬል ፡ በዚያ ፡ ሥፍራ ፡ ተጨማሪ ፡ አሥር ፡ ዓመታት ፡ ቢቆይ ፡ ምናልባት ፡ መላውን ፡ የመስፍኑን ፡ ግዛት ፡ እንደዚያ ፡ ባራቆተው ፡ ነበር ።

ታራስ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። አይሁዱ ፡ ራሱን ፡ በአደፈ ፡ ጨርቅ ፡ ተከናንቦ ፡ ይፀልያል ። በሃይማኖቱ ፡ መሠረት ፡ ሲፀልይ ፡ ምራቁን ፡ መትፋት ፡ ስላለበት ፡ ለመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ለመትፋት ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡ ከኋላው ፡ የቆመውን ፡ ቡልባን ፡ አየ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባን ፡ ለሚይዝ ፡ ሰው ፡ የተዳረገው ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ብልጭ ፡ አለበት ። ግን ፡ ለሃብት ፡ በመጓጓቱ ፡ ሃፍረት ፡ ተሰማውና ፡ በአይሁድ ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ዘወትር ፡ እንደ ፡ ትል ፡ የሚርመሰመሰውን ፡ የወርቅ ፡ ፍላጐት ፡ ከሃሳቡ ፡ ለማጥፋት ፡ አጥብቆ ፡ ሞከረ ።

አይሁዱ ፡ ወዲያው ፡ እጅ ፡ እየነሳ ፤ አብረው ፡ እንዳይታዩም ፡ በጥንቃቄ ፡ በሩን ፡ ሲቆልፍ ፡ ታራስ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ «ያንኬል! ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሕይወትህን ፡ አድኛታለሁ ። እኔ ፡ ባላድንህ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ቆራርጠው ፡ ይጥሉህ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ያንተ ፡ ተራ ፡ ነው ። አንድ ፡ የምትረዳኝ ፡ ነገር ፡ አለ ።»



«የምን ፡ እርዳታ? የምችለው ፡ ነገር ፡ ከሆነ ፡ ለምን ፡ አልረዳዎትም?»

«በንግግር ፡ ጊዜ ፡ አታጥፋ ። ቶሎ ፡ ወደ ፡ ዋርሶ ፡ ውሰደኝ ።»

ያንኬል ፡ በመደነቅ ፡ ቅንድቦቹን ፡ ሸብሸቦ ፤ «ወደ ፡ ዋርሶ! እንዴት ፡ ወደ ፡ ዋርሶ?» አለ ።

«በወሬ ፡ ጊዜ ፡ አታጥፋ ፡ ነው ፡ የምልህ ። ወደ ፡ ዋርሶ ፡ ውሰደኝ ። የመጣው ፡ ይምጣ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳየውና ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ሳናግረው ፡ እፈልጋለሁ ።»

«ለማን ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ ቃል?»

«ለእሱ ፤ ለኦስታፕ ፤ ለልጄ!»

«እንዴት? ጌታዬ ፡ አያውቁም ፡ እንዴ ፡...»

«ሁሉንም ፡ አውቃለሁ ። እኔን ፡ ይዞ ፡ ለሚያቀርብ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ዳርገዋል ። የነፍሴን ፡ ዋጋ ፡ ያውቁታል ፤ እኒህ ፡ አህዮች! እኔ ፡ ለአንተ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ እሰጥሃለሁ ። አሁን ፡ ሁለቱ ፡ ሺ ፡ ይኸውልህ ፤ የቀረውን ፡ ስመለስ ፡» አለና ፡ ቡልባ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ከቆዳ ፡ ከረጢት ፡ ዘረገፈለት ።

አይሁዱ ፡ ወዲያው ፡ ፎጣ ፡ አመጣና ፡ ገንዘቡን ፡ ሸፈነው ። ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ዱካት ፡ አንስቶ ፡ በጣቱም ፡ በጥርሱም ፡ እየመረመረ ፡ ያደንቅ ፡ ጀመር ።

«አቤት ፡ እንዴት ፡ የሚያምሩ ፡ ሳንቲሞች! አቤት ፡ የወርቁ ፡ ማማር! ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ወርቅ ፡ የዘረፉት ፡ ሰው ፡ ይብላኝለት ! መቸም ፡ ይህን ፡ መሳይ ፡ የሚያምር ፡ ዱካት ፡ ተዘርፎ ፡ ባህር ፡ ገብቶ ፡ ራሱን ፡ ይገድላል ፡ እንጂ ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ እንኳን ፡ በሕይወት ፡ እንዳልቆየ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።»

«አንተንም ፡ ሳልጠይቅ ፡ እኔው ፡ ብቻዬን ፡ ወደ ፡ ዋርሶ ፡ በሄድሁ ፡ ነበር ። ግን ፡ መደበቅና ፡ ማታለል ፡ ስለማይሆንልኝ ፡ እነዚያ ፡ የተረገሙ ፡ ፖሊሾች ፡ ያውቁኝና ፡ ሊይዙኝ ፡

ይችላሉ ። እናንት ፡ አይሁዶች ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ በተለይ ፡ የተፈጠራችሁ ፡ ናችሁ ። ዘዴውን ፡ ሁሉ ፡ ታውቃላችሁ ። ሰይጣንን ፡ ራሱን ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ማታለል ፡ አያቅታችሁም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ወዳንተ ፡ የመጣሁ ። ወዲህም ፡ ደግሞ ፡ በዋርሶ ፡ ብቻዬን ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ልሠራ ፡ አልችልም ። በል ፡ አሁን ፡ ጋሪህን ፡ ጫንና ፡ እዚያ ፡ አድርሰኝ!»

«ለመሆኑ ፡ ጌታዬ ፡ እንደሚያስቡት ፡ እንዲያው ፡ ተነስቼ ፡ ባዝራዬን ፡ ጭኜ ፤ ሂጅ ፡ ግራጭ ! በማለት ፡ ብቻ ፡ የምንደርስ ፡ ይመስለዎታል? ጌታዬን ፡ ሳልሸሽግ ፡ እንዲህ ፡ እንዳሉ ፡ በግልጽ ፡ የምወስደዎት ፡ ይመስለዎታል?»

«በላ ፡ ሸሽገኝ ። እንደፈለግህ ፡ አድርገህ ፡ ሸሽገኝ! እንዲያውም ፡ ምናልባት ፡ በባዶ ፡ በርሚል ፡ ብትከትተኝ ፡ ይሻላል ።»

«ውይ! ውይ! ለመሆኑ ፡ ጌታዬ ፡ በበርሚል ፡ ውስጥ ፡ ለመደበቅ ፡ የሚችሉ ፡ ይመስለዎታል? ለሚያይ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በበርሚሉ ፡ ውስጥ ፡ ቮድካ ፡ ያለ ፡ እንደሚመስል ፡ ጌታዬ ፡ አያውቁምን?»

«ታዲያ ፡ ይምሰላቸዋ ።»

«እንዴት! ቮድካ ፡ ይምሰላቸው ?» አለና ፡ አይሁዱ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ጆሮ ፡ ግንዱ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ጸጉሩን ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አነሳው ።

«ምነው ፤ ምን ፡ አስደነገጠህ?» አለው ፡ ቡልባ ።

«ቮድካን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠጣው ፡ መሆኑን ፡ ጌታዬ ፡ እንዴት ፡ አያውቁም? እዚያ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መጠጥ ፡ ይወዳሉ ። ያየ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በርሚሉን ፡ ተከትሎ ፡ ሾንቁሮ ፡ ይሞክርና ፡ ወዲያው ፡ ቮድካ ፡ እንደማይወጣው ፡ ይገነዘባል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ‘አይሁድ ፡ ባዶ ፡ በርሚል ፡ ይዞ ፡ አይሄድም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የተሰወረ ፡ ተንኮል ፡ አይጠፋም! አይሁዱን ፡ ያዙት! አይሁዱን ፡ እሠሩት! ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ተረከቡት! አይሁዱን ፡ ወዲያ ፡



ወህኒ ፡ ቤት ፡ ውሰዱት!’ ይባላል ። ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ ቢሠራ ፡ የሚወነጀለው ፡ አይሁዱ ፡ ነው ። አይሁድን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ነው ፡ የሚገምተው ። አይሁድ ፡ ከሆነ ፡ የሰው ፡ ፍጡር ፡ እንኳን ፡ አይመስላቸውም ።»

«በል ፡ እንግዲያው ፡ አሣ ፡ በተጫነ ፡ ጋሪ ፡ ውስጥ ፡ ደብቀኝ ።»

«አይቻልም ፡ ጌታዬ ። በመላው ፡ የፖላንድ ፡ ምድር ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ተርቧል ። አሣውን ፡ ሁሉ ፡ ይሰርቁና ፡ እርስዎን ፡ ያገኙዎታል ።»

«እንግዲህ ፡ ከፈለግህ ፤ በሰይጣን ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ቢሆንም ፡ አስቀምጠኝ ። ብቻ ፡ እዚያ ፡ ልድረስ!»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አይሁዱ ፡ እጅጌውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየሰበሰበ ፡ ክንዶቹን ፡ ዘርግቶ ፡ ወደ ፡ ታራስ ፡ ቀረበና ፡ «ይስሙኝ! ይስሙኝ ፡ ጌታዬ! ዘዴው ፡ ይኸውልዎት ። የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሕንፃና ፡ የጦር ፡ ምሽግ ፡ አሁን ፡ በየሥፍራው ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ነው ። የፈረንሳይ ፡ መሃንዲሶች ፡ ስለመጡ ፡ በየመንገዱ ፡ ብዙ ፡ ድንጋይና ፡ ሸክላ ፡ ይጓዛል ። ጌታዬ ፡ በጋሪው ፡ ላይ ፡ ይጋደሙና ፡ በላይዎ ፡ ላይ ፡ ሸክላ ፡ እደረድርብዎታለሁ ። ጌታዬ ፡ ጤናማና ፡ ጠንካራ ፡ ይመስላሉ ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ትንሽ ፡ ከበድ ፡ ቢል ፡ ለጉዳት ፡ አይሰጠዎም ። ደግሞ ፡ ከሥር ፡ በኩል ፡ ጌታዬን ፡ ለመመገብ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጃለሁ ፡» አለ ።

ታራስም ፤ «ብቻ ፡ እዚያ ፡ አድርሰኝ ፡ እንጂ ፤ የፈለግኸውን ፡ አድርግ!» አለና ፡ ተስማማ ።

አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቆይቶ ፤ ሸክላ ፡ የተጫነ ፡ አንድ ፡ ጋሪ ፡ በሁለት ፡ አጋሰሶች ፡ እየተሳበ ፡ ከዑማን ፡ ወጣ ። ከአጋሰሶቹ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ረጅሙ ፡ ያንኬል ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ያለ ፡ የቬርስታ ፡ ምልክት ፡ መስሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ጌኛው ፡ ፈረስ ፡ ሲያንገጫግጨው ፡ ከአይሁድ ፡ ቆቡ ፡ ዘልቆ ፡ በጆሮ ፡ ግንዱ ፡ የወረደው ፡ ጸጉሩ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይወዛወዛል ።

## ምዕራፍ ፡ አሥራ ፡ አንድ ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ አሁኑ ፡ የነጋዴዎች ፡ ሥቃይ ፡ የሆኑት ፡ የቀረጥ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ፈታሾች ፡ ስላልነበሩ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የፈለገውን ፡ ነገር ፡ ጭኖ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ሰው ፡ መንገደኛውን ፡ አቁሞ ፡ የፈተሸ ፡ እንደሆንም ፤ ለገዛ ፡ ጥቅሙ ፡ ሲል ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ በተለይ ፡ የተጫነው ፡ ዕቃ ፡ ዓይኑን ፡ የማረከው ፡ እንደሆንና ፡ ሰውየው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሥልጣን ፡ መብት ፡ የኖረው ፡ እንደሆን ፡ ነው ። ሸክላዎቹ ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ስለማያጓጉ ፡ ያለችግር ፡ የከተማውን ፡ በር ፡ አልፈው ፡ ገቡ ። ቡልባ ፡ ከተጋደመበት ፡ ጠባብ ፡ የሸክላ ፡ ወጥመድ ፡ ሆኖ ፡ የመንገዱ ፡ ጫጫታና ፡ የጋሪ ፡ ነጂዎች ፡ ጩኸት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሰማው ። ያንኬል ፡ አቧራ ፡ ባለበሰው ፡ አጭር ፡ አጋሰሱ ፤ ላይና ፡ ታች ፡ እየነጠረ ፡ ዱካውን ፡ ለማደናገር ፡ ከተዘዋወረ ፡ በኋላ ፤ በዋርሶ ፡ ያሉት ፡ አይሁዶች ፡ በሞላ ፡ ስለሚኖሩበት ፤ የቆሻሻ ፡ ወይም ፡ የአይሁድ ፡ መንገድ ፡ ወደሚባለው ፡ ጉራንጉርና ፡ ጨለማ ፡ ሠፈር ፡ አጥፍ ፡ አለ ። ይህ ፡ ሠፈር ፡ የተመነቃቀረ ፡ ቆሻሻ ፡ ጓሮ ፡ የሚመስል ፡ ነበር ። የፀሐይ ፡ ብርሃንም ፡ አርፎበት ፡ የሚያውቅ ፡ አይመስልም ። እድሜ ፡ ያጠቆራቸው ፡ የእንጨት ፡ ቤቶችም ፡ የባሰ ፡ አጨልመውታል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በቤቶቹ ፡ መካከል ፡ ከቀይ ፡ ሸክላ ፡ የተሠራ ፡ የግንብ ፡ አጥር ፡ ይታያል ። ግን ፡ እሱም ፡ ከብዙ ፡ ሥፍራ ፡ መጥቆር ፡ ጀምሯል ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የሚያንፀባርቅ ፡ ኖራ ፡ የተቀባ ፡ ግንብ ፡ የሚታይበት ፡ ሥፍራ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሠፈር ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለዓይን ፡ ያስጠላል ። መንደርተኛው ፡ ሁሉ ፡ የማያስፈልገውን ፡ ማናቸውንም ፡ አሮጌና ፡ ቆሻሻ ፡ ነገር ፤ ለአላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ስሜት ፡ ሳያስብ ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ አውጥቶ ፡ ይጥለዋል ። በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚያልፍ ፡ ሰው ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ከአንዱ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ የተጋደሙትን ፡ የልብስ ፡ ማስጫ ፡ አጠናዎች ፡ በእጁ ፡ ሊነካቸው ፡ ይችላል ። ከአጠናዎቹም ፡ ላይ ፡ የአይሁዶች ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ ቁምጣ ፡ ሱሪዎች ፡ ወይም ፡ የደረቀች ፡ ዳክየ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ይታያሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆንጆ ፡ ቢጤ ፡ የሆነች ፡ የአይሁድ ፡ ልጃገረድ ፡ ፊት ፡ ከነጨሌ ፡ጌጧ ፡ ከአንድ ፡ አሮጌ ፡ መስኮት ፡ ብቅ ፡ ትላለች ። ጸጉራቸው ፡ ቁጥርጥር ፡ ያለና ፡ የተራቆቱ ፡ የአይሁድ ፡ ኩታሮችም ፡ እየተንጫጩ ፡ በጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ይንከባለላሉ ። ጠቃጠቆ ፡ ያዝጐረጐረው ፡ ቀይ ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ አይሁድ ፡ በመስኮት ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ በቋንቋው ፡ ያንኬልን ፡ ሲያነጋግረው ፡ ያንኬልም ፡ ወደዚያው ፡ ሰውየ ፡ ግቢ ፡ ጋሪውን ፡ ነድቶ ፡ ገባ ። በመንገዱ ፡ የሚያልፍ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ አይሁድ ፡ ደግሞ ፡ ቆም ፡ አለና ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ጣልቃ ፡ ገብቶ ፡ ያወራ ፡ ጀመር ። በመጨረሻ ፡ ቡልባ ፡ ከሸክላው ፡ ስር ፡ ተንኳትቶ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሶስቱም ፡ አይሁዶች ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ወሬ ፡ ይዘው ፡ ተመለከተ ።

ያንኬል ፡ ወደሱ ፡ ዞረና ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ደህና ፡ መሆኑን ፡ አስታፕም ፡ በከተማው ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዳለና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ዘበኞቹን ፡ ለመደለል ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆን ፡ ሊያገናኘው ፡ እንደሚሞክር ፡ ነገረው ።

ቡልባም ፡ ከሶስቱ ፡ አይሁዶች ፡ ጋር ፡ ወዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ገባ ።

አይሁዶቹ ፡ እንደገና ፡ በቋንቋቸው ፡ ንግግር ፡ ጀመሩ ። ታራስም ፡ ቋንቋው ፡ ስለማይገባው ፡ እነሱን ፡ በተራ ፡ እያስተዋለ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ የጋለ ፡ የተስፋ ፡ ስሜት ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። የሽማግሌ ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ ወጣት ፡ ልብ ፡ በፍጥነት ፡ ይመታ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ባለው ፡ አነጋገር ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤

«ስሙ ፡ አይሁዶች ፡ ሆይ! የውቅያኖስን ፡ መደብ ፡ መቆፈር ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የሚያቅታችሁ ፡ አይደላችሁም ። አንድ ፡ አይሁድ ፡ ከፈለገ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሊሰርቅ ፡ ይችላል ፤ እየተባለ ፡ ሲተረት ፡ ሲነገር ፡ ኖሯል ። ልጄን ፡ አስታጥን ፡ ነፃ ፡ አውጡልኝ ! ከሰይጣኖች ፡ እንዲያመልጥ ፡ እርዱት ። ይህን ፡ ለሚያደርግልኝ ፡ ሰው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ልሰጠው ፡ ቃል ፡ ገብቼ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደገና ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ለመጨመር ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ጸዋዎቼን ፤ የቀበርኩትን ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፤ ቤቴንና ፡ የመጨረሻ ፡ ልብሴ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ እሰጣችኋለሁ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ እድሜዬን ፡ በሙሉ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ከማገኘው ፡ ሃብት ፡ ግማሹን ፡ ልሰጣችሁ ፡ ቃል ፡ እገባለሁ ።»

ያንኬል ፡ ተስፋ ፡ የመቁረጥ ፡ ትካዜ ፡ እየታየበት ፤ «አዬ ፡ የሚቻል ፡ አይደለም!» አለ ።

ሁለተኛውም ፡ አይሁድ ፤ «የለም ፡ የሚቻል ፡ አይደለም!» አለና ፡ ሶስቱም ፡ አይሁዶች ፡ ተያዩ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሶስተኛው ፡ አይሁድ ፤ «ብንሞክርስ? እግዚአብሔር ፡ ይረዳን ፡ ይሆናል ፡» አለ ።

ከዚያ ፡ ሶስቱም ፡ በጀርመንኛ ፡ ይነጋገሩ ፡ ጀመር ። ቡልባ ፡ ምንም ፡ ቢያዳምጥ ፡ ንግግራቸው ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ። የሚሰማው ፡ ደጋግመው ፡ የሚያነሱት ፡ ማርዶሃይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ያንኬል ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ «ይስሙ ፡ ጌታዬ! በዚህ ፡ ዓለም ፡ ወደር ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ አዋቂ ፡ ሰው ፡ አለና ፡ እሱን ፡ ማማከር ፡ አለብን! ልክ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ጠቢብ ፡ ነው ። እሱ ፡ ሊሠራው ፡ ያልቻለውን ፡ ነገር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊሠራው ፡ አይችልም ፡ ስለዚህ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጠው ፡ ይጠብቁን ፤ የቤቱ ፡ ቁልፍ ፡ ይኸውና ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ እንዳያስገቡ ።»



አይሁዶቹ ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ ወጡ ።

ታራስ ፡ በሩን ፡ ቆለፈና ፡ በመስኮቱ ፡ ቆሻሻውን ፡ የአይሁዶች ፡ መንገድ ፡ ያስተውል ፡ ጀመር ። ሶስቱ ፡ አይሁዶች ፡ መንገዱ ፡ መሃል ፡ ቆመው ፡ በችኮላ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ሌላ ፡ አራተኛ ፡ ቀጥሎም ፡ አምስተኛ ፡ አይሁዶች ፡ መጥተው ፡ ከነሱ ፡ ተደባለቁ ። «ማርዶሃይ ፡» የሚለው ፡ ቃል ፡ አሁንም ፡ ሲደጋገም ፡ ታራስ ፡ ሰማ ። አይሁዶቹ ፡ የመንገዱን ፡ አንዱን ፡ አቅጣጫ ፡ እየተገላመጡ ፡ ሲያስተውሉ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ከዚያው ፡ አቅጣጫ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቅ ፡ አለ ። አይሁዶቹም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ «አሃ ፡ ማርዶሃይ! ማርዶሃይ!» እያሉ ፡ ጮኹ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከያንኬል ፡ ትንሽ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ግን ፡ የባሰ ፡ የተጨማደደና ፡ የላይ ፡ ከንፈሩ ፡ አለመጠን ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ አይሁድ ፡ መጥቶ ፡ በመጓጓት ፡ ከሚጠብቁት ፡ ከአምስቱ ፡ አይሁዶች ፡ ጋር ፡ ተደባለቀ ። እነሱም ፡ በጥድፍያ ፡ ጉዳያቸውን ፡ ሲገልጹለት ፡ ማርዶሃይ ፡ ገልመጥ ፡ እያለ ፡ ታራስ ፡ የቆመበትን ፡ ትንሽ ፡ መስኮት ፡ ይመለከት ፡ ስለነበር ፡ ጉዳዩ ፡ ስለራሱ ፡ መሆኑን ፡ ታራስ ፡ ተገነዘበው ። ማርዶሃይ ፡ እጆቹን ፡ እያወዛወዘ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ንግግራቸውን ፡ ሲያቋርጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲያዳምጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎም ፡ ወደጐን ፡ ምራቁን ፡ እየተፋ ፡ እንደቆመ ፡ የአይሁድ ፡ ቀሚሱን ፡ ገለበና ፡ ቆሻሻ ፡ ሱሪው ፡ እየታየ ፡ ከኪሱ ፡ ጌጣጌጥ ፡ ነገር ፡ አወጣ ። በመጨረሻ ፡ አይሁዶቹ ፡ የቆመው ፡ ጠባቂ ፡ ዝም ፡ እንዲሉ ፡ ምልክት ፡ እስኪሰጣቸው ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጫጫታ ፡ ስለጀመሩ ፡ ታራስ ፡ ስጋት ፡ አደረበት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አይሁዶች ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ እንደማይነጋገሩ ፡ ቋንቋአቸውንም ፡ ሰይጣን ፡ ራሱ ፡ እንኳን ፡ ሊረዳው ፡ እንደማይችል ፡ ትዝ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፡ ልቡ ፡ ረጋ ።

አንድ ፡ ሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ አይሁዶቹ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ገቡና ፡ ማርዶሃይ ፡ ወደ ፡ ቡልባ ፡ ቀርቦ ፡ ትከ

ሻውን ፡ መታ ፡ መታ ፡ እያደረገ ፡ «እኛና ፡ እግዚአብሔር ፡ አብረን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ ከተነሳን ፡ ሁልጊዜ ፡ ይሳካልናል ፡» አለው ።

ታራስ ፡ ይህን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ወደር ፡ የሌለውን ፡ የሰሎሞን ፡ ምትክ ፡ ተመለከተና ፡ አዲስ ፡ ተስፋ ፡ አደረበት ። በእውነትም ፡ የዚህ ፡ አይሁድ ፡ መልክ ፡ ሲታይ ፡ የአሰበው ፡ ነገር ፡ እንደሚሳካለት ፡ እምነትና ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ ነበር ። የላይ ፡ ከንፈሩ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ የጢሙ ፡ ጠጉሮችም ፡ በቁጥር ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ የማይበልጡ ፡ ሲሆኑ ፡ እነሱም ፡ የበቀሉት ፡ በግራ ፡ ገጹ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፊቱ ፡ በተንኮል ፡ ተግባሩ ፡ የአገኛቸው ፡ በትሮች ፡ ምልክት ፡ በብዛት ፡ ይታይበታል ። ከብዛታቸውም ፡ የተነሳ ፡ እንደተፈጥሮ ፡ ምልክት ፡ ሳይቆጥራቸው ፡ አይቀርም ።

ማርዶሃይ ፡ ጠቢብነቱን ፡ ከሚያደንቁለት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ወጥቶ ፡ ሄደና ፡ ቡልባ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ። ውጤቱ ፡ ባልታወቀ ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ደርሶበት ፡ የማያውቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመጓጓት ፡ ስሜት ፡ አደረበት ። ልቡም ፡ በመጓጓት ፡ ትኩሳት ፡ ይነድድ ፡ ጀመር ። አሁን ፡ እንደ ፡ ወርካ ፡ ጠንካራና ፡ ልበ ፡ ጽኑው ፡ የቀድሞው ፡ ቡልባ ፡ አልሆነም ። እርብትብትና ፡ ልበ ፡ ደካማ ፡ ሆነ ። ትንሽ ፡ ድምጽ ፡ ሲሰማ ፡ ወይም ፡ በመንገዱ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ አይሁድ ፡ ውልብ ፡ ሲል ፡ ይደነግጥ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ ሳይበላና ፡ ሳይጠጣ ፡ ዓይኖቹንም ፡ ከትንሽዋ ፡ መስኮት ፡ ሳይለይ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ዋለ ። በመጨረሻ ፡ በአመሻሽ ፡ ላይ ፡ ማርዶሃይና ፡ ያንኬል ፡ ብቅ ፡ ሲሉ ፡ ቡልባ ፡ ልቡ ፡ መምታት ፡ ተሳነው ።

«ታዲያስ? ተሳካላችሁ?» አለና ፡ በመጓጓት ፡ ጠየቃቸው ።

ነገር ፡ ግን ፡ አይሁዶቹ ፡ መልስ ፡ ከመስጠታቸውም ፡ በፊት ፡ በማርዶሃይ ፡ ጆሮ ፡ ግንድ ፡ አጠገብ ፡ ተጠቅልሎ ፡



ይታይ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ ጸጉር ፡ አሁን ፡ አለመኖሩን ፡ ቡልባ ፡ ተመለከተ ። ማርዶሃይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ እንዳሰበ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ከመርበትበቱ ፡ የተነሳ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ለቡልባ ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ። ያንኬል ፡ ራሱም ፡ ጉንፋን ፡ እንዳስጨነቀው ፡ ሰው ፡ አፉን ፡ በእጁ ፡ እያፈነ ፡ ይቅበጠበጥ ፡ ጀመር ።

በመጨረሻ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«አዬ ፡ የኔ ፡ ጌታ! የሚሆን ፡ አይደለም! እግዚአብሔር ፡ ይመስክር ፡ በፍጹም ፡ አይደለም! ሰዎቹ ፡ በጣም ፡ መጥፎ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ማርዶሃይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከሚችለው ፡ በላይ ፡ ጥሮ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ሃሳባችን ፡ እንዲከናወን ፡ አምላክ ፡ አልፈቀደም ። ሶስት ፡ ሺ ፡ ወታደሮች ፡ እዚህ ፡ ሰፍረዋል ፤ እስረኞቹም ፡ ነገ ፡ ሊገደሉ ፡ ነው ።»

ታራስ ፡ የአይሁዶቹን ፡ ዓይን ፡ ዓይናቸውን ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ ። ግን ፡ እንደቀድሞው ፡ በመጓጓት ፡ ወይም ፡ በቁጣ ፡ ስሜት ፡ አይደለም ።

ያንኬል ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፤ «ጌታዬ ፡ ሊያዩት ፡ ቢፈቅዱ ፡ ነገ ፡ በጠዋት ፡ ጀንበር ፡ ሳትወጣ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ዘበኞቹ ፡ ተስማምተው ፡ ከአለቆቹ ፡ አንዱም ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶናል ። ብቻ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ ያሳጣቸውና ፡ እንዴት ፡ ገብጋባ ፡ ፍጥረቶች ፡ ናቸው! ከኛ ፡ ከማናችንም ፡ እንኳን ፡ የባሱ ፡ ስስታሞች ፡ ናቸው! ለያንዳንዳቸው ፡ አምሳ ፡ ዱካት ፡ ሰጥቼ ፡ ለአለቅየው ፡ ደግሞ ፡...» ሲል ፡ ታራስ ፡ እንደቀድሞው ፡ ጽኑና ፡ ቆረጥ ፡ በሆነው ፡ አነጋገሩ ፤ «መልካም ፤ በሉ ፡ ውሰዱኝ!» አላቸው ።

ታራስ ፡ ከጀርመን ፡ አገር ፡ የመጣ ፡ መኮንን ፡ በመምሰል ፡ ሳይታወቅ ፡ እንዲያልፍ ፡ ያንኬል ፡ ባቀረበው ፡ አሳብ ፡ ተስማማ ። አርቆ ፡ አስተዋዩ ፡ አይሁድም ፡ ነገሩን ፡ አስቀድሞ ፡ አስቦበት ፡ ኖሮ ፡ አስፈላጊውን ፡ ልብስ ፡ አዘጋጅቷል ።

ጊዜው ፡ ጨልሞአል ። የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ጸጉረ ፡ ቀዩ ፡
አይሁድ ፡ አንድ ፡ ስስ ፡ ፍራሽ ፡ አመጣና ፡ በአንድ ፡ አግዳ
ሚ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ዳውጃ ፡ አልብሶ ፡ ለታራስ ፡ አነጠፈለት ።
ያንኬል ፡ እንደዚያው ፡ ባለ ፡ ፍራሽ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተጋደ
መ ። ጸጉረ ፡ ቀዩ ፡ አይሁድ ፡ በአንድ ፡ ትንሽ ፡ መለኪያ ፡ አንድ ፡
ነገር ፡ ጠጣና ፡ ኮቱን ፡ አውልቆ ፡ ቁም ፡ ሳጥን ፡ በሚመስ
ል ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ገባ ። በዚያ ፡ ቁም ፡ ሳ
ጥን ፡ አጠገብ ፡ ሁለት ፡ ሕፃናት ፡ የውሻ ፡ ቡችላ ፡ መስለው ፡
ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተጋድመዋል ። ታራስ ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ አልተ
ኛም ፤ ሳይንቀሳቀስ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በጣቶቹ ፡ ጠረጴዛውን ፡
በመቆርቆር ፡ እየተከዘ ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻውን ፡ ከአፉ ፡
ሳይለይ ፡ ያጤስ ፡ ጀመር ። ያንኬል ፡ ጢሱ ፡ እየከነከነው ፡ በእ
ንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ እያነጠሰ ፡ አፍንጫውን ፡ በብርድ ፡ ልብሱ ፡
ሸፈነ ። የጐህ ፡ ብርሃን ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ገና ፡ ፍንጥቅ ፡ ከማ
ለቱ ፡ ታራስ ፡ ያንኬልን ፡ በእግሩ ፡ ጐሽም ፡ አደረገውና ፤
«ተነሳ ፡ አይሁድ ፤ የጀርመን ፡ መኳንንት ፡ ልብስ ፡ ያልከ
ውን ፡ ስጠኝ!» አለው ።

በአንድ ፡ አፍታ ፡ ልብሱን ፡ ለበሰ ፤ ጢሙንና ፡ ቅንድ
ቡን ፡ በቀለም ፡ አጥቁሮ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጠቆር ፡ ያለች ፡ ትን
ሽ ፡ ቆብ ፡ አደረገ ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ በደንብ ፡ የሚያውቁት ፡
ኮዛኮች ፡ እንኳን ፡ ሊለዩት ፡ ባልቻሉም ፡ ነበር ። እድሜው ፡
ከሠላሳ ፡ አምስት ፡ የማይበልጥ ፡ መሰለ ። የጤናማነት ፡ መልክ ፡
በጉንጮቹ ፡ ላይ ፡ ያበራ ፡ ጀመር ። በፊቱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የጦር ፡
ሜዳ ፡ ቁስሉ ፡ ጠባሳም ፡ የበለጠ ፡ ግርማ ፡ ሰጠው ። በወርቅ ፡
ያጌጠው ፡ ልብስ ፡ በእውቅ ፡ እንደተሰፋ ፡ ሁሉ ፡ ልክ ፡ ሆኖ ፡
ተስማማው ።

መንገዶቹ ፡ ገና ፡ ከእንቅልፍ ፡ አልነቁም ። ቅርጫት ፡
የታቀፈ ፡ ገበያተኛ ፡ ፍጥረት ፡ በከተማው ፡ ገና ፡ ብቅ ፡ አላለ
ም ። ቡልባና ፡ ያንኬል ፡ የትቀመጠ ፡ እርኩም ፡ ከሚመስል ፡
አንድ ፡ ቤት ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጥቁርና ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ በአ



ንዱ ፡ ገጽ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ እርኩም ፡ አንገት ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡
የወጣ ፡ የዘበኛ ፡ መቆሚያ ፡ ደርብ ፡ አለ ። ይህ ፡ ቤት ፡ ለብዙ ፡
ተግባር ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ። በውስጡ ፡ የወታደር ፡ ሰፈር
ና ፡ የወህኒ ፡ ቤት ፡ ሲኖረው ፡ እንዲሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይገ
ኝበታል ። እነቡልባ ፡ በሩን ፡ አልፈው ፡ ሲገቡ ፡ ሰፊ ፡ አዳ
ራሽ ፡ አገኙ ። በዚያም ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ተኝቶ
አል ። ፊት ፡ ለፊታቸው ፡ አንድ ፡ አጭር ፡ በር ፡ አለ ። በበሩ
ም ፡ አጠገብ ፡ ሁለት ፡ ዘበኞች ፡ ተቀምጠው ፡ አንዱ ፡ የአን
ዱን ፡ እጅ ፡ በሁለት ፡ ጣት ፡ በመምታት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡
ጨዋታ ፡ ይጫወታሉ ። ዘበኞቹ ፡ የእንግዶቹን ፡ መምጣት ፡
ከምንም ፡ ሳይቆጥሩት ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ ሲጫወቱ ፡ ያንኬል ፤
«እኛ ፡ ነን ፤ ሰማችሁኝ ፡ ጌቶቼ? እኛ ፡ ነን ፡» ባለ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡
ዞወር ፡ አሉ ።

ከዚያ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ አንድ ፡ እጁን ፡ ጓደኛው ፡ እን
ዲመታው ፡ እንደዘረጋለት ፡ በሌላው ፡ እጁ ፡ እያመለከተ ፤
«ግቡ!» አላቸው ።

ገብተውም ፡ በጠባብ ፡ መተላለፊያ ፡ ሄደው ፡ እንደ ፡
መጀመሪያው ፡ ካለ ፡ አዳራሽ ፡ ደረሱ ።

ወዲያው ፤ «ቁም ፡ ማነህ? ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ እንዳ
ያልፍ ፡ ክልክል ፡ ነው!» የሚል ፡ የብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ድምጽ ፡
ሰሙ ።

«እኛ ፡ ነን ፤ እኛ ፡ ነን ፡ የተከበራችሁ ፡ ጌቶቼ!» አለ ፡
ያንኬል ፡ ግን ፡ ማንም ፡ አላዳመጠውም ። እንደ ፡ እድል ፡
ሆኖ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ በአለባበሱ ፡ አለቃ ፡ የሚመስል ፡ አንድ ፡
ወፍራም ፡ ሰውዬ ፡ ገባ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ያንኬል ፤ «ጌታዬ ፡ እኛ ፡ ነን! የሚያው
ቁን ፡ ነን ፡ እኒህ ፡ መኮንንም ፡ በድጋሚ ፡ ለእርስዎ ፡ ምስጋ
ና ፡ ያቀርባሉ ፡» አለ ።

አለቅየው ፡ «ተዋቸው ፡ ይለፉ ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እን

ዳታስገቡ! ጕራዴያችሁን ፡ ሳትፈቱ ፡ እንደውሻ ፡ ተጋድማችሁ ፡ ጠብቁ ፡»አለ ።

ከዚያ ፡ ያንኬል ፤ «እኛ ፡ ነን ፡ …እኔ ፡ ነኝ ፡ …ወዳጆች ፡ ነን!» እያለ ፡ ላገኘው ፡ ሁሉ ፡ እየለፈለፈ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ካለው ፡ በር ፡ ሲደርሱ ፤ «አሁን ፡ ልንገባ ፡ እንችላለን?» አለና ፡ አንዱን ፡ ዘበኛ ፡ ጠየቀው ።

«አዎ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ያሳልፏችሁ ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም ፤ ያን ፡ ተለውጦ ፡ አሁን ፡ በሱ ፡ ስፍራ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ያለው ፡» ሲል ፡ አይሁዱ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፤ «ወይኔ ፡ ወይኔ! ይህ ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ጌታዬ!» አለ ።

ታራስ ፡ ግን ፤ «በል ፡ ሂድ ፡ እለፍ!» አለውና ፡ ያንኬል ፡ በታዛዥነት ፡ ቀድሞ ፡ ተጓዘ ። በወህኒ ፡ ቤቱ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ባለሶስት ፡ ደረጃ ፡ ጢም ፡ ያለው ፡ ወታደር ፡ ቆሞአል ። የጢሙ ፡ የላይኛው ፡ ደረጃ ፡ ወደኋላ ፡ ተጠምዞአል ። ሁለተኛውም ፡ ወደፊት ፡ ሾሎ ፤ ሶስተኛው ፡ ደግሞ ፡ ወደታች ፡ ስለተንጠለጠለ ፡ ቁርጥ ፡ ድመት ፡ አስመስሎታል ።

አይሁዱ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ጀርባውን ፡ አጕበጠና ፡ እየተሽቆጠቆጠ ፡ ወደሱ ፡ ቀረበ ።

«ክቡር ፡ ሆይ! እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ጌታዬ!»

«እኔን ፡ ነው ፡ የምታነጋግረው ፡ አይሁድ?»

«አዎ ፡ እርስዎን ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ መኮንኔ!»

ባለሶስት ፡ ደረጃ ፡ ጢማሙ ፡ ሰውየም ፡ ዓይኖቹ ፡ በደስታ ፡ እያበሩ ፤ «ወይጉድ ፡ ታድያ ፡ እኔኮ ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ ነኝ!» አለው ።

አይሁዱ ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀና ፡ እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡ «ኧረግ ፡ በፈጣሪ ፡ …ወየወዱ ፡ ራሳቸው ፡ መስለውኝ ፡ ነበር! ይገርማል ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ግርማ ፡ አላቸው ! ፈጣሪዬ ፡ ይመስክር ፡ ልክ ፡ ኮሎኔል ፡ ይመስላሉ! እንደኔ ፡ ቢሆን ፡ ጌታዬ ፡ እርስዎን ፡ እንደዝንብ ፡ በሚበር ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ አስቀምጦ ፡ የአንድ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ማድረግ ፡ ነበር!» አለ ።



በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ የታችኛውን ፡ ደረጃ ፡ ጢሙን ፡ እየዳሰሰ ፡ ዓይኖቹ ፡ የደስታ ፡ ብርሃን ፡ ተጐናጸፉ ።

አይሁዱም ፡ ውዳሴውን ፡ ቀጠለ ።

«ወታደሮች ፡ እንዴት ፡ ግሩም ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ልብሳቸው ፡ እንደ ፡ ጸሐይ ፡ ያንጸባርቃል ፤ በየትም ፡ ስፍራ ፡ ያሉ ፡ ቆነጃጅት ፡ ሴቶች ፡ ወታደር ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አቤት ፡ የሚሆኑት ፡ መሆን!»

ወታደሩ ፡ የላይኛውን ፡ ደረጃ ፡ ጢሙን ፡ ጠመዘዘና ፡ እንደሚያስካካ ፡ ፈረስ ፡ በጥርሶቹ ፡ መሃል ፡ አፏጨ ።

አይሁዱም ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፤ «አንድ ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርጉልን ፡ ጌታዬን ፡ እለምናለሁ ። እነሆ ፡ እኒህ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ ልዑል ፤ ኮዛኮቹን ፡ ለማየት ፡ ይፈልጋሉ ። ኮዛኮች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደሆኑ ፡ በሕይወታቸው ፡ አይተው ፡ አያውቁም ፡» አለ ።

የውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ልዑላንና ፡ መኳንንት ፡ ወደ ፡ ፖላንድ ፡ መምጣታቸው ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። እስያ ፡ ቀመስ ፡ የሆነውን ፡ ይህን ፡ የአውሮፓ ፡ ዳርቻ ፡ ለማየት ፡ ሲሉ ፡ ብቻ ፡ ዘወትር ፡ ይመጣሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሞስኮቪንና ፡ ኡክሬይንን ፡ እንደ ፡ እስያ ፡ ክፍል ፡ ነበር ፡ የሚቆጥሩት ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ በመገንዘብ ፡ ወታደሩ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሳና ፡ በበኩሉ ፡ ትንሽ ፡ ቃላት ፡ ለመናገር ፡ አሰበ ።

«ክቡርነትዎ ፡ እነሱን ፡ ለማየት ፡ ለምን ፡ እንደፈለጉ ፡ በእውነቱ ፡ አላውቅም ። እነሱ ፡ ውሾች ፡ እንጂ ፡ ሰዎች ፡ አይደሉም ። ሃይማኖታቸውም ፡ የረከሰ ፡ ነው ፡» አለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባ ፤ «ሃሰት ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! አንተ ፡ ራስህ ፡ ነህ ፡ ውሻ ፤ ሃይማኖታችንን ፡ የረከሰ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ ደፈርህ ? የእናንተው ፡ የከሃዲዎች ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ እርኩስ ፡ » አለ ።

ወታደሩም ፤ «አሃ! ማን ፡ እንደሆንክ ፡ አወቅሁህ ፡ ወዳጄ ፤ አንተም ፡ ራስህ ፡ እዚህ ፡ ከምጠብቃቸው ፡ አንዱ ፡ ነህ ፡

ለካ ! ቆይ ፡ አሁን ፡ ወታደሮቻችንን ፡ ስጠራ ፡ ታያለህ!» አለ ።

ታራስ ፡ ጥፋቱን ፡ ተገነዘበ ፡ ግን ፡ ከሆነ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አልቻለም ። ሆኖም ፡ ያንኬል ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ በዘዴ ፡ አዳነው ።

«እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ጌታዬ! አንድ ፡ ልዑል ፡ እንዴት ፡ ኮዛክ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል? ኮዛክ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብስና ፡ የልዑላን ፡ መለዮ ፡ ከየት ፡ ያመጡ ፡ ነበር?»

«በቃ ፡ ውሸት ፡ አልፈልግም!» አለና ፡ ወታደሩ ፡ ለመጮኽ ፡ አፉን፡ ከፈተ ።

«ግርማዊ ፡ ሆይ! ዝም ፡ ይበሉ! ዝም ፡ ይበሉ! ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው! ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቀውን ፡ ያህል ፡ ውለታዎን ፡ እንከፍለዎታለን ። ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ዱካት ፡ እንሰጥዎታለን ።»

«አሃ! ሁለት ፡ ዱካት! ሁለት ፡ ዱካት ፡ ለኔ ፡ ምንም ፡ አይደል ። ጸጉር ፡ ቆራጭ ፡ የጢሜን ፡ ግማሽ ፡ ሲላጩኝ ፡ ሁለት ፡ ዱካት ፡ ነው ፡ የምከፍለው ። በል ፡ አሁን ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ ስጠኝ ፡ አይሁድ ፤ አለዚያ ፡ አሁን ፡ መጮኼ ፡ ነው!» አለ ።

«አሁን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ምን ፡ አስጠየቀው!» ብሎ ፡ በሃዘን ፡ ፊቱ ፡ ጠውልጐ ፡ የቆዳ ፡ ከረጢቱን ፡ ከወገቡ ፡ ፈታና ፡ ሲመለከት ፡ በውስጡ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ገንዘብ ፡ አለመኖሩን ፡ ወታደሩም ፡ ከመቶ ፡ በላይ ፡ ቁጥር ፡ አለመቻሉን ፡ ተገንዝቦ ፡ ወዲያው ፡ ደስ ፡ አለው ።

ወታደሩ ፡ የበለጠ ፡ ባለመጠየቁ ፡ እንደመጸጸት ፡ ብሎ ፡ ገንዘቡን ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ ሲያገላብጥ ፡ ተመለከተና ፡ ያንኬል ፡ ወደ ፡ ቡልባ ፡ ዞሮ ፤ «ጌታዬ ፡ ቶሎ ፡ እንሂድ! እንዳዩት ፡ እዚህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ክፉዎች ፡ ናቸው ፡» አለው ።

ቡልባ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ወታደሩ ፡ ዞሮ ፤ «እንዴት ፡ አንት ፡ ሰይጣን! ገንዘቡን ፡ ወስደህ ፡ ደግሞ ፡ ኮዛኮቹን ፡ አላሳይም ፡ ልትል ፡ ነው? የለም ፤ ማሳየት ፡ አለብህ ። ገንዘቡን ፡ ከተቀበልህ ፡ እምቢ ፡ ልትል ፡ አትችልም ፡» አለው ።

ወታደሩም ፤ «ሂዱ ፡ ነው ፡ የምላችሁ! አለዚያ ፡ አሁኑኑ ፡ ሰው ፡ መጥራቴ ፡ ነው!» ሲል ፡ ያንኬል ፤ «ጌታዬ! ጌታዬ! ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ እንሂድ ፤ እነዚህ ፡ የተረገሙ ፡ ሰዎች ፡ የሚያስጠላ ፡ ቅዠት ፡ ይጣልባቸው!» እያለ ፡ ቡልባን ፡ ይለምን ፡ ጀመር ።

ቡልባ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ዞረና ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ተጓዘ ፤ ያንኬልም ፡ በከንቱ ፡ ባባከነው ፡ ዱካት ፡ ተማርሮ ፡ ነበርና ፡ ኋላ ፡ ኋላው ፡ እየተከተለ ፡ በጸጸት ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ፤

«እስቲ ፡ ምን ፡ አስቆጣዎት? ያ ፡ ውሻ ፡ የፈለገውን ፡ ቢናገር ፡ ምን ፡ ችገረዎ ፡ ነበር ። እነሱ ፡ ያለ ፡ ዘለፋ ፡ የማይኖሩ ፡ ፍጥረቶች ፡ ናቸው ። ወይኔ! እንዲህ ፡ ያለ ፡ እድል! እኛኑ ፡ ለማባረር ፡ ብቻ ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ ያስከፍለን! እኛን ፡ ግን ፡ ጸጉራችንን ፡ እየነጩ ፡ ፊታችንም ፡ ለማየት ፡ እስኪያስጠላ ፡ ድረስ ፡ ሲቀጠቅጡን ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ የሚሰጠን ፡ የለም! አይ ፡ ፈጣሪዬ! ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አመጣህብኝ!»

ነገር ፡ ግን ፡ የነገሩ ፡ አለመሳካት ፡ ንዴት ፡ የባሰውን ፡ በቡልባ ፡ ዓይኖች ፡ ላይ ፡ እንደነበልባል ፡ ይንቀለቀል ፡ ጀመር ።

«ና ፡ እንሂድ! ወደ ፡ አደባባይ ፡ ሄደን ፡ እንዴት ፡ እንደሚያሰቃዩት ፡ መመልከት ፡ አለብኝ ፡» አለው ።

ያንኬል ፤ «ምነው ፡ ጌታዬ! ለምን ፡ ለመሄድ ፡ ይፈልጋሉ? አሁን ፡ ልንረዳው ፡ አንችልም ፡» ሲል ፡ ቡልባ ፡ ግን ፡ «መሄድ ፡ አለብን!» በማለት ፡ ክርር ፡ አለ ።

አይሁዱም ፡ እንደሞግዚት ፡ በትካዜ ፡ ቁና ፡ ተነፈሰና ፡ ይከተል ፡ ጀመር ።

የመገደያውን ፡ አደባባይ ፡ ለማግኘት ፡ የሚያዳግት ፡ አልነበረም ። ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦበት ፡ ይታያል ። በዚያ ፡ የጭካኔ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ትርኢት ፡ ለተራው ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለከፍተኞች ፡ ሰዎችም ፡ አስደሳች ፡

ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ነበር ። እጅግ ፡ ሃይማኖተኛ ፡ ባልቴቶች፡ እንዲሁም ፡ ፈሪ ፡ ልጃገረዶች ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ከማየት ፡ አይቦዝኑም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከአዩት ፡ በኋላ ፡ በደም ፡ የተጨማለቀ ፡ ሬሣ ፡ በሕልማቸው ፡ እየመጣ ፡ በቅዠት ፡ ቢያስጮኻቸውም ፡ እድል ፡ ካጋጠማቸው ፡ ዳግመኛ ፡ ለማየት ፡ አይታክቱም ። ብዙዎቹ ፤ «አቤት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጭካኔ!» ብለው ፡ እየጮኹ ፡ ዓይናቸውን ፡ ጨፍነው ፡ ፊታቸውንም ፡ ያዞራሉ ። ሆኖም ፡ አገዳደሉን ፡ እስከመጨረሻው ፡ ሳይመለከቱ ፡ አይመለሱም ። አንዳንዶቹም ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተውና ፡ እጆቻቸውም ፡ ዘርግተው ፡ አገዳደሉን ፡ ለመመልከት ፡ ሲንገበገቡ ፡ ይታያሉ ። ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ለመመልከትም ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተራምደው ፡ በማለፍ ፡ በወደዱ ፡ ነበር ።

እዚያ ፡ ከተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ጠባብና ፡ ትንንሽ ፡ ጭንቅላት ፡ መካከል ፡ የአንድ ፡ ሥጋ ፡ አራጅ ፡ ወፍራም ፡ ፊት ፡ ይታያል ። እሱም ፡ እዚያ ፡ ቆሞ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ በአዋቂነት ፡ የሚያመዛዝን ፡ መስሎ ፡ እየተመለከተ ፤ በዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በአንድ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ አብሮት ፡ ስለሚሰክር ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡ ከሚለው ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሠሪ ፡ ጋር ፡ ይነጋገራል ። እዚያ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሕዝብ ፡መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ ስለሚያዩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በማላገጥና ፡ በክፋት ፡ እየተናገሩ ፡ እንዲያውም ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ ውርርድ ፡ ይወራረዳሉ ። አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማየት ፡ ፍላጐት ፡ ብቻ ፡ ያደረባቸው ፡ አፍንጫቸውን ፡ እየጐረጐሩ ፡ የቆሙ ፡ ተራ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

በፊት ፡ ለፊቱ ፡ መስመር ፡ የከተማው ፡ ዘበኞች ፡ ከተሰለፉበት ፡ አጠገብ ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ወጣት ፡ መኮንን ፡ (ወይም ፡ መኰንን ፡ ለመምሰል ፡ የሚጥር ፡) ቆሟል ። አለባበሱ ፡ ሲታይ ፡ በቤቱ ፡ አንድ ፡ ቀዳዳ ፡ ሸሚዝና ፡ አንድ ፡ አሮጌ ፡ ጫማ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡ ሌላውን ፡ ያለ ፡ የሌለውን ፡



ለብሶ ፡ እንደመጣ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። እንደ ፡ ዱካት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ሰንሰለት ፡ በአንገቱ ፡ አጥልቆአል ። ከእጮኛው ፡ ከዩዜሱ ፡ ጐን ፡ ቆሞ ፡ የሃር ፡ ቀሚሷን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ነክቶ ፡ እንዳያበላሽባት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይገላመጣል ። ለእጮኛውም ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ሳይቀር ፡ በዝርዝር ፡ ያስረዳታል ።

«እዚህ ፡ የምታያቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፤ የኔ ፡ ፍቅር ፡ ዩዜሱ ፤ ወንጀለኞቹ ፡ ሲገደሉ ፡ ለማየት ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። ያ ፡ መጥረቢያና ፡ ሌላም ፡ መሳርያ ፡ ይዞ ፡ የምታይው ፡ ሰውየም ፡ ገዳዩ ፡ ሲሆን ፡ እሱም ፡ ወንጀለኞቹን ፡ ካሰቃየ ፡ በኋላ ፡ ይገድላቸዋል ። ከእነሱ ፡ አንዳቸውን ፡ በሽክርክረቱ ፡ ሲሰባብረውና ፡ በሌላም ፡ መንገድ ፡ ሲያሰቃየው ፡ የወንጀለኛው ፡ ነፍሱ ፡ ገና ፡ አትወጣም ። ኋላ ፡ ግን ፡ አንገቱን ፡ ሲቆርጠው ፡ ይሞታል ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ወንጀለኛው ፡ ይጮኻል ፡ ይፈራገጣል ፤ ግን ፡ አንገቱ ፡ ከተቆረጠ ፡ ወዲያ ፡ ለዘለዓለም ፡ መጮኽ ፡ ወይም ፡ መብላትና ፡ መጠጣት ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ የኔ ፡ ፍቅር ፤ ጭንቅላቱ ፡ ከሰውነቱ ፡ ተለይቶ ፡ ስለሚወድቅ ፡ ነው ።»

ዩዜሱ ፡ የሚነግራትን ፡ ሁሉ ፡ በድንጋጤና ፡ በመገረም ፡ ታዳምጣለች ።

የቤቶቹ ፡ ጣራ ፡ ሕዝብ ፡ ተከምሮበታል ። ከየመስኮቶቹም ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። በበረንዳዎቹ ፡ ላይ ፡ የጨዋው ፡ ወገኖች ፡ ተቀምጠዋል ። የአንድ ፡ የምትስቅ ፡ ወይዘሮ ፡ እንደ ፡ ስኳር ፡ የነጣ ፡ የሚያምር ፡ ክንድ ፡ በረንዳውን ፡ ተደግፎ ፡ ይታያል ። በረንዳው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚመለከቱም ፡ መኳንንት ፡ ክብር ፡ የተሰማቸውና ፡ የተጀነኑ ፡ ወፈፍራም ፡ መኳንንት ፡ ነበሩ ። የአማረ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ አሳላፊ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመደሰቻ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ይዞ ፡ እየዞረ ፡ ያሳልፋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ዓይነ ፡ መልካም ፡ ቀበጥ ፡ ወይዘሮ ፡ አንድ ፡ ብስኩት ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ወተ

ት ፡ በመሰሉት ፡ ጣቶችዋ ፡ ታነሳና ፡ ቁልቁል ፡ ወደተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ ትጥላለች ። የተራቡት ፡ ፈረሰኛ ፡ ወታደሮችም ፡ ለመያዝ ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ ሲዘረጉ ፡ ቁመቱ ፡ ከሁሉም ፡ ከፍ ፡ የሚለው ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ቀድሞ ፡ ይቀልበውና ፡ ስሞ ፡ ወደአፉ ፡ ይልከዋል ። ከፎቁ ፡ በረንዳ ፡ ሥር ፡ በተንጠለጠለ ፡ አንድ ፡ የብረት ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ንስር ፡ አሞራም ፡ አንገቱን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጐን ፡ ዘንበል ፡ አድርጐ ፡ ከተመልካቾቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በመሆን ፡ ቁልቁል ፡ ያስተውል ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ በሕዝቡ ፡ መሃል ፡ ጫጫታው ፡ በዛና ፡ ከሁሉም ፡ ወገን ፡ «አመጡዋቸው ፤ ኮዛኮቹን ፡ አመጡዋቸው!» የሚል ፡ ድምጽ ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ።

ኮዛኮቹ ፡ ያለ ፡ ቆብ ፡ ጐፈሬያቸው ፡ ተገልጦ ፡ ጺማቸውም ፡ ሳይላጭ ፡ መጡ ። አመጣጣቸውም ፡ በፍርሃት ፡ ወይም ፡ በሃዘን ፡ ሳይሆን ፡ በረጋ ፡ የኩራት ፡ መንፈስ ፡ ነበር ። ከተዋበ ፡ ውድ ፡ ጨርቅ ፡ የተሰፋው ፡ ልብሳቸው ፡ አርጅቶ ፡ ተቀዳድዷል ። የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ አላዩም ፡ ወይም ፡ እጅ ፡ አልነሱም ። ከሁሉ ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ ኦስታፕ ፡ ነበር ።

ሽማግሌው ፡ ቡልባ ፡ ልጁን ፡ ኦስታፕን ፡ ሲያይ ፡ የተሰማው ፡ ስሜት ፡ ምን ፡ ይሆን? ልቡስ ፡ ምን ፡ አስቦ ፡ ይሆን? ከሕዝቡ ፡ መሃል ፡ ቆሞ ፡ ሁናቴውን ፡ ሁሉ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ። ኦስታፕ ፡ ቆመ ። ከሌሎቹ ፡ በፊት ፡ መሪሩን ፡ ጽዋ ፡ የሚቀምሰው ፡ እሱ ፡ ነው ። ጓደኞቹን ፡ ተመለከተና ፡ ጮኸ ፡ ብሎ ፡ «አንዳችንም ፡ ብንሆን ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ እንድናሰማና ፡ እዚህ ፡ የተሰበሰቡት ፡ እርኩስ ፡ ከሃዲዎች ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያን ፡ በስቃይ ፡ ሲጮኽ ፡ እንዳይሰሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን!» ብሎ ፡ ወደ ፡ መገደያው ፡ ደርብ ፡ ወጣ ።

ቡልባም ፤ «ጐሽ ፡ የኔ ፡ ልጅ! እንዲያ ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ልጅ!» ብሎ ፡ ሸበቶ ፡ ራሱን ፡ አቀረቀረ ።



ገዳዩ ፡ የኦስታፕን ፡ ቡትቶ ፡ ከላዩ ፡ ላይ ፡ መንጭቆ ፡ አወለቀው ። እጅና ፡ እግሩም ፡ ተወጥረው ፡ ታሰሩ ፤ ከዚያ ፡... ግን ፡ ያን ፡ አሰቃቂ ፡ አገዳደል ፡ ዘርዝሮ ፡ በመግለጽ ፡ የአንባቢን ፡ መንፈስ ፡ አናውክም ። ጭካኔው ፡ ያ ፡ የአረመኔ ፡ ዘመን ፡ ያፈለቀው ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ሰው ፡ ደም ፡ ጠማሽ ፡ ወታደራዊ ፡ ኑሮ ፡ በሚኖርበት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠጥሮ ፡ ከሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ ጨርሶ ፡ የራቀ ፡ ነበር ። ይህን ፡ አሰቃቂ ፡ ተግባር ፡ ለመቃወም ፡ የሚሞክሩ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ቢገኙም ፡ ልፋታቸው ፡ ከንቱ ፡ ነበር ። ንጉሡና ፡ እንዲሁም ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፡ መኳንንት ፡ ሳይቀሩ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የጭካኔ ፡ ቅጣት ፡ በኮዛኮች ፡ ዘንድ ፡ የባሰ ፡ ቂም ፡ ከማትረፉ ፡ በቀር ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ቢሞክሩም ፡ ሰሚ ፡ አላገኙም ። አስተዋይ ፡ ባልሆነ ፡ የህፃን ፡ አመራር ፡ ምክር ፡ ቤቱን ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ጉድፍ ፡ ባደረጉት ፡ ሕገ ፡ ወጥና ፡ ትዕቢተኛ ፡ መኳንንት ፡ ፊት ፡ የነገሥታትና ፡ የጠቢብ ፡ መማክርት ፡ ሥልጣን ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ አልነበረውም ።

ኦስታፕ ፡ ስቃዩን ፡ ሁሉ ፡ በጸጥታ ፡ ተቀበለ ፤ ሩቅ ፡ ላሉት ፡ ተመልካቾች ፡ እንኳን ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ፡ የእጅና ፡ የእግሩን ፡ አጥንት ፡ ሲሰባብሩት ፡ እንኳን ፡ እንኳን ፡ መጮኽ ፡ አላቃሰተም ። ታራስ ፡ በሕዝቡ ፡ መሃል ፡ ቆሞ ፡ አንገቱን ፡ እንዳቀረቀረ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ «ጐሽ ፡ ልጄ! እንዲያ ፡ ነው ፡ ልጄ!» ይላል ።

ኦስታፕ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ የሞት ፡ ስቃይ ፡ ጐትተው ፡ ሲወስዱት ፡ ብቻ ፡ ኃይሉና ፡ ጽናቱ ፡ እየሟሟ ፡ የሄደ ፡ መሰለ ። ዓይኖቹን ፡ እያንከራተተ ፡ ዙሪያውን ፡ ተመለከተ ፤ አምላክ ፡ ሆይ! የሚታየው ፡ ሁሉ ፡ እንግዳና ፡ ያልታወቀ ፡ ፊት ፡ ነው! አንድ ፡ ተወዳጅ ፡ ሰው ፡ እዚያ ፡ ቆሞ ፡ አሟሟቱን ፡ ባየለት ፡ ኖሮ! የደካማ ፡ የእናቱን ፡ ሃዘንና ፡ ስቅስቅታ ፡ ለመስማት ፡ ወይም ፡ ደረትዋን ፡ እየደቃችና ፡ ጸጉርዋን ፡ እየነ

ጨች ፡ የምትጮኽ ፡ ሚስት ፡ አልተመኘም ። አሁን ፡ የተመ
ኘው ፡ ጠቢብ ፡ ቃሉ ፡ የሚያጽናናውና ፡ በሞቱ ፡ ሰዓት ፡
አዲስ ፡ ጉልበት ፡ የሚሰጠው ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ ነው ።
እዚህ ፡ ላይ ፡ ብርታቱ ፡ ሁሉ ፡ ከዳውና ፡ ነፍሱ ፡ እየተጨ
ነቀች ፤ «ባትኮ! የት ፡ ነህ? ትሰማኛለህ ?» ብሎ ፡ ጮኸ ።

ረጭ ፡ ባለው ፡ ጸጥታ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡
እስኪንቀጠቀጥ ፡ ድረስ ፡ «እሰማሃለሁ!» ሲል ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡
ድምጽ ፡ አስተጋባ ።

ወዲያው ፡ ፈረሰኛ ፡ ዘበኞች ፡ በፍለጋ ፡ እየተጣደፉ ፡
በግርግሩ ፡ መሃል ፡ ያስሱ ፡ ጀመር ። ያንኬል ፡ የሞት ፡ ያህል ፡
ገረጣ ፤ ፈላጊዎቹ ፡ ፈረሰኞችም ፡ ሲያልፉት ፡ በድንጋጤ ፡ እየተ
ንቀጠቀጠ ፡ ታራስን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ አለ ። ታራስ ፡ ግን ፡
ከኋላው ፡ የለም ፤ አንድም ፡ ምልክት ፡ ሳይተው ፡ ጠፍቶ
አል ።

## ምዕራፍ ፡ አስራ ፡ ሁለት ።

የታራስ ፡ ምልክት ፡ እንደጠፋ ፡ አልቀረም ። መቶ ፡
ሃያ ፡ ሺ ፡ የኮዛክ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ በኡክሬይን ፡ ጠረፍ ፡ ብቅ ፡
አለ ። ይህ ፡ ጦር ፡ እንደቀድሞው ፡ ለዘረፋ ፡ የወጣ ፡ ወይም ፡
ታታሮችን ፡ የሚያባርር ፡ ቀላል ፡ ጦር ፡ አልነበረም ። የሕ
ዝቡ ፡ ትዕግሥት ፡ ስለአለቀ ፡ መላው ፡ አገር ፡ ተነስቶአል ።
የመብቱን ፡ መነካት ፤ የባህሉን ፡ መናቅ ፤ አባት ፡ ያቆየው ፡
ሃይማኖቱንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መደፈር ፤ የባእድ ፡ መሳ
ፍንትንና ፡ ጳጳሳት ፡ ጭቆና ፤ በክርስቲያን ፡ ምድር ፡ የአይ
ሁድን ፡ የበላይነት ፡ ለመበቀል ፡ ሕዝቡ ፡ ቆርጦ ፡ ተነስቶ
አል ።

የጦሩ ፡ አዝማች ፡ ሄትማን ፡ አስትራኺትሳ[3] ፡ ነው ። እሱ
ም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ወጣት ፡ ቢሆን ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ ጐበ
ዝ ፡ ነበር ። ከጐኑ ፡ የጥንት ፡ የጦር ፡ ጓደኛውና ፡ አማካሪው ፡



ጉንያፋ ፡ አለ ። እያንዳንዳቸው ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ወታደ
ር ፡ ያላቸውን ፡ ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ ስምንት ፡ ኮሎኔሎች ፡ ይመ
ራሉ ። በፈረሰኛና ፡ በእግረኛ ፡ ክፍልም ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ መ
ኮንኖች ፡ ነበሩ ። ከተመዘገቡት ፡ ኮዛኮች ፡ ሌላ ፡ በቁጥር ፡
ከእነሱ ፡ የማያንስ ፡ ወዶ ፡ ዘማች ፡ ጦር ፡ በእግርም ፡ በፈረ
ስ ፡ ተከትሎአል ። በየትም ፡ ስፍራ ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ አን
ድነት ፡ ነው ፡ የተቀሰቀሱት ። ከቺጊሪን ፤ ከፔሬያስላቭ ፤ ከ
ባቱሪንና ፡ ከግሉኾቭ ፡ ከላኛውና ፡ ከታችኛው ፡ የድኔፐር ፡
ዳርቻ ፡ በውስጡ ፡ ካሉት ፡ ደሴቶችም ፡ ተነስተው ፡ መጥ
ተዋል ። ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ፈረሶችና ፡ ሰረገላዎች ፡
ሜዳውን ፡ አለበሱት ። ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኮዛኮች ፡ ከስምንቱ ፡
ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ የሆነው ፡ በታራስ ፡ ቡልባ ፡
የሚመራው ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ነበር ። ታራስ ፡ በማናቸውም ፡
ረገድ ፡ ከሌሎች ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል ። የበሰለ ፡ እድሜው ፡ የጦር ፡
ልምዱ ፡ ወታደር ፡ የማዘዝ ፡ ችሎታው ፡ እንዲሁም ፡ በጠላ
ት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ከማናቸውም ፡ የበለጠ ፡ መሪር ፡ ጥላቻ ፡
ከሌሎቹ ፡ ተለይቶ ፡ እንዲታወቅ ፡ አድርጐታል ። ኮዛኮቹ ፡
ራሳቸው ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ የጭካኔ ፡ መንፈሱን ፡ ከመጠ
ን ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ ገመቱት ። በአእምሮው ፡ የሚገባው ፡
ፍርድ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ብቻ ፤ በጦር ፡ ምክር ፡ ስብሰባ ፡ ላይ
ም ፡ የሚያቀርበው ፡ ምክር ፡ የማጥፋት ፡ ምክር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

የተደረገውን ፡ ጦርነትና ፡ የኮዛኮቹን ፡ ሥራ ፡ እዚህ ፡
ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ለመግለጽ ፡ አይመችም ። ሁሉም ፡ በታሪክ ፡
የማስታወሻ ፡ ገጾች ፡ ላይ ፡ ሰፍሮ ፡ ይገኛል ። በሩሲያ ፡ ምድር ፡
በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የተነሳ ፡ ጦርነት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡
የታወቀ ፡ ነው ። ከሃይማኖት ፡ የጠነከረ ፡ ምንም ፡ ኃይል ፡
አይገኝም ። ሃይማኖት ፡ በሞገደኛ ፡ ባህር ፡ መሃል ፡ እንደ
ቆመ ፡ ቋጥኝ ፡ የማይናወጽ ፡ ነው ። የማይሰበር ፡ ግድግዳ
ውን ፡ ከጠሊቁ ፡ ባህር ፡ መደብ ፡ ተክሎ ፡ ቆሞ ፡ ከማናቸው
ም ፡ አንጻር ፡ እየታየ ፡ አላፊውን ፡ ማእበል ፡ በድፍረት ፡ ይ

መለከተዋል ። ከሱ ፡ ጋር ፡ የሚጋጭ ፡ መርከብም ፡ ወየ
ውለት! ተሰባብሮና ፡ ተስነጣጥቆ ፡ በላዩም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተደምስሶ ፡ ይሰምጣል ። የተሳፋሪዎቹ ፡ ሰዎ
ችም ፡ የጭንቅ ፡ ጩኸት ፡ እየሩን ፡ ያናጋዋል ።

የፖላንድ ፡ ጦር ፡ ኮዛኮች ፡ ነጻ ፡ ካወጡዋቸው ፡ ከተሞ
ች ፡ እንዴት ፡ እየሸሸ ፡ እንደሄደ ፤ ወለድ ፡ አግድ ፡ አበዳሪ ፡
አይሁዶች ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ እንደተሰቀሉ ፤ የንጉሡ ፡ ሄት
ማን ፡ ኒኮላይ ፡ ፖቶጽኪይ ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡
ኃያል ፡ ጦር ፡ ፊት ፡ እንደተጨነቀ ፡ ተባርሮና ፡ ተንከራትቶ ፡
በአንድ ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ አብዛኛው ፡ ሠራዊቱ ፡ እን
ዳለቀበት ፡ አስፈሪው ፡ የኮዛክ ፡ ጦር ፡ በፖሎኖየ ፡ ከተማ ፡
ከብቦ ፡ ሠራዊቱን ፡ ጨርሶበት ፡ የፖሊሹ ፡ ሄትማን ፡ የኮዛ
ኮቹን ፡ ፍላጐት ፡ ሁሉ ፡ ለመፈጸም ፤ መብታቸውንም ፡ ለመ
መለስ ፤ በንጉሡና ፡ በሚኒስትሮቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ በመሃላ ፡
ቃል ፡ እንደገባ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ በታሪክ ፡ ማስታወሻዎች ፡
ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ሰፍሮ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ የፖ
ሊሽ ፡ መሃላ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ስለሚያውቁ ፡ በዚህ ፡
አልተታለሉም ። ፖቶጽኪይም ፡ የከተማው ፡ የሩሲያ ፡ ቀ
ሳውስት ፡ ሕይወቱን ፡ ባያተርፉት ፡ ኖሮ ፡ በስድስት ፡ ሺ ፡
ዱካት ፡ በተገዛ ፡ ሰንጋ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በአደባባይ ፡ የመሳ
ፍንትንና ፡ የወይዛዝርትን ፡ ዓይን ፡ ለመማረክ ፡ ባልበቃ ፡ ነ
በር ። ቀሳውስቱ ፡ ልብስ ፡ ተክህኖአቸውን ፡ ለብሰው ፤ ሥዕ
ል ፡ መስቀል ፡ ተሸክመው ፡ በአቡኑ ፡ በራሳቸው ፡ መሪነ
ት ፡ ሲመጡ ፡ ጊዜ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ አን
ገታቸውን ፡ ደፉ ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ለንጉ
ሡም ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ እንዲያ ፡ ያለ ፡ አክብሮት ፡ አላሳ
ዩም ፡ ነበር ። በራሳቸው ፡ የክርስቲያን ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ላይ ፡
ግን ፡ ለማመጽ ፡ ስለአልደፈሩ ፡ ለቀሳውስቶቻቸው ፡ ታዛ
ዥ ፡ ሆኑ ። የኮዛኮቹ ፡ ሄትማንና ፡ ኮሎኔሎቹ ፡ ፖቶጽኪይን ፡
የክርስቲያንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዳይጨቁንና ፡ የኮዛክ



ንም ፡ ክብር ፡ እንዳይነካ ፡ ካስማሉት ፡ በኋላ ፡ ሊለቁት ፡ ተስ
ማሙ ። አንድ ፡ ኮሎኔል ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ባለው ፡ የሰላም ፡
ስምምነት ፡ አልተስማማም ። እሱም ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ነበር ።
ከጸጉሩ ፡ አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ነጨና ፤ «ስሙኝ ፡ ሄትማኑና ፡
ኮሎኔሎች! እንዲህ ፡ ያለ ፡ የሴት ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ! ፖሊ
ሾችን ፡ አትመኑአቸው ። እነዚህ ፡ ውሾች ፡ በኋላ ፡ ይከዱ
ናል!» አለ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሄትማኑ ፡ ውሉ ፡ ቀርቦለት ፡ በፈረመ ፡ ጊዜ ፡
ታራስ ፡ የከበረ ፡ የቱርክ ፡ ጐራዴውን ፡ አወጣና ፡ እንደ ፡
አገዳ ፡ ከሁለት ፡ ሰብሮ ፡ ሰባሪዎቹን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ወረ
ወረና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ደህና ፡ ሁኑ! እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰባሪዎች ፡ እንደገና ፡
ተገናኝተው ፡ ጐራዴ ፡ እንደማይሆኑ ፡ እነሆ ፡ እኛም ፡ ጓደ
ኞቼ ፡ ሆይ ፤ ዳግመኛ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አንተያይም ። እነሆ ፡
የመሰናበቻ ፡ ቃሌን ፡ አስታውሱ! በሞታችሁ ፡ ሰዓት ፡ ታስ
ታውሱኛላችሁ! አሁን ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ የተዋዋላችሁ ፡
መሰላችሁ? አሁን ፡ የሚያልፍላችሁ ፡ መሰላችሁ? የለም ፡
ሌሎች ፡ ናቸው ። ከበላዮቻችሁ ፡ ሆነው ፡ የሚያልፍላቸው ፡
አንተም ፡ ሄትማን ፡ ጭንቅላትህ ፡ እንደስልቻ ፡ ተገፎ ፡ የስ
ንዴ ፡ ገለባ ፡ ከተሞላ ፡ በኋላ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በየገበያው ፡
እየዞረ ፡ ሲታይ ፡ ይኖራል ። እናንተም ፡ መኳንንት ፡ ሆይ ፤
የምትድኑ ፡ አይምሰላችሁ! እንደ ፡ በግ ፡ በብረት ፡ ድስት ፡
ያልተቀቀላችሁ ፡ እንደሆን ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ በስብሳችሁ ፡
ትቀራላችሁ!»

ወደ ፡ ወታደሮቹ ፡ ደግሞ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ወጣቶቼ ፡ ሳትልከሰከሱ ፡ እውነ
ተኛ ፡ የኮዛክ ፡ ሞት ፡ ለመሞት ፡ የምትፈልጉ ፡ እነማናችሁ?
ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ ተመልሳችሁ ፡ ከሃዲ ፡
በመሆን ፡ የፖሊሽ ፡ ቄስ ፡ በጀርባችሁ ፡ አዝሎ ፡ ለመዞር ፡
ትፈልጋላችሁ?»

የቡልባ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ወታደሮች ፡ በሞላ ፤ «እርስዎን ፡ እንከተላለን ፡ ኮሎኔል!» ብለው ፡ ሲጮኹ ፡ ከሌላም ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ብዙዎቹ ፡ ወደሱ ፡ አዘንብለው ፡ ተቀላቀሉ ።

«እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ተከተሉኝ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ቆቡን ፡ ቅንድቡ ፡ ድረስ ፡ አጥልቆ ፡ ለመቅረት ፡ የወሰኑትን ፡ ገላመጠና ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

«በክፉ ፡ ነገር ፡ ስማችን ፡ እንዳይነሳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን! ተከተሉኝ ፡ ጐበዝ! ካቶሊኮቹን ፡ እንጐበኛቸዋለን!»

ይህንን ፡ ተናግሮ ፡ ታራስ ፡ ፈረሱን ፡ ሲሸነቁጥ ፡ መቶ ፡ የሚሆን ፡ ሠረገላና ፡ እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ኮዛኮች ፡ በእግርም ፡ በፈረስ ፡ ተከተሉት ። ዘወር ፡ ብሎ ፡ ከዘመቻው ፡ የቀሩትን ፡ ገላመጣቸው ፡ ዓይኖቹም ፡ በቁጣ ፡ ተሞልተው ፡ ነበር ። ማንም ፡ ሊያስቀረው ፡ አልደፈረም ። መላው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እየተመለከተ ፡ የሱ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ተነጥሎ ፡ ዘመተ ። ታራስም ፡ ዞሮ ፡ የቀሩትን ፡ እንደገና ፡ ገላመጣቸው ።

ሄትማኑና ፡ ኮሎኔሎቹ ፡ አቀርቅረው ፡ ቆመው ፡ መጥፎ ፡ ትንቢት ፡ እንደታያቸው ፡ ሁሉ ፡ በትካዜ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በሃሳብ ፡ ተዋጡ ። ታራስ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ። ሁሉም ፡ እንደተናገረው ፡ ተፈጸመ ። ወዲያው ፡ ብዙ ፡ ሳይቆይ ፡ በካኔቭ ፡ መሃላው ፡ ፈረሰና ፡ የሄትማኑ ፡ እንዲሁም ፡ የሌሎች ፡ የዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ጭንቅላት ፡ ተቆርጦ ፡ በአጠና ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠለጠለ ።

ታራስስ ፡ ከምን ፡ ደረሰ? ታራስ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ወደ ፡ ፖላንድ ፡ ጠልቆ ፡ ገብቶ ፡ ከአሥራ ፡ ስምንት ፡ ከተሞችና ፡ አርባ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ መቅደሶች ፡ አቃጥሎ ፡ ክራኮቭ ፡ ደረሰ ። የገደላቸው ፡ መኳንንትና ፡ ያፈራረሳቸው ፡ የመሳፍንት ፡ ህንጻዎችም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። የታራስ ፡ ኮዛኮች ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የተቀበረውን ፡ የወይንና ፡ የማር ፡ ጠጅ ፡ ከመሳፍንቱ ፡ እቃ ፡ ቤት ፡ ቆፍረው ፡ እያወጡ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ረበረቡት ። ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ልብሶችና ፡ በእቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚያገኙትን ፡ ማናቸውንም ፡ እቃ ፡ ሰባብረውና ፡ ቀዳድደው ፡ አቃጠሉት ። የታራስ ፡ ቋሚ ፡ ትእዛዝ ፡ «ምንም ፡ ነገር ፡ አትማሩ!» የሚል ፡ ነበር ። ቅንድባቸው ፡ ጥቋቁርና ፡ ደረታቸውም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ለነጣው ፡ ፊታቸው ፡ ሉል ፡ ለሚመስለው ፡ የተዋቡ ፡ ወይዛዝርት ፡ እንኳን ፡ ኮዛኮቹ ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ አላሳዩም ። በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ቢጠለሉም ፡ አልዳኑም ። ታራስ ፡ ከነቤተ ፡ መቅደሱ ፡ አቃጠላቸው ። በነበልባሉ ፡ መሃል ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ የነጣው ፡ ጣታቸው ፡ እየተርገበገበ ፡ በሚዘገንን ፡ ድምጽ ፡ ሲጮኹ ፡ ደረቅዋ ፡ ምድር ፡ እንኳን ፡ ባዘነችላቸው ፡ ነበር ። የመስኩ ፡ ሳርም ፡ ሳይቀር ፡ በኃዘን ፡ አንገቱን ፡ በደፋ ። ጨካኞቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ አላሳዩም ። ሕጻናትን ፡ ሳይቀር ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ እያንጠለጠሉ ፡ ነበልባሉ ፡ ውስጥ ፡ ይጨምሩአቸዋል ።

«ይህ ፡ የኦስታፕ ፡ የተዝካር ፡ ድግስ ፡ ነው ፡ እናንት ፡ ከሃዲዎች!»

ታራስ ፡ ይህን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይናገርም ፤ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የኦስታፕ ፡ ማስታወሻ ፡ ድግስም ፡ በደረሰበት ፡ ከተማና ፡ መንደር ፡ ሁሉ ፡ ልማድ ፡ አደረገው ። የፖሊሽ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ሲመለከት ፡ ከተራ ፡ ወረራ ፡ የላቀ ፡ ድርጅት ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ያንኑ ፡ የቀድሞውን ፡ ፖቶጽኪይን ፡ አምስት ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እንዲዘምት ፡ አዘዘው ።

ኮዛኮቹ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ፈረሶቻቸው ፡ እስኪዝሉ ፡ ድረስ ፡ ጋልበው ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ሲሸሹ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በድኔስተር ፡ ዳር ፡ እንደሰፈሩ ፡ ደረሱባቸው ።

ኮዛኮቹ ፡ የሰፈሩበት ፡ የፈራረሰ ፡ ጥንታዊ ፡ ግቢ ፡ ከድኔስተር ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ባለ ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ኮዛ

ኮቹ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እንዳሉ ፡ ገደሉ ፡ ከጀርባቸው ፡ ሆኖ ፡
የንጉሡ ፡ ሄትማን ፡ ፖቶጽኪይ ፡ ከሚዳው ፡ በኩል ፡ በሁለ
ት ፡ አቅጣጫ ፡ ከበባቸው ። ኮዛኮቹ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡
በግንቡ ፡ ፍራሽ ፡ ሽክላና ፡ ድንጋይ ፡ ተከላከሉ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡
ስንቃቸውም ፡ ኃይላቸውም ፡ እየተቀነሰ ፡ ስለሄደ ፡ ታራስ ፡
በጠላቶቹ ፡ መሃል ፡ እየተዋጋ ፡ ለማለፍ ፡ ቆረጠ ። ይህን ፡ ለማ
ድረግ ፡ ሲነሱ ፡ ታራስ ፡ ቆም ፡ ብሎ ፤ «ቆዩ! የትንባሆ ፡ ማጨ
ሻዬን ፡ ጥያለሁ ፤ እነዚህ ፡ ከሃዲ ፡ ፖሊሾች ፡ ትንባሆዬን ፡
እንኳን ፡ አይወስዱትም!» ባይል ፡ ኖሮ ፡ በእውነትም ፡ ኮዛ
ኮቹ ፡ እየተዋጉ ፡ በፈጣን ፡ ፈረሶቻቸው ፡ የጠላቶቻቸውን ፡
ሰልፍ ፡ ጥሰው ፡ ባለፉ ፡ ነበር ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ይህን ፡
ተናግሮ ፡ በባሕርም ፡ በየብስ ፡ አብሮት ፡ ሲዘምት ፡ የኖረው
ን ፡ የትንባሆ ፡ ማጨሻውን ፡ ጐንበስ ፡ ብሎ ፡ በሳሩ ፡ ውስጥ ፡
ይፈልግ ፡ ጀመር ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የጠላት ፡ ወታደሮ
ች ፡ ተንደርድረው ፡ ደረሱና ፡ ኃያል ፡ ትከሻው ፡ ላይ ፡ ሰፈ
ሩበት ፤ ተፍጨርጭሮ ፡ ለማምለጥ ፡ ሞከረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡
የያዙት ፡ ወታደሮች ፡ እንደወትሮው ፡ እየተፈናጠሩ ፡ አልወ
ደቁም ። «አይ ፡ እርጅና! አይ ፡ እርጅና!» አለና ፡ ኃይለኛው ፡
ኮዛክ ፡ አለቀሰ ። ነገር ፡ ግን ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ጉልበት ፡ ለብ
ዙ ፡ ሰው ፡ ጉልበት ፡ ተሸነፈ ፡ እንጂ ፡ በእርጅና ፡ ምክንያት ፡
አልነበረም ። ሠላሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እግርና ፡ እጁን ፡ ተጠ
ምጥመው ፡ ያዙትና ፤ «ተፈላጊውን ፡ ይዘነዋል ፤ እንግዲህ ፡
ለዚህ ፡ ውሻ ፡ የሚገባውን ፡ ፍርድ ፡ እንፈልግለት!» እያሉ ፡
ይንጫጩ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ በጠቅላይ ፡ አዛዣቸው ፡ ፈቃ
ድ ፡ ከንነፍሱ ፡ ሊያቃጥሉት ፡ ተነሱ ። አጠገባቸው ፡ ጫፉ ፡
በመብረቅ ፡ ተመትቶ ፡ ግንዱ ፡ ብቻ ፡ የቀረ ፡ ዛፍ ፡ አገኙና ፡
በብረት ፡ ሰንሰለት ፡ ከግንዱ ፡ ጋር ፡ አሰረው ፡ ከሩቅ ፡ እንዲ
ታይም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ እጆቹን ፡ በምስማር ፡ ቸነከሩዋ
ቸው ። ከዚያ ፡ ከሥሩ ፡ ደረቅ ፡ እንጨት ፡ ከመሩ ፤ ታራስ ፡
ግን ፡ ቁልቁል ፡ ወደነሱ ፡ አልተመለከተም ። እሱን ፡ ለማ



ቃጠል ፡ ስለሚያዘጋጁት ፡ እሳትም ፡ አላሰበም ። እሱ ፡ የሚ
መለከተው ፡ እየተታኮሱ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ የሚከላከሉትን ፡
ኮዛኮች ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከተቸነከረበት ፡ ግን
ድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ቁልጭ ፡ ብለው ፡ ይታዩታል ።

«በርቱ ፡ ጐበዝ ፤ ያችን ፡ ኮረብታ ፡ ድረሱ! ከጫካው ፡
እልፍ ፡ ብሎ ፡ ካለው ፡ ኮረብታ ፡ ከደረሳችሁ ፡ አያገኙዋች
ሁም!» አለና ፡ ጮኸ ። ነገር ፡ ግን ፡ ነፋሱ ፡ ስላገደው ፡ ድምጹ ፡
እነሱን ፡ አልደረሳቸውም ።

«እየ ፡ ጉድ! ጠፉ! በከንቱ ፡ አለቁ!» አለና ፡ በመጨነቅ ፡
ቁልቁል ፡ ወደ ፡ ድኔስተር ፡ ወንዝ ፡ ተመለከተ ።

ወዲያው ፡ በዓ ኖቹ ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ ያበራ ፡ ጀመር ።
ከወንዙ ፡ ዳር ፡ በቁጥቋጦዎች ፡ መሃል ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ የአራት ፡
ጀልባዎች ፡ ጫፍ ፡ ታየው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በአለ ፡ ኃይሉ ፡
ጮኸ ፡ ተጣራ ።

«ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር ፡ ጐበዝ! ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር! በስተግ
ራ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ ቁልቁል ፡ ውረዱ! ከወንዙ ፡
ዳር ፡ ጀልባዎች ፡ አሉና ፡ እንዳይከተሏችሁ ፡ ሁሉንም ፡ ይዛ
ችሁ ፡ አምልጡ!»

ይህን ፡ ሲናገር ፡ ነፋሱ ፡ የሚነፍሰው ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡
ስለነበር ፡ ድምጹ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ደረሳቸው ። ግን ፡ ምክር ፡ በመ
ስጠቱ ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ በመጥረቢያ ፡ ደንደስ ፡
ከኋላ ፡ ጭንቅላቱን ፡ መታውና ፡ የሚያየው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ዞረበት ።

ኮዛኮቹ ፡ ከገደሉ ፡ በሚያወርደው ፡ መንገድ ፡ ሽምጥ ፡
ጋለቡ ። ግን ፡ አባራሪዎቻቸውም ፡ እንደደረሱባቸው ፡ ስለተ
ገነዘቡና ፡ የመንገዱ ፡ ጠመዝማዛነት ፡ መሰናከል ፡ ስለሆነ
ባቸው ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ገቱና ፡ እንደገና ፡
አፏጭተው ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ገርፈው ፡ አስነሱ ። የታታር ፡
ፈረሶቻቸውም ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ተወርውረው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡
ዘለው ፡ ከገደሉ ፡ ጫፍ ፡ ድኔስተር ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ተደፈ

ቁ ። ሁለት ፡ ፈረሰኞች ፡ ብቻ ፡ ከውኃው ፡ ሳይደርሱ ፡ ከገደሉ ፡ ሥር ፡ ካለው ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ከነፈረሶቻቸው ፡ ድምጻቸው ፡ ሳይሰማ ፡ ተከስክሰው ፡ ቀሩ ። ሌሎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ግን ፡ ከነፈረሶቻቸው ፡ እየዋኙ ፡ ደርሰው ፡ ጀልባዎችን ፡ መፋታት ፡ ጀምረዋል ። ፖሊሾቹ ፡ ለመዝለል ፡ እያመነቱ ፡ ከገደሉ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ይህን ፡ ተሰምቶ ፡ የማይታወቅ ፡ የኮዛክ ፡ ድርጊት ፡ ያደንቁ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ደፋር ፡ ኮሎኔል ፡ ግን ፡ አንድሬይን ፡ ወጥመድ ፡ ያገባቸው ፡ የዚያች ፡ ውብ ፡ ቆንጆ ፡ ወንድም ፡ ብዙ ፡ አላመነታም ። ወዲያው ፡ ፈረሱን ፡ ኮለኮለና ፡ ከገደሉ ፡ ላይ ፡ ዘለለ ። ግን ፡ ከውኃው ፡ ሳይደርስ ፡ የሾለው ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ተበጣጥሶ ፡ ወደቀ ። አንጎሉም ፡ ከደም ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ በየቁጥቋጦው ፡ ላይ ፡ ተረጨ ።

በመጥረቢያው ፡ በትር ፡ ደንዝዞ ፡ የነበረው ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ አእምሮው ፡ መለስ ፡ ብሎለት ፡ ወደ ፡ ድኔስተር ፡ ሲመለከት ፡ ኮዛኮቹ ፡ ጀልባዎቹን ፡ እየቀዘፉ ፡ እየራቁ ፡ ሲሄዱ ፡ አየ ። ከላይ ፡ የሚተኮሱ ፡ ጥይቶችም ፡ አልደረሱባቸውም ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሽማግሌው ፡ ኮሎኔል ፡ የታራስ ፡ ቡልባ ፡ ዓይኖች ፡ በደስታ ፡ አንጸባረቁ ።

ከላይ ፡ ሆኖ ፡ ተጣርቶ ፡ እየራቁ ፡ የሚሄዱትን ፡ ጓደኞቹን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤

«ደህና ፡ ሁኑ ፡ ጓደኞቼ! እንዳትረሱኝ! በሚመጣው ፡ የጸደይ ፡ ወቅትም ፡ እንደገና ፡ ለወረራ ፡ እንድትመለሱ! እንዴት ፡ እናንት ፡ ከሃዲ ፡ ፖሊሾች? ኮዛክን ፡ ድል ፡ የሚያደርግ ፡ ፍጥረት ፡ ያለ ፡ ይመስላችኋል? ቆዩማ! ከአሁኑ ፡ እንኳን ፡ በሩቅም ፡ በቅርብ ፡ ንግርት ፡ ይወራል ፡… ከሩሲያ ፡ ምድር ፡ አንድ ፡ ገዥ ፡ ይነሳል ። በምድርም ፡ ላይ ፡ ለሱ ፡ የማይገብር ፡ አንድም ፡ አይገኝም!»

ከሥር ፡ የተከመረው ፡ እንጨት ፡ ተያይዞ ፡ ነበልባሉ ፡ እግሩን ፡ እየጠበሰ ፡ በዛፉ ፡ ወደላይ ፡ ወጣ ። ግን ፡ ምን ፡ እሳት ፡



ነው ፤ ምን ፡ ስቃይ ፡ ነው ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ኃይል ፡ ነው ፡ የሩሲያዊን ፡ ኃይል ፡ የሚያሸንፈው!

ድኔስተር ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ አይደለም ፤ ተከታዮቹ ፡ ውኃዎች ፡ ጨፌዎቹና ፡ ጥልቅ ፡ ጉድጓዶቹም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። እንደ ፡ መስተዋት ፡ የጠራው ፡ ውኃው ፡ ይፈልቃል ። በላዩም ፡ የሚያንዣብቡት ፡ የወንዝ ፡ አሞሮችና ፡ በየጨፌዎቹ ፡ የሚደበቁት ፡ አእዋፍ ፡ ዜማ ፡ ይሰማል ። ኮዛኮቹ ፡ በባለሁለት ፡ መሪ ፡ ጠባብ ፡ ጀልባዎቻቸው ፡ በፍጥነት ፡ እየቀዘፉ ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ። እየቀዘፉ ፡ መሪአቸውን ፡ ቡልባንም ፡ በማንሳት ፡ እያወጉ ፡ ተጓዙ ።

## መግለጫ ።

ኒኮላይ ፡ ጐጐል ፡ በ «ታራስ ፡ ቡልባ» ፡ የሚገልፀው ፡ ዘመን ፡ በኡክሬይን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የከፋ ፡ ዘመን ፡ ነበር ። እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፭፻፷፱ ዓ ፡ ም ፡ በሉብሊን ፡ ዑኒያ ፡ መሠረት ፡ የኡክሬይን ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ሕዝቡ ፡ ፈቃድ ፡ ከፖላንድ ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ ነበር ። የፖላንድ ፡ መኳንንትም ፡ ይህን ፡ ሰፊና ፡ ለም ፡ አገር ፡ የእጅ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ባለሃገሩን ፡ የኡክሬይን ፡ ሕዝብ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ በጭቆና ፡ ያስገብሩት ፡ ጀመር ። ሕዝቡን ፡ ጨርሶ ፡ ፖሊሽ ፡ ለማድረግም ፡ በመሞከር ፡ የኡክሬይንን ፡ ቋንቋ ፡ ከልክለው ፤ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የኡክሬይን ፡ ባህል ፡ ጨቁነው ፡ በጠቅላላው ፡ ሃገሩን ፡ በመንፈስም ፡ ሆነ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ባሪያ ፡ ለማድረግና ፡ ብሄራዊ ፡ ነፃነቱን ፡ ለመግፈፍ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይጥሩ ፡ ነበር ። እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከ ፲፭፻፺፮ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የብሬስት ፡ ዑኒያ ፡ ሲታወጅ ፡ የኡክሬይን ፡ ሕዝብ ፡ ከተጫነበት ፡ የኤኮኖሚና ፡ የፖሊቲካ ፡ ጭቆና ፡ በላይ ፡ ተጨማሪ ፡ የሃይማኖት ፡ ጭቆና ፡ ወደቀበት ። የፖላንድ ፡ መኳንንትና ፡ ቀሳውስት ፡ የሕዝቡን ፡ ሃይማኖት ፡ በግድ ፡ ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ እያስለወጡ ፡ በከሃዲነት ፡ እምቢ ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ በኦርቶዶክስነት ፡ የሚፀናውን ፡ ሁሉ ፡ በጭካኔ ፡ ይቀጡት ፡ ጀመር ።



ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቢከብደው ፡ ሕዝቡ ፡ የጭቆና ፡ ቀንበሩን ፡ አውልቆ ፡ ለመጣል ፡ ተነሳና ፡ በኡክሬይናውያን ፡ ገባር ፡ ባለሃገሮች ፡ ቀስቃሽነት ፡ ብዙ ፡ ሁከት ፡ እያነሳ ፡ መከተ ። ኡክሬይን ፡ ለነፃነቷ ፡ ባደረገችው ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ጉሉህና ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ የፈፀመው ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ የኮበለሉ ፡ ገባሮችና ፡ እንዲሁም ፡ ብሔራዊና ፡ ሰብዐዊ ፡ ጭቆና ፡ አንገፍግፏቸው ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ሃብታሙ ፡ ደቡባዊ ፡ ሩሲያ ፡ የመጡ ፡ ነፃነት ፡ ወዳድ ፡ ሰዎች ፡ ያቋቋሙት ፡ ወታደራዊና ፡ ሕዝባዊ ፡ ድርጅት ፡ ነበር ። ዘመን ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ኮዛኮች ፡ ለነፃነት ፡ የሚያደርጉት ፡ ውጊያ ፡ ቱርኮቹን ፡ ታታሮችንና ፡ የፖላንድንም ፡ መኳንንት ፡ ፍርሃትና ፡ ስጋት ፡ አሳደረባቸው ። በ «ታራስ ፡ ቡልባ» ፡ ውስጥ ፡ በተገለፀው ፡ ዘመን ፤ ማለት ፡ በሺ ፡ ሰባት ፡ መቶኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፤ የዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፤ ያልተለመደ ፡ በሆነው ፡ የአኗኗር ፡ ጠባዩና ፡ በጠንካራው ፡ የጦር ፡ ድርጅቱ ፡ የተነሳ ፤ የኡክሬይን ፡ ሕዝብ ፡ ለነፃነቱና ፡ እንደገና ፡ ከሩሲያ ፡ ለመቀላቀል ፡ ላደረገው ፡ ትግል ፡ ዋና ፡ ግንባር ፡ ሆነ ።

### ገጽ ፡ ፱

[1] ሄትማንቺና ፡—በድኔፐር ፡ ምሥራቃዊ ፡ ወደብ ፡ የሚገኘው ፡ በፖላንድ ፡ ንጉሥ ፡ በተሾመ ፡ ሄትማን ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ የኡክሬይን ፡ ክፍለ ፡ ሃገር ።

### ገጽ ፡ ፱፪

[2] በብረት ፡ ድስት ፡ የተቀቀለው ፡ ሄትማን ፡—በአፈ ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ ሄትማን ፡ ናሊቫይኮ ፡ የተባለው ፡ የኮዛኮች ፡ ድርጅት ፡ መሪ ፡ በፖሊሾች ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ በብረት ፡ ድስት ፡ ተቀቅሎ ፡ መሞቱ ፡ ይነገራል ።

ገጽ ፡ ፻፷፮

[3] ሄትማን ፡ እስትራኒትሳ ፡—ኮዛኮች ፡ በፖሊሽ ፡ ጨቋኞቻቸው ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ተቃውሞ ፡ ከመሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ ሲሆን ፤ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) በ ፲፮፻፴፰ ዓ ፡ ም ፡ በዋርሶ ፡ ከተማ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈጸመበት ፡፡

ገጽ ፡ ፻፷፯

[4] ጉንያ ፡—ጉንያ ፡ ሌወን ፡—(እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) በ ፲፮፻፴፰ ዓ ፡ ም ፡ በተደረገው ፡ ዘመቻ ፡ የእስትራኒትሳ ፡ ቀኝ ፡ ክንድ ፡ የነበረ ፡ ኮዛክ ፡፡

## አንባብያን ፡ ሆይ!

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማ
ዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለ
ዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ትርጉም ፤ ዝ
ግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡
አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብ
ትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።
አድራሻው ፤

21, Zubovsky Boulevard,
Moscow, USSR.